# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የ2009/2010 ኦዲት ዓመት

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት

# አጠቃላይ ዘገባ

**ጥራዝ 2**

**ግንቦት / 2010**
**አዲስ አበባ**

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በ2009/2010 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች ዓመታዊ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም

### መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በፌዴራል መንግስት መዋቅር ስር ባሉ መ/ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነት ግልፅነትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ በኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55/1 እና አንቀጽ 101/4 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣ ናቸው፡፡

## 1.1. የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተሰገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ስርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመ/ቤታቸውን ሂሳብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገልጹለት ሊያድረግ ይችላል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር እንዳአስፈልጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ይሰጣል፤
- አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ፤ ይህን ሂሳብ የሚመለከቱ ጽሑፎች፤

መዘክሮች፤መዝገቦች ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥ ነት ያላቸው መረጃዎች ላይ ያሽጋል፤

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለገንዘብ አያያዝ፤አጠባበቅ፤ የሂሳብ አያያዝና ንብረት አስተዳደር በሚያዘጋጀው መመሪያዎች ላይ አስፈክለጊውን ምክር ይሰጣል፤
- ከሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ጋር የፌዴራልና ክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤
- ከክልል የኦዲት መ/ቤቶችና ቁጥጥር ቢሮዎች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፤

የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.2. <u>የሪፖርቱ ዓላማ</u>

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 በአንቀጽ 13/1 እስከ 4 መሠረት በ2009/2010 የኦዲት ዓመት ባከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2009 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ የ2009/2010 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው፡፡

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች መሰረት ያደረጉት የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን የ2009 በጀት ዓመት ሒሳብ፣ የአለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች የሚሰጡትን የመሰረታዊ ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግስት በገባው ውል መሠረት በብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት፣ የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቀም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቋሙ የመንግሥት ልማት

ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤትና በመ/ቤታችን የተከናወኑ የልዩ ኦዲት ሥራዎችን ነው፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኂላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሣቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት የኦዲት ሥራው እንዳለቀ እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡ ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፤ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ስራም የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፤ የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት መሠረት በማድረግ እና በኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፤ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2009/2010 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የ2009/2010 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ዕቅድና አፈፃፀም፤ ዋና ዋና የስራዎች ክንውን ሪፖርት፤ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች፤ የመፍትሄ ሃሣቦችና አጭር ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

በሁለተኛው ክፍል የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሥራን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የአካባቢና የክዋኔ ኦዲት፤ እንዲሁም መንግሥት ከዓለም ባንክ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ለክልል መንግሥታት የተሰጠውን ሂሣብ ተከታታይ ኦዲትና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ ተጠቃሎ የተዘጋጀውን ሂሳብ ኦዲት ውጤት ያጠቃልላል፡፡

ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በኮርፖሬሽኑና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ የልማት ድርጅቶችና በመንግስት የልማት አጋራች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የኦዲት ውጤትን የሚመለከት ይሆናል፡፡

## 2. የ2009/2010 ኦዲት ዓመት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

### 2.1 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ አምስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ የመጋቢት 1/2009 እስከ የካቲት 30/2010፤ የ174 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና 47 የቅርንጫፎች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ በተያዘው መሠረት የ173/አንድ መ/ቤት በመታጠፉ/ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና የ48 ቅ/ጽ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን የ172 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና አንድ የመንግስት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ የኦዲት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የተላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ከ2008/2009 ኦዲት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| መግለጫ<br>/የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/<br>በጀት ዓመት | ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት | |
|---|---|---|
| | 2008 | 2009 |
| ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት | 27 | 25 |
| ከጥቅት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ | 73 | 87 |
| አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች | 5 | 8 |
| የጎላ ችግር ያለባቸው፣ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው | 53 | 53 |
| ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ/ሪፖርት ያልወጣ/ | - | |
| **ድምር** | **158** | **173** |

## 2.2 <u>የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሣቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ በማሳወቅ ክትትል ተደርጓል፡፡

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና ከታህሳስ 1/2009 እስከ ጥር 30/2010 ዓ.ም አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 46 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 145 በድምሩ 191(ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ

የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን ኦዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ከገጽ 257 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

## 2.3 <u>የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ</u>

የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትን ተከትሎ መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋንና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል በመወሰነው መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታተቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ይከናወናል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2009-2010 የኦዲት ዓመት (Audit Calendar) በሁለቱ ክዋኔ ኦዲት ደይሬክቶሬቶች ከየካቲት/2009 እስከ ጥር 30 የሚጠናቀቁ 20 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 8 /ስምንት/ የክዋኔ ክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች አፈጻፀም ሲታይ በእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው የ20 ለማከናወን በታቀደው መሰረት ሁሉም ኦዲቶች ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላኩ፤ በ6 ቀደም ባሉት ክዋኔ ኦዲቶች ላይ የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች አተገባበር ላይ የክትትል ኦዲት ተደረጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ሪፖርታቸው ወጪ የተደረጉት የክትትል ኦዲቱ ሲጨመር ከ100% መሆኑን ያሣያል፡፡

የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁት 20 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶችና የ6 የክትትል ኦዲት ሪፖርቶቹ ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ ዋና ዋና ግኝቶች በአጭሩ ቀጥሎ ከገጽ 76 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

## 2.4 <u>አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት</u>

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የ2009 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡

### 2.4.1 በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ ያልተተካ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ ሪፖርት መግለጫ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4202 ላይ ሪፖርት የተደረገው ብር **6,989,606.85** በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ የተከሰተ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት መሆኑ ታውቋል፡፡ በጉድለት ከሚታየው ጥሬ ገንዘብ ውስጥ ብር **5,906,964.33** ቀጥሎ በተመለከቱት 8 መ/ቤቶች ላይ የሚፈለግ መሆኑ ታውቋል፡፡

| | |
|---|---|
| 1. የትምህርት ሚኒስቴር | ብር 2,051,111.31 |
| 2. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር | 2,438,996.79 |
| 3. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ግምሩክ ባለስልጣን | 462,610.74 |
| 4. ወለጋ ዩኒቨርስቲ | 260,478.13 |
| 5. የሀገር መከላከያሚኒስቴር | 243,487.77 |
| 6. የሰመራ ዩኒቨርስቲ | 123,599.27 |
| 7. የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር | 206,555.32 |
| 8. ብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት | 120,125.00 |

ከላይ ከተራ ቁጥር 1. እስከ 6 ድረስ በተጠቀሱት መ/ቤቶች ላይ የሚታየው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንዲተካ ከዚህ ቀደም በቀረበው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ታውቋል፡፡

### 2.2.2 ውዝፍ ተንጠልጣይ ሂሳብ

በፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ ሪፖርት መግለጫ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4201 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ብር **125,100,183.60** ውዝፍ ተንጠልጣይ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ በውዝፍ ከሚታየው ተንጠልጣይ ሂሳብ ውስጥ ብር **87,921,154.64** ቀጥሎ በተመለከቱት 8 መ/ቤቶች ላይ የሚፈለግ መሆኑ ታውቋል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. የውሀና መስኖ ኢነርጂ ሚኒስቴር | ብር | 3,705,851.11 |
| 2. የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር | | 11,360,225.74 |
| 3. የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ | | 12,552,792.13 |
| 4. የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ | | 3,441,603.42 |
| 5. ደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ | | 21,885,312.36 |
| 6. ጅጅጋ ዩኒቨርስቲ | | 6,518,273.23 |
| 7. የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ | | 10,109,926.35 |
| 8. ብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት | | 8,347,170.30 |

ከላይ ከተራ ቁጥር 1. እስከ 4. ድረስ በተዘረዘሩት መ/ቤቶች የሚገኘው ተንጠልጣይ ሰነድ እንዲወራረድ ካልሆነም ገንዘቡ እንዲሰበሰብ ከዚህ ቀደም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ እንዲተካ እንዲሁም ውዝፍ ተንጠልጣይ ሂሳብ እንዲወራረድ ካልሆነም ገንዘቡ እንዲመለስ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

**የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ**

- **በገቢ ዕቅድ ተይዞ ያልተሰበሰበ ገቢ**

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 10ለ የሂሳብ መግለጫው የሂሳብ አያያዝ ስርአቱን፡የአገር ውስጥ ገቢ በጀት ከተሰበሰበው ጋር ገቢ እና እርዳታ የታወጀ በጀት ከተስተካከለው በጀት እና ከወጪው ጋር ተነጻጽሮ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ በየገቢ አርዕስቱ ተለይቶ በዕቅድ የተያዘው ገቢ በዕቅዱ

መሰረት የተሰበሰበ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ ከታች በተዘረዘሩት የገቢ አርእስቶች ብር **46,499,543.00** ለመሰብሰብ የታቀደ ቢሆንም ምንም ዓይነት ገቢ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል)

| **ተ.ቁ** | **የሂሳብ መደብ** | **መግለጫ** | **ለመሰብሰብ የታቀደ ገቢ** | **የተሰበሰበ ገቢ** |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 1211 | የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | 3,000.00 | 00 |
| 2 | 1212 | የፕላስቲክ ምርቶች | 16,252,028.00 | 00 |
| 3 | 1234 | የጽሕፈት መሳሪያዎች | 7,111.00 | 00 |
| 4 | 1254 | ጸጉር ማስተካከል እና የቁንጅና ሳሎን | 1,259.00 | 00 |
| 5 | 1269 | ሌሎች አገልግሎቶች | 2,967.00 | 00 |
| 6 | 1385 | ምግብ | 29,633,178.00 | 00 |
| 7 | 1432 | የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች | 600,000.00 | 00 |
| ድምር | | | **46,499,543.00** | |

በእቅድ የተያዘው ገቢ ሊሰበሰብ ያልተቻለበት ምክንያት ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት የእርምት እርምጃ እንዲደረግ ለወደፊቱም የገቢ ዕቅድ በታቀደው መሰረት እየተከናወነ ለመሆኑ ከክንውኑ ጋር በየጊዜው በመገምገም በገቢ ዕቅድ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሄ መሰጠት እንዳለበት አሳስበናል፡፡

- **በገቢ ዕቅድ ሳይካተት የተሰበሰበ ገቢ**

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል5 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2ሀ መሰረት አመታዊ በጀት ሲዘጋጅ በበጀት አመቱ ውስጥ ሊሰበሰብ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ሊይዝ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በ2009 በጀት አመት ውስጥ ከመንግስት ኢንቨስትመንት ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ እንዲሁም ከውጭ ሀገር ብድርና

እርዳታ ሊገኝ የሚችለው ገቢ ሙሉ በሙሉ አስቀድሞ በገቢ በጀት ዕቅድ የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከመንግስት ኢንቨስትመንት ብር 40,388,466.41 ከሃገር ውስጥ ገቢ ብር 422,462,219.77 በድምሩ ብር **462,850,686.18** ገቢ የተገኘ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ የገቢ በጀት ዕቅድ ሳይያዝ የተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል)

| ተ. ቁ | የገቢ ሒሳብ መደብ | የገቢ ምንጭ | በ2009 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ ያልተያዘ ገቢ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| | | **የመንግስት ኢንቨስትመንት** | | |
| 1 | 1461 | ሞኤንኮ ኩባንያ | 13,670,856.00 | |
| 2 | 1461 | ሜድሮክ ወርቅ አምራች ድርጅት | 26,717,610.41 | |
| | | ድምር | | 40,388,466.41 |
| | | **ከሃገር ውስጥ ገቢ** | | |
| 3 | 1119 | ሌሎች ገቢዎች | 824,799.33 | |
| 4 | 1299 | ሌሎች የቴምብር ቀረጥ | 410,220,496.71 | |
| 5 | 1422 | የደረጃዎች ምደባ ክፍያ | 11,416,923.73 | |
| | | ድምር | | 422,462,219.77 |
| ጠቅላላ ድምር | | | | **462,850,686.18** |

ስለሆነም የበጀት ዓመቱ የገቢ እቅድና ዝግጅት በጥናትና በበቂ መረጃ የተደገፈ ሊሆን እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

➢ **ከገቢ እቅድ በታች የተሰበሰበ የኢንቨስትመንት ገቢ**

በ2009 በጀት ዓመት ከመንግስት የልማት ድርጅቶች መሰብሰብ ያለበት ገቢ በታቀደው መሰረት የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በበጀት አመቱ በበጀት አመቱ ከብሔራዊ ሎቶሪ ድርጅት ይገኛል ተብሎ የታቀደው ብር 187,770,000.00 ሲሆን የተሰበሰበው ገቢ ግን ብር 101,988,508.94 በመሆኑ ክንውኑ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር በብር 85,781,491.06 (46%) አንሶ ተገኝቷል፡፡

የተሰበሰበው ገቢ በታቀደው መሰረት ለምን እንዳልተሰበሰበ በማጣራት በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ለወደፊቱም በጥናትና በመረጃ የተደገፈ የገቢ መሰረተ ግምት እንዲዘጋጅ ሆኖ የገቢ እቅዱ ከክንውኑ ጋር በየጊዜው እየተገመገመ ወቅታዊ የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል ፡፡

➢ **ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ እና ትርፍ**

**ድርሻ በእቅዱ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ**

በ2009 በጀት ዓመት ውስጥ ቀደም ብለው ከተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ገቢ፤በበጀት አመቱ ከሚሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ገቢ፤ከተሸጡ ድርጅቶች የሊዝ ክፍያ ፤ከልማት ድርጅቶችና ወደ ግል ከተዛወሩ ድርጅቶች የብድር ተመላሽ በድምሩ ብር **1,162,460,000.00** ለመሰብሰብ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ከተገኘው ገቢ ብር **663,410,000.00** ብቻ በመሆኑ የገቢ እቅዱ ከክንውኑ ጋር ሲነጻጸር በብር **499,050,000.00** የሚያንስ መሆኑ ታውቋል፡፡

| **ተ.ቁ** | **የመ/ቤቱ ስም** | **የበጀት ዓመቱ ዕቅድ** | **የበጀት ዓመቱ ክንዉን** | **ክንውን ከዕቅድ በማነስ** |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቀደም ብሎ ከተሸጡ የመንግስት ልማት ድርጅቶች የሚሰበሰብ ገቢ | 971,140,000.00 | 648,040,000.00 | 323,100,000.00 |
| 2 | ከልማት ድርጅቶችና ወደ ግል ከተዛወሩ ድርጅቶች የብድር ተመላሽ | 183,790,000.00 | 13,980,000.00 | 169,810,000.00 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | ከተሸጡ የልማት ድርድቶች የሊዝ ክፍያ | 7,530,000.00 | 1,390,000.00 | 6,140,000.00 |
| | ጠቅላላ ድምር | **1,162,460,000** | **663,410,000.00** | **499,050,000.00** |

የተሰበሰበው ገቢ በታቀደው መሰረት ለምን እንዳልተሰበሰበ በማጣራት በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ለወደፊቱም በጥናትና በመረጃ የተደገፈ የገቢ መሰረተ ግምት እንዲዘጋጅ ሆኖ የገቢ እቅዱ ከክንውኑ ጋር በየጊዜው እየተገመገመ ወቅታዊ የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

- **ከመልሶ ማበደር ያልተሰበሰበ የብድር ወለድ ገቢ**

መንግስት ከውጭ ሀገር በብድር ያገኘውን ገንዘብ በመልሶ ማበደር ስምምነት መሰረት ለልማት ድርጅቶች የሚያበድር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ተበዳሪዎች ከመንግስት የተበደሩትን ገንዘብ በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ ከሁለት ድርጅቶች ላይ፡-

1. ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የብድር ወለድ ብር 19,584,410.83
2. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የብድር ወለድ 619,263,691.96

በድምሩ ብር 638,848,102.79 የብድር ወለድ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡
ከላይ ከተመለከተው የብድር ወለድ ውስጥ ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የሚፈለግ የብድር ወለድ ብር 10,082,479.19 ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የሚፈለግ የብደር ወለድ ብር 174,456,726.04 እንዲሰበሰብ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው የ2007 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ከውጭ ሃገር በብድር የተገኘው ገንዘብ በመልሶ ማበደር ስምምነት መሰረት ብድር የተሰጣቸው ድርጅቶች ዋናውን ገንዘብና ወለዱን ጭምር በገቡት የግዴታ ውል መሰረት ክፍያ እንዲፈጽሙ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

- **የ2008 በጀት ዓመት ትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ሳይቀርብ ገቢ የተደረገ ሂሳብ**

በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 ክፍል 6 አንቀጽ 28 ቁጥር 2 እና ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 730/2004 አንቀጽ2(1) ከተመለከቱት የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮኖቻቸው ሙሉ በሙሉ በመንግስት ከተያዙ የአክሲዮኑ ማህበራት የተጣራ ትርፍ እንዲሁም ሽያጭ ገቢ እንደሚደረግ ተመልክቷል። ይሁን እንጂ በመንግስት ከተያዙ ድርጅቶችና በመንግስት የአክሲዮን ድርሻ ካላቸው ማህበራት እና ከመንግስት የማዕድን ሥራዎች ድርሻ ከሦስት ድርጅቶች ብር ብር **98,070,677.42** የተሰበሰበ ቢሆንም የድርጅቶቹ የ2008 በጀት ዓመት የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ያልቀረበ በመሆኑ የተሰበሰበው ገቢ መንግስት ማግኘት በሚገባው ልክ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም።(ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል)

| ተ.ቁ | የድርጅት ስም | ብር |
|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት | 3,000,000.00 |
| 2 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር | 68,353,067.01 |
| 3 | ሜድሮክ ወርቅ አምራች ድርጅት | 26,717,610.41 |
| | ድምር | **98,070,677.42** |

ስለሆነም ድርጅቶቹ በመንግሰት የሚፈለግባቸውን ገንዘብ በሙሉ ገቢ ለማድረጋቸው የተጣራ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሆኖ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ ገቢ ማድረግ በነበረባቸው ልክ ለመሆኑ እንዲረጋገጥ አሳስበናል።

- **ለመንግስት ፈሰስ ያልተደረገ የተጣራ ትርፍ**

በመንግስት የኢንቨስትመንት ገቢ መሰረት የተጣራ ትርፍ ያገኙ ድርጅቶች ያገኙትን የተጣራ ትርፍ በመመሪያው መሰረት ሙሉ በሙሉ ፈሰስ ማድረግ እንዳለባቸው ተመለክቷል፡ ይሁን እንጂ አምቼ የተባለው ድርጅት ባቀረበው የ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ ኦዲት ሪፖርት መሰረት ካገኘው የተጣራ ትርፍ ብር 28,458,779.00

ውስጥ( 30 %) የመንግስት ድርሻ ብር 8,537,633.70 ወደ መንግስት ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታወቋል፡፡

የተጣራ ትርፍ ያገኙ ድርጅቶች ያገኙትን ትርፍ ወደ መንግስት ማዕከላዊ ግምጃ ቤት በወቅቱ ፈሰስ እንዲያደርጉ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

### 8.2 የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ

➢ **ተቀጽላ ሌጀር የሌለው የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳብ**

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 በሂሳብ መዝገብ ላይ  ምዝገባ የተከናወነለት ሂሳብ በየሂሳብ መደቡ ተለይቶ በሂሳብ ሌጀር ላይ መመዝገብ እንዳለበት ያዛል፡፡በዚሁ መሰረት የበጀት ዓመቱ ሂሳብ ሪፖርት ሲዘጋጅ ለተሰብሳቢ እና ለተከፋይ ሂሳቦች ተገቢው  ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶላቸው በአግባቡ የሚያዙ መሆኑን እና ተገቢው ክትትል የሚደረግ  መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

- ከ2008 በጀት ዓመት የዞረ በድምሩ ብር **40,808,723.76** በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4209 እና 4210 ለ2009 በጀት ዓመት የመነሻና የመክፈቻ ሂሳብ ተብሎ የተመዘገበ ቢሆንም ተቀጽላ ሌጀር የሌለው በመሆኑ ተሰብሳቢው ሂሳብ የቆየበት ጊዜ የባለዕዳው ስም ወይም ከማን ላይ እንደሚሰበሰብ ባለመገለጹ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ከላይ በተጠቀሰው የተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምት ያልተደረገበት መሆኑ ታውቋል፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ ከ2008 በጀት ዓመት የዞረ  ብር **1,801,530.99** በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5054 ለ2009 በጀት ዓመት የመነሻ ሂሳብ ተብሎ የተመዘገበ ተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ ቢሆንም ተቀጽላ ሌጀር የሌለው በመሆኑ ተከፋይ ሂሳቡ የተከሰተበትና ፡ የቆየበት ጊዜ እንዲሁም ባለጥቅሙ ባለመገለጹ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ከላይ በተጠቀሰው የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳብ ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምት ያልተደረገበት መሆኑ ታውቋል፡፡ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | ቀን | የባንክ ሂሳብ | የሂሳብ መደብ | መግለጫ | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 01/11/2008 | C1 | 4209 | የተሰብሳቢ ሂሳብ መነሻ | 8,269.99 |
| 2 | 01/11/2008 | C8 | 4209 | ›› ›› | 40,000,453.77 |
| 3 | 01/11/2008 | E2 | 4210 | ›› ›› | 800,000.00 |
| **የተሰብሳቢ ሂሳብ ድምር** | | | | ›› ›› | **40,808,723.76** |
| 1 | **01/11/2008** | C30 | **5054** | የተከፋይ ሂሳብ መነሻ | 1,801,530.99 |
| **የተከፋይ ሂሳብ ድምር** | | | | | **1,801,530.99** |

ከላይ የተጠቀሱት የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳቦች ዝርዝር መረጃ በማጣራት መረጃው በጥንቃቄ እንዲጠበቅ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም የሚመለከታቸው የበላይ አካሎች ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡ አስገንዝበናል፡፡

2.5 **<u>የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጄክት</u>**

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተም የ2009/2010 ኦዲት ዓመት በ251 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና ከተማ አስተዳደር፣ በክልል ደረጃ)፣ ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋዊ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፤ በኦዲት ዓመት የ251 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተከናውነው ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ተልኳል፡፡ በሌላም በኩል መ/ቤቱ ከመሠረታዊ አገለግሎት ከለላ ኦዲት በተጨማሪ የወረዳዎች የፍትሃዊ የሃብት ተጠቃሚነት የ“Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service” ፕሮግራም ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ መለኪያዎችን የማረጋገጥ ጥያቄዎች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሲቀርብ የማረጋገጥ ሥራው ያካናውናል፡፡ በዚሁ መሠረት 8 ኦዲቶችን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 16 የኦዲቶች ሥራ ተጠናቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የማረጋገጥ ኦዲት ሪፖርት ቀርቧል፡፡

## 2.6 የልዩ ኦዲት ስራዎች

በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በተለያዩ አካላት ጥያቄ 11 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 4 ሥራቸው ተጠናቅቆ የአንዱ ሪፖርት ሪፖርቱ ለጠያቂ አካል የተላከ ሲሆን ሌሎቹ በቅርቡ የሚላኩ ይሆናል፡፡ የቀሪዎቹ ሥራ በመፈጠን ላይ ይገኛል፡፡

## 2.7 የኦዲት ጥራትና ሌሎች የኦዲት ሥራዎች

በመ/ቤቱ የሚከናወኑ ኦዲቶች ደረጃቸውንና ጥራታቸውን ጠብቆ እንዲሠሩ የዚህ ዓመት ዕቅድ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን የኦዲት ጥራት የሥራ ክፍልም ይህንኑ መሠረት በማድረግ የቅድመ እና የድህረ ኦዲት ቁጥጥር ሥራዎችን ለማከናወን አቅዷል፡፡

በዚህም መሠረት የኦዲት በጀት ዓመት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ተግባራት በአራት ደረጃዎች ማለትም ቅድመ ኦዲት፤ የኦዲት ስትራቴጅክ እቅድ ደረጃ፤ የዝርዝር ኦዲት ስራ እና የሪፖርት ማቅረቢያ ደረጃ በሚል ተከፋፍሎ የሚከናወን ሲሆን የኦዲት የሥራ ደረጃዎችን የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ ሥራዎችም ይህንኑ ደረጃዎችን ተከትሎ የሚሠራና የሚፈጸም ሲሆን የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ ሥራዎች ደግሞ ሥራው ሣይጠናቀቅ በሂደት ላይ እንዳለ (pre-issuance) ወይንም የኦዲት ሥራው ከተጠናቀቀና ሪፖርት ወጭ ከሆነ (post issuance) በኋላ ሊከናወኑ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት በ2009/10 ዓመት የኦዲት ጥራትን ከማረጋገጥ አንጻር በእያንዳንዱ የኦዲት ቡድን ደረጃ የሚሠራው ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ገለልተኛ በሆነና በኦዲት ሥራው ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ በሌለው ቡድን የሚከተሉት ሥራዎች ታቅደው ተፈጽሟል፡፡ በዚህም መሠረት አፈጻጸሙን በተመለከተ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

በ12 መ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ላይ በስትራቴጂክ እቅድ የኦዲት ደረጃ ሥራዎች በኦዲት ሂደት ላይ እያሉ የኦዲት ጥራት ለማረጋገጥ ታቅዶ 8ቱ ሥራዎች የጥራት ማረጋገጥ ሥራው ተጠናቆ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡ እንደዚሁም በ12 መ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊናት ኦዲት ላይ በዝርዝር እቅድ የኦዲት ደረጃ ሥራዎች በኦዲት ሂደት ላይ እያሉ የኦዲት ጥራት ለማረጋገጥ ታቅዶ ሥራው በ9 መ/ቤቶች ላይ የጥራት ማረጋገጥ ሥራው ተጠናቆ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡ ነገር ግን  የ4 መ/ቤቶች የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ ክለሳ የስትራቴጂክ ዕቅድ የሥራ ደረጃ ጨርሰው ሪፖርት

ባለማቅረባቸው እንዲሁም የ3 መ/ቤቶች የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ ክለሳ የዝርዝር ዕቅድና የመስክ ሥራ ጨርሰው ሪፖርት ባለማቅረባቸው እንዲሁም በመስክ ሥራ በመጠመዳቸው ምክንያት የጥራት ማረጋገጥ ሥራው በተቀደው ጊዜ አልተሰራም፡፡ ይሁን እንጂ ሥራዎቹ በቅርብ ቀናት የሚጠናቀቁ ይሆናል፡፡ ባለፈው ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ሳይጠቃለሉ ዞረዉ የመጡ 16 ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡

በተቋሙ የኦዲት ጥራት ዳይሬክቶሬት እና በAFROSAI-E peer review ጥራት ማረጋገጥ ሪፖርት መሰረት በስትራቴጂክ እቅድና በዝርዝር እቅድ ላይ የተሰጡ ማሻሻያ ሃሳቦች መተግበራቸውን ለመከታተል ታቅዶ የክትትል ሥራው ከላይ የስትራቴጂክና የዝርዝር እቅድ በተከናወነባቸው መ/ቤቶች ላይ ክትትሉ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በ2007/2008 እና በ2008/2009 በጀት ዓመቶች የጥራት ማረጋገጥ ክለሳ ወቅት በተገኙ ግድፈቶች ላይ ከኦዲት ሥራ አስኪያጆች, ከኦዲት ዳይሬክተሮችና ከመ/ቤቱ ኃላፊዎች ጋር በተለያዩ ቀናት ውይይቶች ተደርጓል፡፡

## 3. <u>ሌሎች ዋና ዋና የዕቅድ ክንውኖች</u>

### 3.1 <u>የመ/ቤቱን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ</u>

የመ/ቤቱ ፋ/ግ/ንብረት አስተዳደር ቀልጣፋና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ መፈጸም፣በቅድሚያ የተከፈሉ ሂሳቦችን /ሰነዶችን/ በፍጥነት ማወራረድ እንዲሁም ክፍያ የተፈፀመባቸውን ሰነዶች መዝግቦና አደራጅቶ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ማስመርመርና ከኦዲተሮች ለሚነሳ ጥያቄ ምላሽ መስጠት፣ሁሉም ግዢዎች በመንግሥት የግዢ አዋጅና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት እንዲፈፀሙ በማድረግ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለው የግዢ ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣ የመ/ቤቱን የግዥ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የግዥ እቅድ አዘጋጅቶ ለግዥ ኤጀንሲ እና ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ማቅረብ፣ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በሚፈለገው ጥራት መጠንና ተመጣጣኝ በሆነ ወጪ ገዝቶ በወቅቱ ማቅረብ በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ የፋይናንስና የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት እና በየወሩ የዜሮ ሚዛን እንቅስቃሴ ሪፖርት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ማቅረብ፣ የመ/ቤቱን ንብረት አጠቃቀምና አያያዝ እንደዚሁም ቁጥጥር ሥርዓት ማጠናከር፣ የክፍሉን ሥራዎች በኢፍሚስ በመታገዝ መስራት ዋና ዋና ሥራዎች ናቸው፡፡

## 3.2 ሥራ ላይ የዋለው በጀት

ከዚህም አንጻር በ2010 በጀት ዓመት ለመ/ቤታችን መደበኛ በጀት ብር 76,443,603.00 እንዲሁም ካፒታል በጀት ብር 52,000,000 በድምሩ ብር 128,443,706 የተፈቀደ ሲሆን መደበኛ በጀት የ9 ወር ዕቅዱ ብር 57,343,384.75 ሲሆን አፈጻጸሙም ግን ብር 53,421,347.64 (93.16%) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የ2010 የመጀመሪያው የ9 ወር የበጀት አጠቃቀም በዋና ዋና የወጪ አርዕሰቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| የሂሳብ መደብ | ለ9 ወር የታቀደ በጀት | የ9 ወር አፈጻጸም | ልዩነት | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|
| 6100 | 44,200,000.00 | 46,559,477.47 | (2,359,477.47) | 105.33% |
| 6200 | 9,031,419.75 | 6,766,243.13 | 2,265,176.62 | 74.91% |
| 6300 | 3,761,340.00 | 78,631.31 | 3,682,708.69 | 2.09% |
| 6400 | 350,625.00 | 16,995.73 | 333,629.27 | 4.84% |
| ድምር | 57,343,384.75 | 53,421,347.64 | 3,922,037.11 | 93.16% |

የዘጠኝ ወር የሥራ ማስኬጃ በጀት አጠቃቀም ከዕቅድ ጋር ሲነፃፀር በሂሳብ መደብ 6300 እና 6400 እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን ለዚህ ዋንኛው መንስኤ የሥራ ማስኬጃ በወቅቱ ጠይቆ ማምጣት ያለመቻል ሲሆን ይህ እንዳይሆን ደግሞ ዋና እንቅፋት የነበረው ከግንቦት 2009 ጀምሮ አዲሱ የIFMIS ስርዓት መተግበር በመጀመሩና ይህ ሥርዓት ደግሞ ከሀምሌ ወር ጀምሮ Online እንዲሆን በመወሰኑና ሠራተኞች ሥልጠና የወሰዱ ቢሆንም ከሥርዓቱ ጋር ሊላመዱ ባለመቻላቸው የስራ ማስኬጃ የመጣው ከነሀሴ አጋማሽ በኋላ መሆኑ፣ የቋሚ ዕቃዎች ግዥ ለመፈጸም በተደገገሚ ጊዜያት ጨረታ የወጠ ቢሆንም ባለመሳከቱ ምክንያት ግዥ በወቅቱ መፈጸም በለመቻሉ እና በዶላር ምንዛር እጥረት በማጋጠሙ ምክንያት የዓለም ዓቀፍ መዋጮ በወቅቱ ለመክፈል በለመቻሉ የተፈጠረ ሲሆን በቀጠዩ ጊዜያት (በአራተኛ ሩብ ዓመት) ሊስተካከል እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

ሒሳብ መዘጋትን በተመለከተ የ2009 በጀት ዓመት ሁሉም በወቅቱ ተዘግቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በዳይሬክቶሬቱ ከሚከናወኑት የመደበኛ ሂሰብ፣ የፒቢኤስ ሂሰብ (PBS)፣ የፒኤፍ ሂሰብ (PFM)፣ የዩኤንድፒ ሂሰብ (UNDP) በኢፍሚስ ተመዝግቦ ወቅታዊ ሪፖርት እስከ መጋቢት 30 ያለው ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት መላክ ተችሏል፡፡ ፋ/ግ/ንብረት አስተዳደር ቀልጣፋና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ ተፈፅሟል፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ሂሳቦችን /ሰነዶችን/ የማወራረድ ሥራ ተሰርቷል፣ በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ የፋይናንስና የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት እና በየወሩ የዜሮ ሚዛን እንቅስቃሴ ሪፖርት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ቀርቧል፡፡

በሌላ በኩል ግዥን በተመለከተ የግዥ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በማኔጅመንትና ግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተገምግሞ ከፀደቀ በኂላ በማፅቀፍና በመ/ቤቱ የሚገዛው ተለይቶ ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተልኳል፡፡ ከዕቅዱም ውስጥ በግልጽ ጨረታ እንዲገዙ ከተወሰኑት ውስጥ አስራ ስምንት ሎቶች ጨረታ ወጥቶ የግምገማ ተከናዉኖ የተወሰኑ ዕቃዎች ግዥ የተፈጸመ ሲሆን የአንዳንዶቹ ጨረታ የሚፈለገውን ደረጃ ባለመሞላቱ ውድቅ ተደርጎ ግዥውን መፈጸም አልታቻለም፡፡ ሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚፈለገው መጠንና ተመጣጣኝ በሆነ ወጪ ከማዕቀፍ ግዥ ተገዝቶ በወቅቱ እንድቀርብ ተደርጓል፡፡ ቀሪው የማዕቀፍ ግዥ በአቅራቢዎች መጋዜን ባለመኖሩ ምክንያት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልገሎት አቅራቢዎችን እንዲለውጥልን በማድረግ ለኦዲቱ ሥራ የሚያስፈልገው ግብዓት እንዲሟላ ለማስቻል እየተሠራ ይገኛል፡፡

በመ/ቤታችን ውስጥ ወደ አዲሱ ቢሮ ከመዛወር ጋር ከፍተኛ የንብረት ክምችት የተፈጠረ ሲሆን የምንጠቀምባቸውን ንብረቶች በተመለከተ አዲሱን የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት IFMIS በመጠቀም ወደ ሲስተም እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ያገለገሉ ንብረቶች ማስወገድን በተመለከተ አገልግሎት የማይሰጡ እጅግ ባርካታ የአይ.ቲ ዕቃዎች በመንግስት ንብረት ማስወገድ መመሪያ መሰረት ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር በመስጠት የተወገዱ ሲሆን ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት መጠነኛ ብልሽት ያላቸዉ ደግሞ ለአፋር፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ አፋር ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በስጦታ እንዲተላለፉ ተደልድሎ የወሰደ

ሲሆን በሌላ በኩል የማንገለገልባቸው ወንበር፣ ጠረጴዛና የመሳሰሉ የቢሮ ዕቃዎችን በተመለከተ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ለአፋር፣ ለቤንሻንጉል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች እንዲሁም መ/ቤታችን ለሚገኝበት የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 በስጦታ ዕቃ የወሰዱ ሲሆን በሌላ በኩል አነስተኛ አቅም ያለውና አሁን ላለንበት ህንፃ የሚያገለግል በቀድሞ ቢሮአችን ስንጠቀምበት የነበረውን ጄነሬተር ለፌዴራል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጅንሲ በስጦታ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ የሚወገዱ አሮጌ ጎማዎችና ባትሪዎችን በተመለከተ በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በኩል እንዲወገዱ ጥያቄ ቀርቦና ተመዝግቦ በመጠባበቅ ላይ ነን፡፡ ከአዳዲስ ተሽከርካሪዎች ጋር መጥቶ ለረዥም ጊዜ ተቀምጠው የነበሩ የመለዋወጫ ዕቃዎች በተመለከተ በመ/ቤታችንም ሆነ በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በኩል በ2009 እና በ2010 ለማስወገድ ተሞክሮ ባለመቻሉ አሁን በስጦታ ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በስጦታ ማስተላለፍ ሥራ ተከናውኗል፡፡

በሌላ በኩል የነዳጅ ቁጥጥሩን ለማገዝ እንዲረዳ ከመስክ ተሽከርካሪዎችና ከበላይ ኃላፊዎች መኪኖች ውጭ ላሉት 20 ተሽከርካሪዎች የተዘጋጀው የቶታል አቢሲኒያ ካርድ ላይ የተፈቀደላቸውን ነዳጅ በመሙላትና በኦንላይን (online) ሲስተም በመቆጣጠር፣ በመመዝገብና ወቅታዊ ሪፖርት መስራት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለመስኪ እንዲሁም በከተማ ውስጥ አገልግሎት ለምሰጡ ሁሉም ተሽከርካሪዎች የተጓዙበት ርቀት የመመዝገብ ሥራና የነዳጅ አጠቃቀም በኖርማላይዜሽን ምጣኔ መሠረት ስለመሆኑ መከታተል እንዲሁም በኩፖን ነዳጅ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ ይገኛል፡፡

### 3.3 <u>የመረጃ አስተዳደርና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ</u>

የመ/ቤቱን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከፍ ለማድረግና ሁሉንም ሥራዎች በIT ለማስደገፍ በርካታ ተግባራት የታቀዱ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በተቋሙ ውስጥ የወረቀት አልባ ሥርዓትን በመተግበር የወረቀት፣ የቀለምና ተያያዥ የጥገና ወጪዎችን ከመቀነስና የመረጃ አያያዝ ሥርዓታችንን ከማጠናከር አንጻር ባለፈው ዓመት የተጀመረውን በቢሮም ሆነ ከቢሮ ውጭ ከኦዲተሮቻችን ጋር የሚደረጉ

የመረጃ ልውውጦች በoutlook አማካኝነት Corporate e-mail system በመጠቀም እንዲከናወን ተወስኖና ሥርዓት ተዘርግቶለት የወረቀትና ተዛማጅ የህትመት ወጪዎችን መቀነስ ከመቻሉም ሌላ የመረጃ ልውውጡ እንዲቀላጠፍ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም ሥርዓት እንዲሆን ማን ይህንን ሲስተም እንደሚጠቀምና እንደማይጠቀም በኢንፎርሜሽን ሲስተም የሥራ ክፍላችን በየቀኑ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱን የአይቲ አስተዳደር (IT Governance) ለማጠናከር አስራ አምስት (15) ሰነዶች ማለትም የአይቲ ስትራተጂ፣ የአይቲ ኦዲት ስትራተጂ፣ የአይቲ አመራር ኮሚቴ ቻርተር፣ የአይቲ መዋቅር፣ የአይቲ አስተዳደር መመሪያ፣ የአይቲ ደህንነት መመሪያ፣ የአይቲ ኦዲት ኦፕሬሽን መመሪያ፣ የመረጃ አያያዝ፣ አስተዳደር፣ አጠቃቀምና የስርጭት መመሪያ፣ የአገልግሎት ቀጣይነትና የአደጋ መከላከያ ዕቅድ፣ የአይቲ የለውጥ አስተዳደር መመሪያ፣ የላፕቶፕ የአጠቃቀም መመሪያ፣ የአይቲ መሣሪያዎች ግዥ መመሪያ፣ የአይቲ ንብረት አስተዳደር ስራ ሂደት መመሪያ፣ የአይቲ የአገልግሎት የውጫዊ (Outsourcing) መመሪያ፣ የአይቲ አደጋ ዳሰሳና የአስተዳደር ዕቅድ ተቀርፀው፣ ተገምግመውና በሚፈለገው መጠን ተሻሽለው ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ ስራዎችና ክትትሎች ተደርጓል፣ ከነዚህ ሰነዶች ውስጥም አስር (10) ሰነዶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በመ/ቤቱ የበላይ አመራሮች ፀድቀው ተግባራዊ መሆን እንዲችሉ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

የአይቲ ኦዲትን በመ/ቤቱ ውስጥ በማቋቋምና አንድ እርምጃ ወደፊት በማራመድ የኦዲት ሽፋናችንን ለማሻሻልና ለማጠናከር የተለያዩ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የአይቲ ኦዲት ስትራቴጂዎችን የመንደፍ፣ ማኑዋልን የማዘጋጀት፣ የኦዲት ቡድኑን የማደራጀት፣ የኦዲት ቡድኑን አቅም የመገንባት፣ ልምዶችን የማዳበርና ወደ ሙከራ የአይቲ ኦዲት ስራ እንዲገቡ የማድረግ ስራዎች ይገኙበታል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአሁኑ ሰዓት የመጀመሪያው የሙከራ የአይቲ ኦዲት በፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ተከናውኖ በጥሩ ሁኔታ ሪፖርቱ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን ሁለተኛው የአይቲ ኦዲት ደግሞ በንግድ ሚኒስቴር በተያዘለት ዕቅድ መሰረት በመስክ የስራ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱን ስራ በተቀላጠፈ ሁኔታ በቴክኖሎጂ ለማገዝ የተለሙ፣ የተሻሻሉና ለትግበራ ዝግጁ የሆኑ ስምንት (8) ስርዓቶችን ማለትም የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የሪከርድና ማህደር፣ የላይብረሪ፣ የአይቲ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የውጤት ተኮር፣ የኦዲት አስተያየት መከታተያ፣ የኢ-ለርኒንግና የኦዲት ስልጠና አስተዳደር ስርዓቶችን ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ለማዋል ስርዓቶቹን የመፈተሽ፣ መረጃዎችን የማደራጀት፣ ተጠቃሚዎቹን የማብቃትና ድጋፍ የማድረግ በርካታ ስራዎች ተሰርቷል። አተገባበራቸው ውጤታማ እንዲሆንም ክትትል እየተደረገ ይገኛል።

አዲስ የመረጃ ማዕከል ግንባታ ለማከናወን ከዲፊድ በተገኘ ድጋፍ የመረጃ ማዕከሉን ፕሮጀክት ከፍላጎት ጥናት እስከ ትግበራ፣ ክትትልና የሰው ሃይልን እስከ ማብቃት ድረስ ተቀርፆ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ የሚገኝ ሲሆን ለመረጃ ማዕከሉ ግንባታና ዝርጋታ የሚያገለግሉ የፕሮጀክቱ ከ80 ፐርሰንት በላይ የሆኑ በርካታ ዕቃዎችም ወደ መ/ቤቱ የገቡና ትግበራውም በሂደት ላይ ይገኛል።

አዲሱን የመረጃ ማዕከል ግንባታ በማጠናከር የመ/ቤቱን የኦዲትና ተያያዥነት ያላቸውን በርካታ የስራ ሂደቶች የሚያቀላጥፉና የሚያግዙ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማለትም የአይቲ ቴሌፎን፣ የቪዲዮ ኮንፈረንስ፣ የህንፃ ሰርቪላንስ፣ አይፒ ቲቪ፣ የተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ መልዕክቶችን ማስተላለፊያ፣ የኢ-ለርኒንግ፣ የሰዓት መቆጣጠሪያ፣ የኢሜል ስርዓት ማሻሻያ፣ የመረጃ አስተዳደር፣ የስራ ግንኙነት ስብሰባዎችንና ውይይቶችን ማስተናገጃ፣ የመረጃ ቋት፣ የመኪኖችን ስምሪት ማስተዳደሪያ፣ የአንቲ-ቫይረስ ሶፍትዌርና ተያያዥነት ያላቸውን የአይቲ መገልገያ መሳሪያዎችን ለማስተዋወቅ፣ ለማደስና ተግባራዊ ለማድረግ ከፍላጎት ጥናት እስከ ግዥ ሂደት የመከታተል በርካታ ስራዎች ተሰርቷል።

በመ/ቤቱ ውስጥ የኦዲት ስልጠና ማዕከልን ለማደራጀትና ለማጠናከር ለአምስት ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ የአይቲና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች፣ ፈርኒቸሮችና የስልጠና ክፍሎቹን የዝርጋታ ስራዎች ከዲኤፍአድ በተገኘ ድጋፍ የስልጠና ማዕከሉን የማቋቋም ስራዎች ተሰርቷል።

በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ኮንስትራክሽንና አስተዳደር ቢሮ በኩል ለመ/ቤቱ እየተከናወነ ያለውን የኔትወርክ ዝርጋታ ፕሮጀክት ስራን የማስተባበርና የመከታተል ስራዎች ተሰርቷል፡፡

በተጨማሪም በመ/ቤቱ ውስጥ ተግባራዊ ሆነው አገልግሎት እየሰጡ ያሉትን ስድስት (6) ስርዓቶችን ማለትም የኮርፖሬት ኢሜይሉን (Outlook)፣ ድረ-ገፁን፣ የስርዓቶች ፖርታልን (መግቢያን)፣ የኢፍሚስ ስርዓትን፣ የአይቤክስ ስርዓትንና የኢንተርኔት አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆኑና አገልግሎታቸው እንዳይቋረጥ የክትትልና የድጋፍ ስራዎች ተሰርቷል፡፡

የመ/ቤቱን ተሽከርካሪዎች የሥምሪት አሰራራቸውንና ቁጥጥሩን ለማገዝ የሚረዳ ሥርዓት (Fleet Management System (GPS)) ለመዘርጋት አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና የግዥ ሂደቱን የመከታተል ስራ ተሰርቷል፡፡ አጠቃላይ የኦዲት ግኝቶችን በማዕከለዊ የመረጀ ቋት ማሰበሰብና ግኝቶች ላይ ክትትል ማድረግ የሚችል ሥርዓት (Audit Recommendation Tracking System) ለመዘርጋት በጥናቱ መሰረት ስርዓቱ እንዲለማ የማስቻልና ሲስተሙን በመገምገም እንዲስተካከሉ የተሰጡ ግብአቶቸንና ሲሰተሙን ያለበትን ሁኔታ የመከታተል ለሲስተሙ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመጠቀሚያ ማኑዋል፣ የሲስተም አስተዳደር ማኑዋልና የስልጠና ማኑዋል እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል በተለያዩ የሬጎላሪቲና የክዋኔ ኦዲቶች ላይ ከአይቲ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የማማከር ስራዎች ተሰርቷል፡፡ የአይቲ ኦዲተሮች ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ ኦዲት ማከናወን የሚያስችላቸውን አቅም የመገንባት የሚከናወነውን ኦዲት አለም አቀፍ ደረጃዎችን የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ በኦዲቱ የሚገኙ የአሰራር ክፍተቶች በበቂ መረጃ የተደገፉ እንዲሆኑና ኦዲቱ በበቂ ክትትል የታገዘ እንዲሆን ለማድረግ በርካታ ስራዎች ተሰርቷል፡፡

በሌላ በኩል የተበላሹ የኣቲ ዕቃዎችን ጠግኖ ሥራ ላይ ከማዋል አንጻር የሃርድዌር (ላፕቶፕ፣ ዴስክቶፕ፣ ፕሪንተር፣ ኮፒየር፣ ማባዣ) ቅድመ ጥገና ስራዎችን፣ የሶፍትዌር ቅድመ ጥገና ስራዎች፣ በስቶር ውስጥ ያሉ የሃርድዌሮችን (ላፕቶፕ፣ ባትሪ፣ ቻርጀር፣ ፕሪንተር፣ ድስክቶፕ) በመለየት የቅድመ ጥገና ስራዎች፣ እና

ከተጠቃሚዎች በሚመጡ ጥያቄዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መገልገያ መሳሪያዎች ላይ የፍተሻ ስራዎችን የማከናወንና የድጋፍ ስራዎች በመሠራት ላይ ናቸው፡፡

## 3.4 አደረጃጀትና የሰው ሀይል አቅም ግንባታ በተመለከተ

የሰው ሀብት ሥራ አመራር እና አቅም ግንባታ አንጻር በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት በማድረግ የአደረጃጀትና መዋቅር ጥናት ማዘጋጀት፤ የመ/ቤቱን የማስፈፀም አቅም በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፤የመ/ቤቱን ሠራተኞች ለማብቃት እና ለማስተዳደር የሚያስችል የምዘና፣ የሰው ሀብት ዕውቀትና ክህሎት እንደዚሁም ሥነ-ምግባርና አመለካከት የሚያሳድጉ ሥራዎችን በማከናወን በዋነኛነት የሠራተኛውን አመለካከትና ቁርጠኝነት በማሳደግ በሙሉ አቅሙ ለተልዕኮው ስኬት እንዲረባረብ ማድረግ በ2010 ቁልፍ ሥራዎቻችን ተደርጎ ታቅዷል፡፡

ከዚህ አንፃር ለመ/ቤቱ የተፈቀደ የስራ መደብ ለኦዲት ባለሙያ 645 እና ለድጋፍ ሰጪ 314 በድምሩ 959 ሲሆን መጀመሪያው ተግባር ተደርጎ የተወሰደው የመ/ቤቱ የሰው ኃይል አቅርቦት ማሻሻል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በዘጠኝ ወር ውስጥ 87 ኦዲተሮችንና 23 የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን በድምሩ 110 ሠራተኞች ተቀጥረው ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በመ/ቤቱ ውስጥ ያሉትም ነባር ሠራተኞች እንዲረጋጉና ተስፋ እንዲሰንቁ ለማስቻል በዘጠኝ ወር ውስጥ 49 ኦዲተሮች እና 2 የድጋፍ ዘርፍ በድምሩ ለ51 ሠራተኞች የደረጃ ዕድገት ተሰጥቷል፡፡ በእኚህ በተወሰዱ እርምጃዎች የተነሳ የመ/ቤቱን የሰው ኃይል ቁጥር 3ቱን የበላይ ሀላፊዎች ጨምሮ 633 ማድረስ የተቻለ ሲሆን አሁን ያለው ሠራተኛ በዘርፍና በፆታ ሲታይ ደግሞ የሚከተለውን ገጽታ ያሳያል፡፡ የበላይ አመራር በድምሩ 3 ሲሆን ወንድ 1 ሴት 2 በኦዲት ዘርፍ በአጠቃለይ 418 ሠራተኛ ያለ ሲሆን ከፆታ አንጻር ሲታይ ደግሞ ወንድ 279 ሴት 139 ናቸው፡፡ በአንፃሩ የድጋፍ ዘርፍ ወንድ 96 ሴት 116 በድምሩ 212 ሠራተኞች በሥራ ላይ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በዘጠኝ ወሩ ውስጥ ከኦዲት ዘርፍ 49 ከድጋፍ ዘርፍ 9 በድምሩ 58 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ እና በዲሲፒሊን የለቀቁ መሆናቸው ታውቋል፡፡ በአጠቃላይ ለመ/ቤቱ ከተፈቀደለት የሥራ መደቦች ውስጥ 326

የሥራ መደቦች በሰው ሃይል ያልተሸፈኑ መደቦች ሲሆኑ እነኝህን ክፍት የሥራ መደቦችን ለመሙላት መ/ቤቱ በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል የመ/ቤቱን የማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት በማድረግ የመ/ቤቱ ሰራተኞች ደንብ ተዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲላክ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም የአደረጃጀትና መዋቅር ጥናት በማዘጋጀትና በማጠናቀቅ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡

የመ/ቤቱ ሠራተኛ ልምድና ክህሎት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ባለመሆኑ ረጅምና አጭር ጊዜ ዕቅድ ተይዞ ሥራዎች በመሠራት ላይ ሲሆን በረጅሙ ጊዜ በተለይ ለኦዲት ሠራተኞች ድጋፍ በማድረግ Professional Accountancy ትምህርትን ተከታትለው Professional Auditors እንዲሆኑ ማስቻል ሲሆን ከዚህ አንጻር ማስታወቂያ ወጥቶ የተወሰኑት ተመልምለው ትምህርቱን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡ በመ/ቤቱ ድጋፍ ሁለተኛ ድግሪ በመማር ላይ የነበሩ 4 ሠራተኞች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡

ከአጭር ጊዜ አንጻር ቀጣይነት ያለው ሥልጠና ለመስጠት እንዲያስችል በብሪታኒያ መንግሥት ድጋፍ እየተደራጃ ያለውን ሥልጠና ማዕከልና ማቴሪያል በመጠቀም ተቀማጭነቱ ብሪታኒያ ሀገር በሆነው Certified Institute of Public Finance Accountants (CIPFA) አማካይነት የአሠልጣኞች ሥልጠና በመስጠት በሥልጠናው ላይ የተሳተፉት በተቋሙ አማካይነት ፈተና እንዲሰጣቸው ተደረጎ ቋሚ አሳልጣኞች እስከሚቀጠሩ ድረስ ወደፊት የሚሰጡ ሥልጠናዎችን የሚሰጡ ሠራተኖች ተለይቷል፡፡ በዚህም መሠረት በሥልጠናው ከተሳለፉት 75 ሠራተኞች መካከል 30 የሚሆኑት ፈተናውን በማለፈቸው ተመርጧል፡፡

በሌላ በኩል በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ይህንኑ ያልተደራጀውን ማዕከል በመጠቀም በድምሩ 416 ለሚሆኑ ሠራተኞች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡ ዝርዝር የሥልጣና መስክና የሠልጣኞች ብዛት በፆታ ጭምር ተዘርዝሮ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በሌላ በኩል የመ/ቤቱን የሰው ሀብት፤ የቤተ-መጽሀፍትና መዝገብ ቤት ሥራዎችን በመረጃ ቴክኖሎጂ የማስደገፍ ሥራዎች ተጀምረው መረጀዎችን ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ሥራ ተጠናቋል፡፡ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሠራተኞች የትምህርት ዕድል በማፈላለግ በማንዴላ፤ በሰሌክት፤ዳሎል፤ማይክሮ፤ኩዊንስ እና ጌጅ ኮሌጅ የርቀት ትምህርት ለ22 ሠራተኞች የትምህርት ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ነገር ግን ወደ ሥርዓቱ የገቡትን መረጃዎች የማጥራትና በተለይ የሰው ሀብት መረጃው በእያንዳንዱ ሠራተኛ እንዲረጋገጥ የማድረግ ተግባራት ተጀምሮ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ቤተ መጽሀፍትንና መዝገብ ቤትን በተመለከተ ሥርዓቱ ከለማ የቆየ በመሆኑ በተፈለገው መንገድ ሊሄድ ባለመቻሉ የራሱ የሆነ መፈትሄ የሚፈለግ ይሆናል፡፡

## 3.5 <u>ከውጭና ህዝብ ግኘኙነት አንፃር</u>

የውጭና የሕዝብ ግንኙነት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ተልዕኮ፤ ራዕይና ዓላማዎችን ለማሳካት በሚደረገው ርብርብ ሁሉን አቀፍ የኮሙኒኬሽን አግባቦችን በመጠቀም የውስጥና የውጭ ኮሚኒኬሽን ተግባራትን በማከናወን የተቋሙን መልካም ገፅታ ለመገንባት፣ ወቅታዊና ትክክለኛ የተቋሙን መረጃ ለሠራተኛው፣ ለባለድርሻ አካላትና ለህብረተሠቡ እንዲደርሳቸው በመስጠትና በማሳወቅ በኦዲት ውጤቶች ላይ የጋራ መግባባት በመድረስ ተግባራዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችል የህዝብ ግንኙነት ሥራዎችን መሥራት ዋነኛዎቹ ናቸዉ፡፡

ከተልዕኮውም አንጻር በተለያዩ መረጃ ለሚፈልጉ ተገልጋዮች መረጃ መስጠት፤ የተለያዩ መድረኮችን ማስተባበር፣ ዜናዎችና መረጃዎችን በማዘጋጀት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የኦዲዮ ቪዥዋል ሥራ መሥራት፤ ሚዲያ ሞኒተር ማድረግና ተደራሽ ማድረግ፣ መረጃዎችን በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በአግባቡ ማደራጀትና ጥቅም ላይ ማዋል፣ለዘገባዎች ምላሽ መስጠት፣የሶማሊያ ሪፐብሊክ መንግስት የዋና ኦዲተር መ/ቤት የልዑካን ቡድን ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፤ ከተለያዩ ምዲያዎች ጋር ቃላ ምልልስ ስራ ተሰርቷል፤ ከመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ለኢትዮጵያ ዓመታዊ መፅሔት መረጃ የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡ 21 ዜና መጽሄቶች ተዘጋጅተው ለተቋሙ ሠራተኞች በማስታወቂያ ሰሌዳ

በመለጠፍና በአውትሉክ በመላክ እንዲደርሳቸው በማድረግ ለሠራተኛውን ግንዘቤ ማስጨበጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የአመታዊ ኦዲት መጽሄትን ለማሳተም የእርማት ስራ ተሰርቷል፡፡ የልሳነ ኦዲተር መጽሔት ስርጭት ተከናውኗል፡፡

በሌላ በኩል ተቋሙን የሚገልፅ መፅሐፍ ለማዘጋጀት መረጃዎችን ከስቶር፣ ከቤተመጻፍትና በክፍል ከሚገኙ የተለያዩ ምንጮች የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ መረጃዎችን የመውሰድ ስራ ተሰርቷል፡፡ በድረ ገጽ 14 ዜናዎችን የመጫን ስራ ተሰርቷል፡፡

## 3.6 <u>የለውጥ ሥራ አመራርና መልካም አስተዳደርን በተመለከተ</u>

ቀደም ሲል በመ/ቤቱ የሚታዩና በተለያየ መንገድ የሚገለጹ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በተመለከተ የሥራ አመራሩ በጋራ በመሆን 21 ችግሮችንና መገለጫዎቻቸውን የለየ ሲሆን ሠራተኛውም በችግሮቹና መፍትሄዎቻቸውን በተመለከተ ግልጽና ዝርዝር ውይይት በማድረግ ችግሮች በሁሉም ተሳትፎ መፈታት እንደሚኖርባቸው ከስምምነት ተደርሶ እነኚህን ችግሮች ለመቅረፍ ወይም ለማስወገድ 153 ተግባራት እንዲከናወኑ ከስምምነት ተደርሷል፡፡ ከነኚህ ተግባራት ውስጥ 70 የሚሆኑት የተፈፀሙ ሲሆን ቀሪዎቹ የ2010 መደበኛ ዕቅድ አካል ተደርጎ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የራሱን ዕቅድ አካል በማድረግ ዕቅዱ ተዘጋጅቷል፡፡ አፈጻጸሙንም በተመለከተ የመደበኛው ሪፖርት አካል ሆኖ በመቅረብ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የለውጥ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት የለውጥ ስራዎች አተገባበርን በመደገፍና በመከታተል የተጣለበትን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት እንዲችል የ2010 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ እቅዱን በተሳትፎ በማዘጋጀትና የጋራ በማድረግ ተፈጻሚ በማድረግ ላይ ነው፡፡

በመሆኑም የለውጥ ሥራውን በተመለከተ የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲታቀድ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል ዕቅዱን በውጤት ተኮር መሠረት በአራቱ እይታ እንዲያቅድና በየደረጀው ተፈራርሞ ወደ ትግበራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በአፈጻጸም ረገድ የሥራ ክፍሎች የተለያዩ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን ፎርማቶች ተዘጋጅተው የተሠራጩ ቢሆንም በዋነኛነት የተሠራውን ሥራ በየዕለቱ መዝግቦ በመያዝና በአፈጻጸም ረገድ ከፈጻሚው ጋር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ይህንን ሂደት በመረጃ

ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለማቃለል ታስቦ የተለያዩ አማራጮች የታዩ ሲሆን በመጨረሻም ሥርዓቱን ኦቶሜት ለማድረግ ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘውን ሶፍትዌር የማለመድ ሥራ በመሠራት ላይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የ2010 በጀት ዓመት የዳይሬክቶሬቱን እቅዱን ከተቋሙ እቅድ በመነሳት የማዘጋጀትና የጋራ የማድረግ፣ የለውጥ ስራዎች አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የግኝት መረጃዎች፣ ከሪፖርትና ግብረ መልስ እንዲሁም አካላዊ ግምገማና ግብረ መልስ በመነሳት መገምገም፣ ወርሀዊ የለውጥ ሥራዎች የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ ጥንካሬና ክፍተትን እንዲሁም የቀጣይ አቅጣጫዎችን የሚያመላክት ግብረ መልስ የማዘጋጀትና የማሰራጨት እና የቡድን ሳምንታዊ ውይይት የለውጥ ቡድን አደረጃጀቶችን በአዲስ መልክ በማደራጀት ወደ ስራ የማስገባትና የማጠናከር ሥራዎች ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም የዳይሬክቶሬቱን ቢኤስሲ እቅድ መሰረት በማድረግ ለፈጻሚዎች እንደ የደረጃቸው እቅድ ካስኬድ በማድረግና በመፈራረም ሁሉም ፈጻሚ ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከዚሁ በመነሳት ሳምንታዊ የክፍሉና የሰራተኞች እቅድ ሳይቆራረጥ የማዘጋጀት፣ በየሳምንቱ የእቅድ አፈጻጸሙን በቡድን ውይይት አግባብ በመገምገም ልምድ መለዋወጥ፣ የማስተካከያ ተግባራትን የመፈጸምና መረጃዎችም ለቀጣይ ጉዳዮች ግብአት እንዲሆኑ የጋራ በማድረግ አደራጅቶ የመያዝ ተግባራት ተከናውኗል፡፡
በሌላ በኩል በክትትልና ድጋፍ አግባብ በውጤት ተኮር ስርአት እቅድ ዝግጅትና እንዲሁም በምዘና መመሪያ ዙሪያ ክፍተት ተለይቶ ለኦዲት ዘርፍ ዳይሬክቶሬት ለ185 ባለሙያዎች ለሁለት ቀን ግንዛቤ ለመፍጠር የምክክር መድረክ በማዘጋጀት መስጠት ተችሏል፡፡

በውጤት ተኮር ስርአት መንገድ ሁሉም ባለሙያዎች እንዲመዘኑ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ሥርዓቱን ኦቶሜት ለማድረግ ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘውን ሶፍትዌር ከተቋሙ ሥራ አንጻር እንዲጣጣም የማለመድ ሥልጠና ሥራ በመሠራት ላይ እንገኛለን፡፡

### 3.7 <u>የመ/ቤቱ ህግ ጉዳዮች በተመለከተ</u>

ከመ/ቤቱ ሁሉም የስራ ክፍሎች ለሚቀርቡ የቃልም ሆነ የጽሁፍ ጥያቄዎች ተገቢውን የህግ አስተያየት በወቅቱ መስጠት፤ መ/ቤቱ በሚከስባቸው ሆነ

በሚከሰስባቸው ጉዳዮች ላይ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ክስና መልስ አዘጋጅቶ ለፍ/ቤት በማቅረብ መከታተልና ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ የመ/ቤቱን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ፣ ኦዲተሮች የሙያ ምስክርነት እንዲሰጡ በፍ/ቤት በሚጠሩበት ወቅት በፍ/ቤት አብሮ በመገኘት የሙያ እገዛና ድጋፍ ማድረግ፤ በፍ/ቤት የሚገኙትን የፍ/ብሔር ክርክሮች በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተከታትሎ ከግብ ማድረስ፣ በተሰጠው ውሳኔ ላይም ቅሬታ ከተሰማን የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በማቅረብ ተከራክሮ የማስወሰን ስራ ተሰርቷል፡፡

በመ/ቤታችን እና በተለያዩ ግለሰቦች መካከል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ በከሳሽ መ/ቤት፣ የፌ/ዓቃቤ ህግ እና በተከሳሾች መካከል ስላለው የጽሁፍና የቃል ክርክርና ምላሽና ውሳኔ ተሰጥቷል እየተሰጠም ይገኛል፡፡ በከሳሽ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር እና በተከሳሽ በእነ ደስታ ገርባ መካከል ባለው ክርክር የሂሳብ ማጣራት ሥራ አከናውኖ ሪፖርት እንድንልክ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ፍ/ብሔር ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ላይ ተገቢውን ምላሽ ለፍ/ቤቱ የመፃፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በልዩ የኦዲት ሥራ ላይ ለሚገኙ ኦዲተሮች ከቀረጽ ነፃ ስለሚገቡ መኪኖችን አስመልክቶ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከገቢዎችና ጉምሩክ ጋር በተፃፃፉት ደብዳቤዎችና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮጀክት ውለታን አስመልክቶ ዝርዝር የህግ ድጋፍና ምክር ተሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ከልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ከሠው ኃብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በተጠየቁ ሁለት የህግ አስተያየት ጥያቄዎች ላይ ተገቢው አስተያየት በጽሁፍ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም መ/ቤቱ ለሚፈጽማቸው የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዥዎች ከአቅራቢዎች ጋር ለሚያደርገው ስምምነት ውል እንዲያዘጋጅ ሲጠየቅ የውል ሰነድ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡

የመ/ቤቱን ማሻሻያ አዋጅ መሰረት በማድረግ ተሰርቶ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበው የመ/ቤቱ የሰራተኛ አስተዳደር ደንብ ረቂቅ ላይ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠትና ተጨማሪ ግብዓቶች ካሉም በማካተት ረቂቁን አዳብሮ እንዲፀድቅ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡ የመ/ቤቱ አዲሱ የሠራተኞች አስተዳደር

ደንብ የአማረኛ ቅጅ በማጠናቀቅና የእንግሊዘኛውን ትርጉም በመስራት የመ/ቤቱን የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ረቂቅ የማጠናቀቅ ሥራ ተሰርቷል።

በተጨማሪም አማረ ላቀው የተፈቀደለት የሂሳብ አዋቂና የታክስ አማካሪ የመ/ቤታችንን መልካም ስምና ተግባር በእጅጉ ያጎደፈ የሙያ አስተያየት የሰጠ በመሆኑ ምርመራው ተጣርቶ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ደብዳቤ ተጽፎ ተልኳል።

የመ/ቤቱ የፍርድ ባለዕዳ የነበሩት አቶ ውብሊቀር አያሌው በተወሰነባቸው ውሳኔ መሠረት ለመ/ቤታችን ገቢ ሳያደርጉ የቀረባቸው ብር 3,300.00 ውስጥ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) ገቢ ያደረጉ ሲሆን ቀሪውንም በጥር ወር ውስጥ አጠናቀው ገቢ እንዲያደርጉ ቃል የገቡ ሲሆን የአለማየሁ ብርሃኑ፣ የትናየትዘርፋ፣ አማራ ላቀው እና የሌሎችም ከህግ ጋር ተያያዥ ጉዳዮች ክትትል እየተደረገ ይገኛል።

### 3.7 የዕቅድ ዝግጅትና ሪፖርት አቀራረብ

በተቋም ደረጃ የተቀረጹ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚያስችል በበቂ ጥናትና መረጃ ላይ የተመሰረተ የተቋሙን ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የጸደቀውን የሥራ እቅድና በጀት በሥራ ላይ ስለመዋሉ በየወሩ፤በሩብና በግማሽ ዓመቱ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ድጋፍ መስጠት እንዲሁም ለሚመለከተው አካል መላክ፣ በዕቅድ አፈጻፀም ሪፖርት ላይ የተሠሩና ያልተሠሩ ሥራዎች ላይ ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ ማዘጋጀት ሥራዎችን መሥራት በዚህ ረገድ የታቀዱ ቁልፍ ሥራዎች ናቸው።

ከዚህ አንፃር ከ2011 እስከ 2012 የ2 ዓመታት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንዲሁም የ2010 ዕቅድን መሠረት በማድረግ የመ/ቤታችን የየወሩና ሩብ ዓመት የስራ ማስኬጃና ደመወዝ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ተዘጋጅቶ ለገ/ኢ/ት/ሚንስቴር የተላከ ሲሆን ይህንኑ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ዕቅድ መሠረት በማድረግ በጀት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጠይቆ በማምጣት ሥራ ላይ እንዲውል ተገቢው ጥረት ተደርጓል። ተጠይቆ የመጣውን በጀትም በተመለከተ በተደለደለበት የበጀት አርዕስት ሥራ ላይ እንዲውል የበጀት ክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ የተቋሙን ሥራዎች በ5 ዓመት

ስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በመምራትና በገምገሚ በየወሩ በሩብና በግማሽ ዓመቱ ከየሥራ ክፍሎቹ የሚቀርቡ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችም ላይ ተገቢውን ግብረ መልስ እየሰጠ ይገኛል፡፡ ሪፖርቶቹንም በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲደርስ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል በየዓመቱ ኦዲት ተደርገው የተሰጠባቸው የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ የተወሰዱ እርምጃዎችን በማዕከላዊ መረጃ ቋት የማደራጀትና መከታተል ሥራዎች በመሠረት ላይ ሲሆን ከ2002-2006 ባለፈው የበጀት ዓመት የተደራጃ ሲሆን አሁን በዋንኛነት ከ2007-2008 ዓ.ም ያለው የኦዲት ግኝቶችን የማደራጀትና የማመዛዘን ሥራን በተመለከተ የፋይናንስና ህጋዊናት የ146 መ/ቤቶችና 31 ቅርንጫፎች እንዲሁም የክዋኔ 21 ኦዲቶችና ክትትል ኦዲቶች ተሰርቷል፡፡ 2008/2009 ዓ.ም ያለው የኦዲት ግኝቶችን የማደራጀትና የማመዛዘን ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## 3.8 <u>ዘርፉ ብዙ ጉዳዮች ሴቶችና ወጣቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ስርዓተ ጾታ ዙሪያ</u>

ከዘርፉ ብዙ ሥራዎች አንጻር ሥርዓተ ፆታና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና እንዲሁም የአካባቢ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ለመሥራት የታቀደ ሲሆን በ9 ወራት ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውኗል፡፡

ሥርዓተ ፆታን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተሻለ ሥራ ለመስራት እንዲያስችል ረቂቅ የሥርዓተ ፆታ ማካተቻ መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ለሚመለከታቸው አካል ቀርቦ ውይይት ተደረጎበት ዳብሮ የሚፀድቅና ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የተቋቋመውን ፎረም ኮሚቴ አባላትን ዉይይት ማድረግና መደገፍ፣ ማገገዝና መከታተል ሥራዎች ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ዓለም ዓቀፍ የወጣቶች ቀንን አስመልክቶ በወጣቶችና በጎ አድራጎት ዙሪያ አንድ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች እንዲደርስ በአዉት ሉክና በወረቀት በተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል፡፡

ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀንን አስመለክቶ ወደ አረጋዊያን ማህበር በመጎብኘት ተከብሯል፡፡ በሌላ በኩል የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ስራ አመራር ፖሊሲ ከስርዓተ ፆታ አንፃር ተግባራዊ መሆኑን የመከታተል ስራ ተሰርቷል፡፡ በሌላ በኩል የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ስራ አመራር ፖሊሲ ከስርዓተ ፆታ አንፃር ተግባራዊ መሆኑን የመከታተል ስራ

ተሰርቷል። የጸረ-ጾታዊ (ነጭ ሪቫን) ቀን በማክበር  በሴቶች ጥቃትና መንስኤዎቻቸው በሚመለከት የግንዛቤ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን የመ/ቤቱን ሠራተኞች የፆታና እድሜ መረጃን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል። ለመ/ቤቱ ሴት ሰራተኞች ቅድሚያ ጤና ከመጠበቅና ከመንከባከብ አንጻር የማህጸን ጫፍ ቅድመ ምርመራ እንዲያደርጉ ለ7 ሴት ሠራተኞች የማስተበበር ስራ ተሰርቷል።

በመ/ቤቱ ውስጥ ከጤናና አከባቢ ደህንነት አንጻር ልዩ ልዩ ተለለፊና ተለለፊ ያልሆኑ በሽታዎች ዙሪያ ለምሳሌ ስለ ኤችኣይቪ፣ ስለ ጉባት፣ ካንሰር፣ መፀዳጃ ቤት አጠቃቀም፣ ስለ ዓይን፣ ታይፎድና ታይፌስ፣ ስለ ስኳር፣ ስለ ጭንቀት፣ ስለ ኮልስቲሮል፣ ስለ ስጋራ ሱስ፣ ስለ ውፍራት፣ ስለ አጣዳፊ ተቅማጥ፣ ስለ ጀርባ ህመም ወዘተ ሥልጠና የተሰጠ እንዲሁም መረጃዎችን በአውት ሉክ በመለክ ሠራተኛ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል።

የሴቶችንና ወጣቶችን አቅም ከማሳደግ አንጻር የልምድ ልውውጥ ማድረግ በመስፈለጉ በተመረጡ የፌዴራል መ/ቤቶች ዉስጥ ያሉ የሴቶችና ወጣቶች ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ጋር የተደረገ ሙያዊ ድጋፍና የልምድ ልዉዉጥ  ስራ ከማጠናከር አንጻር ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሴቶችና ወጣቶች ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጋር ቼክ-ሊስት በማዘጋጀት ሙያዊ የመደጋገፍ ስራዎች ተሰርቷል።

### 3.9 <u>የውስጥ ቁጥጥር ሥራዎችን በተመለከተ</u>

የመ/ቤቱ ሀብትና ንብረት ከምዝበራ፣ ከማጭበርበር፣ ከስርቆት፣ አላግባብ ከመጠቀምና ከብልሽት መጠበቁን፣ የሚዘጋጁት የፋይናንስ መግለጫዎች ትክክለኛና ተአማኒነት ያላቸው መሆኑን፣ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በኦዲት በማረጋገጥ እና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን በመፈተሽ፣ አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን በማጣራት እንዲሁም የመ/ቤቱ አመራሮች፣ሠራተኞችና ሌሎችም የሚጠይቁትን ሙያዊ የምክር አገልግሎት በመስጠትና በማገዝ የመ/ቤቱ ዓላማ፣ ተልዕኮና ግብ እንዲሳካ ጥረት ማድረግ በግማሽ ዓመቱ የታቀዱ ዋነኛ ሥራዎች ናቸው።

በዚህም መሠረት የ2009 በጀት ዓመት የጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ ቆጠራ በውስጥ በኦዲተሮች ኦዲት ተደርጓል፡፡ 2009 መጨረሻ የአላቂ ንብረት ከወጪ ቀሪ ቆጠራ ለዚህ ዓለማ በተቋቋመው ኮሚቴ ሲደረግ በውስጥ ኦዲት ክትትል የተደረገ ሲሆን ይህንኑም መሠረት በማድረግ የአላቂ ቢሮ ዕቃዎች እና ሌሎች አላቂ ዕቃዎች ከወጪ ቀሪ የቆጠራ ማመዛዘኛ ተሠርቷል፡፡ በተጨማሪም የ2009 በጀት ዓመት የመደበኛና የPBS ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት ላይ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚታየውን የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ተልኳል፡፡ የ2010 በጀት ዓመት እስከ የካቲት 30/2010 መደበኛ እና የPBS ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ ረቂቅ ሪፖርት ለማዘጋጀት ዝግጅት እየተደረገ ሲሆን የዋና ገ/ያዥና የረዳት ገ/ያዥ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በየወሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የተሽከርካሪ ነዳጅ አጠቃቀም ኦዲት ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በሕግ ዳይሬክቶሬት በተጠየቀ የአንድ ኦዲተር የ2 አመት የውሎ አበል ተመላሽ ሂሣብ የማጣራት ሥራ ተሰርቶ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ከሐምሌ እስከ ጥቅምት ድረስ የ49 የመስርያ ቤቱ ሠራተኞች ዕድገት እና የ90 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ሕግና ደንብንና ተከትሎ መፈጸሙን እንዲሁም ስርኣተ ጾታን ያማከለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም መ/ቤታችንን በተመለከተ በውስጥም ይሁን በውጭ ኦዲተሮች የተገኙ የኦዲት ግኝቶችና አስተያየቶች እርምጃ አወሳሰድ በተመለከተ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 3.10 <u>የክትትልና ድጋፍ ሥርዓትን በተመለከተ</u>

የመ/ቤቱን ዕቅድ አፈጻጸም በሚገባ ለመከታተልና ችግሮችም ሲያጋጥሙ በፍጥነት ለመፍታት የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ተዘርግቶ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተሉት የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ተዘርግቶ በተቋም ደረጃ እየተፈጸመ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት፤

- እያንዳንዱ ቡድን ሥራውን በየሣምንቱ እንዲገመግም ሥርዓት ተዘርግቶ እየተፈጸመ ይገኛል፡፡
- ሥራ አስኪያጆች ከከፍተኛ ኦዲተሮች ጋር በየ15 ቀኑ እየተገናኙ ሥራቸውን እየገመገሙ ይገኛሉ፡፡

- ❖ ዳይሬክተሮችና ሥራ አስኪያጆችም በየ15 ቀኑ እየተገናኙ ሥራቸውን እየገመገሙ ይገኛሉ፡፡
- ❖ የዘርፍ ም/ዋና ኦዲተሮችና ዳይሬክተሮችም እንደዚሁ በየ15 ቀኑ እየተገናኙ ሥራቸውን እየገመገሙ ይገኛሉ፡፡
- ❖ የዘርፍ ም/ዋና ኦዲተሮችና ዋና ኦዲተሩም በየ15 ቀኑ እየተገናኙ ሥራቸውን እየገመገሙ ይገኛሉ፡፡
- ❖ አጠቃላይ የሥራ አመራሩ በየወሩ እየተገናኘ የዕቅድ አፈጻጸሙን እየገመገሙ ይገኛሉ፡፡

**<u>በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ</u>**

1. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡
2. በዚሁ መሠረት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ወቅት በ2008 ኦዲት ላይ በተደረገው የክትትል ኦዲት 68 መ/ቤቶች እና 11 ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡
3. በአጠቃላይ ሲታይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድና ለማስተካከል በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል ቢታይም ገና ወደ ሚጠበቀው ደረጃ ሊደርስ አልቻለም፡፡ አንዳንድ መ/ቤቶች በቀላሉ እርምጃ ወስዳው ሊያስተካክሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች እንኳን ማረም አልቻሉም፡፡ ለምሳሌ ይቋረጡ የተባሉ ህጋዊ ያልሆኑ ክፍያዎችንና ህግና ሥርዓት ያልተከተሉ ግዢዎችን እንኳን ማቆም ያልፈለጉ ተቋማት አሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ጥብቅ እርምጃ ተወስዶ ሊገታ ይገባል፡፡
4. ይህን ሁኔታ ለመለወጥ መ/ቤታችን ከሚያደርገው ጥረት ጎን ለጎን የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጣንካራና ተከታታይ ይፋዊ መድረክ በማዘጋጀት ኦዲት ተደራጊዎች ስለወሰዱት እርምጃ መጠየቁና ሌሎችም የም/ቤቱ ቋሚ

ከሚቴ አባላት የሚከታተሏቸው መ/ቤቶች በኦዲት ግኝት ላይ የወሰዱትን እርምጃ በጥብቅ እየተከታተሉ በመሆኑ ኦዲት ተደራጊዎች እርምጃ እንዲወስዱ ጫነ እየፈጠረ ቢሆንም በኦዲት ተደራጊዎች በኩል ግን አሁንም ለዚህ ጉዳይ የበለጠ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

5. በሌላ በኩል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከዚህ አንፃር እያደረገ ያለው ክትትልም ተቋማት የኦዲት ግኝት ላይ ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ የራሱ ተፅዕኖ በማሳደር ላይ የሚገኝ ቢሆንም አንዳንዶች በኦዲት ግኝቱ ተምረንበታል ኦዲቱ ጠቅሞናል እያሉ ወደሚታይ ተጨባጭ እርምጃ ሣይሻገሩ ለመድረክ ፍጆታ ብቻ እያዋሉት ይገኛል፡፡

6. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) መሠረት ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰደ፤ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት መፈጸም ሲኖርበት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ በህግ እንደሚቀጣ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ወይም እንዲያስወስድ በተከበረው ም/ቤት በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ዝርዝሩ ለፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የተላለፈ ቢሆንም ኦዲት ተደራጊዎች ተገቢውን እርምጃ ወስደው እንዲያሳውቁ ደብዳቤ ከመጻፍ ውጭ በተጨባጭ የተገኘ ውጤት የለም፡፡

7. በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) መሠረት ተገቢውን እንዲወስድ አሁንም የተከበረው ም/ቤት ተገቢ አቅጣጫ እንዲሰጥ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ በሌላ በኩል ኦዲት ተደራጊዎችም ቢሆንኑ አሁንም በዚህ መልኩ ከሚደርስ ተጠያቂነትና ቅጣት ለመደን ሌላ ተጨማሪ ጊዜ ሳይወስዱና ሳይዘገዩ በአስቸኳይ ተገቢውን እርምጃ ሊወስዱና የተዘረገውን አሠራርና ሥርዓት አክብረው ሊሠሩ ይገባል፡፡

**<u>የ2009 በጀት ዓመትና 2010 በጀት ዓመት</u>**
**<u>የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም</u>**

8. በ2009 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር **79,290,102.00** በጀት ተፈቅዶ ብር **74,480,486.86** ወይም 93.93% ሥራ ላይ የዋለና ያልተሰራበት ብር **4,809,615.14 (6.07%)** የነበረ ሲሆን፣ ለ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ከተፈቀደው መደበኛ ብር 76,443,603.00 ለካፒታል ብር 52,000,000.00 በድምሩ ብር 128,443,603.00 ውስጥ እስከ መጋቢት 30/2007 የነበረው የዘጠኝ ወር በጀት ብር 59,163,892.72 ሲሆን በዘጠኝ ወር ውስጥ ስራ ላይ የዋለው ደግም ብር 53,544,230.46 ወይም 90.5% ሆኗል፡፡

**<u>መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች</u>**

9. አሁንም ያልተሸሻለውና ፈተና እየሆነብን ያለው ችግር ኦዲት ተደራጊዎች አልፎ አልፎ ምቹ የሥራ ቦታ ለኦዲተሮች ያለማመቻቸትና የሚጠየቁትን ማስረጃ በወቅቱ ያለመስጠት፣ ለኦዲት ማስታወሻዎች በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት፤ ኦዲተሮች ሥራቸውን አጠናቀው የመውጫ ስብሰባ አድርገው ከወጡና ወደ ሌላ ሥራ ከተሰማሩ በኃላ በኦዲት ወቅት ያላቀረቡትን ማስረጃዎች አሉን በማለት በርካታ ሠነዶችን መ/ቤታችን ድረስ ጭነው ማምጣት፣ ለረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት ከኦዲቱ ጋር ተያይዞ እያጋጠሙንና ሊስተካከሉ የሚገባ በቀጣዩ የኦዲት ሥራችን ላይ ጭምር ጫና እያስከተሉ ያሉና ሊፈቱ የሚገባቸው ችግሮች ናቸው፡፡

10. በሌላ በኩል ከመ/ቤታችን የሥራ ባህርይ የተነሣ ኦዲተሮችችን ከሌሎች የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች በተለየ ዓመቱን በሙሉ መስክ ላይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ነገር ግን አሁን ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ለመስክ የሚከፈላቸው የቀን ውሎ አባል ወጪያቸውን ሊሸፍን ባለመቻሉ ኦዲተሮቻችን በፍጹም ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ሥራቸውን በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ይዘው የሚሄዱት የመንግሥት ንብረትና ሠነድ ጭምር ለአደጋ የሚጋለጥ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው ሁሉ ይህንን ችግር ተገንዝበው የመ/ቤታችን የቀን የውሎ አባል ጉዳይ በልዩ ሁኔታ እንዲመለከቱትና ድጋፍ እንዲያደርጉልን እጠይቃለሁ፡፡

**<u>የ2010/2011 ኦዲት ዓመት ዕቅድ</u>**

11. በ2010 በጀት ዓመት በጀት ከተመደበላቸው 183 የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ ቀደም እንዳሉት ዓመታት 8 የሚሆኑት ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 176 ተቋማት በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በሌላ በኩል ከመጋቢት 2009 እስከ ጥር 2010 ድረስ 24 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 6 የክትትል ኦዲቶችን በማከናወን 28 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በ264 የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡ ሁሉም የኦዲት ዓይነቶች ሲሠሩ የኦዲት ጥራት ስለመረጋገጡ በየደረጀው ያሉ ሀላፊዎች ተኩረት ሰጥተው ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ እንዲያደረጉ ኦዲተሮችም ሥረዎቻቸውን ስታንዳርዱን ተከትለው እንዲያከናወኑ አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል፡፡

**<u>ማጠቃለያ</u>**

1. በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው የፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ የሁሉም የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት በታቀደው መሠረት የተከናወነ በመሆኑ ዕቅዱን መቶ በመቶ መፈፀም የተቻለ ከመሆኑም በላይ የኦዲት ሽፋኑንም በተመለከተ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ የ100% አፈጻጸም ማስቀጠል ተችሏል፡፡

2. የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 20 አዳዲስና 8 የክትትል ኦዲት በድምሩ 28 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ 20 አዳዲስና 6 የክዋኔ ኦዲት የክትትል ሪፖርቶችን ጨምሮ 26 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም በሁለት የክትትል ኦዲቶች ጉድለት አጠቀላይ አፈጻጸሙ 92.86% ሆኗል፡፡

3. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲትን በተመለከተ በ251 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱን ለማከናወን ታቅዶ በ251 (100%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ በሌላ በኩል በፍትሃዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮገራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services - ESPES, Program for Result) የገንዘብ ፍሰት አመልካቾችን የማረጋገጥ ሥራ (Verfication) በ8 ወረዳዎች ለመከናወን ታቅዶ በ16 ወረዳዎች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

4. የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በየዓመቱ ኦዲት እየተደረጉ የሚታዩ የፋይናንስ እንዲሁም የንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም ክፍተቶች እየተለዩ የማሻሻያ ሀሳብ በየዓመቱ የሚሰጥ ቢሆንም በርካቶቹ መ/ቤቶች በሚፈለገው ደረጃ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው በቂ የማስተካከያ እርምጃ ባለመውሰዳቸው በየዓመቱ ተመሳሳይ ጉዳዮች አሁንም የኦዲት ግኝት ሆነው በመታየት ላይ ናቸው፡፡

5. ስለሆነም እነኚህ በየዓመቱ እየተደጋገሙ ያሉት የኦዲት ግኝቶች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው አስገዳደጅ እርምጃ ተወስዶ ሊስተካከሉና ሊታረሙ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱና አጠቃላይ ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ26 ጥራዝ፤ አስተያየት ሊሰጥባቸው ያልተቻለ የ8 መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርትና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት ተሰጠባቸው 53 መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች ለየብቻ ተዘጋጅተው ለተከበሩ አፈ-ጉባዔ የተላኩ በመሆኑ ሪፖርቶቹን በም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ታይተው በሚመለከታቸው አካለት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትልና ግፍት ሊደረግ ይገባል፡፡

6. እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በ2009 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲትም ወቅት ዋንኛ የኦዲት ግኝት ሀነው የቀጠሉት በወቅቱ ያልተወራረዱ ወይም የልተሰበሰቡና ያልተከፈሉ ውዝፍ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚከናወኑ ግዥዎችና የሚፈጸሙ ወጪዎች እንደዚሁም አላግባብ ከህግ ውጪ የሚፈጸሙ የጥቅማ ጥቅምና

ሌሎች ከፍያዎች፣ የመንግሥት የግንባታዎች ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት ያለመጠናቀቅ እያስከተለ ያለው ተጨማሪ ወጪና ፕሮጀክቶቹ በታሰበው ጊዜ አገልግሎት ያለመጀመር እያስከተለ ያለው የመልከም አስተዳደር ችግር፤ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ተደጋጋሚ ችግሮች፤ ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ጉድለቶች፤ እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ጉድለቶች ናቸው፡፡

7. እነኚህን ጉድለቶች ከማሳየትና እንዲታረሙ ከማሳሰብ በተጨማሪ ዋና ዋና ለሚባሉት ግኝቶች ሊወሰዱ የሚገቡ የመፍትሄ ሀሳቦች በ2008 ሪፖርት ወቅት የተጠቆሙ ቢሆንም በሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ተቆጣጣሪ አካለት እርምጃ ባለመወሰዱ ችግሮቹ አሁንም ዘልቀው መጥቷል፡፡

8. በሌላ በኩል ባለፉት ዓመታት ባደረግናቸው ኦዲቶች ያላግባብ የፈጸሙትን ክፍያ እንዲያስመልሱና ከተዘረጋው የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ውጭ እየተፈጸሙ ያሉ ተግባራትን እንዲያቋርጡ በተደጋገሚ አሳስበን ያልፈጸሙ ተቋሚትና በየደረጀው ያሉ ሀላፊዎቻቸውን በተመለከተ የ2008 የኦደት ሪፖርት ለተከበረው መ/ቤት በቀረበበት ወቅት በተሰጠው መመሪያ መሠረት ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ከ2002 እስከ 2008 ያለው የኦዲት ግኝት ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ የተላለፈ ቢሆንም እስከ አሁን ተወስዶ የተገለፀልን እርምጃ የለም፡፡ ተገቢው ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ተጠያቂነት ካልተረጋገጠ ይህ ጉዳይ እልባት ሊያገኝ አይችልም፡፡

9. በመሆኑም የሚደረገው ኦዲት የአሠራር ክፍተቶችን በማረም ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የበለጠ አስተዋፅኦ እንዲያደርግና እሴት እንዲጨምር በአዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ያላግባብ የተከፈለው የመንግሥት ገንዘብ እንዲመለስ፤ ከተዘረገው አሠራርና ሥርዓት ውጭ በመሆናቸው እንዲቋረጠ የተባሉት ተግባራት በፍጥነት እንዲቆሙ፤ አሠራርና ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው የተባሉት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እንዲፈጸሙ ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከተቸው መ/ቤቶችና ተቆጣጣሪ አካላት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ የተከበረው ም/ቤት የበለጠ ግፊትና ክትትል በማድረግ ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጥ በድጋሚ እየጠየቅሁ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሠግናለሁ፡

## የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

## ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

መ/ቤታችን በ2009/2010 የኦዲት ዓመት በ174 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና በ48 ቅ/ጽ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ ባቀደው መሰረት የ173 መ/ቤቶችና የ44 ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ የቀረበ ሲሆን በኦዲቱ የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ክፍል የሚነሱ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች አብዛኞቹ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱና በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

### I. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

### 1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

#### 1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ 5 መ/ቤቶች ብር 927,522.46 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 2 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ3 መ/ቤቶች ብር 2,953,621.96 በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-2/1 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 1.2 <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች</u>

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በተለያዩ መ/ቤቶችና ተጠሪ የሆኑ ቅ/ጽ/ቤቶች በርካታ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ-3/ሀ-መ እና አባሪ-4 እና 4/1 ተመልክቷል፡፡/

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፤

- በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ እጅ መያዝ ከሚገባው በላይ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት የተገኘ በ1 መ/ቤትና የተለያዩ መ/ቤቶች በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 767,077.37 ፤
- የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ ያላስገቡ በ2 መ/ቤቶች ብር 3,474,137.59 መገኘቱ፣
- የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ 2 መ/ቤቶች፤
- የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ /ዴቢት/ በ1 መ/ቤትና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 167,543,104.87 መገኘቱ እና በ2 መ/ቤት ብር 14,788,427.82 መደበኛ ሚዛን ያልሆነ- (መክፈቻ ሚዛን) (ክሬዲት ባላንስ) ያለው የጥሬ ገንዘብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ ላይ በየወቅቱ ቁጥጥር በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲተገበር፤ በኦዲት የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

እንዲተካ፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 2 የተሰብሳቢ ሂሳብ

### 2.1 በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ116 መ/ቤቶች እና በ15 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 5,835,334,951.52 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ-6 እና አባሪ-6/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ብር | 52,074,277.63 |
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | " | 3,682,154,951.75 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 510,191,429.81 |
| የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 1,172,375,148.70 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 318,249,742.67 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 100,289,400.96 |
| **ጠ/ድምር** | ብር | 5,835,334,951.52 |

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 1,004,811,500.39 ፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 3,745,300,525.75 ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 264,830,787.34 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 111,142,869.56 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 709,249,268.48 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው፡፡ በተጨማሪም በ10 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር

1,332,235,294.08 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑ ታውቆል፡፡

ከውዝፍ ተሰብሳቡ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ያዙት የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር3,526,111,909.99፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 572,280,328.63፤ የውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 194,467,448.89፤ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር173,651,200.77፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 112,701,810.27፤ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት 6 ተጠሪ ተቋማት ብር 90,694,883.75፤ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 78,256,261.03 የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 58,763,114.41 ፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 67,156,467.64 እና ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤትና 9 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 52,074,277.63 ይገኙበታል፡፡የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብም የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር1,215,751,975.22 እና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 54,687,040.37 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም፤ ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

## 2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ12 መ/ቤቶች ብር 151,669,167.02 መሆኑ
- በአንድ መ/ቤት ያለአግባብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ የተሰረዘ ብር 500,231.72 መኖሩ፤

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ-7 ሀ እስከ ሐ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ /እንዲሰበሰቡ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

# 3 የገቢ ሂሳብ

## 3.1 በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ ተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ ሰባት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,463,463,992.66 ፤በሌሎች በ49 መ/ቤቶች ብር 49,295,431.76 በድምሩ ብር 1,512,759,424.42 የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ/VAT/፤ ቅድመ ግብር(withholding tax)፤ የአክስዮን ትርፍ ድርሻ፤ እና በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበ እና በሌሎች 22 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ቅጣት ሂሳብ ብር 77,082,375.48 እና ገቢ ያልተፈረገ የውል ማስከበሪያ ብር 1,256,965.48 ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በሁለት መ/ቤቶች ብር 8,132.60 እና በአንድ መ/ቤት የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ የወጪ መጋራት ሂሳብ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-9 እና 9/1 እስከ አባሪ - 9/3 ተመልክቷል/

ገቢ ለመሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበው ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ብር | 1,463,463,992.66 |
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | " | 375,886.11 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 14,784,874.29 |
| የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 33,017,042.07 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 753,095.85 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 364,533.44 |
| **ጠ/ድምር** | ብር | **1,512,759,424.42** |

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 985,860,235.77፣ ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 119,398,319.73 ፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 86,691,742.14፤ ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 70,980,332.17 ፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 41,581,761.09፤ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 37,911,841.04 ሲሆን ፤ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,473,484.63፤ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 6,054,599.28፤ ሀዋሳ ኒቨርሲቲ ብር 5,783,522.79 እና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,542,798.37 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ፣ ማራገፊና ኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው

ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ</u>

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስር ባሉት ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 6,220,131,548.44 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ እና በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ባለመስጠቱ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን 2 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ግብር፤ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 1,619,812,240.90 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 8 እና 8/1 ተመልክቷል/

በተጨማሪም ከሱቅና የቢሮ ኪራይና ሌሎች ውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ሂሳብ ወለድና ቅጣት በ3 መ/ቤቶች ብር 6,431,747.45 እና ከሰጡት አገልግሎት ሽያጭ ላይ ውዝፍ ሂሳብ በ4 መ/ቤቶች ብር 64,695,033.19 በወቅቱ /በአባሪ- 8/2/ ያልተሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ውዝፍ ገቢ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,922,242,000.48 ፤ የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 620,102,798.87 ፣ በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 333,325,596.16 እና ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 121,824,984.30 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የዱቤ ሽያጭ በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር

58,070,344.30 ከፍተኛ ሲሆን፤ የዱቤ ሽያጭን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውዝፍ የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል ፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 3.3 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 32,840,678.91 ፤እንዲሁም በ7 መ/ቤቶች የማስከፈያ የዋጋ ተመን/ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 14,333,161.16 እና በሌሎች 2 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-10 እና አባሪ-14 ተመልክቷል/

ዋና ዋና ምክንያቶቹም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ መግቢያ ደረሰኝ (ማንኛውም እቃ ሲመጣ የሚመዘገብበት) ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ፤የውስጥ ገቢ ሂሳብ ምዝገባ ባለመካሄዱ እና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ እንቅስቃሴን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች እና መግለጫዎች ባለመዘጋጀታቸው፤ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በሌላም በኩል ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያለሳወቁ 95 ግብር ከፋዮች ፤የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 36 ግብር ከፋዮች እና ኤክሳይስ ታክስና ተርኦቨር ታክስ ያለሳወቁ

26 ግብር ከፋዮች የተገኙ ሲሆን፤በድምሩ 157 ግብራቸውን ያላሳወቁ በመሆኑ፤ የሚፈለግባቸው ግብር ምን ያህል እንደሆነም፤ ስለመክፈላቸው/ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.4 በገቢ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተተ የገቢ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ13 መ/ቤቶች ብር 367,716,599.48 እና በሌላ አንድ መ/ቤት በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ያልመዘገቡና ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት እና በሶስት መ/ቤቶች በብር 1,044,169.02 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-11 እና አባሪ-13 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 6,925,512.52 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 354,156,078.28 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 6,635,008.68 |
| በድምር | ብር | 367,716,599.48 |

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 3.5 የተሰበሰበው ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች

በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜውና በሰኔ 30/2009 የሚታየው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት /ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች ብር 165,597,719.82 ለማዕከላዊ ግምጃቤት ፈሰስ ያልተደረገ የባንክ ሂሳብና በአንድ መ/ቤት ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ብር 264,072.40 ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-5 እና አባሪ-12 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈሰስ መሆን እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በሚሰበስቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

## 3.6 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

### 3.6.1 በገቢዎችና ጉምሩክ ባላስልጣንና ቅ/ጽ/ቤቶች

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል አራት ምዕራፍ አንድ አንቀፅ 96/1/ሀ/5 ዕቃዎች በአየር የተጓጓዙ በሚሆኑበት ጊዜ ለአየር ትራንስፖርት የተከፈለውን አንድ ሶስተኛ(1/3) ወጪ መወሰድ እንዳለበት እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 111/08 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 14(1)(መ) መሰረት ሌሎች ወጪዎች ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበ ከሆነ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተካተው ቀረጥና ታክሱ እንደሚሰላ ይደነግጋል፡፡ ***የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*** በዚህ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ገቢ ዕቃዎችን እያስተናገደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለናሙና ባየናቸው

ዲክላራሲዮኖች አማካኝነት ወደ ሀገር የገቡት ዕቃዎች የትራንስፖርት ወጪው በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የተካተተው ከሌሎች ወጪዎች ጋር በመደመር እና የሁለቱንም ድምር አንድ ሶስተኛውን በመውሰድ ሲሆን ነገር ግን በአዋጁ መሰረት የትራንስፖርት ወጪን ብቻ አንድ ሶስተኛ ወስዶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መደመርና እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን ለብቻው ወስዶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተደምሮ እንዲሰራ ያልተደረገ ሲሆን ይህንን የአሰራር ክፍተት አስመልክቶ በ2007 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየታችን ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድበት ተብሎ የተገለጸ ቢሆንም ቅ/ጽ/ቤቱ ለአሰራር ክፍተቱ የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ የቆየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶቹ እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አስመጪዎቹ በየቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን ቀረጥና ታክሳቸው በገቢ ዕቃዎች ቡድን ሳይሰላላቸው /Assess ሳይደረግ የቆዩ ቢሆንም ዲክላራንቱ ያቀረበው የቀረጥና ታክስ መጠን በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 26,803,896.09 ትክክለኛ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ /Assess ያልተደረገ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን ከአሲኩዳ የመረጃ ዘዴ ከወሰድነው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 71 እና 73 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃዉ አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ከተጠናቀቀ እና ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና ወይም በቦንድ ያስያዘዉ ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ወይም ዋስትናው መታደስ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከአዋጁ አንጻር በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢዉ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑንና በአዋጁ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር በማይወጡት እቃዎች ላይ በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ መሆኑን ወይም ዋስትናው እንዲታደስ ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት

ሲደረግ በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 235,177,463.32 ዋስትናው ያልታደረሰ ወይም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ሲሆን በተጨማሪ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በ2008 በጀት ዓመት ሰነድ ያልተገኘላቸው የዋስትና ሂሳቦች ብር 32,470,457.32 እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም ተገቢ እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ ታይቷል፡፡

➢ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀፅ 10(3 እና 5) መሰረት በቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ወደ አገር የገባ ጥሬ እቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጪ ገበያ መላክ እንዳለበት ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጥሬ እቃውን ባህሪ መሰረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ሊፈቅድ እንደሚችል ነገር ግን የመጠቀሚያ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ወይም ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ 50% እንዲከፍል እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ባስገቧቸው ጥሬ እቃዎች ልክ በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ ምርት ለውጪ ገበያ የሚያቀርቡ መሆኑን፣ ይህ ካልሆነ ግን ከቀረጥና ታክስ ነፃ አስገብተው ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ***በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት*** በኩል በተለያዩ አስመጪዎች አማካኝነት ወደ ሀገር የገቡ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ጥሬ ዕቃዎች በቫውቸር ስርአት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ቢሆንም በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ በመሆኑ በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ (1)ሀ-ኘ በተገጸው መሰረት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች ከገቢ ላይ አለመቀነሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ወጪዎች በትክክል ከገቢ ላይ የሚቀናነሱ ስለመሆኑ አስፈላጊው መረጃ ሳይኖር ከገቢ ላይ እንዲቀናነስ የተደረገ ወጪ በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 13,741,882.62 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ወይም ተቀባይነት ያላቸው ወጪዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 79/1995 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ በአግባቡ መቅረቡን፣ ተቀናንሶ መሰላቱን እንዲሁም የተመላሽ ሂሳብ በትክክል ወደ ሚቀጥለው ወር መተላለፉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ተመላሽ ሂሳቦች ወደሚቀጥለው ወር ሲተላለፉ በአግባቡ የማይተላለፉ በመሆኑ በብልጫ የዞረ የተጨማሪ እሴት ታክስ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብምሩ ብር 4,070,094.00 መኖሩ ታውቋል፡፡
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ምዕራፍ 1 ክፍል 1 አንቀጽ 4 ማንኛውም በዚህ ህግ የሚሸፈን ገቢ ያገኘ ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት ግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ግብር ከፋዮቹን ለይቶ በመመዝገብ ግብር እንዲከፍሉ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ከደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት በተገኘው መረጃ መሰረት በግብር ከፋይነት ተመዝግበው የሚታወቁት ግብር ከፋዮች በግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት በኩል ተመዝግበው ከተያዙት ጋር ሲነጻጸር 12 ልዩነት የሚያሳይ በመሆኑ በልዩነት የታዩትን 12 ግብር ከፋዮች የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት መዝግቦ ያልያዛቸው በመሆኑ ግብር ከፋዮቹ ገቢያቸውን እያሳወቁ የሚከፍሉ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በየቅ/ጽ/ቤቱ ግብር የሚከፍሉ ድርጅቶች በተደጋጋሚ ኪሳራ በሚያሳውቁበት ጊዜ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ለናሙና ከመረጥናቸው ግብር ከፋዮች ውስጥ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት 2 ግብር ከፋዮች ከ2004 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም እስከ ለ3 እና ለ4 ዓመታት ኪሳራ ያሳወቁ ቢሆንም ምንም ዓይነት ክትትል እና ማጣራት አለመደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የሽያጭ መመዝገቢያ የሚጠቀም ማንኛውም ንግድ ድርጅት ዓመታዊ እና ወርሃዊ ግብር በሚከፍልበት ጊዜ በሽያጭ ማጠቃለያ/ዜድ ሪፖርት ላይ ባሳየው ሽያጭ መጠን መሰረት ዓመታዊ ንግድ ትርፍም ሆነ ወርሃዊ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲያሳውቁ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በተገኘ ወርሃዊ ማጠቃለያ ዜድ ሪፖርት (summery report) መሰረት ስለመሆኑ ከሰነዱ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ በ 2 ቅ/ ጽቤቶች በድምሩ 12 ግብር ከፋዮች በማስረጃው መሰረት አሳውቀው ስለመክፈላቸው ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

### 3.6.2 ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

- **በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ**

  በአገር ዉስጥ ገንዘብ የሚሰበሰበው ገቢ በገቢ ደረሰኝ መሂ/1 ወይም ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ በሚታተም ደረሰኝ ብቻ መሆን እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ከሐምሌ 1/2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በገቢ ሂሳብ ሂሳብ መደቦች 1443 እና 1489 ብር 4,623,489.88 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ የሰበሰበ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጥቁር አንበሣ ሆስፒታል መድሃኒት በመደበኛ በጀት የሚገዛ እና ከመድሃኒቱ ሽያጭ በበጀት ዓመቱ ብር 18,376,464.77 እንደተሰበሰበ በሂሳብ ሪፖርት ላይ የተመለከተ ሲሆን መድሃኒቱ በመደበኛ በጀት የተገዛ በመሆኑ በመልሶ መሸጥ የተገኘው ገቢ ሂሳብ ለበጀት መተኪያ ተደርጎ መመለስ ሲገባው አላግባብ ወደ ሆስፒታሉ የውስጥ ገቢ ሂሳብ አካውንት ገቢ የተደረገ መሆኑ፤
- የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ከእንስሳትን አባላዘር፣ የፈሳሽ ናይትሮጅን በሽያጭ የሚያቀርብ ሲሆን የምርት መሸጫ ዋጋ ተመን ሐምሌ 21 ቀን 1985 ዓ.ም ከምርት ማዳቀል አገልግሎት ዋና ክፍል ለአባላዘርና ፈሰሽ ናይትሮጅን ማምረቻና ማከፋፈያ ዋና ክፍል በተጻፈው ማስታወሻ መሰረት ተመኑ የማምረቻ ዋጋ ጥናት ተደርጎ የመሸጫ ተመን እስኪወሰን ድረስ ሥራ ላይ የሚውል መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ማዕከሉ ለሚያመርታቸው ምርቶች የማምረቻ ዋጋ ጥናት በማድረግ የሽያጭ ዋጋ ተመን ያላዘጋጀና በሚመለከተው አካል ያላጸደቀ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፤ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ላይ የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ አንዳንዶቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

## 3.7 የገቢ ሂሳብ ዕቅድ አፈጻጸም

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በዕቅድ የያዙትን ገቢዎች የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ሀ/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት፡-ብር 25,871,660,000.00(13%)

ለ/ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 144,854,097.14(29%)

ሐ/ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 23,903,871.70(18%)

መ/ የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ ብር 2,718,181.42(21%)

ከዕቅዱ በታች መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ለመ/ቤቶቹ የገቢ ዕቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

# 4 የወጪ ሂሳብ

## 4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ19 መ/ቤቶች ብር 110,033,859.03 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---:|
| ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ብር | 382,811.47 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 45,625,308.47 |
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | " | 275,219.17 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 248,497.22 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 63,502,022.70 |
| በድምር | ብር | 110,033,859.03 |

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው፤ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,575,478.53 ፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 22,123,507.92 ፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 27,044,750.71 እና የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ብር 11,185,435.72 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

## 4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ68 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 506,026,502.67 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 47,387,440.09 |
| ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | " | 30,809.00 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 259,472.31 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 46,362,033.19 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 382,858,985.30 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 29,127,762.78 |
| በድምር | ብር | **506,026,502.67** |

ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች፤ ትምህርት ሚኒስቴር ብር157,383,533.13፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 60,183,740.86 ፤አክሱም ዩኒቨርስቲ ብር 52,804,956.36፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 46,209,145.83፤ ውጭ ጉዳዩ ሚኒስቴር ብር27,350,000.00 እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 20,426,334.68 ዋና ዋናዎቹ

ሲሆኑ፤ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ(አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ፤ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና  በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጐላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት  ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች  የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### 4.3 <u>ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣ በ98 መ/ቤቶችና በ14 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር  189,895,337.99 እና በአሜሪካ ዶላር በድምሩ $ 49,990.00  ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 13,842,066.47 |
| በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | " | 19,581,842.40 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 53,305,483.52 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 77,263,498.42 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 22,356,415.38 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 3,546,031.80 |
| በድምር | ብር | 189,895,337.99 |

ሆኖ ተገኝቷል።

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር40,253,397.51 እና በአሜሪካ ዶላር $12,400.00 ፤የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ብር 19,175,755.52 ፤ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 18,799,243.82 ፤ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,268,727.60 ፤ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,491,954.72 እና የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 9,624,735.53 እና የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ብር 8,186,199.07 ሲሆኑ፤ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣ ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ ለውጭ ጉዞ ከወሰዱት የውሎ አበል ሂሳብ በመመሪያው መሰረት መመለስ ሲገባቸው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም ፤ መ/ቤቱን ለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት ባሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል።

ከዚሁ በተጨማሪ በ6 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብር 10,518,758.51 የስራው ባህሪ በቋሚነት ወይም ቀጣይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ እና በ15 መ/ቤቶች ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 24,184,740.66 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል። /ዝርዝራቸው በአባሪ-19/1 እና አባሪ- 19/2 ተመልክቷል/

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ገንዘብ ከሚመለከታቸው ወደ መንግስት ካዝናተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል።

## 4.4 በብልጫ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ22 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 9,724,581.41 እና በ27 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 10,362,826.73 በጠቅላላው ብር 20,087,408.14 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፤ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 4.5 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ97 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 487,958,696.75 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 15,802,727.15 |
| ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | " | 30,317,650.23 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 16,680,513.56 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 191,198,092.46 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 198,603,552.67 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 45,048,311.30 |
| በድምር | ብር | 487,958,696.75 |

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡-ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር193,896,805.57፤መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 92,502,156.98፤ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገበው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር30,272,104.0፤ የዋጋ ወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 21,440,931.65 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 149,329,074.05 ናቸው፡፡

ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር61,168,638.68፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 61,085,880.38 ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 43,283,741.84 ፤ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,164,123.08 ፤ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,059,148.78 ፤ መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር21,687,300.80፤ የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ ዩኒቨርሲቲ ብር21,174,423.27፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 17,696,548.64 እና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር12,964,399.77 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ በ5 መ/ቤቶች የብር 13,026,244.39 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-21/1 ተመልክቷል፡፡/

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

### 4.6 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶችና በአንድ ቅ/ጽ/ቤት በብር 83,593,320.38 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ2 መ/ቤቶች ብር 1,102,109,933.36 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-22 እና አባሪ- 22/1 ተመልክቷል/

ገቢ ያልሆነው ንብረት ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | ብር | 37,506.00 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 72,552,517.99 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 9,396,307.55 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 1,606,988.84 |
| በድምር | ብር | **83,593,320.38** |

ከዚህም ውስጥ የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማትኢንስቲትዩት ብር 71,128,769.99፤ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,383,772.80፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,662,342.75፤ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ብር 1,396,148.00 እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ብር 1,364,859.58 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ወይም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ ማስረጃ ካላቀረቡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸውም፣ የብሔራዊ

የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,090,989,091.41 እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ብር 11,120,841.95 ናቸው።

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል።

## 4.7 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 41,966,889.32 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዘግቦ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ- 28 ተመልክቷል/

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል።

## 4.8 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ82 መ/ቤቶች ብር 986,372,435.29 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል።/ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | | 16,662,458.29 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | ብር | 282,669,321.13 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 92,563,479.26 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 569,766,564.97 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 24,710,611.64 |
| በድምር | ብር | **986,372,435.29** |

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 168,489,008.43 ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 74,626,574.30 ፤ወላይታ ዩኒቨርስቲ ብር 34,470,720.73 እና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,491,835.02፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 21,895,096.81 እና የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 20,426,911.53 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 4.9 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ38 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 85,400,239.14 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2009 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | ብር | 22,233,142.37 |
| የፋይናንስን ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | " | 3,859,112.27 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 56,698,992.36 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 2,608,992.14 |
| በድምር | ብር | **85,400,239.14** |

ሲሆን፤ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ/ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ4 መ/ቤቶችና ሁለት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 24,767,649.35 ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ወይም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/ ከዚሁ የሂሳብ ሪፖርት ጋር በተያያዘ በ2 መ/ቤቶች ብር 844,611.60 በድጋሚ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ እና ብር 1,444,970.18 በብልጫ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 4.11 ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች፤

ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የወጡ የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተከናወኑ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ሥምምነት ያልቀረበለትና በአዋጁ መሠረት በዋና ውል ላይ 25% በማስላት ብቻ ተጨማሪ ውል መግባት ሲገባው፣ ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ውል የተገባ በ5 መ/ቤቶች ብር 16,319,714.09 ፤ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ያልተፈረመ በ1 መ/ቤት ብር 4,025,000.00 በድምሩ በብር 20,344,714.09 ተከፍሎ መገኘቱ፤
- ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ፤በ2 መ/ቤቶች ብር 3,576,138.91፤
- በ5 መ/ቤቶች ብር 267,085,966.34 ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያ ሠርትፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ መገኘቱ፤
- በ3 መ/ቤቶች ብር 23,130,699.31 በተከፋይነት ያልተያዘ ፤ በጀት ሳይፈቀደለት የመያዣ ሂሳብ መከፈሉ ተረገግጦል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- አባሪ-20/1 እስከ አባሪ-20/5 ተመልክቷል/

በመሰረቱ ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለበቸው፡፡ የግንባታ ክፍያ በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት መቀነስ ነበረበት፡፡ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ አገልግሎት ሳይገኝ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

በመሆኑም የማማከሪ ስራዎችም ገለልተኛና የሙያ ብቃት በተሰጣቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን፤ተጨማሪ ውል ሲያስፈልግም ሕጉ በሚፈቅደው ልክ እንዲሆንና በአጠቃላይ

የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 4.12 በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

በወጪ ተመዘገቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ12 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 18,051,060.71 እና በቦርድ ያልፀደቀ ብር 39,648,133.82 ፤በ2 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 8,279,360.54 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ እና በ7 መ/ቤቶችና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች ብር 211,225,466.81 መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-26 እና 26/1 እና አባሪ-33/ለ ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኘነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 4.13 ሌሎች ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዘ የሚታዩ ችግሮች

### 4.13.1 የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ

የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ከተለያዩ የግንባታ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን የተጠናቀቁት የግንባታ ሥራዎች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ኮሌጁ ከአሊ ሞሚን ጠቅላላ የውሀ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ጋር ለውሀ መስመር ዝርጋታ ግንባታ በብር **7,379,375.32** ውል የፈጸመና ሥራውም ተጠናቆ ከተቋራጩ ጋር ጊዜያዊ ርክክብ የፈጸመ ቢሆንም፡-
  - በውሀ መስመሩ ላይ ተዘርግተው የነበሩት በርካታ የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች ከመሀል የተነሱና በገዋኔ ከተማ በሚገኘው ውሀ ስራዎች

ኮንስትራክሽን ድርጅት ግቢ ውስጥ ሜዳ ላይ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን፣ በውሀ መስመሩ ላይ የቀሩት የውሀ ማስተላለፊያ ቧንቧዎችም ቢሆኑ አልፎ አልፎ የወላለቁ መሆኑ፤

- ኮሌጁ የውሃ መስመሩን ዝርጋታ ርክክቡ ከፈጸመበት ከመስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 60,000.00 የውሀ ማመላለሻ ቦቴ መኪና ተከራይቶ በድምሩ ብር 540,000.00 ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ ከመሆኑም በላይ ወጪው አሁንም የቀጠለ መሆኑ፤
- ኮሌጁ ከሁሴን ኢብራሂም ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር በብር **9,221,913.25** የመኖሪያ ቤት ግንባታ ውል የፈጸመና ሥራው ተጠናቆ ርክክብ የተከናወነ ቢሆንም ለግንባታው የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ማስወገጃ አብሮ ስላልተገነባለት ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመታት በላይ ተቆልፎ የሚገኝ መሆኑ፤
- ኮሌጁ ኤፍ ኤ ዋይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር በብር 5,468,710.00 የህንጻ ጥገና ግንባታ ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ጥገናው ከመጋቢት **2006** ዓ.ም ጀምሮ በስምንት ወራት ውስጥ ማለቅ እንዳለበት ቢጠቀስም ግንባታው ከመዘግየቱም በተጨማሪ የጥገናው ሥራ ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ በተቋራጩ ላይ ምንም ዓይነት ህጋዊ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

➢ ብር 4,409,902.50 ቅድሚያ ክፍያ መስጠት ሲገባ ብር 14,699,675.00 ሙሉውን ጠቅላላ የውሉን ዋጋ ተሰጥቶ የተገኘ መሆኑ፤

**በወላይታ ዩኒቨርሲቲ** በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 11 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

**በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ**

➢ በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 4 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ በውሉ በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሠረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 8 የህንጻ ተቋራጮች መኖራቸው ታውቋል፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱት አሰራሮች እንዲስተካከሉ የተጀመሩት ግንባታዎች በጊዜያቸው እንዲጠናቀቁና በውል በተቀመጠው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው የደረሰው የጉዳት ካሳ እንዲጠየቅበት አሳስበናል፡፡

# 5 <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

## 5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ት/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ74 መ/ቤቶችና በ12 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 789,616,771.63 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን | ብር | 91,229,531.87 |
| የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች | " | 33,769,155.94 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 70,006,646.80 |
| የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 561,748,905.23 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 340,571.66 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 32,521,960.13 |
| ድምር | ብር | 789,616,771.63 |

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 46,920,159.94 ፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 113,557,523.40 ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 15,796,869.41 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 32,993,267.39 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 580,348,951.46 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡ በተጨማሪም በ6 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 177,292,636.49 በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ለማን እንደሚከፈል፤ መቼ እንደተከሰተ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 444,126,372.81፤በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 53,982,806.33፣ ፤ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ብር34,323,631.25፣ በገ/ጉ ባ/ሞጆ ቅ/ጽ ቤት ብር 22,431,939.13፤አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,401,956.01 እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብር 18,402,285.79 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የተከፋዩን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለባቸው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር95,816,056.39 እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 32,302,818.25 እና ሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 22,649,840.58 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑ እየተጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

## 5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ሌሎች ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ያልተመዘገበ የግንባታ የቅድመ ክፍያ ተመላሽ በሶስት መ/ቤቶች ብር 5,318,289.92 እና የመያዣ ተከፋይ ሂሳብ ያልተመዘገበ በአንድ መ/ቤት ብር 392,974.88 መገኘቱ፤
- በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ በ2 መ/ቤቶች ብር 505,688.91 መገኘቱ፤ (አባሪ-27/1)
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ8 መ/ቤቶችን ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 42,013,985.99 መኖሩ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ3 መ/ቤቶች ብር 82,444,473.66 ተገኝቷል፡፡
- መደበኛ የመነሻ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ (ዴቢት ሚዛን) የተከፋይ ሂሳብ በ3 መ/ቤትና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,301,372.12 መኖሩ፤
  /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል፡፡

## 6 የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ41 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀትና የውስጥ ገቢ ብር 765,807,523.17 እና ከካፒታል በጀት ብር 132,675,821.28 በድምሩ ብር 898,483,344.45 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 3,120,487.35 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 339,537,427.65 |
| የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 202,875,267.40 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | | 6,729,911.39 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 346,220,470.66 |
| ጠ/ድምር | ብር | 898,483,344.45 |

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 330,099,679.28 ፣ የፌ/ቴክኒክና ሙያ ት/ትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 184,334,927.00፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብር 75,535,092.74፣ የወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 48,993,357.87፤ አሶሳ

ዩኒቨርሲቲ ብር 43,493,792.01፤ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 36,092,729.98 እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,382,001.57 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ7 መ/ቤቶች እና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 211,225,466.81 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች እና በ2 መ/ቤቶች ብር2,363,085.86 ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበን ሂሳብ በጀት ሳያስፈቅዱ ወጪ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በ150 መ/ቤቶች ብር 2,718,103,111.41 እና ካፒታል ብር 4,060,527,838.33 በድምሩ ብር 6,778,630,949.74 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 816,712,645.58 |
| የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | " | 291,074,233.48 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | " | 659,899,212.60 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | " | 1,328,728,994.66 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | " | 2,124,338,098.30 |
| ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | " | 1,557,877,765.12 |
| ጠ/ድምር | ብር | 6,778,630,949.74 |

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- ትምህርት ሚኒስቴር ብር 552,751,378.98፤የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 442,587,357.18 ፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 444,892,606.80፤ የአ.አ.ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 373,137,325.30፤ አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 347,481,497.23 ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 291,074,233.48 ፤ ቤተ መንግስት አስተዳደር ብር 254,352,530.36 እና አምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 248,701,428.64 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

# 7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

## 7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-34/ሀ እስከ አ ተመልክቷል፡፡/

| የግኝቶች መግለጫ | መ/ቤቶች | ቅ/ጽ/ቤቶች |
|---|---|---|
| ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ | 30 | 4 |
| ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ | 18 | 2 |
| የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ | 19 | |
| ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ | 9 | 7 |
| የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች | 9 | 7 |
| አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው | 18 | 4 |
| አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው | 45 | 13 |
| ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው | 17 | |
| በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች | 1 | |

| | | |
|---|---|---|
| በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው:- 59 የተለያዩ ተሽከሪካሪዎችና 63 ሞተር ብስክሌቶች ሲሆን፤ በ4ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት ያልተገለጸ | | 7 |
| የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለጹ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር131,538.68 ይገኙበታል) | 8 | |
| የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤ | 1 | |
| የንብረት ጉድለት የተገኘባቸው ፤ ዋጋቸው ብር 38,073.53 እና 1 ታብሌት ኮምፒዩተር | 4 | |
| በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች | 1 መ/ቤት | |
| ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች | 7 | 2 |

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል፡፡ እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸውና ሊወገዱ የሚገባ የተለያዩ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች በበርካታ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| የግኝቶች መግለጫ | ብዛት | | |
|---|---|---|---|
| | የመ/ቤቶች | ተሽከርካሪዎች | ሞተር ብስክሌቶች |
| ሊብሬ ያልቀረበላቸው | 25 | 120 | 38 |
| በብልሽት ምክንያት የቆሙ | 31 | 325 | 37 |
| የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣ | 9 | 21 | 25 |
| የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ | 16 | 119 | 2 |
| የሞተር ቁጥር የሌላቸው | 2 | 8 | |
| የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት | 1 | 2 | |
| የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ | 4 | 39 | 2 |
| የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ | 1 | | |
| በኃላፊ ተወስዶ ተመላሽ ያልተደረገ ተሽከርካሪ(1 ኒሳን ፓትሮል መኪና) | 1 | 1 | |
| ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ | 1 | 1 | |

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 /ሀ እስከ ቀ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፣ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣላቸውና ሰሌዳ የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

## 8 ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ68 መ/ቤቶች እና 11 ቅ/ጽ/ቤቶች/ተጠሪ ጽ/ቤቶች

በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱና አሁንም ትኩረት እንዲሰጥበቸው ያህል /ዝርዝሩ በአባሪ-36/1 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየዘርፉና በየመ/ቤቶቹ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ በመጀመሪያ በቀረበው እያንዳንዱ ሪፖርት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል፡፡

<u>የክዋኔ/አካባቢ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

**1.የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን የተፋሰስ ልማትና የውሃ ሀብት አስተዳደር አፈጻጸምን በተመለከተ**

- **በአባይ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች ልማትና እንክብካቤን በተመለከተ፡-**

1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአባይ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል የልማትና እንክብካቤ ተግባራት በማከናወን በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ስነ- ምህዳርን ከጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
2. በባለስልጣኑ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ (ከ 2008 - 2012 ዓ.ም) በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ስነ-ምህዳርን ከጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ስነ-ምዳሮች እንክብካቤ በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ቡአካ፣ ርብ እና አርጆ ዲዴሳ ንዑስ ተፋሰሶች ሥር በሚገኙ ወረዳዎች፣

- በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የመሬት መንሸራተት፣ ቦረቦሮችና አፈር መሸርሸር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ፣ ከእንሽስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ በተፋሰሱ ዙሪያ የደን መጨፍጨፍ፣ በህጋዊም ሆነ ህገ ወጥ መንገድ ከተራራማ ቦታዎችና ከተቦረበሩ መሬቶች አሸዋ ማውጣት መኖሩ፤ ከከፍታ በላይ ተራራማ ቦታዋች የሚታረሱበት ሁኔታ መኖሩንና ወደ ወንዝና ሀይቅ የሚገባ ደለል በየጊዜው እየጨመረ መሆኑ፣
- በአርጆ ዲዴሳ ንዑስ ተፋሰስ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን በጊንቢ ወረዳ እና

አካባቢው በ2009 ዓ.ም በተከሰተ የመሬት መንሸራት ምክንያት 18 የአባወራ ቤቶች ላይ ጉዳት መድረሱ፤ የድልድይና፣ አስፋልት መሰረተ ልማት እየተጎዳ መሆኑን፣ በምዕራብ ወለጋ ዞን ነጆ እና ቦጂ ዲርመጂ ወረዳዎች በመሬት መንሸራተት ምክንያት ወደ 1.4 ሄክታር የሚገመት መሬት ተገምሶ የሄደ መሆኑ እና እስከ 15 ሜትር ጥልቀት ያለው ገሊ የተፈጠረ መሆኑ፣

- በቆጋ ግድብ የላይኛው ተፋሰስ የሚገኙ አብሮ መኖር፤ ይነሳ ለምርት፣ ስራ በተግባር እና ፊለገ ህይወት ቀበሌዎች የተፋሰስ ልማት ስራ ቀጣይነት ባለው መልኩ ባለመሰራቱ ለአፈር መሸርሸር የተጋለጡ በመሆናቸው ምክንያት ወደ ግድቡ የሚገባው ደለል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ፣ በፊንጫ ንዑስ ተፋሰስ ላይ የመሬት መራቆት በመስፋፋቱ በተለይ ከፍተኛ ቦረቦሮች በቁጥርና በስፋት እየበዙ መምጣታቸው፣

ከተከለሱ መረጃዎችና እና በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- **በተፋሰሱ ለረግረጋማ መሬት አስተዳደር፤ ለወንዝና ለሐይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀምን በተመለከተ እና የተራራማ ቦታዎች ከከፍታ በላይ አለመታረሳቸውን በተመለከተ**

3. በተፋሰሱ ለረግረጋማ መሬት አስተዳደር፤ ለወንዝና ለሐይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም እና ከከፍታ በላይ ተራራማ ቦታዎች እዳይታረሱ የተሟላ የፖሊሲ ማእቀፍ እንዲሁም ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
4. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በቡአካ ንዑስ ተፋሰስ መቂት ወረዳ 021 ቀበሌ ማሰሩት እማሙዝ ተፋሰስ፣ 029 ቀበሌ ቆላ ዋርካ እና ደጋ ዋርካየ ተፋሰስ፣ 022 ቀበሌ ደብር ተፋሰስ ከከፍታ በላይ ተራራማ ቦታዎች የሚታረሱ መሆኑ እንዲሁም በወረዳው የተቀሩት ቀበሌዎችም የሚታረሱ እና በቀጥታ ወደ አባይ የሚፈሱ መሆኑ፤ በርብ ንዑስ ተፋሰስ ፋርጣ ወረዳ ጊምጂ ተፋሰስ ከከፍታማ ቦታ በተጨማሪ የተፋሰሰ ስራ የተሰራባቸው ቦታዎች ሳይቀሩ የሚታረሱ መሆኑ፤
- እንዲሁም በተፋሰሱ የሚገኙ የውኃ አዘል መሬቶችን የመለየትና ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል የረግረጋማ መሬቶችን ይዞታ የሚያሳይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የረግራጋማ መሬቶችን ዘላቂነት ባለውና የተፈጥሮ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ለመንከባከብና ለመጠቀም የሚያስችል የማኔጅመንት ዕቅድ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ለረግረጋማ መሬት አስተዳደር፣ ለሃይቆችና ወንዞች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም እና ከከፍታ በላይ ተራራማ ቦታዎች እንዳይታረሱ የተሟላ የፖሊሲ ማእቀፍ እንዲሁም ደንብና መመሪያ በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/2000 ዓ.ም ተቆጣጣሪው አካል አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር በመመካከር እና በመተባበር የተወሰኑ የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ወሰን መከለል እና በተከለሉ የውሃ አካላት ዳርቻዎች ክልል ውስጥ ያሉ እጽዋት ሽፋኖች ወይም ዛፎች እንዳይመነጠሩ ወይም እንዳይቆረጡ እንዲሁም የመኖሪያ ቤቶች እንዳይገነቡ መከልከል እንዳለባቸው ቢገልጽም፤ በተፋሰሱ የረግረጋማ መሬት አስተዳደርና የሀይቆች ዳርቻ ክልልን የሚመለከት ጥናት ያልተካሄደ እና የሀይቆች ዳርቻ ክልል (Buffer Zone) እና የረግረጋማ መሬት ወሰን የሚያሳይ ካርታ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
    - በጣና ንዑስ ተፋስስ ብቻ እ.ኤ.አ ከ1986 እስከ 2013 (1978-2005 ዓ.ም.) በተደረገ ጥናት በተፋሰሱ አብዛኞቹ ረግረጋማ መሬቶች ወደ ደረቃማ ስፍራዎች ተቀይረው ለተለያዩ አገልግሎቶች እየዋሉ መሆኑ፣
    - በጣና ንዑስ ተፋሰስ የጣና ሐይቅን የወረረዉ መጤ አረም እምቦጭ /Water Hyacinth/ 40 ሺህ ሄክታር አካባቢ የሚሆን የጣና የሀይቅና ረግረጋማ መሬቶች የሸፈነ መሆኑና 18 ቀበሌዎች በመጤው አረም ተጠቂ መሆናቸው፣
    - የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በፈር ዞን አካባቢ ሊሰሩ ከሚገባቸው የተፋሰስ ልማት እና እንክብካቤ ስራዎች አንጻር እስካሁን ምንም አይነት እንቅስቃሴ ያልተጀመረ መሆኑ፣
    - በቆጋ፤ በርብ እና ደዴሳ መስኖ ግድቦች ዙሪያ ጥብቅ ክልል (Buffer Zone) ያልተለዩ መሆኑ እና  በግድቦቹ ዙሪያ የእርሻ ስራ የሚከናወን እና ከብቶች የሚሰማሩበት መሆኑ፣

ከተከለሱ መረጃዎችና በመስክ ጉብኝት ታውቋል፡፡

➢ **በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች ተፅዕኖ ግምገማን በተመለከተ፡-**

5. በወንዞች፣ ሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት በማከናወን በወንዞች፣ በሀይቆችና በሌሎች የውሃ አካላት ላይ የሚፈጥሩትን ተፅዕኖ ለይቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የሚጠኑ ጥናቶች ላይም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት አስተያየት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

6. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በተፋሰሱ ውስጥ ባሉ ወንዞች፣ በሀይቆችና በሌሎች የውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች በሚያሰጠኑዋቸው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ላይ ጉልህ ጉዳት በማያደርሱ መልክ መጠናቱን በማረጋገጥ አስተያየት እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑ፣ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ የውሃ አካላቶች ዙሪያ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ እንዳያስከትሉ በተጠናው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት መሰረት እየተከናወኑ ስለመሆኑ በባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉ፣ ታውቋል፡፡

➢ **በተፋሰሱ የውሃ አካላትን፣ ሐይቆቹንና የብዝሀ ሕይወቱን ሕልውና ከብክለት መከላከልን በተመለከተ፡-**

7. ከከተሞችና ከእንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን አካባቢውን በማይጎዳ መልኩ ማዘጋጀትና ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዞችና ሐይቆች ከመለቀቁ በፊት ቆሻሻው መታከሙን ማረጋገጥ እና በአካባቢ ጥበቃ ህግና መርህ መሠረት ባደረገ መልኩ ተግባራዊ መደረጉን ክትትል መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ሀይቆቹንና የብዝሀ ህይወቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ አሉታዊ ተጽኖዎችን የመለየት፣ የመቀነስና የመከላከል ስራን ከባለ ደርሻ አካላት ጋር በመሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

8. በተፋሰሱ አካባቢ የሚገኙ ከከተሞችና ኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች ወደ ተፋሰሱ የውሃ አካላት ለመልቀቅ ከተፋሰሱ ፈቃድ የሚስፈልግ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት

- በተፋሰሱ አካባቢ የሚገኙ ከከተሞችና ኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች ወደ ተፋሰሱ የውሃ አካላት ለመልቀቅ ከተፋሰሱ ፈቃድ የሚያስፈልግ

ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ከሦስት ድርጅቶች በስተቀር ሌሎቹ ኢንዱስትሪዎች ከምርት ክፍላቸው የሚለቀቀው ውሃ በካይ የሆኑ ንጥረ ነገሮችንና ውሁዶችን የያዘ የተበከለ ውሃና ያለምንም ቅድመ ማጣራት ወደ ወንዞችና ሃይቆች የሚለቁ መሆኑ፣ የታከመ ቆሻሻ ውሃን ወደ ወንዝም ሆነ ወደ ሀይቅ ለመልቀቅ ፍቃድ የሌላቸው መሆኑ ነገር ግን ፍሳሻቸውን ያለፈቃድ ወደ ተፋሰሱ የውሃ አካላት የሚለቁ መሆኑ፣

- ከከተሞች፣ ከሆቴሎች፣ ከፋብሪካዎች፣ ከሆስፒታሎች፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ እና ከመሳሰሉት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ወደ ሐይቆቹም ሆነ ወንዞች የሚለቁት ቆሻሻ እየጨመረ መሄዱና መታከሙ ላይ ቁጥጥር በባለስልጣኑ የማይደረግ መሆኑ፣

ከተከለሱ ማረጃዎችና በመስክ ምልከታ መታወቁ፣

> **በተፋሰሱ የውሃ መጠቀሚያ ክፍያ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

9. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ የውሃ መጠቀሚያ ክፍያ ስርዓት በመዘርጋትእና የአጠቃቀም መመሪያ በማዘጋጀት ከተጠቃሚዎች የውሃ አገልግሎት ክፍያ እንደአገልግሎቱና አጠቃቀሙ ዓይነት መሰረት ገቢ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

10. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በውሃ ክፍያ ላይ የአከፋፈል ታሪፍ መመሪያ አለመኖሩ፣ በተለያዩ አካባቢዎች በባለሥልጣኑ የሚታወቁ ከፍተኛ የውሃ ሀብት የሚጠቀሙ 185 ድርጅቶች ለሚጠቀሙት በዓመት በአማካኝ 1,549,207,487 ሜትር ኪዩቢክ ውሃ የሚከፍሉት ክፍያ አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

> **ባለስልጣን መ/ቤቱ የተፋሰሱን ዋና ዋና ወንዞች የደለል መጠን መረጃ በመሰብሰብና፣ መተንተኑን በተመለከተ**

11. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተፋሰሱን ዋና ዋና ወንዞች የደለል (sedimentation) መጠን መረጃ በመሰብሰብና፣ በመተንተን ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ማደራጀት አለበት፡፡ መረጃዎቹንም መሰረት በማድረግ ደለሉን ለመከላከል የተፋሰስ ልማት ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

12. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተፋሰሱ ውስጥ፣

- የላይኛው የአባይ ተፋሰስ ውስጥ  የጀማ ንዑሰ ተፋሰስ 19-27 ሚሊዮን ቶን በዓመት፣ የደቡብ ጉጃም ንዑሰ ተፋሰስ 11-17 ሚሊዮን ቶን በዓመት፣ የአርጆ ደዴሳ ንዑሰ ተፋሰስ 12-14 ሚሊዮን ቶን በዓመት፣ በአማካኝ  የአፈር ደለል ይዘው

የሚጓዙ ይህም ከፍተኛ መሆኑን፣

- በደለል መረጃቸው ያልተሰበሰበና ለአጠቃቀም ምቹ በሆነ መልኩ ያልተደራጁ የተወሰኑ ወንዞች መኖራቸው፣
- በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ ወንዞች፣ ሀይቆች እና ግድቦች በከፍተኛ ሁኔታ በደለል ተጠቂ ቢሆኑም በቂ የሆነ የደለል መረጃ አለመኖሩ፣ ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- በተፋሰሱ ያለውን ችግር ለመቀልበስ የሚያስችል የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ በጉዳታቸው መጠን ከፍተኛ የሆኑ የመሬት መንሸራተት፣ የደን መራቆት፣ ቦረቦሮችና አፈር መሸርሸር እና የፕሮጀክት ዶክመንት የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች በመለየት እና የፋይናንስ ምንጭ በማፈላለግ ፕሮጀክት ቀርጾ የመልሶ ማልማት ሥራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊሰራ እንደሚገባ፣
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ለረግረገማ መሬት አስተዳደር እና ለሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም የተሟላ የፖሊሲ ማእቀፍ እንዲሁም ደንብና መመሪያ ከሚመለከታቸው የመንግስተ አካላት ጋር በትብብር በማዘጋጀት እና በመትገበር ረግረገማ መሬት እና የሃይቆች ዳርቻ ጥብቅ ክልል (Buffer Zone) መጠበቅ፣ የውሃ አካላት ዳርቻዎች፣ ረግረጋማ መሬቶች እንዳይታረሱ በማድረግ ማልማትና መንከባከብ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም እንዲያግዘው በውሃ አካላት ጥበቅ ክልል (Buffer Zone) እና የረግረጋማ መሬት ወሰን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ የውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሲከናወኑ የባለሥልጣን መ/ቤቱ አስተያየት የሚጠየቅበትን እና በወንዞች፣ በሀይቆችና በሌሎች የውሃ አካላት ላይ የሚፈጥሩት ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ አለማሳደሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ላይ የተቀመጡ የመከላከያና የጉዳት ተጽዕኖ መቀነሻ ተግባራት ወደ ሥራ መተግበራቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ ማንኛውም አካል በውሃ ሀብቱ ከመጠቀሙ በፊት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ማውጣቱን እና ፈቃድ ሳወጡ በውሃ ሀብቱ የሚጠቀም አለመኖሩን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፤ በተጨማሪም በተፋሰሱ ወደሚገኙ የውሃ አካላት ፍሳሽ ቆሻሻን ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ፈቃድ ሊሰጥና በፈቃዱ

መሰረት ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዞች ከመለቀቃቸው በፊት እየታከመ መለቁቅን (በተመረጡ ቦታዎች በተፋሰሱ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ጥራትን ለማወቅ የሚያስችል መሳሪያ በማቆም ጭምር) ማረጋገጥ አለበት፡፡ እንዲሁም ከባለድርሻ አካለት ጋር በመተባበር ከከተሞችና እንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን አካባቢውን በማይጎዳ መልኩ መዘጋጀታቸውንና ተፋሰሱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለማሳደራቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

☞ የውሃ ተጠቃሚዎች ለሚጠቀሙት ውሃ የሚከፍሉት ክፍያ ስርዓት በመዘርጋትና የታሪፍ ተመን በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ወደ ተግባር መሸጋጋር ይጠበቅበታል፡፡

☞ የተፋሰሱን ዋና ዋና ወንዞችና ሐይቆች የደለል (sedimentation) መጠን መረጃ በመሰብሰብና፣ በመተንተን ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ በማደራጀትና በመተንተን የወንዞቹና የሀይቆቹ እና እነርሱን መሰረት ተደርገው የተሰሩትን እና ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸውን የተለያዩ ግድቦች በደለል አማካኝነት ጉዳት እንዳይደርስባቸው የቅድመ መከላከል ሥራ የሚሠራበትን ሁኔታዎች በየጊዜው ሊያመቻች ይገባል፡፡

በማለት የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

## 2. በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን በተመለከተ

### ➢ በየዘርፉ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎችን አመራረጥን በተመለከተ፣

13. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዘርፉ ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ የመምረጫ መስፈርት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊያዘጋጅ፣ በመምረጫው መስፈርት መሰረት ቴክኖሎጂዎችን የሚመርጥ ኮሚቴ ሊያቋቁምና መረጣውን ሊያካሄድ ይገባል፡፡

14. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ቴክኖሎጂን ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት በማዘጋጀት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣ በየዘርፉ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጫው መስፈርት መሰረት የሚመርጥና የሚገመግም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በበላይነት የሚመራ ኮሚቴ መቋቋም ሲገባው ያልተቋቋመ መሆኑ፣ በየዘርፉ ወይም በየተቋሙ ቴክኖሎጂዎች ያለ መምረጫ መስፈርት እየተመረጡ መሆናቸው፣

- ወደ ሀገር ውስጥ በተለያዩ ዘርፎችና ዩኒቨርስቲዎች ቴክኖሎጂዎች በተለያዩ መንገዶች ወጥነት በጎደለው መልኩ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡና ኮፒ የሚደረጉ መሆናቸውን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ባለድርሻ አካላት ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **አገልግሎት የማይሰጡ ቴክኖሎጂዎች የሚወገዱበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

15. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዳዲስ ሆነው አገልግሎት የማይሰጡም ሆኑ አገልግሎት ሰጥተው ተበላሽተው የተቀመጡ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው በአግባቡ ሊወገዱ የሚችልበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

16. ይሁን እንጂ የጨረር አገልግሎት ሰጥተው የተበላሹ እቃዎችን በኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ እንዲወገዱ የሚደረግበት ሁኔታ ከመኖሩ ውጭ በናሙና ተመርጠው በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በመካከለኛና ከፍተኛ ማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይታወቁ መሆኑ፣ በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው የሚወገዱበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **የቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

17. ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም በመፍጠር የሚያስችል ስርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

18. ቴክኖሎጂን በማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም ለመፍጠር እንዲቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2006 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡ ነገር ግን እስካሁን ድረስ 17 የቀጠና ፎረም አስተባባሪዎች ከመመስረትና በትስስሩ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ትውውቅ ከመከናወኑ ባለፈ በትስስሩ የተከናወኑ ተግባራት ላይ ውስንነት መኖሩና ለውጥ ያመጣ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማትም ሆነ ከዩኒቨርስቲዎች

የሚወጡ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በተግባር ለመፈፀም ወደ ተለያዩ የኢንዱስትሪ ተቋማት በሚላኩ ጊዜ ተቋማቱ በተማሩት ትምህርት ላይ የማይመደቡ በመሆናቸው ትክክለኛውን ዕውቀት ይዘው የማይወጡ መሆኑን በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ባለድርሻ አካላት ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **ችግር ፈቺ ተብለው የሚከናወኑ ምርምሮች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩ መሆኑን በተመለከተ፣**

19. በከፍተኛ ምርምር ተቋማት የሚከናወኑ ምርምሮችና ጥናቶች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበትን ሥርዓት ሚ/ር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

20. ይሁን እንጂ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸው በከፍተኛ ምርምር ተቋማት የሚሰሩ ምርምሮች እና ጥናቶች ተለይተው ወደ ተግባር ሊሸጋገሩ የሚችሉበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለናሙና ከታዩትም ውስጥ፡

- ለአዲስ አበባ ተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በ2008 ዓ.ም አንድ ልጅ በሰራው ምርምር እንዲሸለም ከማድረግ ውጭ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር የተደረገበት አግባብ የሌለ መሆኑ፣
- ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮ፣ የምስራቅ ጀኔራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ የኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የአዳማ እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ሚ/ቴር መ/ቤቱ የፈጠራ ስራን ከመሸለምና ምርምሮችን አወዳድሮ የገንዘብ ድጋፍ ከማድረጉ ውጪ ወደ ተግባር እንዲለወጡ ያልተደረገ መሆኑን፣
- በምርምር የተደረሰባቸው፣ የፈለቁ ወይም የተቀዱ ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርትና ምርታማነት አለመቀየራቸው፣ የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከላት ያልተቋቋሙ መሆናቸው፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

21. በመሆኑም

- በሀገር ውስጥ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ለየዘርፉ የሚያገለግል የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅና በተዘጋጀው መምረጫ መስፈርት መሰረት ቴክኖሎጂዎችን የሚመርጥ ለየዘርፉ ኮሚቴ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በማቋቋም

ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ሽግግሩ እንዲከናወን የሚደረግበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ለቴክኖሎጂ ሽግግር ወደ አገር ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ ሳይውሉ ወይንም በሥራ ላይ ተበላሽተው ያሉ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው ሰው፣ እንስሳትና አካባቢን በማይጎዱ መልኩ የሚከማቹበት እና የሚወገዱበት ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር ለማስቻል የተዘረጋው የትምህርት ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር ለመፍጠር የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊነቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጥልቀት ሊፈትሽና የመፍትሔ አቅጣጫ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- ችግር ፈቺ ተብለው ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበት ስርዓት በመዘርጋትና ተግባር ላይ እንዲወጡና ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለምርምሩ መነሻ የነበሩት ችግሮች የሚፈቱበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም በምርምር የተደረሰባቸው፣ የፈለቁ ወይም የተቀዱ/ኮፒ የተደረጉ/ ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርትና ምርታማነት ለመቀየር የሚያችሉ የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከላትን በማቋቋም ምርምሮቹ ወደ ተግባር ተቀይረው ለባለድርሻ አካላት እና ለተጠቃሚዎች የሚሰራጨበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በማለት የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

## 3. በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሠራተኛ ማህበራት አደረጃጀትና መብት አጠባበቅን በተመለከተ

➢ **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች በማህበር የመደራጀት መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታ ስለመሆኑ፣**

22. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች በማህበር የመደራጀት መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ለማበረታታትና ለመደገፍ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

23. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ሥልጣን የተሰጣቸው የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ሠራተኞች በማህበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ለማድረግ የማበረታታትና የመደገፍ ሥራ መስራት ቢገባቸውም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራል የመንግስት የልማት ድርጅቶች

የሚሰሩ ሠራተኞች እንዲደራጁ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን በተለያዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ በሁሉም ድርጅቶች የሚሰሩ ሠራተኞች በማህበር የመደራጀት መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ ድጋፍ ባለመደረጉ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የተለያዩ አሰሪ ድርጅቶች መካከል የሰራተኛ ማህበር የተቋቋመባቸው ከ1,700 ያልበለጡ እንደሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰራተኛ ማህበር ሊቋቋምባቸው ከሚችሉ 7,614 ድርጅቶች መካከል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና በስሩ በሚገኙ የክፍለ ከተማ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤቶች ተደራጅተው የተመዘገቡ ከ542 የማይበልጡ የሰራተኛ ማህበራት ብቻ መኖራቸው፣ እንዲሁም በአስተዳደሩ ከሚገኙ በናሙና ከታዩ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤቶች የሰራተኛ ማህበር ሊቋቋምባቸው ከሚችሉ በየካ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ 730 አሰሪ ድርጅቶች መካከል በ56 (7.67%) ድርጅቶች፣ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ 987 አካባቢ ከሚሆኑ አሰሪ ድርጅቶች መካከል በ56 (5.67%) ድርጅቶች፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ 1,243 አሰሪ ድርጅቶች መካከል በ18 (1.45%) ድርጅቶች ብቻ የሰራተኛ ማህበራት የተቋቋሙ መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተሰብስበው ከተተነተኑ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

25. ከዚህ በተጨማሪም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰበታ ከተማ ከሚገኙ 775 አሰሪ ድርጅቶች መካከል በ65 ድርጅቶች፣ በዱከም ከተማ ከሚገኙ 552 አሰሪ ድርጅቶች መካከል በ21 ድርጅቶች ብቻ የሰራተኛ ማህበር እንደተደራጀ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **ሠራተኞች ከስራቸው ጋር በተያያዘ ምክንያት በማህበር እንዳይደራጁ ከሚከለክላቸው ነገሮች ጥበቃ ስለመደረጉ፣**

26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ከስራቸው ጋር በተያያዘ ምክንያት በማህበር እንዳይደራጁ ከሚከለክላቸው ነገሮች ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያደርግ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ ሰራተኞች በማህበር የመደራጀት መብት እንዳላቸው በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት ላይ እና በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በግልጽ የተቀመጠ

ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች በማህበር እንዳይደራጁ ከሚከለክላቸው ነገሮች ጥበቃ እንዲደረግላቸው፣ እንዲሁም የሰራተኛ ማህበራት እንዳይደራጁ በሚከለክሉ አሰሪ ድርጅቶች ላይ ስለሚወሰድ አስገዳጅ ህጋዊ እርምጃ የተቀመጠ የአሰራር ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

➢ **ለሰራተኛ የሚከፈል አነስተኛ የመነሻ ደመወዝ (minimum wage) መጠንን በተመለከተ፣**

28. በብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና እስትራቴጂ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሰራተኞች የሚከፈል ዝቅተኛ የደመወዝ መጠንን በተመለከተ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ በብሔራዊ የስራ ስምሪት ፖሊሲና ስትራቴጅ ላይ አነስተኛ የመነሻ ደመወዝ መጠን ለመወሰን የሚያስችል ስርዓት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲዘረጋ የሚደነግግ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ሥርዓቱ እንዳልተዘረጋ ታውቋል፡፡

**በፌደራልና በክልል የተደራጁ የሰራተኛ ማህበራትን ዝርዝር መረጃ እና በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ስለመኖሩ፣**

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የሚመለከቱ አገር አቀፍ መረጃዎች የሚያዙበት የመረጃ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚዘረጋው የመረጃ ሥርዓት በፌደራልና በክልል የተደራጁ የሰራተኛ ማህበራትን ዝርዝር መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ብሔራዊ የመረጃ ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ቢደነገግም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተግባራዊ አለመሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል የተደራጁ የሰራተኛ ማህበራትን ዝርዝር መረጃ ያልያዘና በኢትዮጵያ አጠቃላይ የተደራጁ የሰራተኛ ማህበራት ብዛት በትክክል እንደማይታወቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

31. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተደራጁ የሠራተኛ ማህበራት ከአሰሪዎቻቸው ጋር የህብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ሊያበረታታና ድጋፍ ሊሠጥ የሚገባ ቢሆንም ከ2007-2009 ባሉት በጀት ዓመታት ውስጥ በህዳር 2008 ዓ.ም እና በጥር

2009 ከአስራ ሦስት የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ አሰሪና ሰራተኛ ማህበራት አመራሮች እንዲሁም በግንቦት 2009 ዓ.ም ከአስራ ሁለት የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ የአሰሪና መሰረታዊ የሰራተኛ ማህበራት አመራሮች በህብረት ድርድርና ስምምነት ላይ ስልጠና በመስጠት ድጋፍ ቢያደርግም በክልሎች እና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ አስፈፃሚዎች፣ ለኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን እና በተለያዩ ዘርፎች ለተደራጁ የሰራተኛ ማህበራት ኢንዱስትሪ ፌዴሬሽኖች የሰጠው ድጋፍ አለመኖሩ፤

32. በመሆኑም፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌደራል የመንግስት የልማት ድርጅቶች በተጨማሪ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ አሰራር መዘርጋቱን ለማረጋገጥ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ ድርጅቶች የሚሰሩ ሠራተኞች በማህበር የመደራጀት መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ የሚያስችል ስርዓት ከሚመለከታቸው የክልል መስተዳድር አካላት ጋር በመተባበር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህንንም በማድረግ መደራጀት እያለባቸው ያልተደራጁ ማህበራት የሚደራጁበትን መንገድ በማመቻቸት ሠራተኞቹ በህገመንግስት የተሰጠ የመደራጀት መብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀውን ሰባት አመት ያስቆጠረ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ረቂቅ አዋጅ ከጊዜው ሁኔታ ጋር ወቅታዊ በማድረግ እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ግብአት በማካተት በሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ በማድረግ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች በህገመንግስቱ እና በአሰሪና ሠራተኛ አዋጁ የተሰጣቸውን መብት ተጠቅመው በማህበር እንዳይደራጁ ከሚከለክላቸው ነገሮች ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያደርግ ሥርዓት እና የሰራተኛ ማህበራት እንዳይደራጁ በሚከለክሉ አሰሪ ድርጅቶች ላይ ስለሚወሰድ ህጋዊ እርምጃ ግልጽ የሆነ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲጠበቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አነስተኛ የመነሻ ደመወዝ መጠን (minimum wage) ለመወሰን የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እና ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም በፌደራልና በክልል የተደራጁ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሚተዳደሩ የሰራተኛ ማህበራትን እና የአሰሪ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡

የሚሉ የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 4. በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ ብቃትና ውጤታማነትን በተመለከተ

➢ **የሚከናወኑ የላቦራቶሪ ምርመራዎችና ለምርመራ ወደ ውጭ የሚላኩ ናሙናዎችን በተመለከተ፤**

33. መ/ቤቱ ያቋቋመው ላቦራቶሪ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራዎችን በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ በማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ ናሙናዎችን ቁጥር መቀነስ ይገባል፡፡ የተቋቋመው ላቦራቶሪ ደረጃውን ጠብቆ አገልግሎት እንዲሰጥ ብቃቱ በየጊዜው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

34. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በመ/ቤቱ ላቦራቶሪ የተለያዩ የላቦራቶሪ ዕቃዎች የተሟሉ ባለመሆናቸው፣ ሥራ ላይ ሳይውሉ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች በላቦራቶሪው መጋዘን ውስጥ የተከማቹ በመሆኑ፣ የተበላሹ የላቦራቶሪ ዕቃዎች በወቅቱ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ የማይደረግ በመሆኑ፣ በላቦራቶሪው ውስጥ አዳዲስ ማሽኖች ተገዝተው ለረጅም ጊዜ ሥራ ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ በመሆኑ ወደ ውጪ የሚላኩ ናሙናዎች መጠን እየጨመረ መምጣቱን ከማዕድን ሚኒስቴር በተገኘው ማስረጃ መሰረት ለማየት ችለናል፡፡

➢ **በመ/ቤቱ ላሉ የላቦራቶሪ እና የድሪሊንግ (ቁፋሮ) መሳሪያዎች የካሊብሬሽን ስራ እና የጥገና አገልግሎት መሰጠቱን በተመለከተ፤**

35. የቁፋሮ (የድሪሊንግ) እና የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጡ መሳሪያዎች በትክክል አገልግሎት እንዲሰጡ በየጊዜው ካሊብሬት ሊደረጉ ይገባል፡፡ ካሊብሬሽንም ሆነ መደበኛ ጥገና ለማከናወን የሚያስችል አሰራር ስርዓት በመ/ቤቱ ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

36. ይሁን እንጂ፡-

- በቀረበልን ማስረጃ መሰረት በላቦራቶሪ ላይ ካሊብሬሽን የተከናወነው በትግራይ ክልል ብቻ በሚገኙ የመ/ቤቱ ወርቅ ሚዛኖች ላይ ሲሆን በላቦራቶሪው ውስጥ ያሉት ማሽኖችና የናሙና ማድረቂያ ማሽን ካሊብሬት ያልተደረጉ መሆኑ፣ የቁፋሮ/ ድሪሊንግ ማሽኖች ካሊብሬት ስለመደረጋቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- የማዕድን መቆፈርያ መሳሪያዎች ረጂም ጊዜ ያገለገሉ መሆናቸው እና የሞተር እድሳት ተደርጎላቸው ስለማያውቅ አስፈላጊውን የቁፋሮ ልኬት (ፓራ ሜትር) በመጠቀም ቁፋሮ ለማካሄድ እንዳልተቻለ እና ይህ ችግር አሁንም ድረስ ያልተቃለለ መሆኑ፣
- ብሔራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት በሰራው የካሊብሬሽን ስራ ላይ መ/ቤቱ ማስተካከያ እየሰራ እንዲሄድ በዕቃው ላይ ያለውን ክፍተት በሰርተፍኬት ላይ መዝግቦ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ በሰጠው የማስተካከያ ሃሳብ መሰረት እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- በአብዛኛው መ/ቤቶች ማሽኖችን ካሊብሬት ለማስደረግ የሚመጡት አስገዳጅ ሁኔታ ሲመጣ እንጂ በመርሀ ግብር መሰረት አለመሆኑን የብሔራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት የስራ ሃላፊዎች መግለፃቸው፣
- እንዲሁም መደበኛ ጥገና በዕቅድ ተይዞ መከናወኑ ሲጣራ የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና እንክብካቤ ክፍል የሶስት አመት (ከ2007-2009 ዓ/ም) ዕቅድ አፈፃፀም 29%፣ 15% እና 15% መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

- **የመ/ቤቱን የናሙናዎች እና የንብረቶች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ፤**

37. በመ/ቤቱ የሚገኙ የቁፋሮ /ድሪሊንግ፣ እና የላቦራቶሪ ንብረቶችን በአግባቡ ለመያዝና ለመጠቀም የሚያስችል የንብረት አያያዝና አጠቃቀምሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ያገለግሉ እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች (የቁፋሮ ማሽኖች፣ የላቦራቶሪ ማሽኖች፣ ኬሚካሎች) እና ለምርመራ የመጡ ናሙናዎች አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
38. ይሁን እንጂ
    - ከተገልጋዮች የሚመጡ ናሙናዎች በተዝረከረከ ሁኔታ የሚቀመጡ መሆኑን፣

- ምርመራቸው የተጠናቀቀ ናሙናዎች በመ/ቤቱ መጋዘን ውስጥ ሳይወገዱ ከ30 ዓመት በላይ በላይ ተጠራቅመው የተቀመጡ መሆኑን፣
- መካኒሳ በሚገኘው የላቦራቶሪው መጋዘን ውስጥ በባህርይ የማይገናኙ ንብረቶች እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆናቸውን፣ በመካኒሳና በዋናዉ ግቢ ዉስጥ የሚገኙ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የቁፋሮ (ድሪሊንግ) መሳሪያዎች እንዲሁም ጥገና ቢደረግላቸው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የማዕድን ቁፋሮ ማሽኖች (ሪጎች) ሜዳ ላይ በመቀመጥ ለፀሀይና ለዝናብ በመጋለጥ አግባብ ላልሆነ ብክነት የተዳረጉበት ሁኔታ መኖሩን፣ በተጨማሪም በ1979 ከጃፓን (የዋጋ መጠናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው) ተገዝተው የገቡ ማሽኖች እስከ አሁን ድረስ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆናቸውን፣
- ICP-OES (Inductively Coupled Plasma Optical Emission Spectrometry) የተባለው ማሽን ከ7 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መሆኑን፣ በወቅቱ AAS (Atomic Absorbtion Spectrometer) የተባለው ማሽን በቁጥር ሁለት የተገዛና አንዱ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ሁለተኛው ያለአገልግሎት ከ5 አመት በላይ የተቀመጠ መሆኑን፣ የላቦራቶሪው ዕቃ ግምጃ ቤት ከ2007-2009 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ውስጥ ቆጠራ ተደርጎለት የማያዉቅና የቋሚ ዕቃ መዝገብ የሌለው መሆኑን፣

- **የመስሪያ ቤቱን ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም በተመለከተ፤**

39. የተለያዩ የማዕድን ፍለጋ ፕሮጀክቶች የአፈፃፀም መርሀ ግብር ሊዘጋጅላቸውና በመርሀ ግብሩ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የመ/ቤቱን የሶስት አመታት ማለትም ከ2007-2009 ዓ/ም ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማየት እና ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- የሰው ሀይል ፍልሰት በከፍተኛ ሁኔታ ያለበት መስሪያ ቤት እንደሆነ በተደጋጋሚ በችግር እየተገለጸ ዕቅዶች ከፍተኛ (ከ100%- እስከ 500% በላይ) አፈፃፀም ማሳየታቸው መ/ቤቱ ዕቅድ ሲያቅድ ጥናትን መሰረት የማያደርግ መሆኑን፣ በየአመቱ ዕቅድ ሲታቀድ የመጀመሪያውን አመት አፈፃፀም በማየት ለቀጣዩ አመት ማሻሻያ ማድረግ የሚገባ ሲሆን በዚህ መልኩ የማይታቀድና ከአቅም በታች በማቀድ ከፍተኛ አፈፃፀም እንዲታይ የሚደረግ መሆኑን፣ በሌላ በኩል በመ/ቤቱ ዝቅተኛ አፈፃፀም የሚታይባቸው ዕቅዶች መኖራቸው

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **በማዕድን ስራ ከተሰማሩ ተቋማት የጂኦሳይንስ መረጃዎችን መሰብሰብን፣ በዘመናዊ መልኩ ማደራጀትን፣ ማሰራጨትና የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤**

41. መ/ቤቱ የስነ ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለመሰብሰብ፣ ለማስተዋወቅ እና በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ ይሁን እንጂ የስነ ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለመሰብሰብ፣ ለማስተዋወቅ እና በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት የሚያስችል መመሪያ የሌለ መሆኑን፣ በተለያዩ ተቋማት የተጠኑ የማዕድን ጥናቶች መረጃ ወደ መ/ቤቱ ወጥ በሆነ መልኩ የማይሰበሰቡ መሆኑን፣ በመ/ቤቱ የተሰበሰቡ ናሙናዎች አስፈላጊውን መረጃ አካተው ለተገልጋይ ዝግጁ ለማድረግ ቢታቀድም በእቅዱ መሰረት የማይከናወን መሆኑን፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የማይተዋወቁ መሆኑን፣ የኮርና የአለት ናሙናዎችን ደህንነት ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ ደረጃዉን የጠበቀ ጂኦሙዚየሙ በማደራጀትና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራ አለመሰራቱን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. በመሆኑም፡-

➢ በመ/ቤቱ የተለያዩ ላቦራቶሪ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የተገዙ ማሽኖችና ኬሚካሎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና መጠገን የሚገባቸውንም በአፋጣኝ ጥገና እንዲደረግላቸው በማድረግ የጥራት ማረጋገጥ ስራ ሊሰራ እና ሌሎች ላቦራቶሪው ላይ መስተካከል ያለባቸውን ክፍተቶች በማስተካከል ተገቢውን ቀልጣፋ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከ10 ዓመት በፊት የተጀመረው የመ/ቤቱ ላቦራቶሪ አለምአቀፍ ዕውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ የጀመረውን ዕቅድ በፍጥነት ወደ ተግባር በማሸጋገር ወደ ውጭ የሚላኩ የማዕድን ናሙና ምርመራዎችን መጠን ሊቀነስና ለምርመራ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ የሚቀነስበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

➢ መስሪያ ቤቱ ተግባሩን ለማከናወን የሚጠቀምባቸው የቁፋሮ (ድሪሊንግ)፣ የላቦራቶሪ እና የጂኦሳይንስ መሳሪያዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች ለብልሽት እንዳይዳረጉ ቅድመ መከላከል ሥራ ለመስራት የሚያስችል የመደበኛ ጥገና ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

በተጨማሪም ከልኬትና ተመሳሳይ የመለኪያ አገልግሎት የሚሰጡ የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ የተለያዩ ማሽኖች እና መሳሪያዎች በየአመቱ ትክክል ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል ካሊብሬት ሊያስደርግ ይገባል፡፡

- በመ/ቤቱ ለምርመራ የሚመጡ ናሙናዎችን በአግባቡ ለመያዝና ምርመራቸው ተከናውኖ ካለቀ በኋላም ናሙናዎቹ በባለቤቶቹ የሚወሰዱበትን የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ለረጅም አመታት የተከማቹ ናሙናዎችን የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የአገልግሎት ጊዜያቸው በማብቃቱ ተጠግነው ስራ ላይ የማይውሉና ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ንብረቶች ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በአገር ውስጥ አይወገዱም የተባሉትን ኬሚካሎችም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባባር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሚወገዱበትን ሁኔታ በማመቻቸት እንዲወገዱ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለመወጣት እንዲስችለው የሚያዘጋጃቸውን ዕቅዶች በበቂ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ሊሆን ይገባል፡፡ ዕቅድ በሚታቀድበትም ጊዜ ያለፉ አመታትን ዕቅድ አፈፃፀም በማገናዘብና መሰረት በማድረግ የቀጣይ አመታትን ዕቅድ ሊያዘጋጅ የሚገባ ሲሆን አፈፃፀሙንም በተመለከተ በዕቅዱ መሰረት እንዲከናወን በትኩረት ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡

  መ/ቤቱ የሚያከናውናቸዉ ስራዎች ለሀገሪቱ የማዕድን ኢንቨስትመንት እድገት ወሳኝ ሚና ያለዉ በመሆኑ ለተገልጋዮች ጥራት ያለው መረጃ በተሟላ መልኩ ለማቅረብ እንዲቻል ዕቅድን መሰረት በማድረግ የስነ-ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት መሰብሰብና ማደራጀት እንዲሁም በመ/ቤቱ ያሉ መረጃዎችን መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቱን መሰረት በማድረግ ማደራጀትና የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ማስተዋወቅ ይገባዋል፡፡

## 5. በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የምግብ ደህንነት እና ጥራት ቁጥጥር አፈጻጸም በተመለከተ

- **የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

44. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ለምግብ አምራች ድርጅቶች፣ ለጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪዎች፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና

ለአከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ ማገድ እና መሰረዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ

- ባለሥልጣኑ ድርጅቶቹ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከወሰዱ በኋላ ክትትል በማድረግ ፈቃዱ መታደሱ እንዲረጋገጥና ፈቃድ ባለማሳደሳቸው እንዲጠየቁ በማድረግ መታገድ ያለበት እንዲታገድና ፈቃዱም መሰረዝ ካለበት እንዲሰረዝ የሚያደርግበት ሥርዓት የዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉ፣

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የምግብ አምራቾች፤ ላኪዎች፤ አስመጪዎችና አከፋፋዮች ፋይል፤

- በናሙና ተመርጠው ከቀረቡት ፋይሎች ውስጥ የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ሳይከናወን ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለ37 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲታደስ መደረጉ፤
- ከባለስልጣኑም ሆነ ክክልል ከሚመለከታቸው አካላት ፈቃድ ሳይኖራቸው ምግብ የሚያመርቱና የጥራት መቆጣጠር ላብራቶሪ ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች መኖራቸው፣
- ለባለሥልጣኑ የምግብ ማምረት ፈቃድ የመለሱ ድርጅቶችን ሥራ ላይ እንዳሉ በማድረግ የኢንስፔክሽን እቅድ ውስጥ እንዲካተቱ መደረጉ፤
- በባለሥልጣኑ በ2010 ዓ.ም ኢንስፔክሽን ይደረግባቸዋል ተብለው ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ተብለው የተለዩ ድርጅቶች ውስጥ ጥብቅ ክትትል እየተደረገባቸው ነው ተብለው በእቅድ ከተያዙ ድርጅቶች ሁለቱ (2) ዘግተው ፈቃድ የመለሱ መሆኑ፣
- ድርጅቶቹ መስፈርት ባለማሟላታቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ፈቃድ የተከለከሉ የምግብ አምራች ድርጅቶች ከፌዴራል ባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ እንዲያገኙ መደረጉ፣

ታውቋል፡፡

➢ **በሀገር ውስጥ የተመረተና ከውጭ ሀገር እንዲገባ የተደረገ ምግብን ለመሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ለማቅረብ የሚያስችል ፈቃድን በተመለከተ፤**

46. ማንኛውም ምግብ ሲመረት፣ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ወደ ውጭ ሲላክ፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ ሲጓጓዝ፣ ሲሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ሲቀርብ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያውቀውና ፈቃድ እንዲያገኝ ሊደረግ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በመቆጣጠሪያ ኬላና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ከሚደረግ ኢንስፔክሽን ውጪ ምግብ ሲጓጓዝ እንዲሁም ገበያ ላይ የዋሉ ምግቦችን ደህንነት እና ጥራት የማይረጋገጥ፣ የድህረ ገበያ ቅኝት በማድረግ እና የቁጥጥር ሥራ በማካሄድ አስፈላጊው እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **የምግብ ምዝገባ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤-**

48. ከውጭ አገር ለሚገባም ሆነ በአገር ውስጥ ለሚመረት ማንኛውም ምግብ፤ የምግብ ምዝገባ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በአገር ውስጥ ለሚመረትና ከውጭ አገር ለሚገባ ማንኛውም ምግብ የምግብ ምዝገባ ስርዓት (ምግቦቹ የተመረቱበት እና የአመራረት ሂደታቸው ምን እንደሚመስል ታይቶ የሚመዘገብበት ስርዓት) የተዘረጋ ቢሆንም የህጻናት እና ተጨማሪ (መደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ ምግብ) ምዝገባ ብቻ የሚያከናውን ሲሆን በሌሎቹ ምግቦች ላይ የምግብ ምዝገባው እየተከናወነ አለመሆኑ፣

  ታውቋል፡፡

➢ **ማንኛውም ምግብ ጤናማ አጠባበቅ እየተደረገለት ስለመሆኑ፤**

49. ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን ወይም የተቀበለውን መስፈርት ተከትሎ ለማንኛውም ምግብ ጤናማ አጠባበቅ በማድረግ ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብን በሚያከማችበት፣ ለዕይታ

በሚያቀርብበት፣ በሚያሽግበት ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ ምግቡ በተገቢው የሙቀት መጠን እንዲቀመጥ እና እንዲጓጓዝ እየተደረገ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩ የምግብ ማምረቻ ድርጅቶች

- በናሙና ተመርጠው በታዩ ድርጅቶች በቀዝቃዛ ስፍራ መቀመጥ እና መጓጓዝ የሚገባው ምርት በቀዝቃዛ ስፍራ ተቀምጦ እንዲጓጓዝ እና ወደ ገበያ ሲቀርብም እንደየ ባህሪው በጥንቃቄ እንዲያዝ አለመደረጉ፣

- ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሁኔታ ተጠብቆ እየተጓጓዘና እየተከማቸ አለመሆኑ፣

- የምግብ አምራች፣ አስመጪና አከፋፋይ የሆኑ ደርጅቶች ማንኛውንም ምግብ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ጤናማ በሆነ መንገድ ለማምረትና ለመጠበቅ የሚያስችል የክምችት ሥርዓት መመሪያ አለመኖር፣

- በምግብ ማምረቻዎች አከባቢ የእሳት ማጥፊያ፣ ምግቡን ማከማቻ ቦታ፣ የሠራተኞች የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ ክሊኒክ፣ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር፣ አየር ማዘዋወሪያ (ኤሲ)፣ ጽዳት መጠበቂያ ላውንደሪ፣ የድንገተኛ አደጋ መውጫ በር ወ.ዘ.ተ) የሌላቸው ድርጅቶች መኖራቸው፣

- ምግቦች በክምችትም ሆነ ለሽያጭ በሚቀርቡበት ጊዜ በፀሀያማ ቦታ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩ፣

- የምግብ ማከማቻዎቹ ንጽህና የሌላቸው፣ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ያለው የተሟላ የምግብ ማጓጓዣ የሌላቸው መሆኑ፣

- ከውጭ የሚገቡ ምግቦች የክምችት እና የማጓጓዝ ሂደት ላይ ባለሥልጣኑ ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናን በተመለከተ፣**

50. እንደሥራው ባህሪ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በሥራ ወቅት የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ድርጅቶቹም መስፈርቱን አሟልተው ሠራተኞቻቸው እንዲሰሩ የሚያደርጉ ስለመሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በሥራ ወቅት የምግቡን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት የሚጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ፣
- በናሙና በታዩ እና በምርት ላይ ከነበሩ ከሶስቱ ሁለቱ የምግብ አምራች ድርጅቶች የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት እንደማይጠቀሙ እንዲሁም ምግቦችን ጓንት ሳይጠቀሙ በእጃቸው ወደ ማሽኒያዎች እንደሚያስገቡ፣ በናሙና የታዩ ሁሉም የምግብ አምራች ድርጅቶች በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መሰረት የግል ንጽህናቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል በቂ የልብስ ማጠቢያ ቦታ፣ የምግብ መመገቢያ ቦታ፣ በቂ የመጸዳጃ ቤትና የገላ መታጠቢያ ቦታ ያልተሟላ መሆኑ፣

  ታውቋል፡፡

➢ **በባለሥልጣኑ የሚከናወን የኢንስፔክሽን ሥራን በተመለከተ፡**

51. ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የኢንስፔክሽን ሥራ የምግብ ፈቃድ በሰጣቸው ድርጅቶች ላይ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው ከድርጅቶቹ ፋይል ጋር ሊያያዝና የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ድርጅቶቹም በተሰጣቸው አስተያየት መሰረት የዕርምት እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ በወሰዱ በአምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይና አጓጓዥ ድርጅቶች በባለሥልጣኑ በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት፡-

- የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው በባለሥልጣኑ ከፋይላቸው ጋር የማይያያዝ መሆኑ፤
- የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑ፤
- በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኘው ክፍተት ድርጅቶቹ የገቡትን ግዴታ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ማስተካከያ ስለማድረጋቸው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል በማድረግ የማይረጋገጥ መሆኑን

ታውቋል፡፡

➢ **የተሟላ የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ መኖሩን በተመለከተ፤-**

53. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች ሊያደራጅና ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- የምግብን ደህንነትና ጥራት ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በማደራጀት የተሟላ የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፤
- በናሙና ተመርጠው በታዩ አዳማ ኳራንቲን ጣቢያ፤ ሞጆ ኳራንቲን ጣቢያ፤ቃሊቲ ኳራንቲን ጣቢያ እንዲሁም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ የኤርፖርት ተርሚናል እና የአዲስ አበባ ኤርፖርት ካርጎ መግቢያና መውጫ ኬላ የምርመራ ላብራቶሪዎች አለመኖር፤
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚቆጣጠረው የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ (ፓስተር) ላብራቶሪው አስፈላጊ በሆኑ መሳሪያዎችና ግብአቶች ያልተደራጀና ደረጃውን የጠበቀና ሁሉንም መስፈርት (Parameter) ለመስራት የሚያስችል ላብራቶሪ አለመሆኑ፤
- የምግብ የጥራት ምርመራ በፓስተር የሚደረገው በሁለት ምግቦች ላይ ማለትም በጨውና ዘይት ላይ ብቻ መሆኑ በሀገር ውስጥ የምግብ አምራቾችም በማምረቻ

ተቋማቸው ውስጥ የተሟላ ላብራቶሪ የሌላቸው እና ሙሉ በሙሉ ላብራቶሪም ክፍል ያላደራጁ አምራቾች መኖራቸው፤

- በየኬላዎች የሚገኙ ኢንስፔክተሮች በእይታ (physical & organoleptic inspection) ለሚያደርጉዋቸው ምርመራ የሚያግዙ የተሟላ መሳሪያ (Sampling tools) የሌላቸው መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

➢ **በምግቦች ላይ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ መደረጉን በተመለከተ**

54. ባለሥልጣኑ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ በሁሉም ምግቦች ላይ እንደምግቡ አይነት የፊዝኮኬሚካል፤ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ ሊደረግ ሲገባ 18(አስራ ስምንት) የምግብ አይነቶች ብቻ ተለይተው ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ውጭ በሚገኝ በግል ድርጅት ላብራቶሪ የምግብ ጥራት ምርመራ የሚደረግ መሆኑ፤
- የምግብ ላብራቶሪ ምርመራ የሚያከናውነው ብሌስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ የተባለ የግል ተቋም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት ወይም ከራሱ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ስለመሆኑ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለማቅረቡ፤
- ባለሥልጣኑ በኦሮሚያ ክልል ለሚገኘው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ በስሩ ከሚያስተዳድረው ሰበታ ኢንዱስትሪያል ኮምፕሌክስ የጁስ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የማንጎ ጁስ ናሙና ተወስዶ በብሌስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ  የፊዚኮኬሚካል እና የማይክሮባዮሎጂ የተከናወነው ፍተሻ ውጤት ለውስጥ መረጃ ብቻ እንዲጠቀሙብትና ላብራቶሪው በኢትዮጵያ ውስጥ በማንጎ ጁስ ፍተሻ አክርዲቴሽን የምግብ ጥራት ማረጋገጫ ተግባር ለማከናወን ፈቃድ የሌለው እና በተቋሙ የተከናወነው ምርመራ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ በቀን መስከረም 12/2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 02/12/32/545 የገለጸ መሆኑ፣ በተቃራኒው ግን ባለሥልጣን

መ/ቤቱ ከጨውና ከምግብ ዘይት በስተቀር ከውጭ የሚገቡ ምግቦችን የማንጎ ጁሶችን ጨምሮ በዚሁ ላብራቶሪ እንዲመረመሩ በውስጥ ማስታወሻ ቁጥር ም/ጥ/ም/ዳ 093/08 በቀን 14/08/08 ዓ.ም ለማዕከላዊ ቅ/ጽ/ቤት ያሳወቀ መሆኑ፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የምግብ ላቦራቶሪ ምርመራ የሚያከናውነውን የግል ተቋም የምግብ ምርመራ እንዲያከናውን የመረጠበት መስፈርት እና የተገባ ውል የሚያሳይ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በባለሥልጣኑ ያልቀረበ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

➢ **ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል ምርመራ መደረጉን በተመለከተ፡**

55. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ምግቦችን ናሙናዎች በመውሰድ ወይም በመቀበል ምርመራ በማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

- ✓ የምርመራው ናሙና አወሳሰድ በስርዓት የማይመራ መሆኑ፤
- ✓ ናሙናዎቹን ወደ ላቦራቶሪ እራሱ የምግብ አስመጪው እንዲወስድ የሚደረግ መሆኑ፤
- ✓ ከጤና ኳራንቲን ጣቢያዎች የሚላከው ናሙና ውጤት የሚመጣው በቀጥታ ለላከው ጣቢያ ሳይሆን ለባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት መሆኑ እና የምርመራው ውጤት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ መፈቀዱ ከአስመጪዎቹ ፋይል ጋር እንዲያያዝ ወደ ጣቢያዎቹ/ኬላዎቹ የማይላክ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ✓ የምርመራው ውጤት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ፈቃድ በሚሰጡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (ኳራቲን ጣቢያዎች) ተጠናቅሮ እንዲያዝ አለመደረጉ እና በናሙና የሚወሰደው የፐርሰንት መጠን አለመወሰኑ፣
- ✓ እንዲሁም ባለሙያዎቹ የማያውቁዋቸው የምግብ አይነቶች በመኖራቸው ናሙና ለመውሰድ የሚቸገሩበት ሁኔታ መኖሩ፤
- ✓ የምግብ ጥራትን በሚመረምሩ በሀገሪቱ ያሉ የመንግሥትና የግል ላብራቶሪዎች የሚጠቀሙባቸውን እስታንዳርዶች አገሪቱ በምትመራባቸው መሰረት ስለመሆናቸው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣

ለማሳያ፡- በማንጎ ጁስ ምርመራ በተደረገ ወቅት በኢትዮጵያ የማጎ ጁስ ደረጃ (Ethiopian Standard for Mango juice- Specification) (ES 2856:2016 በ ምርመራ ዘዴ (Test method) ES ISO 6633 መሰረት ሊድ ከፍተኛ መጠን 0.05 max መሆኑን ደረጃ ሲያስቀምጥ ነገር ግን ብሌስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ ሰርቪስ ኃላ.የተ.የግ.ማ ሊድ ከፍተኛ መጠን 0.30 max በመጠቀሙ 0.20 ሊድ (ከሚፈቀደው 15 ከመቶ በላይ የሆነ) የሊድ መጠን ያለውን የማንጎ ጁስ ወደ ገበያ እንዲሰራጭ የፈቀደ መሆኑ፣

- ✓ ለግል መጠቀሚያ ተብለው የሚገቡ ምግቦች እስከ 100 ኪ.ግ እና ለፕሮጀክት መጠቀሚያ ተብለው የሚገቡ ምግቦች ላይ ምርመራ እንዲከናወንባቸው አለመደረጉና ሳይመረመሩ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፣
- ✓ በኬላዎች ላይ ናሙና ለመውሰድ የሚያስችል በቂ ማራገፊያና ማቆያ ቦታ አለመኖር፤
- ✓ በተደጋጋሚ ከውጭ ምግብ የሚያስገቡ አስመጪዎች ላይ እስከ ስድስት ወር ምርመራ የማይካሄድ መሆኑ፤(Sampling based on frequency)መሆኑ፤
- ✓ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ የተጭበረበሩ፣የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦች ላይ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ የማይደረግ መሆኑ፤
- ✓ ባለስልጣኑ የተከለሱ ወይም ከባእድ ነገር ጋር የተቀላቀሉ ምግቦችን ለመለየት የሚያስችል ላብራቶሪ እንዲቋቋም አለማድረጉ፤
- ✓ ተበላሹ ተብለው የሚቀርቡ አንድ አይነት የሆኑ ምግቦች ወደ ብሌስ ላብራቶሪ እና የኢትዮጵያ የተሰማሚነት ምዘና ድርጅት ተልከው ውጤታቸው የተለያየ መሆኑን፤

ታውቋል፡፡

➢ **ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ ገላጭ ጽሁፍ ያለው መሆኑን በተመለከተ፤-**

56. ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ በግልጽ የሚነበብና በቀላሉ የማይለቅ የምግቡን ይዘት ብቻ የሚገልጽ ጽሁፍ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ ገላጭ ጽሁፋቸው በደንብ የማይታይና የማይነበብ፣ ከሁለቱ ቋንቋ ውጭ በሌላ ቋንቋ የተጻፈባቸው፣ የምግቡን ይዘት የማይገልጹ፣ ከምግቡ ይዘት በተጨማሪ መጠቀስ የማይገባው ማስታወቂያ መሰል ሌላ ማብራሪያ የተጻፈባቸዉ ምግቦች በገበያ ላይ መኖራቸው፣
  ታውቋል፡፡

➢ **የምግብ ጥሬ ዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ቁጥጥርና ፈቃድን በተመለከተ፡-**

57. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የምግብ ጥሬ ዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የመግቢያና የሙውጫ ፈቃድ የሚሰጥበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና በሀገር ውስጥ በሚመረቱ የምግብ ጥሬ ዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር ለማካሄድና ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑ፤አስመጪዎችና አምራቾች እንደ ግብዓት የሚጠቀሙበትን ጥሬ እቃ እና የማሸጊያ ቁሳቁስ ለማስገባት ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ተጨማሪ ፈቃድ የማይጠይቁ መሆኑ፤ማሸጊያዎቹ አንዴ ታትመው ለረጅም ጊዜ በማከማቻ የሚቆዩ በመሆኑ ምግቡ እንደተመረተ ማሸጊያዎቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉ፤ የምግብ ማሸጊያዎቹ የምግቡን ጥራት ከማስጠበቅ አኳያ የተዘጋጁ ስለመሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቁጥጥር እና ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **ለህብረተሰቡ እየቀረቡ የሚገኙ ምግቦች ትክክለኛ ና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው መለየታቸውን በተመለከተ፡-**

58. በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት በሀገር ደረጃ በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ለሚገኙት ምግቦች የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ምግቦች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ህጋዊና ህገወጥ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምግቦች እንዲለዩ ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በሀገር ደረጃ በአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ተመርተው በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ የሚገኙ ምግቦችን ለመቆጣጠር ባለሥልጣን መ/ቤቱ

- የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ህጋዊና ህገወጥ ምግቦችን በመለየት ህብረተሰቡ እንዲያውቃቸው አለማድረጉ፤
- የምግብ ንግድ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሀን ወይም በማናቸውም መንገድ ሲተላለፍ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት መሆኑ እንዲረጋገጥ አለመደረጉ፣

  ታውቋል፡፡

➢ **የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፤-**

59. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው፣ ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማቹ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ፤ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ ምግብና ጥሬ ዕቃ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑን ካተረጋገጠ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩ የመቆጣጠሪያ ኬላዎች እና የሀገር ውስጥ የምግብ ማምረቻዎች፡-

- እያንዳንዱ የምግብ ምርት ዓይነትና መጋዘን ላይ የምርቱን ዓይነት፣ ምርቱ ያለበትን ሁኔታ (አያያዝ፣ አቀማመጥና የቆይታ ጊዜው ያለበትን ደረጃ) እና ሌሎች ስለምግቡ የሚገልጹ መረጃዎች በየጊዜው ስለመለጠፋቸው ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤
- የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማች አለመደረጉ እና ለዚህም ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤
- ከደረጃ በታች በመሆናቸው የሚወገዱ ምግቦች ጥቅም ላይ ከሚውሉ ምግቦች ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ ተደባልቀው እንዲቀመጡ መደረጉ በመስክ ምልከታ ወቅት መታወቁ፤
- የሚወገዱ የምግብ ምርቶች ተለይተው በአግባቡ ባለመያዛቸው በሰው ጤና ላይ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ የሚያዙበት ሁኔታ መኖሩ፣ እንዲሁም
- የጥራት ችግር ያለባቸው እና በመጋዘን እንዲቀመጡ የተደረጉ ምግቦች ተመዝግበው እንዲቀመጡ በማድረግ የተመዘገቡት ምግቦች በሙሉ ስለመወገዳቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፤
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦችና ጥሬ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ እና ከውጭ አገር የገባ ምግብ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ አግባብ ባለው መንገድ መወገዱን ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ መደረጉን በባለሥልጣኑ የሚረጋግጥበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉ፤
- በሀገር ውስጥ ለሚወገድ ምግብ የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ተቆጣጣሪዎች በተገኙበት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዋጅና ደንብ መሠረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች በተውጣጣ ኮሚቴ አማካይነት አካባቢያዊ ተጽዕኖ በማያሳድር መልኩ እንዲወገድ ለማድረግ ባለስልጣኑ የተያዘው (የጥራት ጉድለት ለበት የተባለው) በሙሉ ስለመወገዱ የማያረጋግጥ እና ቃለ ጉባኤውን አጠናቅሮ የማይዝ መሆኑ፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ምግብን ለማስወገድ ጥያቄ ሲቀርብ አንድ ተወካይ ከመላክ ውጭ ምግቡ ስለሚወገድበትና በሰው ጤንነት ላይ ስለሚያስከተለው ጉዳት የማያረጋግጥ መሆኑ፤
- ከሁለት ዓመት በላይ ተቀምጠው በሰው ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሩዝ፣ ወተት፣ ጭማቂ፣ በናሙና በታዩ መጋዘኖች ተቀምጠው መገኘታቸው፤ ታውቋል፡፡

በመሆኑም

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የምግቦችን ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን የቁጥጥር ደረጃዎች አዘጋጅቶለምግብ አምራች ድርጅቶች፣ለጥራት መቆጣጠሪያ ላብራቶሪዎች፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ማደስ፣ ማገድ እና መሰረዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዲሆንና ማንኛውም ምግብ ሲመረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ወደ ውጭ ሲላክ፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ ሲጓጓዝ፣ ሲሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ሲቀርብ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እንዲያውቀውና ፈቃድ እንዲያገኝ በማድረግ ከውጭ አገር ለሚገባም ሆነ በአገር ውስጥ ለሚመረት ማንኛውም ምግብ፤ የምግብ ምዝገባ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

❖ ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብን በሚያከማችበት፣ ለዕይታ በሚያቀርብበት፣ በሚያሽግበት ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ ምግቡ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ውስጥ መሆኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ በባለሥልጣኑ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

❖ ባለሥልጣኑ እንደሥራው ባህሪ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በሥራ ወቅት የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት የሚያደርጉ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው ከፋይላቸው ጋር እንዲያያዝና የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ መሰጠት አለበት፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በማደራጀት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ በማድረግ በምግብ መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞትና የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል መርምሮ ምንነታቸውን የሚያረጋግጥበትና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተከለሱ፣የተበላሹ፣የተጭበረበሩ፣የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ በማድረግ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ በግልጽ የሚነበብና በቀላሉ የማይለቅ የምግቡን ይዘት ብቻ የሚገልጽ ጽሁፍ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የምግብ ጥሬዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የመግቢያና የሙውጫ ፈቃድ የሚሰጥበት ስርዓትሊዘረጋ ይገባል፡፡
- በሀገር ደረጃ በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ለሚገኙት ምግቦች የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ህጋዊና ህገወጥ ምግቦች እንዲለዩና የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማቹ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ፤ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ ምግብና ጥሬ ዕቃ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በማለት የማሻሻያ ሃሳብ አቅርበናል፡፡

## 6.በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር የደን ውጤቶች ዝውውርና ቁጥጥር ሥርዓት አፈጻጸም

➢ **የወጡ ህጎች በሚለከታቸው አካላት ተግባራዊ ለመደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፣**

60. የደን ውጤቶችን በተመለከተ የወጡ ህጎች በሚለከታቸው አካላት ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ የሚኒስቴር መቤቱም በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ህጎች ተግባራዊ ለመደረጋቸው በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የኦሮሚያ እና ደቡብ ክልሎች በሚገኙ በሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች፡-

- የአካባቢ ጥበቃ፣ የደንና አየር ንብረት ለውጥ ጽ/ቤት እንዲሁም በነዚህ አካባቢ በታዩ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮዎች፣ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤቶች ፣ የደንና የዱር እንስሳት ድርጅቶች እና ኬላዎች በደን ውጤቶች ዝውውርና ቁጥጥር ዙሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልሎች ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልል በሜጫ ወረዳ በእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ፅ/ቤት በኩል የሚሠጠው የከሰል ዝውውር ፈቃድ ለህገ ወጥ አሰራር የተጋለጠ በመሆኑ የይለፍ ደብዳቤን የማከራየት፣ የመሸጥ አሰራር የተለመደ መሆኑ፣ ፈቃዱ በህገወጥ ደላሎች እየተዘጋጀ የሚሸጥበት ሁኔታ መኖሩ፣ በትግራይ ክልል የአንደርታ ወረዳ በህጋዊ መንገድ በተሰጠ የአጣና መነገጃ ቦታ ላይ ከሰልም አብሮ እየተሸጠ መሆኑ፣ እንዲሁም የእንደርታ ወረዳ ከሰል ማከማቸት ህጉ የሚከለክል ቢሆንም የከሰል ማከማቻ ዲፖ ቦታ ከሰል ለሚነግዱ ሰዎች መስጠቱ፣ በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማ ሀውልቲ ክፍለ ከተማ አድሃ ቀበሌ ህገ ወጥ የሆነው የከሰል ምርት ከህጋዊው አጣና ጋር ተከማችቶ እየተሸጠ መሆኑ፣
- እንዲሁም በ3 ክልሎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር በተደረገው ጥናት፡-
  - ✓ ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን ህገ ወጥ የደን ምርት ዝውውር መኖሩ፣ ህገ ወጥ የደን ውጤቶች ዝውውርና አጠቃቀም ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱ በተለይ ከሰል በኮንትሮባንድ ወደ ሶማሌ ላንድ እየተላከ መሆኑ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2007 በጀት ዓ.ም የዕቅድ አፈጻጸም ላይ እንደተገለጸው የአጣና ምርቶቹ ህገ ወጥ በሆነ

መልኩ በሱዳን በኩል እስከ ግብፅ ሊቢያ፤ ቱኒዝያና ሞሮኮ ድረስ እየተሰራጨ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **በደን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ህጎች ላይ በቂ ግንዛቤ መስጠቱን በተመለከተ፣**

61. የደን ፖሊሲውን እና ተያያዥነት ያላቸው ህጎች ለፈጻሚውና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የማስተዋወቅ ስራ በበቂ ሁኔታ ሊሰራ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል ለሚገኙ እና የደን ውጤቶች ዝውውር እና ቁጥጥር ለሚመለከታቸው አካላት ለአመራሩ፣ ባለሙያው፣ ፖሊስ፣ ፍትሕ አካላትና ለህብረተሰቡ በደን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ህጎች ላይ በቂ ግንዛቤ መፍጠር አለመቻሉን እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሰው ኃይል የተደራጀ ባለመሆኑ በደን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ህጎች ላይ ግንዛቤ እንዳልሰጡአቸውና ወደ ታች ወርደው በበቂ ሁኔታ በህጎቹ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ አለመሰራቱ ታውቋል፡፡

➢ **ሕገወጥ የደን ውጤቶች ዝውውር ላይ የተሳተፉ ለህግ ቀርበው ውሳኔ እንዲያገኙ መደረጉን በተመለከተ፣**

62. የደን ውጤቶችን በህገ ወጥ በሚያዘዋውሩ ሁሉ ላይ በአዋጅ 542/1999 መሰረት ለህግ ቀርበው ውሳኔ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ፡-

- ✓ የደንና ደን ውጤቶች በህገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር ከመውረስ ውጪ ምንም እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ ለማሳያ ያህል፡-
    - ➢ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በሲዳማ ዞን በዳሌና በበንሳ ወረዳ በቀን 8/12/09 ሰሌዳ ቁጥር 3-39328 በህገ ወጥ መንገድ በቁጥር 684 ዋንዛ ጉብን እና ቁመቱ 2 ሜትር የሆነ በቁጥር 156 የፈረንጅ ጽድ ጭኖ ሲሄድ በተደረገው ቁጥጥር ተይዞ የጫነው ብቻ ተወርሶ ተሽከርካሪው እንዲለቀቅ መደረጉ፣
    - ➢ በቀን 29/06/09 ሰሌዳ ቁጥር 3-09170 አ.አ በህገ ወጥ መንገድ በቁጥር 334 ቀረሮ (ጣውላ) ጭኖ ሲሄድ በቁጥጥር ስር ውሎ የጫነው ተወርሶ ተሽከርካሪው የተለቀቀ መሆኑ እንዲሁም በቀን 08/02/10 ሰሌዳ ቁጥር 3-

99098 አ.አ 7 ጉበን ጣውላ ጭኖ ሲሄድ በቁጥጥር ሥር ውሎ የጫነው ተወርሶ ተሽከርካሪው የተለቀቀ መሆኑ፣

እንዲሁም ባየናቸው ክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች እንዲሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማየት እንደተቻለው ህገ ወጥ የደን ውጤቶች ዝውውርና የደን ጭፍጨፋ በተመለከተ ጅምር የቁጥጥር ስራ ቢኖርም፤

- ✓ የመስክ የድጋፍና ክትትል እና የ2008 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው በሚፈለገው መጠን ተጠናክሮ እየተሰራበት እንዳልሆነና ፍርድ ቤቶችና ፖሊስ ህገወጦች ላይ የሚወስዱት እርምጃ ብዙውን ጊዜ አስተማሪ እንዳልሆነና ህጉን ተንተተርሶ አጥፊዎች የማይቀጡ መሆኑ፣
- ✓ ፖሊሶች ጥፋተኛውን ከያዙ በኋላ የሚለቁ መሆኑ ለመጥቀስ ያህል፡- በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሶኩሩ ወረዳ በነሐሴ 2009 ዓ.ም በቁጥር 1064 ረከቦት በህገወጥ ጭኖ ሲሄድ የተያዘ አይሱዙ ቢገኝም ሾፌሩ አምልጦ ሲሄድ የመኪናው ባለቤት እርምጃ ሳይወሰድበት መለቀቁ፣
- ✓ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሲዳማ ዞን በበንሳ እና ዳሌ ወረዳዎች በጥቅምት 2010 ዓ.ም ህገወጦች ከተያዙ በኋላ መኪናቸው አስተዳደራዊም ሆነ ህጋዊ ቅጣት ሳይሰጣቸው እንዲለቀቁ የተደረገ መሆኑ፣
- ✓ በተጨማሪም በሚጠፋው ጥፋት (የደን መጨፍጨፍ) ልክ ተመጣጣኝ ቅጣት የማይሰጥ መሆኑ፣ በህገወጥ ዛፍ ቆረጣ ወንጀል የሚያዙ አጥፊዎች በድርድርና በሽምግልና የሚለቀቁ፣ መሆኑና የደን መጨፍጨፍ ወንጀል እንደሌሎች ወንጀሎች ትኩረት የሚሰጠው አለመሆኑ፣

  ታውቋል፡፡

➢ **የደን ጉዳዮችን የሚመለከት መደበኛ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎት መቋቋሙን በተመለከተ፡**

63. የደን ጉዳዮችን የሚመለከት በመደበኛ ፍርድ ቤት ልዩ የደን ጉዳዮች ችሎት እንዲቋቋም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በደን ጉዳዮች ላይ ዳኞች ብቃታቸውን ሊያሳድጉ እንዲችሉ የደን ህጎች ላይ ስልጠና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊሰጥ ይገባል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በጥር ወር 2008 ዓ.ም ባደረገው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ የአካባቢና የደን ጉዳዮችን የሚመለከት በመደበኛ ፍ/ቤት ልዩ ችሎት እንዲቋቋም ለማድረግ ቢያቅድም

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ጉዳዮችን በሚመለከት በልዩ ችሎት ፍርድ ቤት እንዲቋቋም ያላደረገ መሆኑና በደን ህግ ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አለመቻሉ፣

➢ **ለደን ውጤቶች የሚሰጠው ፍቃድ በማኔጅመንት ዕቅድ መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣**

64. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለደን ውጤቶች የሚሰጠው ፍቃድ የሀገሪቱን ውስን የደን ሀብት ዘለቄታዊ አጠቃቀም በአገናዘበና የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት መዛባት በማያስከትል መንገድ ክልሎች በሚያዘጋጁት የማኔጅመንት ዕቅድ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ክልሎች ለደን ውጤቶች የሚሰጡት ፍቃድ የማኔጅመንት እቅድን መሰረት በማድረግ መሆን ሲገባው፡-

- የሀገሪቱን ውስን የደን ሀብት ዘለቄታዊ አጠቃቀም በአገናዘበና የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት መዛባት በማያስከትል መንገድ በሚዘጋጅ በማኔጅመንት ዕቅድ መሰረት እንዳልሆነና የደን ዘርፉ ሥራ ችግሮችን በሚፈታ ምርምር እና በማኔጅመንት ፕላን የተደገፈ አለመሆኑ እና በብዛት በልምድ ላይ የተመሰረተ መሆኑ፣
- በክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አካባቢዎች ያለምንም ንግድ ፈቃድ በህገወጥ መንገድ በግንዲላ ስንጠቃ ስራ የተሰማሩ ግለሰቦች መኖራቸውና ተገቢው እርምጃ የማይወሰድባቸው መሆኑ፣
- ፈቃድ ወስደው ነገር ግን ስራቸውን ያቋረጡ ግለሰቦች ፈቃዳቸውን እንዲመልሱ ወይም እንዲሰረዝ የማይደረግ መሆኑና የንግድ ፈቃዳቸውን በህገወጥ መንገድ ለሚሰማሩ ግለሰቦች አሳልፈው በመስጠት አላግባብ እንዲጠቀሙበት የሚያደርጉ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ካደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት የግል እንጨት መሰንጠቂያዎች አብዛኞቹ ፍቃድ የሌላቸው፣ ለጣውላ የሚጠቀሙበት ግንድ በውል ከየት እንደሚያገኙ የማይታወቁ መሆኑ፣

- በክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ በደን ውጤቶች ስራ ላይ ለሚሰማሩ ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ሳይጠየቅ በቀጥታ የንግድ ፈቃድ የሚሰጥበት አሰራር መኖሩ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው አጣና የሚነግዱ አካላትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በመተባበር ያልዘረጋ መሆኑ፣
- በደን ውጤቶች ንግድ ዘርፍ ለሚሰማሩ ግለሰቦች ለጥሬ እቃ የሚጠቀሙበትን ደን ምንጩ ከየት እንደሆነ እና ያለው የደን መጠን (Potential) ሳያረጋግጥ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ፣
- በክልል የሚገኙ ፈቃድ ሰጪ አካላት ለቤትና ቢሮ እቃዎች ስራ ፈቃድ ሲሰጡ የሚጠቀሙት ጥሬ እቃ የፋብሪካ ውጤት እንጂ የደን ውጤት አይደለም በሚል የመጣውን ፈቃድ ጠያቂ ሁሉ የማኔጅመንት ዕቅድ ባይኖራቸውም የሚያስተናግዱ መሆኑ፣
- በደን የንግድ ስራመደቦች የብቃት ማረጋገጫ ድጋፍ የተሰጣቸው አካላት በተሰጣቸው ፈቃድ መሠረት ስለመተግበራቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልሎች ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣

  ታውቋል፡፡

➢ **በደን የስራ መስክ ለተሰማሩ የሚሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ እና አተገባበርን በተመለከተ፡-**

65. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደን የስራ መስክ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ እንደሚሰጥ ሊወስን፣ በዚሁ መሰረት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መስፈርት ሊያወጣ፣ በመስፈርቱ መሰረት ሊሰጥና በተሰጣቸው ፈቃድ መሠረት ስለመተግበራቸው ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና ክፍተቶች ሲኖሩ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደን የስራ መስክ ለሚሰጠው የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ የጊዜ ገደብ አስቀምጦ በዚሁ መሰረት የሚተገብር ቢሆንም በደን የንግድ ስራ መደቦች የብቃት ማረጋገጫ ድጋፍ የተሰጣቸው አካላት፣ በተሰጣቸው ፈቃድ መሠረት መተግበራቸውን በተመለከተ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2007 እና በ2008 ዓ.ም ምንም አይነት ክትትል ያላደረገ እና በ2009 ዓ.ም አንድ ጊዜ ብቻ ( የዕቀዱን 25%) ለ10 ባለሃብቶች ክትትል የተደረገ መሆኑ፣
- በትግራይ ክልል በመቀሌ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ አንድ አንድ ባለሀብቶች መጋዘናቸውን ለሌላ ስራ የሚጠቀሙበት እና መጋዘን ሳይኖራቸው ፍቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ ለእንጨት ምርቶች ማከማቻ መጋዘን ስፔሲፊኬሽን (መስፈርት) ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት በደን ውጤት ስራ ላይ ከተሰማሩ ባለሃብቶች ቢዝነስ ፕላን (አጭር ፕሮጀክት ፕሮፋይል) ሳያቀርቡ የደን ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **የደን ውጤቶች ዝውውርና ቁጥጥር ሥራ በቅንጅት መከናወኑን በተመለከተ፡-**

66. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ክልሎች ከሌሎች አግባብ ካላቸው ድርጅቶች ማለትም ከጉምሩክ፣ ከፖሊስ፣ ከቀበሌ አስተዳደር እና ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በቅንጅት ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- የአካባቢ ጥበቃና ደን ልማት ጽ/ቤቶቹ ከጉምሩክ፣ ከፖሊስ፣ ከቀበሌ አስተዳደር እና ከየአካባቢዎቹ ህብረተሰብ ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አሰራር እጥረቶች ያሉበት መሆኑ፣
- በተለያዩ ክልሎች ለማየት እንደተቻለው እስከ ቀበሌ አስተዳደር ድረስ መዘርጋት ያለበት የደን ግብረ ሃይል መዋቅር በአግባቡ ተዘርግቶ ወደ ተግባር እንዳልገባና ከሌሎች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራሩ ደካማ መሆኑ፣

➢ **የደን ውጤቶች መቆጣጠሪያ ኬላዎች መቋቋማቸውን በተመለከተ፣**

67. በመንግስት ደኖች መግቢያና መውጫ መንገዶች እንዲሁም በጥናት በተመሰረተ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ በሚቋቋሙ የደን ውጤቶች ዝውውር ህጋዊነትን መቆጣጠሪያ ኬላዎች ክልሎች ቁጥጥር ሊያካሄዱና ሚኒስቴር መ/ቤቱም በተዘረጋው የቁጥጥር ስርዓት ስለመሰራቱ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በታዩ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልሎች አብዛኛው አካባቢዎች የደን ኬላ ባለመኖሩ ለመጥቀስ ያህል በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሲዳማ ዞን በሸበዲኖ፣ በበንሳና በዳሌ ወረዳዎች እንዲሁም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በዶዶ፣ በማና፣ በሊሙና በሚዛን አካባቢዎች፡-

- ሕገወጥ የደን ሃብት ውጤት ዝውውሩ ከፍተኛ በመሆኑ የተፈጥሮ ደን ሃብቱ ከመጨፍጨፉ በተጨማሪ መንግስት ከደን ውጤቶች ማግኘት የሚገባውን ገቢ ማግኘት አለመቻሉ፣
- በሁሉም የመንግስት ደኖች መግቢያና መውጪያ ላይ ኬላ የሌለ መሆኑና ኬላዎች ያሉባቸው ቦታዎችም በጥናት መሰረት ስላልተቋቋሙ በሌሎች አዋሳኝ ቦታዎች ላይ ህገወጦች እየሰሩና በከፍተኛ ሁኔታ የደን ውጤቶች እየተዘዋወሩ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዶዶ ወረዳ የአካባቢ ጥበቃ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን የመንግስት ደኖች ሲስማኬዶና በርሲስ የሚባሉ እንዳሉና በመግቢያና በመውጪቸው ላይ ኬላዎች እንደሌሉ ኬላዎች ቢኖሩ የበለጠ የደን ውጤቶች ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚቻል እንደነበረ፣ ኬላዎች ባለመኖራቸው ችግር እየተፈጠረባቸው እንዳለ በተለይ ምሽት ላይ በስራቸው ላይ ስለማይሆኑ የቁጥጥር ሂደቱ የላላ እንደሆነ ኬላዎች ቢኖሩ ቁጥጥሩ ይጠናከር እንደነበረና ፖሊሶች ጥቆማ እያደረጉ ከነሱ ጋር በመተባበር እየሰሩ መሆኑን መግለጻቸው፣

➢ **የደን ውጤቶች ሲዘዋወሩ ተገቢው ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፣**

69. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ውጤቶች ዝውውርን በተመለከተ ሥርዓት ሊዘረጋና ክልሎችም በዚሁ መሰረት እንዲፈጽሙ ሊያደርግ እና ተፈጻሚነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ ክልሎች የደን ውጤቶችና ምርቶች ከቦታ ቦታ ከመጓጓዙ በፊት ባለቤቱ የደን ሃብቱ ለሚገኝበት አካባቢ ላለው አካል በቅድሚያ በማሳወቅ የደን ማዘዋወሪያ ፈቃድ መያዝ እንዳለበት ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

    - ናሙና ተመርጠው በታዩ ቦታዎች በህጋዊ መንገድ እንዲሰራባቸው የተፈቀዱ የዛፍ ዓይነቶች ብቻ ሳይሆን እንዳይቆረጡ የተከለከሉ ሀገር በቀል ዛፎች (ቀረሮ፣ ዋንዛ፣ ዝግባ፣ ጥቁር እንጨት፣ ወይራ፣ ዶቅማ) ሳይቀሩ በግልፅ

የሚዘዋወሩበትና ተገቢው ቁጥጥር የማይደረግበትና በህገወጥ እየተጨፈጨፉ መሆኑ፣

የይለፍ ፈቃድ አሰጣጥን አስመልክቶ፡-

- የሚመለከታቸው አካላት የተጫነው የደን ውጤት ምን አይነትና ምን ያህል መሆኑን በአካል ሳያረጋግጡ ፈቃድ የሚሰጡ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሲዳማ ዞን አለታ ወንዶና ቦና ወረዳዎች የደን ሃብት በመቀነሱ ሳቢያ ለደን ውጤቶች ምንም ቦሌታ (የይለፍ ፈቃድ መስጫ) እንዳይሰጥ በክልሎቹ ቢከለከልም በህገ ወጥ መንገድ በተዘጋጀ ፎርጅድ ቦሌታ የሚያዘዋውሩ መሆኑ፣
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሲዳማ ዞን አለታ ወንዶና ቦና ወረዳዎች ከቦሌታ ውጪ በደብዳቤ የደን ውጤቶች እንዲያልፍ የሚያደርጉ መሆኑ፣
- በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልላዊ መንግስት ሲዳማ ዞን አለታ ወንዶ ወረዳና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ አርሲ ዞን በፖሊስ የተያዙ ፎርጅድ ቦሌታ (በህገወጥ ተመሳስለው የተሰሩ) መኖራቸው፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን ስራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ህገወጥ የይለፍ ወረቀት መኖሩና በነጭ ወረቀት ሲሰራ የነበረበት አከባቢዎችም፣ በአንድ ይለፍ ወረቀት በተደጋጋሚ የሚሰሩ ባለሃብቶች መኖራቸውን፣ እንዲሁም በፎርጅድ ቦሌታ ሲንቀሳቀስ የታያዘ በምዕራብ አርሲ ዞን ላይ ተይዞ በፍርድ ቤት ደረጃ ሁኔታው የተያዘ መሆኑ፣
- ከሲዳማ ዞን ፖሊስና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ፎርጅድ (በህገወጥ ተመሳስለው የተሰሩ) የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች (ከ7 በላይ መስሪያ ቤቶች) የይለፍ ወረቀቶችና የፈቃድ ማስረጃዎች ማህተሞችና ቲተሮች ተቀርጸው በህገወጥ መንገድ የደን ውጤቶች ግብይትና ስርጭት በሰፊው እየተሰራባቸው መሆኑ፣
- የይለፍ ወረቀት የሚሰጠው በተለያዩ ተቋማት መሆኑ ማለትም በጅማ ዞን ላይ በሚገኙ ሦስት ተቋማት በአካባቢ ጥበቃ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን፣

በኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ጅማ ቅርንጫፍ፣ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት እንዲሁም በደቡብ ክልል በንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት የሚሰጥ መሆኑ፣

➢ **በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወር የሚያዙ የደን ውጤቶች የሚያዙበት፣ የሚቀመጡበት እና የሚወገዱበት ሥርዓትን በተመለከተ፣**

70. በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወር የሚያዙ የደን ውጤቶች የሚያዙበት፣ የሚቀመጡበት እና የሚወገዱበት ሥርዓት በአዋጅ ቁጥር 542/1999 ዓ.ም መሰረት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ በህገወጥ ዝውውር ውስጥ የነበሩና በቁጥጥር ስር የዋሉ የደን ውጤቶች

- በተለያዩ ቦታዎች ተከማችተው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆናቸው፣
- በህገወጥ መንገድ የተገኙ የደን ውጤቶች የሚወገድበት ስርዓት በየዞኑና በየወረዳዎቹ የተለያየ (ወጥ የሆነ ሥርዓት የሌለው) መሆኑ፣ ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን 10% ለጠቋሚው፣ 50% ለደን ልማቱ (ለወረዳው) እና 40% ለመንግስት ገቢ የሚያደረግበት አሰራር ያለ ሲሆን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በሲዳማ ዞን በበንሳ ወረዳ 60% ለጠቋሚ እና 40% ለመንግስት ገቢ የሚደረግ መሆኑ፣
- በናሙና በኦዲቱ ተመርጠው በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ከተወረሰ የደን ሽያጭ ገቢ ክፍፍል የሚከናወንበት የአፈጻጸም መመሪያ የሌለ በመሆኑ በአንዳንድ ወረዳዎች የሽያጩን ሙሉ ገቢ ለመንግስት የሚያስገቡበትና በሌሎች ወረዳዎች ለልማት ማህበሮች እንደሚያስገቡና ወጥ የሆነ አሰራር የሌለ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **የደን የአገልግሎት ክፍያን (ሮያሊቲ) በተመለከተ፣**

72. ከደን የሚገኙትን ግልጋሎቶች እያገኙ ያሉ ድርጅቶች ሮያሊቲ (የአገልግሎት ክፍያ) ተተምኖ ሊከፍሉና ክልሎችም የደን ውጤቶች የአገልግሎት ክፍያ ተመን አዘጋጅተውና በሚመለከተው አካል አጸድቀው ተግባራዊ ሊያደርጉ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ውጤቶች የአገልግሎት ክፍያ ተመን ክልሎች ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- በትግራይ፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ እና አፋር ክልሎች የሮያሊቲ ክፍያ ተመን አለመዘጋጀቱን፣ በደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች በሚገኙ ሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች የሮያሊቲ ክፍያ መመሪያ የሌለ መሆኑ እና ሮያሊቲ ክፍያ የሚከፈልባቸው ወረዳዎች ያሉ ቢሆንም ያለ መመሪያ በግምት የሚያስከፍልበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የሮያሊቲ ክፍያ በየክልሉ እንዲሰበሰብ ስርዓት ቢዘረጋም ክልሎች ግን እገዛ ከማድረግ አኳያ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ግንቦት 2009 ዓ.ም የመስክ ክትትል ሪፖርት ማወቅ መቻሉ፣
- በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎቹ የተሰበሰበውን የሮያሊቲ ክፍያ መጠን የሚያሳይ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉ፣
- የሮያሊቲ ክፍያን በተመለከተ ገቢው ለደን ልማቱ በቀጥታ የሚውልበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ውጤቶች የአገልግሎት ክፍያ ተመን ክልሎች ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ያልተከታተለና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **ከውጭ እየገባ ያለውን በርካታ ቶን የጣውላና መሰል ምርት እና ሌሎች የደን ውጤቶች በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ መደረጉን በተመለከተ፣**

73. ሚኒስቴር መ/ቤቱና ክልሎች ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት ከውጭ እየገባ ያለውን በርካታ ቶን የጣውላና መሰል ምርት እና ሌሎች የደን ውጤቶች በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ እና የደን ውጤት ተረፈ ምርቶች እንዳይባክኑ እሴት በመጨመር ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

74. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዓመታዊ ዕቅዱ ውስጥ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት ከውጭ እየገቡ ያለውን የደን ውጤቶች በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት እና የደን ውጤት ተረፈ ምርቶች እንዳይባክኑ እሴት በመጨመር ለተለያዩ ምርቶችና ጥቅሞች እንዲውሉ የተለያዩ ሀገሮችን ተሞክሮ ያካተተ የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ ያቀደ ቢሆንም፡-

- የደን ውጤቶች የስራ መስክ ለዜጎች የስራ እድል እንዲሁም የገቢ ምንጭ እንዲሆን በ2008፣ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመታት በዕቅድ የያዘ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት ከውጭ እየገባ ያለውን በረካታ ቶን የጣውላና መሰል ምርት እና ሌሎች የደን ውጤቶች በሀገር ውስጥ ምርት እንዲተካ ድጋፍና እገዛ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሀገራችን በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጅግ በርካታ የደን ውጤቶችን ከተለያዩ አገሮች እያስገባች መሆኑ፣ ለምሳሌ ለደን ውጤቶች በ2007, በ2008 እና በ2009 ዓ.ም እንደቅደም ተከተላቸው ብር 1,441,096,441.43፣ 2,241,895,998.47 እና 858,915,716 ወጪ የተደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ውጤት ተረፈ ምርቶች እንዳይባክኑ እሴት በመጨመር ለተለያዩ ምርቶችና ጥቅሞች እንዲውሉ የተለያዩ ሀገሮችን ተሞክሮ ያካተተ የአሰራር ማንዋል እንዳላዘጋጀና ስልጠናም ያልሰጠ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ልማትና አጠቃቀም ሥራዎችን የሚመራበት የደን ፖሊሲና አዋጅ በ1999 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም ላለፉት አስር አመታት አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዱ ዘርፉን የተመለከተ ደንብና መመሪያ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ያልተዘጋጀ መሆኑን፤

ታውቋል፡፡

75. በመሆኑም

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ ያሉ የተለያዩ የደን ውጤቶችን የሚመለከቱ የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም አዲስ የወጡ ሕጎች ተግባራዊነታቸውን ለማረጋገጥ ለክልሎችና ለሌሎች ፈጻሚ አካላት በበቂ ሁኔታ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የከሰል ማክሰልን በተመለከተ የሚፈቀድበትም አግባብ ካለ ሁሉም ባለድርሻ እንዲመክሩበት በማድረግ በሁሉም ክልሎች ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ✓ በአመራሩ፣ በባለሙያው በፖሊስ፣ በፍትሕ አካላትና በህብረተሰቡ ዘንድ በደን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ህጎች ላይ በቂ ግንዛቤ ስለሌለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማስተዋወቅ ስራውን በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም በቀላሉ ተደራሽ በሆኑት ሚዲያዎች፣ በፓምፕሌቶች እንዲሁም ባለድርሻ አካላትንና ሕብረተሰቡን በአካል በመጋበዝ መስራትና በህገወጥ

መንገድ እየወደመ ያለውን የሀገሪቱን የተፈጥሮ የደን ሃብት እንዲጠብቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ✓ በደን ሀብት ላይና በደን ውጤቶች ዝውውር ላይ ጥፋት የሚያደርሱ በህጉ መሰረት ተጠያቂ የሚሆኑበት አሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም በሕገወጥ የደን ውጤቶች ዝውውር ላይ የሚሳተፉትን አካላት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን አማራጭ መንገዶችን በማጥናት ወደ ሌላ የስራ መስክ የሚሰማሩበትን መፍትሔ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር በመሰረታዊ አሰራር ሂደት ለውት ጥናት ላይ አስፈላጊ ነው ብሎ የወሰነውን የደን ጉዳዮችን የሚመለከት የመደበኛ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎት እንዲቋቋም ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በመተባበር ወደ ተግባር ሊሸጋገር ይጋበል፡፡ በተጨማሪም በደን ጉዳዮች ላይ የሚወጡ አሠራሮችና መመሪዎችን በፌዴራልና በክልል ለሚገኙ ለዳኞች፣ ለአቃብያነ ህግ እንዲሁም ለፖሊስ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ✓ በደን ውጤቶች ለሚሰማሩ የንግድ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ፈቃድ ጠያቂዎቹ የማኔጅመንት ዕቅድ እንዲያቀርቡ የሚያደርግና የቀረበው ዕቅድ የሚገመገምበትና ውጤቱ ታይቶ ፈቃድ የሚሰጥበት አሠራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በደን ሙያ የሥራ መስክ ለሚሰማሩ ፈቃድ ጠያቂዎቹ ማሟላት የሚገባቸውን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊደረግ እና ያለፈቃድ የሚከናወን ህገወጥ ንግድን ለመከላከል የሚሳችል ሥርዓት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ባለፈቃዶቹ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱና ክልሎች በይበልጥ ትኩረት ሰጥተው ከጉምሩክ፣ ከፖሊስ፣ ከቀበሌ አስተዳደርና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ቀጣይነት ያለው እና ችግር ፈቺ የሆነ ጠንካራ የቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱ እና ክልሎች በመንግስት ደኖች መግቢያና መውጪያ መንገዶች እንዲሁም በጥናት በተመሰረተ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ በሚቋቋሙ የደን መቆጣጠርያ ኬላዎች በማቋቋም ህገወጥ የደን ውጤቶች ዝውውርን መቆጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ደኖች ወይም የደን ውጤቶችና ምርቶች ከቦታ ቦታ ከመንጓዙ በፊት ባለቤቱ የደን ሀብቱ ለሚገኝበት ወረዳ ለሚገኘው የአካባቢ፣ የደን እና የዱር እንስሳት ቢሮ፣ ለአካባቢ ጥበቃና

የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን ወይም በየክልሉ ለሚገኙ ይህ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች በማሳወቅ የደን ማዘዋወርያ ፈቃድ (የይለፍ ፈቃድ) እንዲይዙ በማድረግ ህገወጥ የይለፍ ፈቃድ ይዘው የሚንቀሳቀሱትን በመቆጣጠርና በመቅጣት የሀገሪቱን ውስን የደን ሀብት አግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ለደን ውጤቶች ዝውውር ፈቃድ የሚሰጠው አካል ተለይቶ ሊቀመጥና ተደራራቢ የሆኑ ፈቃድ የመሰጠት አሠራሮች ሊወገዱ ይገባል፡፡

- ✓ በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወሩ የተያዙ የደን ውጤቶች ሲያዙ የሚከማቹበትና የሚወገዱበት ወጥ የሆነ አሰራር ተዘርግቶ ተግባረዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በህገወጥ መንገድ የተያዙ የደን ውጤቶች የሚገኝ ገቢ ክፍፍል ድርሻን በተመለከተ በየደረጃው ግልጽ የሆነ መመሪያ ወጥቶ ተግባረዊ በማድረግ ለብልሹ አሰራር የሚከፍቱ አካሄዶችን ማቀረት ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ ከደን የሚገኙትን ግልጋሎቶች እያገኙ ያሉ ድርጅቶች ሮያሊቲ (የአገልግሎት ክፍያ) ተተምኖ ሊከፍሉ፣ ሁሉም ክልሎች የደን ውጤቶች የአገልግሎት ክፍያ ተመን አዘጋጅተውና በሚመለከተው አካል አጸድቀው ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሮያሊቲ ክፍያ መረጃ በሁሉም ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ተጠናቅሮ እንዲያዝና በተፈለገው ወቅት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ውጤት ተረፈ ምርቶች እንዳይባክኑ እሴት በመጨመር ለተለያዩ ምርቶችና ጥቅሞች እንዲውሉ የተለያዩ ሀገሮችን ተሞክሮ ያካተተ የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ የደን ጠባቂዎችና የደን ውጤት ዝውውር ተቆጣጣሪዎች በሥራቸው ላይ በሚሆኑበት ወቅት በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል በሚወስነው መሰረት ዩኒፎርም እንዲለብሱ እና መታወቂያ እንዲይዙ አስፈላጊውን ቁጥጥር በማድረግ እየወደመ ያለውን የሀገሪቱን የደን ሀብት ከጥፋት መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

በማለት የማሻሻያ ሃሳብ ሰጥተናል፡፡

## 7.የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለትራንስፎሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል አፈፃፀም በተመለከተ፤

➢ **ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በጥናት የለየና ችግሮቹ የሚፈቱበትን ስልት ነድፎ መተግበሩን በተመለከተ፣**

76. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በጥናት ሊለይ ይገባል፡፡ የተለዩት ችግሮች የሚፈቱበትን ስልት ሊነድፍ፣የሚነድፋቸው ስልቶች ዕድገትን፣አካባቢያዊ ዘላቂነት፣ አስተማማኝ የገበያና የምርት ማቀነባበር ብቃት እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ሊያካትቱና በጥናቱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና የትግራይ ክልሎች የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የተከናወኑ ጥናቶችን በተመለከተ፡-

- ኤጀንሲው በ2008 በጀት ዓመት የግብርና የምርት ማቀነባበሪያን ማስተዋወቅና የምርት ማቀነባበርን አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ እና የባለድርሻ አካላት ምክክር በማድረግ፣ የድርጊት መርሃ ግብር ማፅደቅን አቅዶ ያላከናወነ ሲሆን በ2009 እና 2010 በጀት ዓመትም በዕቅዱ እንዲካተት ያላደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት መቻሉ፣

78. ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ላይ ያሉ ችግሮች በመለየት አስፈላጊውን ስልት በመንደፍ ችግሮቹን መፍታት ሲገባው የሚገባው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት፡-

- የግብዓት አቅርቦት (ምርጥ ዘሮች፣ ማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣ የፀረ ተባይ እና አረም መደሃኒቶች) በወቅቱ እና በበቂ ሁኔታ ለአርሶ አደሩ የሚቀርብበትን ሁኔታ አለመመቻቸቱ፣ የአርሶ አደሩን የግብአት ፍላጎት ለማወቅ የደሰሳ ጥናት አለማድረግ እና የግብርና ግብአት ፍላጎት በግብርና ባለሞያዎች በአግባቡ ያለ መለየት አርሶ አደሩም ያለው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ በቂ የሆነ ግብአት እና ቴክኖሎጂ ያለመጠቀም ሁኔታ መኖሩ፣
- የገጠር ፋይናንስ የአቅርቦት ጥራትን በተመለከተ ብድር በወቅቱ አለማግኘት፣ የቁጠባ ወለድ መጠኑ አበረታች አለመሆን፣ ግብርናው ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ተጋላጭ በመሆኑ አበዳሪዎች ብድር ለመስጠት ፍላጎት አለመኖር፣ አገልግሎቱ በሞባይል ባንኪንግ አለመሆን፣ የብድር ሰጪ ተቋማት በገጠር ቀበሌዎች ተደራሽ አለመሆን እና ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ስለገጠር ፋይናንስ በቂ እውቀት የሌላቸው መሆኑ፣

- በአርሶ አደሩ አካባቢ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አለመኖር እና ገበያ ተኮር ምርት ማምረት አለመቻሉ፣
- አዳዲስ የሚከሰቱ አረሞችና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚመጡ ችግሮች በወቅቱ እየተፈቱ አለመሆኑ፣
- ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ ከመሰራጨቱ በፊት ጥራቱ የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉ፣
- አርሶ አደሩ ለአፈር አይነቱ ያልተመከሩ ማዳበሪያዎችን በመጠቀም ምጥን ማዳበሪያዎች በሰብል እና በአፈሩ ላይ ጉዳት እያደረሱ ያለበት ሁኔታ መኖሩ፣
- መሬት ለምነት ማጣት (የአፈር አሲዳማነት) በመጨመሩ ለአብነት በኦሮሚያ ክልል ካለው 6.01 ሚሊየን ሄክታር የሚታረስ መሬት ውስጥ ከሁለት እስከ ሦስት ሚሊየን ሄክታር የሚሆነው መሬት በአሲዳማነት መጠቃቱ እና ችግሩ ቀድሞ ከነበረበት የአገሪቱ ምዕራባዊ ክፍል ወደ ሰሜናዊና ደቡባዊ የአገሪቱ ክፍሎች እየተስፋፋ እንደሆነ እና በየአመቱ በስምንት በመቶ የምርትና ምርታማነት እድገት ለማስመዝገብ የተያዘውን እቅድ እንዳይሳካ ማነቆ መሆኑ በዚህም ምክንያት አርሶ አደሩ ቀደም ሲል ሲያመርታቸው የነበሩ ዋና ዋና ሰብሎች ከምርት ውጪ እንዲሆኑና አሲዳማነትን የሚቋቋሙ ውስን ሰብሎች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የተገደዱ መሆኑ፣

➢ **የአፈር ለምነት ደረጃ እና የማዳበሪያ ፋብሪካዎችን ማቋቋምን በተመለከተ፡-**

79. ኤጀንሲው የአፈር ለምነት (Ethiosis) ደረጃ እና የማዳበሪያ አጠቃቀም ጥናት ተጠናቆ ፍኖተ ካርታው ለሶስት (አማራ፣ ደቡብ እና ትግራይ) ክልሎች አሰራጭቷል፡፡ ይሁን እንጂ

- ጥናቱ የማዳበሪያ አጠቃቀም ላይ ግልጽ የሆነ ምክረ-ኃሳብ የሚሰጥ ባለመሆኑ ጥናቱ በአጠቃላይ በናሙና የተለየ እንጂ በቀበሌ፣ በጎጥ እና በአርሶ አደር ማሳ ደረጃ ተግባራዊ በሚሆንበት መልኩ ተለይቶ የቀረበ አለመሆኑ፣
- በጥናቱ መሰረት ንጥረ ነገሮችን ከውጭ አገር በመግዛት እንደ የአካባቢው አፈር ለምነት ይዘት በተዘጋጀው የማዳበሪያ አጠቃቀም ምክረ-ሃሳብ ቀመር ምጥን ማዳበሪያዎችን አቀነባብሮ ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ታስበው የተቋቋሙ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካዎች አገር ውስጥ ተቀነባብሮ ከሚሸጠው ምጥን ማዳበሪያ ከውጪ

ከሚገባው ጋር ሲነፃፀር በዋጋ ውድ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ማምረት አለመቻላቸው፣

- ኤጀንሲው በሰጠው ምክረ ሃሳብ መሰረት ፋብሪካውን ያቋቋሙ የገበሬዎች ኅብረት ስራ ዩኒዬኖች ማለትም በአማራ ክልል (መርከብ)፣ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል (መሊቅ)፣ በትግራይ ክልል (እንደርታ) የተባሉት ሶስት የህብረት ስራ ዩኒየኖች ለኪሳራ የተዳረጉ ሲሆን ኪሳራቸውን በዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል፡-

➢ **መርከብ ህብረት ስራ ዩኒየን**

 ➢ አገልግሎት የማይሰጥ 59 ሺ 84 ኩንታል ቦሮን፣ ዚንክ እና ፖታሽ መጋዘን ውስጥ ተከማችቶ በየወሩ ለኪራይ 100 ሺ ብር ወጪ እየተደረገ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ 46 ሺ 192 ኩንታል ፖታሽ ያለጥቅም መጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣

 ➢ ለወለድ 390 ሺ ብር እና ለ14 ቋሚ ሰራተኞች ያለሥራ በየወሩ 40 ሺ ብር እንዲከፍል እየተገደደ ሲሆን

➢ **መሊቅ የስልጤ ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን**

 ➢ በአግባቡ ጥናት ሳያደርግ ያስገባው 53 ሺ ኩንታል ፖታሽ ጥቅም ላይ ያልዋለ እና በመጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣

 ➢ ዩኒየኑ በየወሩ 70 ሺ ብር ለኪራይና ተጨማሪ የአስተዳደር ወጪ እንዲከፍል የተገደደ መሆኑ እና ፖታሹም የተበላሸ መሆኑ፣

 ➢ ፋብሪካው በአግባቡ ስራውን ባመስራቱ ምክንያት በየዓመቱ 6 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ እየከሰረ መሆኑ፣

➢ **እንደርታ ህብረት ስራ ዩኒየን**

 ➢ በ2006 ዓ.ም በምክረ ሃሳቡ መሰረት ከውጭ አገር ፖታሽየም ክሎራይድ፣ ቦራክስ እና ዚንክ ሰልፌት ጥሬ እቃዎችን ብር 42,529,037.33 (አርባ ሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ሰላሳ ሰባት ከ33 ሳንቲም) ወጪ በማድረግ ወደ አገር ውስጥ ቢያስገባም ጥሬ እቃዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸውና ጥቅም ላይ ሊውሉ ባለመቻላቸውና ለብልሽት መዳረጋቸው፣

 ➢ ለሌሎች ቀጥተኛ ላልሆኑ ወጪዎች ብር 33,267,986.42 መዳረጉ፣

 ➢ በአጠቃላይ 75,797,023.75 ዩኒየኑ የከሰረ መሆኑ፣

➢ የበቾ ወሊሶ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ

➢ የማምረት ሥራ ጀምሮ የፕሮጀክቱ አካል የነበሩ ተግባራት ያልተጠናቀቁ በመሆኑ ምጥን ማዳበሪያ የማምረት ሥራ ያቋረጠ መሆኑ፣

➢ **ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ጥናቶች ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እና ተግባራዊ መሆናቸውን በተመለከተ፡-**

80. በኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶች የአርሶ አደሩን እና የአስፈፃሚ አካላትን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ እና ሊተገበሩ የሚችሉ ሊሆኑ፤ጥናቶቹ ተግባራዊ መደረጋቸውን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ሊከታተል ይገባል፡፡ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ጥናት ቢያደርግም ጥናቶቹ፡-

- የአነስተኛ አርሶ አደሩን እና የፈፃሚዎችን ፋላጎት እና አቅም መሰረት ያደረገ አለመሆኑ፣ ለዚህም ማሳያ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ፕሮጀክት እ.አ.አ ሚያዝያ 2016 ተጀምሮ መጋቢት 2018 መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም ፕሮጀክቱን ለመጀመር ስትራቴጂ ተቀርጾ ነገር ግን የአርሶ አደሩን አቅም ያላገናዘበ እና አርሶ አደሩ አቅሙን ለማጎልበት የሚያስችል ሌሎች አማራጮች ባለመኖራቸው ወደ ተግባር ያልተገባ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ያከናወናቸው ጥናቶች እና ምክረ ሀሳቦች በሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ጥናቶቹና ምክረ ሀሳቦቹም በሚመለከታቸው ተቋማት/ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የፌዴራልና የክልል ህብረት ሥራ ኤጀንሲዎችና ማህበራት፣ የክልል ግብርና ቢሮዎች ያልተተገበሩ መሆናቸው፣

➢ **ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግባቸው ቦታዎች ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት ማዘጋጀቱን እና ክልሎች የተመደበላቸው በጀት እንዲያውቁት መደረጉን በተመለከተ፡-**

81. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ በኃላፊነት የሚመራቸው ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ቦታ (ክልል፣ዞን እና ወረዳ) የሚመርጥበት ግልጽ የሆነ መምረጫ መስፈርት ሊያዘጋጅ እና በመስፈርቱ መሰረት ቦታዎቹ ሊመረጡ እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ የሚደረጉባቸው ክልሎች የተመደበላቸውን በጀት እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

**ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉበት ቦታ የሚመረጥበት መስፈርት በተመለከተ፣**

- ኤጀንሲው ከቀጥታ ዘር ግብይት በስተቀር ሌሎች ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉባቸው ቦታዎች (ክልል፣ ዞን እና ወረዳ) የመረጠበትን መስፈርት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ ሲሆን ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ከሚያደርግባቸው ክልሎች ጋር ሳይገናኝ በቀጥታ በወረዳዎች ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑ፣

**ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ለሚደረጉባቸው ለእያንዳንዱ ክልል የተመደበውን በጀት ማሳወቅን በተመለከተ፣**

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በጀት በተመለከተ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚደረግባቸው እያንዳንዳቸው ክልሎች/ወረዳዎች ስለተመደበላቸው በጀት እና ስለ ፕሮጀክቱ ዝርዝር ተግባራት እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **ኤጀንሲው የሚመራቸው ፕሮጀክቶች ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎች ማለፋቸውን በተመለከተ፣**

82. ኤጀንሲው የሚመራቸው ማንኛውም ፕሮጀክቶች፤ በፕሮጀክት እቅድ፣ ትግበራ፣ አመራር፣ ግምገማና የመማማር ሂደት መመሪያ (project planning, implementation, monitoring, evaluation and learning process guideline) ላይ የተቀመጡትን የትግበራ ቅድመ-ዝግጅት (Implementation set-up) ሙከራና ማሻሻያ (testing and refinement) እና ማስረከብ (handover) ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎች እንዲያልፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች መካከል ለኦዲቱ በናሙና የተመረጡት የግብርና ግብአት መከታተያ፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የቀጥታ ዘር ግብይት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት፣ የግብርና አገልግሎት ማዕከል፣ ሞዴል የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል አቅም ግንባታ፣ የግብአት ኩፖን ሽያጭ እና አውቶሜት ኢ-ቫውቸር ሲስተም እና የምጥን

ማዳበሪያ ፕሮጀክቶች ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎች ማለፋቸውን የሚሳይ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ መቅረብ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

➢ **ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚጠናቀቁ ስለመሆኑ፣**

84. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ለሚመለከተው የረጅም ጊዜ ተግባር ባለቤት (deliverable owner) የስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡
በኦዲቱ ወቅት ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በአራቱ (ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣አማራና ትግራይ) ክልሎች ስር በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ከሚተገብራቸው ፕሮጀክቶች በናሙና ተመርጠው የታዩት፡-

- **የግብርና ግብዓት መከታተያ ፕሮጀክቱ** እቅድ ዲዛይኑ ጥቅምት 2009 ዓ.ም (እ.አ.አ ኦክቶበር 2016) ኢንኩቤሽኑ ታህሳስ 2010 ዓ.ም. (ዲሴምበር 2017) ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታየው በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በስልጤ ዞን ስልጢ ወረዳ ከፕሮጀክት ዲዛይን ጊዜው በፊት በ2008 ዓ.ም የካቲት አካባቢ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የተቋረጠ መሆኑ፣
- **የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ፓይለት ፕሮጀክትን** ሚያዚያ 2008 ( አፕሪል 2016) ጀምሮ መጋቢት 2010ዐ.ም (ማርች 2018 ለማጠናቀቅ አቅዶ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ወደ ተግባር አለመግባቱ፣ ይህን ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ ከአቀዳቸው ወረዳዎች በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጦ በታየው በደቡብ ክልል ሀዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ ሆሳዕና ከተማ ላይ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- **የቀጥታ ዘር ግብይት ፕሮጀክት** እ.አ.አ ታህሳስ 2014 ተጀምሮ መጋቢት 2017 መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በሲዳማ ዞን ሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ ገና በመስከረም 2010 ዓ.ም በጅምር ላይ ያለ ሲሆን በትግራይ ክልል እንደርታ ወረዳ ደግሞ የተቋረጠ መሆኑ፣
- **የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት ፕሮጀክት** እ.ኢ.አ 2007 ዓ.ም ተጀምሮ 2012 ዓ.ም መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታየው በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን አንገጫ ወረዳ ዶዮ ገና ከተማ የሚገኘው የዘርታ ከምባታ ዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየን በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

እና ሰልፍ ሄልፕ አፍሪካ ከሚባል ድርጅት በተገኝ ብር 299,786.19 ድጋፍ በ2009 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም የላቦራቶሪ እቃዎችና ባለሙያ እንዲኖረው አለመደረጉ፣ ፕሮጀክቱ ቢዝነስ ዕቅድ፣ ግምገማና የማስፋፊያ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፣ የዘርታ ከምባታ ዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየን የመጋዘን ችግር ያለበት ሲሆን ዘሮቹ ምቹ ባልሆነ ቦታ ተቀምጠው ለብልሽት የተዳረጉ መሆኑ፣ በኤጀንሲው አማካይነት በሰልፍ ሄልፕ አፍሪካ የሚካሄደው የመጋዘን ግንባታ በቁፋሮ ደረጃ ላይ ብቻ ሲሆን በታቀደውና በውሉ መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ፣

- **የግብርና አገልግሎት ማእከል ግንባታ ፕሮጀክትን** ኤጀንሲው ከዩ.ኤስ.ኤድ ባገኘው ድጋፍ እ.ኢ.አ ሐምሌ 2015- ሚያዝያ 2018 ድረስ ተግባራዊ ለማድረግ ያቀደው ፕሮጀክት ሲሆን በናሙና ተመርጠው ከታዩ ወረዳዎች ውስጥ ከኦሮሚያ ክልል የወሊሶ፣ ከደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል የሆሳዕና ግብርና አገልግሎት ማዕከል ፕሮጀክቶች በ2009 ዓ.ም ስራ የጀመሩ ቢሆንም :-
    - ✓ ማዕከላቱ ከቀጥታ የዘር ግብይት ፕሮጀክት ጋር ትስስር ያልፈጠሩ፣
    - ✓ ለአርሶ አደሩ ግብዓቶችን የሚያቀርቡት ከግል ነጋዴዎች በፕሮፎርማ በመግዛት በመሆኑ ፕሮፎርማው የሚወስደው ጊዜ ረዘም ያለ ስለሆነ አርሶ አደሩ ግብአት በወቅቱ እንዳያገኝ ማድረጉ፣
    - ✓ የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ምርታማነት እንዲጨምር በቴክኖሎጂ በኩል የተጀመረ ስራ አለመኖሩ፣
    - ✓ የተሻሻሉ ፀረ-አረሞች ከገበያ በመጥፋታቸው ፀረ-አረሞችን በብቃትና በጥራት እያቀረቡ አለመሆኑ፣በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ድጋፍ የሚቀርብላቸው ብቃትና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ- አረም አለመኖሩ፣
    - ✓ የግብርና ሜካናይዜሽን የአቅርቦት ሰንሰለት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል አለመኖሩ፣
    - ✓ የግብርና ግብዓትን ጅምላ ንግድ ከሚያከናውኑ ዩኒዬኖች እና ከግብርና ፌዴሬሽን ጋር አለመተሳሰራቸው፣
    - ✓ የማዕከላቱ ውጤታማነት እንዲረጋገጥ የመምራት፣ የማሰልጠን እና የክትትል ስራ እየተሰራ አለመሆኑ፣
    - ✓ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት ማቋቋሚያ ቦታዎች የቅድመ አካባቢ ጥናት ምርምራ ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ዳሰሳ ጥናት አለመካሄዱ፣

- ✓ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት በተቀመጠው መስፈርት ማለትም (ቦታው ፍሳሽን ለማስወገድ አመቺ በሆነ አቅጣጫ ላይ የተቀመጠ፣ ግድግዳዎቹ ኬሚካልና ሌላ ፍሳሽን ሊከላከሉ የሚችሉ፣ጭስ ማውጫ ያለው፣ ወለሉ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል፣ በቂ አየር እና ብርሃን ሊያስገባ የሚችል ወዘተ..) በማሟላት ያልተገነቡ መሆናቸው፣
- ✓ በሚፈለገው የሰው ሃይል ያልተሟሉ መሆኑ፣ የግብአት ፍላጎትና አቅርቦት ዳሰሳ አለመደረጉ፣ መተዋወቅ ያለባቸው ቴክኖሎጂዎች እንዲለዩ እና እንዲተዋወቁ አለመደረጋቸው፣
- ➢ በአቅራቢያቸው ካሉ ቀበሌ ሳተላይት ሱቆች ጋር ያልተሳሰሩ እና የገበያ መር የግብርና ምክረ ኃሳብ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ➢ የእንስሳት መድኃኒት ግዢ ጋር ተያይዞ መመሪያ ባለመኖሩ በምትኩ የሰብል ግዢ መመሪያን እየተጠቀሙ መሆኑ፣
- ➢ ማዕከላቱ ለሚያካትቷቸው ግብዓቶች፣ ቴክኖሎጂዎች እና አገልግሎቶች ሰርቶ ማሳያ እና መስክ ምልከታ ያልተደረገ ሲሆን በደቡብ ክልል ሃዋሳ ከተማ ሰርቶ ማሳያውን ጥር 1 ቀን 2009 ዓ.ም ተጀምሮ መጋቢት 2010 ዓ.ም ለማጠናቀቅ የታቀደ ቢሆንም እስከ መስከረም 2010 ዓ.ም ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ፣

➢ **የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል አቅም ግንባታ ፕሮጀክት** መጋቢት 2008 ዓ.ም (ማርች 2016) ተጀምሮ መጋቢት 2010 ዓ.ም. (ማርች 2018) መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታየው በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ቶሌ ወረዳ ስራ ለመጀመር በሚያዝያ ወር 2008 ዓ.ም ሳይት መረጣ የተደረገ ቢሆንም የተከናወኑ ስራዎች አለመኖራቸው፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ኦክስፋም በተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አማካይነት በክልሉ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ 12 ሚሊየን ብር ተመድቦ ስራው እንዲሰራ ታስቦ የነበረ ቢሆንም ድርጅቱ በክልሉ ስራውን ሳያከናውን ለደቡብ ክልል ልማት ማህበር ያስረከበው ቢሆንም ማህበሩ ከተቋሙ ሲረከበው የተሰጠው በጀት በቂ ባለመሆኑ የፕሮጀክቱን ስራዎች ማስቀጠል አለመቻሉን የደቡብ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ ከሰጠው ምላሽ ለመረዳት መቻሉ፣

➢ **የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ማቋቋም ፕሮጀክት** እ.ኢ.አ በ2012 ተጀምሮ በ2015 ተጠናቆ ማምረት እንደሚጀምር በኤጀንሲው የታቀደ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ፡-

**በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው የበቾ ወሊሶ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ፡-**

- ✓ በ2006 ዓ.ም ተመርቆ በ2007 ዓ.ም የማምረት ስራ የጀመረ ቢሆንም የፕሮጀክቱ አካል የሆኑ ተግባራት ማለትም መጋዝን ግንባታ በኤጀንሲው ብር 3,028,756 ድጋፍ በ30/1/2008 ዓ.ም ተለቆ በ2009 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም አለመጠናቀቁ፣
- ✓ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ለፋብሪካው ተገዝቶ በ12/14/2015 የቀረበ የላቦራቶሪ ዕቃዎች ቢኖሩም ባለሙያ በመቅጠር እንዲጀምሩ አለመደረጉ፣
- ✓ ኬሚካሎችን ለማዋሃድ የሚያገለግል (Relitech) መሳሪያ ተገዝቶ የቀረበ ቢሆንም አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣
- ✓ የፋብሪካው ፍሳሽ ማስወገጃ ማሽን ተገዝቶ ሞተር ባለመገጠሙ እስካሁን ስራ ላይ አለመዋሉ፣ ከፋብሪካው የሚወጣ ተረፈ ምርት ማስወገጃ ቦታ ባለመኖሩ ፋብሪካው ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን 900 ኩንታል የሚሆን ተረፈ ምርት ፋብሪካው ውስጥ ተከማችቶ ያለመሆኑ፣
- ✓ ለፋብሪካው ተገዝተው ስራ የጀመሩ ማሽኖች በየጊዜው የሚበላሹ መሆናቸው፤
- ✓ ለፕሮጀክቱ ምርት ማሳያ የተመረጠ የገበሬዎች የስልጠና ማዕከል ያልተለየ መሆኑ፣ ለሰርቶ ማሳያ ተግባራት ለልማት ጣቢያ ሰራተኞችና ለሚተገብሩ አርሶ አደሮች የተሰጠ ስልጠና፣ ለሰርቶ ማሳያ ወደ ማዕከላት የተሰራጨ ማዳበሪያ እና ከሰርቶ ማሳያው የተሰበሰበ መረጃና የተሰጠ ትንታኔ አለመኖሩ፣
- ✓ ዩኒዬኑ ግብዓት በራሱ ስለማይገዛና መንግስት ስለሚያቀርብ በኤጀንሲው የግብዓት ቲም ከባንክ ብድር እንዲያገኝ ያልተመቻቸለት መሆኑ፣ለህብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬኑ የተዘጋጀ የንግድ ስራ ዕቅድ አለመኖሩ፣

- በደቡብ ክልል ስልጤ ዞን የሚገኘው የመሊቅ ምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ በ2008 ዓ.ም ማምረት ቢጀምርም በ2009/10 ምርት ዘመን ማምረት ያቆመ፣ የተገነባው ፋብሪካ ለዩኒየኑ እንደ መጋዝን እያገለገለ፣ ለፋብሪካው የተቀጠሩ ሰራተኞች ስራ የሌላቸው በመሆኑ በዩኒየኑ ሌላ ስራ ላይ ተመድበው እየሰሩ፣ ለፋብሪካው ሊገነባ የታሰበው

መጋዝን ግንባታው ያልተጠናቀቀ መሆኑ እና ሌሎች የፕሮጀክቱ አካል የሆኑ ስራዎች ያልተጠናቀቁ መሆናቸው፣

- በትግራይ ክልል የሚገኘው የእንደርታ ምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታው ተጠናቅቆ 2007 ዓ/ም ስራ የጀመረ ቢሆንም፡-
  - ✓ ስለ ፋብሪካው እውቀት ያለው ማናጀር ያልተቀጠረለት፣የንግድ ማማከርና የንግድ ስራ እቅድ ያልተሰራለት፣የኦፐሬሽናል፣የአስተዳደርና የቴክኒክ ስልጠና እና የትግበራ ድጋፍና ክትትል ያልተደረገለት፣
  - ✓ የሚያመርተውን ማዳበሪያ ከገበያ ጋር የማስተሳሰር ውስንነት ያለበት ሲሆን በዚህ ምክንያት 425 ኩንታል ከፍላጎት በላይ ተመርቶ በመጋዘን ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
  - ✓ ፋብሪካው ደስት አብዞርቨር እና የተረፈ-ምርት (ዌስቴጅ) ማከማቻ ቦታ የሌለው፣ የሰራተኛ ሴፍቲ መጠበቂያ፣ የላብራቶሪ እቃዎች የተገዙ ቢሆንም ያልተተከሉ (not installed) እና የላብራቶሪ ባለሙያ ያልተቀጠረለት መሆኑ፣

➢ የህብረት ስራ ማህበራት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት እ.ኢ.አ ፕሮጀክቱ እንደ ሙከራ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል በሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት ሙከራ ለማድረግ ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል ተጀምሮ በእስኬል አፕ ደረጃ ላይ ሳይደርስ የተቋረጠ ሲሆን በትግራይ ክልል ግን ያልተጀመረ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

**➢ ኤጀንሲው ወደ ተግባር ባለቤቶች የሚተላለፉ ፕሮጀክቶችን ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

85. ኤጀንሲው ወደ ሚመለከተው የተግባር ባለቤት ያስተላለፋቸው ፕሮጀክቶች ተግባራዊነታቸውን የሚከታተልበትና ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ ከግብአት ኩፖን ሽያጭ በስተቀር ሁሉም ፕሮጀክቶች ወደ ተግባር ባለቤቶች አልተላለፉም፡፡ ወደ ተግባር ባለቤቶች መተላለፉ የተገለፀው የአግሮሜት ፕሮጀክት ጋር ተያይዞ ኤጀንሲው የሜትሮሎጂን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የአውቶማቲክ የአየር መመዝገቢያ ጣቢያ ተከላ በተመለከተ ያከናወናቸው ስራዎች በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስቱ

ክልሎች (ትግራይ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ) የአየር ትንበያ መረጃዎችን በመተንተን በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ፣

ታውቋል፡፡

➢ **የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ**

86. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ ባለድርሻ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን በሚተገብሩበት ወቅት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡

87. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው፡-

- በስትራቴጂዎች ውስጥ የተቀመጡ የመፍትሄ ሃሳቦች (የፖሊሲ ማሻሻያ፣ አሰራሮች) ባለድርሻ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን በሚተገብሩበት ወቅት ተግባራዊ ማድረጋቸውን በስልጠና እና በመስክ ክትትል እና ድጋፍ እንደሚያደርግ ቢገልፅም ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣
- በሚያዘጋጃቸው እና በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ላይ በተመሳሳይ የስልጠና ዓይነቶች ተመሳሳይ ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ እንዲሳተፉ የሚያደርግ መሆኑ፣
- የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዱ (የገብስ፣የጤፍ፤ስንዴ፣በቆሎ ወ.ዘ.ተ) ስትራቴጂዎች ኤጀንሲው በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች ያልላከ ሲሆን እነዚህን ስትራቴጂዎች ተጠቃሚዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ማለትም (በአማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ ወ.ዘ.ተ) እንዲተረጎሙ በማድረግ ተጠቃሚዎች እንዲደርሳቸው ያላደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

➢ **ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ለማስፈጸም የሚያከናውናቸው ተግባራትን መገምገሙን በሚችልበት መንገድ ማስቀመጡን በተመለከተ፣**

88. ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ሊያስቀምጥና በመስፈርቱ መሰረት ሊገመግም ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ

- የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ስትራቴጂክና አመታዊ እቅድ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ተግባራት ሊለኩ በሚችሉበት ማለትም የእቅድ አፈፃፀም ላይ ያሉ ተግባራት ከእቅዱ ጋር ለማነፃፀር በሚያስችል መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- ቀደም ሲል ኤጀንሲው ፕሮጀክቶቹን ለግምገማ ሲጠቀምበት የነበረው (አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ) በሚል ብቻ ይገለፅ የነበረው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት አፈፃፀም መለኪያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ከ50 በመቶ በታች ቀይ (እጅግ የዘገዩ)፣ ከ50-70 በመቶ ቢጫ (በመጠኑ የዘገዩ) እና ከ75 በመቶ በላይ አረንጓዴ (በጥሩ አፈፃፀም) ያሉ በሚል በማስተካከል በ2009 የአጀንዳው ዓመታዊ አፈፃፀም ላይ የተጠቀመበት ቢሆንም ይህ ገደብ (range) የተግባሩን አጠቃላይ ሁኔታ እንጂ እያንዳንዱ ተግባር ያለበትን ዝርዝር ሁኔታ ለመገምገም/ለማወቅ የማያስችል መሆኑ፣

  ታውቋል፡፡

➢ **ኤጀንሲው የተግባር ባለቤቶች የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ያጠና መሆኑን በተመለከተ፣**

90. ኤጀንሲው ለተግባር ባለቤቶች የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ሊያጠና እና በጥናቱ መሰረት ሊተገብር ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ለአጀንዳ ባለቤቶች ክፍተታቸውን ለይቶ ድጋፍ ለማድረግ የሚያግዘው የድጋፍ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያላደረገ እና የተግባር ባለቤቶቹ በራሳቸው በአፈጻጸም ወቅት ችግሮች በሚገጥሟቸው ጊዜ በሚጠይቁት የድጋፍ ጥያቄ መሰረት ብቻ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑ

ታውቋል፡፡

➢ **ለትራንስፎርሜሽን አጀንዳ የተግባር ባለቤቶች የተደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ፣**

92. ኤጀንሲው በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለዩ ተግባራትን ለሚፈፅሙ የተግባር ባለቤቶች (በስትራቴጂክ ዝግጅት፣ ዝርዝር ችግር በመፍታት፣ በአቅም ግንባታ፣ የማስተባበር፣ የቴክኒክ፣ የትንተና፣ የሥራ አፈፃፀም፣ የሀብት ማሰባሰብ/ ማስተዳደር እና የልዩ ሥራ) ድጋፍ ሊያደርግ

ይገባል፡፡

93. ይሁን እንጂ

- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራትን የሚፈፅሙ የተግባር ባለቤቶችን ለመደገፍ Enhancing ATA's Transformation Agenda Deliverable (TAD) Implementation Support Model ቢያቀርብም በተዘጋጀው ሞዴል መሰረት ያደረገው ድጋፍ እንዲሁም ሞዴሉም በወረቀት ደረጃ ያለ እንጂ በተቀረፀው ሞዴል መሰረት የተሰሩ ስራዎችንም በተመለከተ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት አለመቅረቡ፣
- በተጨማሪም በአስፈጻሚ አካላት የሚተገበሩና የትግባራ ክትትል የሚያደርግባቸው ተግባራት የስራው ባለቤት ለሆኑ ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን የማስፈፀም ድጋፍ መስጠት፣ በተቀመጠላቸው አቅጣጫ የሚተገብሩትን ስልት መደገፍና አፈጻጸማቸውን በመደገፍ የተግባሩ ባለቤቶች ጠንካራ ስራ ሰርተው ከጉድለቶቻቸው የሚወጡበትና ያልተፈፀሙ ተግባራት እንዲፈፀሙ ጠንካራ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት በቋሚ ኮሚቴው አስተያየት የተሰጠው ሲሆን በአስተያየቱ መሰረት ያደረገው ማስተካከያ ስለመኖሩ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ማቅረብ አለመቻሉ፣

እንዲሁም ከሀብት ማስተዳደር ጋር ተያይዞ ኤጀንሲው

- በየክልሉ ለሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች የያዘውን የበጀት እና የጊዜ መጠን የማያሳውቅ መሆኑ፣
- በማዳበሪያ ፋብሪካዎች እና በሌሎችም ፕሮጀክቶች የሚገጥሙ የቴክኒክ ችግሮች ላይ ኤጀንሲው በወቅቱ ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ እና
- ኤጀንሲው በፕሮጀክቶቹ ሥራ ላይ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተግባር ባለቤቶች እንዲሳተፉበት እና የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው ግንዛቤ ሊፈጥር አለመቻሉ፣

  ታውቋል፡፡

➢ **በሙከራ (Pilot) ደረጃ ተሞክረው የስራው ባለቤት እንዲያስፋፋቸው የተደረጉ ስራዎች መኖራቸውን በተመለከተ፣**

94. ኤጀንሲው በሙከራ /ፓይለት ደረጃ ሊሞከሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ከባለድርሻዎች ጋር

በጋራ በመሆን ካከናወነ በኋላ ውጤቱ ተገምግሞ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው ሊያደርግና ሥራውን ሊደግፍ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ከጥምር እርሻ ሥርዓት (Clustering) በስተቀር በፓይለት ደረጃ ሊሞከሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ካከናወነ በኋላ ውጤቱ ተገምግሞ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው ያደረጋቸው ስራዎች አለመኖራቸው፣

95. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትራንስፎሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን አስመልክቶ ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ኤጀንሲው የትራንስፎሜሽን አጀንዳ እቅድና አፈፃፀም ሪፖርቶችን በማጠናቀር ለትራንስፎሜሽን ካውንስሉ የሚልክ ቢሆንም፡-

- በትራንስፎሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ አስመልክቶ የሚያደርገው ክትትል ጠንካራ አለመሆኑ ለዚህም ማሳያ የአጀንዳው ባለቤቶች ያሉበትን ደረጃ በተመለከተ ፈፃሚዎች በየጊዜው ያሉበትን ደረጃ በጋራ እየገመገመ አፈፃፀማቸው ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ፣
- ለቋሚ ኮሚቴው የሚልከው የትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በአስፈጻሚ አካላት የሚተገበሩና የትግበራ ክትትል የሚያደርግባቸው ዘርፎች ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መፍትሄዎችን በሚያሳይ መልኩ ገምግሞ ሪፖርቱን ለቋሚ ኮሚቴው የማይልክ መሆኑንና መሻሻልም እንዳለበት ቋሚ ኮሚቴው አስተያየት የሰጠው ቢሆንም በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት ያደረገው ማስተካከያ ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣
- የአጀንዳው ባለቤቶች ያሉበትን ደረጃ በመገምገም አስፈላጊውን ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- ኤጀንሲው ለሰብል ምርትና ምርታማነት እድገት ማነቆ የሚሆኑ ችግሮች በተደጋጋሚ ሊከሰቱ የሚችሉ በመሆናቸው ችግሮች በየጊዜው በጥናት ሊለይ ይገባል፡፡ ችግሮችን ለመፍታት የሚነድፋቸው ስልቶች አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ

ሊያደርግና አገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ያላትን አስተዋፅኦ እንዲጨምር ሊያደርግ በሚችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የሚያከናውናቸው ጥናቶች የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ፍላጎትና አቅም እንዲሁም በቀላሉ ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ በየጊዜው የሚያከናውናቸው ጥናቶችም ተግባራዊ መደረጋቸው የአሰራር ስርአት ዘርግቶ መከታተል ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ በአራቱም ክልሎች በሚገኙ ወረዳዎች ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ፕሮጀክቶች ለያንዳንዳቸው ፕሮጀክቶች እንደ አይነታቸው ወረዳዎችን የሚመርጥበት መስፈርት በማዘጋጀት በመስፈርቱ መሰረት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ሊያደርግ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግባቸው ክልሎች/ወረዳዎች ደግሞ ስለተመደበላቸው በጀት በግልፅ እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን በሶስቱ የትግበራ ደረጃዎች ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት በማጠናቀቅ እና የረጅም ጊዜ ባለቤቶች በራሳቸው ሊፈፅሙ እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ድጋፍ በማድረግ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በሚደረጉባቸው ወረዳዎች የሚገኙ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለማሳካት የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጠቃሚ እንደሆኑ አምኖ የመረጣቸውን ፕሮጀክቶች ሙከራ በተቀመጠላቸው የጊዜ በማጠናቀቅ የረጅም ጊዜ ባለቤቶች እንዲያስፋፉ ሊያስተላልፍና የተግባር ባለቤቶቹ በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት በአመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ በመገምገም ፕሮጀክቶች ያሉባቸውን ግድፈቶች በወቅቱ እንዲያስተካክሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት የሚፈቱበትን ስልት መንደፍና የሚነደፉ ስልቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን መከታተል ያለበት እንደመሆኑ አገሪቱ ግብርናውን ለማዘመን የነደፈቻቸውን ስልቶች በፈፃሚ አካላት

ተግባራዊ መደረጋቸውን ወይም አለመደረጋቸውን በየጊዜው በመከታተል በአፈፃፀም ወቅት የሚገጥማቸውን ችግሮች ሊፈታ ወይም እንዲፈቱ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት ለመደገፍ የሚያስችለውን ዝርዝር ተግባራትን የያዘ እቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ወደ ተግባር በመግባት አፈጻጸሙን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ሊያስቀምጥ ወይም የአጀንዳው ባለቤቶች እንዲያስቀምጡ ድጋፍ በማድረግ እቅድና አፈፃፀሞችን በማነፃፀር የተገኙ ድክመቶች በወቅቱ እርምት እንዲሰጥባቸው ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው ለትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ ፍላጎታቸውን በየጊዜው በማጥናት ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት የሚፈፅሙ አካላት ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ በተለያዩ የድጋፍ አይነቶች (በስትራቴጂክ ዝግጅት፣ ዝርዝር ችግር በመፍታት፣ በአቅም ግንባታ ፣ የማስተባበር፣ የቴክኒክ፣ የትንተና ፣የሥራ አፈፃፀም፣ የሀብት ማሰባሰብ/ማስተዳደር እና የልዩ ሥራ) ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ ሥራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ካከናወነ በኋላ ውጤቱ ተገምገሞ ቀጣይነቱ ሲረጋገጥ ብቻ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው ግብርናውን ለማሳደግ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን የሚፈፅሙ አካላትን የደረሱበትን ደረጃ የሚከታተልበት ስርዓት በመዘርጋት በአፈፃጸማቸው ወቅት ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች እንዲፈቱ ሊያደርግ ወይም የሚፈቱበትን መንገዶች ማመላከት ይኖርበታል፡፡

በማት የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

## 8.በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ፓርኮችን የማልማት እና የማስተዳደር ሥራዎች አፈፃፀምን በተመለከተ፡-

➢ **ኮርፖሬሽኑ ጥናት እያጠኑ የሚገኙ አማካሪ ድርጅቶች ላይ የሚያደርገውን የክትትልና የቁጥጥርን በሚመለከት፣**

96. ኮርፖሬሽኑ የአገራዊ ማስተር ፕላንን መሰረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ማስተር ፕላን፣ የአዋጭነት ጥናት፣ የአካባቢ ጥበቃ ጥናት (Enviromental Impact Assement) እና የማህበራዊ ደህንነት ጥናት (Social safeguard) ሊያስጠና ይገባል፡፡ ጥናቶችንም እያጠኑ የሚገኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር አማካሪ ድርጅቶች የጥናት ሥራቸውን በወቅቱ አጠናቀው እንዲያቀርቡ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

97. ይሁን እንጂ በኮርፖሬሽኑ ጥናቶችን እያጠኑ የሚገኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር አማካሪ ድርጅቶች በገቡት ውል መሰረት የጥናት ሥራቸውን በወቅቱ አጠናቀው እንዲያቀርቡ ተገቢውን ግብረ መልስ ለመስጠት የሚያስችል የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ባለማድረጉ ጥናቶቹ በወቅቱ ያልተጠናቀቁ መሆናቸው ታውቋል፡፡

➢ **በኢንዱስትሪ ፓርኮች የተገነቡ የማምረቻ ሼዶችን ማከራየት እና የኪራይ ገቢ እየተሰበሰበ ስለመሆኑ፤-**

98. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የተገነቡ የማምረቻ ሼዶችን ለማከራየት እና የኪራይ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ኮርፖሬሽኑ ከፋብሪካ ሼዶች ኪራይ እና ሌሎች ተጓዳኝ አገልግሎቶች ለመሰብሰብኦዲቱ ወቅት ሥርዓት የዘረጋ ቢሆንም በተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ተጠቅሞ በእቅዱ መሰረት ገቢ ያልሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **ኮርፖሬሽኑ መመሪያዎች እና የአሰራር ማንዋሎችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

99. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅን ተከትሎ ፓርኮችን ለመምራት፣ ለማስተዳደር እና ለማስተዋወቅ /ለማርኬቲንግና ፕሮሞሽን/ የሚያገለግሉ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መመሪያዎች እና የአሰራር ማንዋሎችን ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

100. ይሁን እንጂ መመሪያዎችና ማንዋሎች ሳይዘጋጁ፣ የተዘጋጁትም ለረጅም ጊዜ ሳይፀድቁ በመቆየታቸው እንዲሁም በውጭ ምንዛሪ እየተከፈለ የተሰራ ሥራ በወቅቱ

አለመጠናቀቁ ኮርፖሬሽኑ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ አሰራሮችን ለመተግበር የያዘውን ዕቅድ የሚያጓትትና በሁሉም ቦታ ወጥ በሆነ መልክ እንዳይሰራ የአሰራር ክፍተት እንዲፈጠር እና ተገቢውን አገልግሎት ለተገልጋዩ እንዳይሰጥ እያደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

➢ **የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እና የጥራት ደረጃ እየተገነቡ ስለመሆኑ፤**

101. በኮርፖሬሽኑ የሚገነቡና የሚለሙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እና የጥራት ደረጃ ለማጠናቀቅ የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኮርፖሬሽኑ በኩል የክትትልና እና የቁጥጥር ስራ ማነስ ፓርኮች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርክ ልማቱ ላይ የተሳተፉ ሥራ ተቋራጮችም ሆኑ የግንባታ አማካሪ ድርጅት ውል ከመፈፀማቸው በፊት ብቃታቸው እና አቅማቸው በበቂ ሁኔታ ሳይረጋገጥ ውል የተዋዋሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ **በኢንዱስሪ ፓርኮች ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ለመከላከል የሚደረገውን ክትትልና ቁጥጥር በሚመለከት፣**

103. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚታዩ ውስጣዊ ችግሮች እና ከባለሀብቶች የሚነሱ ቅሬታዎችን ተቀብሎ የሚፈታበትን የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡ እንዲሁም ለሚነሱ ውስጣዊ ችግሮች እና ከባለሀብቶች የሚነሱ ቅሬታዎችን በወቅቱ የተፈቱ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

104. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በቦሌ ለሚ እና በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጣዊ የተለያዩ ችግሮች በወቅቱ መፍትሔ አለማግኘት በፋብሪካዎቹ ምርት የማምረት እና የኤክስፖርት ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑ፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ ከባለሀብቶች የሚነሱ ቅሬታዎችን በወቅቱ ምላሽ እየሰጠ ባለመሆኑ ባለሀብቶች ሥራቸውን በአግባቡ እንዳያከናውኑ ያደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ **በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የተፈጠረ የሥራ ዕድል እና ተቀጠርው የሚሰሩ ሰራተኞች ፍልሰት ከፍተኛ ስለመሆኑ**

105. ኮርፖሬሽኑ ውጤታማ የፓርክ አስተዳደርን ለባለሀብቱ ተደራሽ ለማድረግ

ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የስራ ዕድል እንዲፈጠርና ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች እንዲያድጉ በማድረግ ፓርኮቹ የተቋቋሙበትን አላማ እንዲሳካ ሊያደርግ ይገባል፡፡

106. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የሰራተኛው ፍልሰት ከዓመት ዓመት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመምጣቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሰራተኛ ፍልሰቱን መቀነስ የሚቻልበት መንገድ አለመፈጠሩ፣ ከዚህም በተጨማሪ ዜጎች በሚፈጠረው የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከማድረጉም ባሻገር በምርት እና በኤክስፖርት ሒደት ሀገሪቱ ልታገኝ የሚገባትን የውጪ ምንዛሪ ዝቅተኛ እንዲሆን የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- **የፋብሪካ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የሚገኝ ገቢን በተመለከተ፣**

ኮርፖሬሽኑ ውጤታማ የፓርክ አስተዳደርን ለባለሀብቱ ተደራሽ ለማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች እንዲያድጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

107. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኮርፖሬሽኑ እቅዶችን ሲያቅድ ቀድሞ የነበረውን አፈፃፀም በመገምገም ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ሊደረስበት የሚችል ወይም ተቀራራቢ እቅድ አለመታቀዱ፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች አፈጻጸም የተራራቀ እንዲሆን ያደረገ መሆኑና ሀገሪቱ ልታገኝ የሚገባውን የውጪ ምንዛሪ ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረጉ ታውቋል፡፡

- **ኮርፖሬሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የጋራ እቅድ የሚያዘጋጅና አፈፃፀሙን በመገምገም ግብረመልስ የሚሰጥ ስለመሆኑ**

108. ኮርፖሬሽኑ ከባለድርሻ አካላት (ከመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት፣ ከፋይናንስ ተቋማት፣ የትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ባለሀብቶችና ሌሎችም) ጋር በቅንጅት በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀትና በመፈራረም እንዲሁም በወጣው ዕቅድ መሰረት አፈፃፀሙን በመገምገም ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

109. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኮርፖሬሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ የጋራ ዕቅድ ቢያዘጋጅም በሚፈለገው ደረጃ ባለመሆኑ እና አፈፃፀሙን በመገምገም ግብረ መልስ ባለመስጠቱ ባለድርሻ አካላት በኢንዱስትሪ ፓርኩ ኃላፊነታቸውን ከመወጣት አኳያ መስራት በሚገባቸው መጠን እየሰሩ አለመሆኑን

ለማወቅ ተችሏል።

110. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በአዘጋጀው የፓርኮች ግንባታ ጋይድላይን ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ሲገነባ ሲገባ የቦሌ ለሚ ቁጥር 1 ኢንዱስትሪ ፓርክ የንግድ ሱቆች፣ የመረጃ ማዕከል (data center)፣ የስብሰባ አዳራሽ (conference room)፣ አምቡላንስ፤ የፓርኩ አጥር ዙሪያውን አለመታጠሩ (አለመከለሉ)፣ እና በኢንዱስትሪ ፓርኮች ተቀጥረው ለሚሰሩ ሰራተኞች መኖሪያ ቤት ታሳቢ ያልተደረገ መሆኑና እንደዚሁም በሀዋሳ በኢንዱስትሪ ፓርክ ተቀጥረው ለሚሰሩ ሰራተኞች መኖሪያ ቤቶች ታሳቢ ያልተደረጉ መሆኑ፣

111. የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እና የጥራት ደረጃ እየተገነቡ ስለመሆኑ ለማጣራት በተደረገው ኦዲት የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ የ19 ፋብሪካ ሼዶች እና መሰረተ ልማት ግንባታ 100% ለመፈጸም ታቅዶ 27.78%፤ የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ የ15 የፋብሪካ ሼዶች እና ተጓዳኝ የሆኑ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታዎች 100% ለማከናወን ታቅዶ 22.40%፤ የጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ የ 9 ፋብሪካ ሼዶች እና መሰረተ ልማት ግንባታ 70% ለመፈጸም ታቅዶ 5.41%፤ የቦሌ ለሚ ምዕራፍ ሁለት ኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ 50% ለማከናወን ታቅዶ የ13.17%፤ የቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ 50% ለማከናወን ታቅዶ 6.4%፣ የባህርዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ የ13 ፋብሪካ ሼዶች እና መሰረተ ልማት ግንባታ 30% ለማከናወን ታቅዶ የካሳ ክፍያ፣ የሳይት ፕላን ርክክብ፣ የሃይድሮሎጂ ጥናት መጀመሩ እና የግንባታ ስራ ከሚሰራ ተቋም ጋር ውል መፈፀም በስተቀር ሌሎች የታቀዱ ስራዎች ያልተከናወነ መሆኑ፤ የደብረብርሃን፣ አረርቲ እና አይሻ/ደዋሌ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እንደቅደም ተከተላቸው 15%፣ 8% እና 8% የፋብሪካ ሼዶች እና የመሰረተ ልማት ሥራዎች 30% ለማጠናቀቅ ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑ፤

112. በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የተገነቡ የማምረቻ ሼዶችን ማከራየት እና የኪራይ ገቢ መሰብሰብን በተመለከተ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከተገነቡት 20 የፋብሪካ ሼዶች ውስጥ 11፣ በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ደግሞ ከተገነቡ 52 ሼዶች ውስጥ 48 የተከራዩ ሲሆን የተቀሩት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተከራዩ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ በ2009 በጀት ዓመት ከፋብሪካ ሼዶች ኪራይ እና ሌሎች ተጓዳኝ አገልግሎቶች ብር180,862,187.00 ለመሰብሰብ አቅዶ ብር 65,786,436.22 የእቅዱን (36%) ብቻ

የተሰበሰበ መሆኑን፤

113. ኮርፖሬሽኑ ውጤታማ የፓርክ አስተዳደርን ለባለሀብቱ ተደራሽ በማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች ለማሳደግ ከቦሌ ለሚ  ኢንዱስትሪ ፓርክ በ2008 130 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 16.9 ሚለዮን ብቻ በማግኘቱ አፈፃፀሙ 13.03% መሆኑ፣ በ2009 በጀት ዓመት ከቦሌ ለሚ  ኢንዱስትሪ ፓርክ 40 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 23.8 ሚለዮን በማግኘቱ አፈፃፀሙ 59.79% መሆኑ፣ እንደዚሁም በ2009 በጀት ዓመት በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የፋብሪካ ምርቶችን ኤክስፖርት በማድረግ 50 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 1.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በማግኘት አፈፃፀሙ 2.91% ብቻ በመሆኑ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ዝቅተኛ የወጪ አፈጻጸም እንዳላቸው ከተከለሱ መረጃዎች መታወቁ፤

114. ኮርፖሬሽን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲያመርቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በቦሌ ለሚ ቁጥር 1 እና በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ  የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ያልገቡ መሆኑን፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም

- ኮርፖሬሽኑ ጥናቶችን እያጠኑ የሚገኙ  የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር አማካሪ ድርጅቶች በገቡት ውል መሰረት የጥናት ሥራቸውን በወቅቱ አጠናቀው እንዲያቀርቡ ተገቢውን ግብረ መልስ ለመስጠት የሚያስችል ድጋፍ ፣ ክትትል እና  ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከፋብሪካ ሼዶች ኪራይ እና ሌሎች ተጓዳኝ አገልግሎቶች መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ ባቀደው እቅድ መሰረት በወቅቱ መሰበሰብ አለበት፡፡
- በኮርፖሬሽኑ መዘጋጀት ሲገባቸው ያልተዘጋጁ መመሪያዎችና ማንዋሎች ማዘጋጀት እና ተዘጋጅተው በረቂቅ ደረጃ ያሉትም በሚመለከተው አካል ፀድቀው ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡ እንዲሁም  ኮርፖሬሽኑ የውጭ ምንዛሪ እየከፈለ በውጭ አማካሪ የሚያሰራው የውስጥ አሰራሩን የሚያጠናክሩ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ማኑዋሎችን እና መመሪያዎች ተጠናቀው ተግባራዊ መደረግ

አለባቸው፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ተገንብተው የተጠናቀቁትም ሆነ በግንባታ ላይ ያሉ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት እና የጥራት ደረጃ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ድጋፍ መደረግ አለበት፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጣዊ ችግሮችን ለመቅረፍ የክትትልና የቁጥጥር ስራ በተጠናከረ መልኩ በመስራት አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ እንዲሁም ከባለሀብቶች በተደጋጋሚ የሚነሱ ቅሬታዎችን በወቅቱ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
- በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የተፈጠረ የሥራ ዕድል እና ተቀጠርው የሚሰሩ ሰራተኞች ፍልሰቱን ለመቀነስ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት በጋራ በመሆን መስራት አለባቸው፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች አፈፃፀም ባቀደው መሰረት መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም እቅድ ሲታቀድ ቀድሞ የነበረውን አፈፃፀም በመገምገም እና ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ዕቅዶችን በመከለስ መገኘት ባለበት መጠን መታቀድ አለበት፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ የጋራ ዕቅድ በመዘጋጀት እና በመፈራረም፣ እንዲሁም አፈፃፀሙን በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት አለበት ፡፡

በማለት የማሻሻያ ሃሳብ አቅርበናል፡፡

## 9.በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት የእንስሳት ክትባትና ሪኤጀንቶችን ማምረት፣ መድኃኒቶችን የማቀነባበር እና የአያያዝ ሥርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ

➢ **የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋና ዉጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡-**

115. የኢኒስቲትዩቱ የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋ፤ ውጤታማና የሃገሪቱን ፍላጎት አሟልቶ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ የውጭ ምንዛሬ ለሃገሪቱ የሚያስገኝ ሊሆን ይገባል፡፡

116. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ምርቶቹን ወደ ሌሎች አሀጉራት ተወዳደሮ ለመሸጥ የኢንስቲትዩቱ የአመራረት ቴክኖሎጂ ዓለም ዓቀፍ ገበያ የሚፈልገውን የመልካም

አመራረት ዘዴን (Good manufacturing practice) ስታንዳርድ የማያሟላና የእውቅና ሠርተፊኬት የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ **የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋና ዉጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡-**

117. የኢኒስቲትዩቱ የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋ፤ ውጤታማና የሃገሪቱን ፍላጎት አሟልቶ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ  የውጭ ምንዛሬ ለሃገሪቱ የሚያስገኝ ሊሆን ይገባል፡፡

118. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አማካይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የክትባት ማሰራጫ ጣቢያና ቀዝቃዛ መጋዘኖችን /Cold Room/  ባለመዘጋጀታቸው፡-

- በ-200C መቀመጥ ያለበት ክትባት በበረዶ ሣጥን ሲጓጓዝ መንገድ ላይ በረዶው እየቀለጠ ክትባቱ ለብልሽት እየተዳረገ እና ክትባቱ ለእንስሳቱ ሲሰጥ በሽታን የመከላከል ብቃቱ እየቀነሰ የመጣ መሆኑን፣
- በተጨማሪም የብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ዝግጁነት ሥራ አመራር ኮሚሽን ቀደም ሲል በግብርና ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ወቅት በተመረጡ የአገሪቱ አካባቢዎች ቀዝቃዛ መጋዘኖች /Cold Room/ አስገንብቶ ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ እንዲቻል በኮሚሽኑ፣ በኢንስቲትዩቱ እና በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች ግብርና ቢሮዎች ጋር በ2005 ዓ.ም የአጠቃቀም ሶስትዮሽ ውል ተፈራርሞ በዚሁ መሰረት እንዲገነቡ ለሥራ ተቋራጭ ከተሰጡ 16 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ውስጥ፡- የ7ቱ የካቲት 25/2002 ዓ.ም ተጀምሮ በ120 የሥራ ቀናት፣ የ7ቱ መጋቢት 27/2004 ዓ.ም ተጀምሮ በ90 የሥራ ቀናት እና የ2ቱ ሚያዝያ 12/2004 ተጀምሮ በ90 የሥራ ቀናት ለማጠናቀቅ ከሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባ ቢሆንም የ16ቱም ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ ከታሰበው ከስድስት(6) ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፣
- እንዲሁም የተጀመሩት 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖች በባለቤትነት የሚከታተላቸው አካል ባለመኖሩ ፀሀይ፣ ዝናብና ንፋስ እየተፈራረቀባቸው  በመፈራረስ ላይ የሚገኙ መሆኑ፣ ለ16 ቀዝቃዛ መጋዝኖች 30% ቅድሚያ ክፍያ ለተቋራጮች የተከፈለ ሲሆን  በኦሮሚያ ክልል በነጌሌ ቦረና፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ሚዛን አማን ከተማ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ለመገንባት የታሰቡት ሶስት መጋዘኖች ግንባታቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ

ታውቋል፡፡

➢ **የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ ማቅረብን በተመለከተ፡-**

119. ኢንስትቲዩቱ የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ በማቅረብ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ሊያሟላ ይገባል፡፡

120. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስትቲዩቱ የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ በማቅረብ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ማሟላት የሚገባው ቢሆንም የአፍታ (Foot and Mouth Disease)፣ የፍየሎች ሳንባ በሽታ የእብድ ውሻ፣ የግመል መከላከያ ክትባቶች እና የሳላይን ዉሃ በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ የማይቀርብ መሆኑ፣ ኢንስትቲዩቱ የሚያቀርበው አባሰንጋ (Anthrax) ባለ 100 ዶዝ፣ የአባጎረባ (Black leg) እና የጎሮረሳ (Bovine Pasteuellosis) የክትባት ምርቶች በባለ 50 ዶዝ ብቻ በመሆኑ የደንበኞች ፍላጎት እና አቅምን ያገናዘበ በተለያየ መጠን ተከፋፍሎ የማይቀርብ መሆኑ፣

**የተለያዩ ኬሚካሎችና ክትባቶች አያያዝ፤ አጠቃቀም እና አወጋገድ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

121. ኢንስቲትዩቱ የሚጠቀምባቸውን የተለያዩ ኬሚካሎች አያያዝ፤ አጠቃቀም፣ የተበላሹና ጊዜ ያለፈባቸዉ የክትባት ምርቶችን ጨምሮ የሚወገድበት የንብረት አያያዝና የአወጋገድ መመሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

122. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ጊዜ ያለፈባቸው የክትባት ምርቶች አያያዝ፣ አጠቃቀምና የአወጋገድ መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፣ በየወረዳው ጥቅም ላይ ያልዋሉና ጊዜ ያለፈባቸዉ የክትባት ምርቶች ሳይወገዱ ለዓመታት ተጠራቅመው የሚገኙ መሆኑ፣ በአንዳንድ ወረዳዎች ክትባትን የንብረት አወጋገድ መመሪያን ተጠቅመው እንደማንኛውም አካባቢ የማይጎዳ ንብረት በመቁጠር የሚያስወግዱ መሆኑ፣ በኢንስቲትዩቱ ክትባት ማምረቻ ክፍል ውስጥ ካልሽም ክሎራይድ እና የተለያዩ ባይሎጅካሎች ከ15 ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፣ እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ የተበላሹ ኬሚካሎች ማጠራቀሚያ መጋዘን/ስቶር ውስጥ

ለብዙ ዓመታት ቤቱ አብሮ እስኪዝግ ድረስ የተቀመጡ ኬሚካሎች ያሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

**የአካባቢና የባለሙያ ደህንነት የሚጠብቅ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

123. በኢንስቲትዩቱ የአካባቢና የባለሙያ ደህንነት የሚጠብቅ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

124. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በየክትባት ማምረቻ ክፍሎች ለክትባት ብክለት መከላከያ ለጤና ጠንቅ የሆኑትን ጨረር የሚጠቀሙ ሲሆን የጨረር መጠን በሰው ጤና ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በሚመለከታቸው አካል እንዲረጋገጥ ያላደረጉ መሆኑና በትክክለኛው መንገድ ለመከላከል አስቸጋሪ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም -

- ኢንስቲትዩቱ ለአገሪቱ ብቸኛ የክትባት አምራች ተቋም በመሆኑ የክትባት ማምረቻ ክፍሎች በመልካም አመራረት ዘዴን (GMP) በማደራጀት፣ እና በምርት ሂደትና ከተመረተ በኃላ የሚከሰቱ ብክለትና ብክነትን በመቀነስ የሃገሪቱን ፍላጎት ከማሟሟላት አልፎ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ውጭ ሀገር የሚላከውን የክትባት መጠን በማስፋት ለሃገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ አማካይ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች የክትባት ማሰራጫ ጣቢያዎችን በማዘጋጀት የሚያመርታቸው ክትባቶች ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ በቀላሉ የሚደርስበትን ሁኔታ ሊያመቻችና በማጓጓዝ የሚከሰተውን ብክነት ሊቀነስ ይገባል፡፡
- ቀደም ሲል አሁን ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ዝግጁነትና ሥራ አመራር ኮሚሽን የተባለው በግብርና ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ወቅት በተመረጡ የአገሪቱ አካባቢዎች ቀዝቃዛ መጋዘኖች /Cold Room/ አስገንብቶ ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ ተብለው የተጀመሩትና ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለባቸው 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታቸው ተጀምሮ በአሁኑ ወቅት እየፈራረሱ ያሉና የሶስት ቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታ ያልተጀመረ በመሆኑ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን ያልተጀመሩትም ሆነ በጅምር ላይ ያሉት ተጠናቀው ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ ለታለመላቸውት ዓላማ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህንንም

በማድረግ ኢንስቲትዩቱ እያመረተ ለእንስሳት በሽታ መከላከያነት የሚቀርባቸው የክትባት ምርቶች በተለያየ አካባቢ በማጓጓዝ፣ በአከመቻቸትና አጠቃቀም ጉድለት ምክንያት  በእንስሳት ላይ ጉዳት እያደረሰ በህብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታ የፈጠረበትን ምክንያት በጥናትና ምርምር በመፈተሽ የህብረተሰቡ ችግር ሊፈታ ይገባል፡፡

- ኢንስትቲዩቱ በአገሪቱ ወስጥ ያሉትን የእንስሳት በሽታ በጥናት በመለየት የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የመከላከያ ክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጊዜ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የበሽታ ስርጭት እንዲቀንስ በማድረግ የእንስሳት ሀብት ለአገሪቱ የግብርና ኢኮኖሚ የበኩሉን አስተዋጽኦ ኢንዲያበረክት ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የእብድ ውሻ በሽታ ከሰው ጤና አንፃር፣ የአፍታ እና የአባጎረባ (Black Leg) ክትባቶች ዋጋቸው የህብረተሰቡን አቅም ያገናዘበ እንዲሆን ለማድረግ ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር አማራጭ መፍትሔዎችና አጥንቶ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የክትባት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀትና ለተጠቃሚው ደንበኞች በማሰራጨት በየክልሉ፣ በየዞንና ወረዳ ተበላሽተው የተቀመጡ የክትባት ምርቶች እንዲወገዱ ሊያደርግና ወደፊትም ክትባቶቹ ሳይበላሹ ሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መፍትሔ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- ለአገሪቱም ሆነ ለኢንስቲትዩቱ ትልቁ ሀብት የሰው ኃይል በመሆኑ በየማምረቻ ክፍሎቹ ለብክለት መከላከያ የሚጠቀሙት ጨረር መጠን ምን ያህል እንደሆነ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲረጋገጥ በማድረግ ሠራተኞቹን ከአደጋ የሚከላከልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

በማለት የማሻሻያ ሃሳብ አቅርበናል፡፡

## 10.በኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቁርኘት ፐሮግራም፤ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አፈፃፀም በተመለከተ

➢ **የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸው አምራቾች የሚመረጡበትን መስፈርት በተመለከተ፡**

125. የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸው አምራቾች የሚመረጡበት የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅና በሚመለከተው አካል ሊፀድቅ እንዲሁም አምራቾች በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ሊመረጡ ይገባል፡፡

126. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የቁርኝት ፕሮግራም ግብዓት ሽግግር የሚተገበርባቸውን አምራቾች ለመምረጥ የሚያስችል የተዘጋጀ መስፈርት አለመኖሩን እና በኢንስቲትዩቱ ለቁርኝት ግብአት ሽግግር ተብለው የተመረጡ ምንም አይነት ኢንዱስትሪዎች የሌሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ **የቁርኝት ፕሮግራም ግብአትን በመጠቀም የዘርፉን አምራቾች ክፍተት በመለየት እቅድ አዘጋጅቶ ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤**

127. ኢንስቲትዩቱ ለቁርኝት ፕሮግራም ግብአት ሽግግር እቅድ በመያዝ የአምራቾችን ክፍተት በመለየት በክፍተቱ መሰረት ሊደግፍ፤ የማረጋገጫ ዝርዝር አዘጋጅቶ ሊከታተልና ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

128. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ ለፋብሪካዎች የሚያደርገው ድጋፍ፣ ግብረ መልስ መስጠት ላይ፣ ዕቅድ ክንውን በትክክል አዘጋጅቶ መላክ ላይ፤ የክትትል ስልቱ ተከታታይነት መኖሩ ላይ ክፍተት መኖሩን፤ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ መስራት የሚገባውን ያልሰራ መሆኑን፤ በተለይ ከግብይት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ፋብሪካዎች ላይ ያለውን ችግር ለይቶ ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ ላይ የትኩረት ማነስ መኖሩን እና ምርትና ምርታማነትን ለመደገፍ ክፍተት ያልተለየ መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ **በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ስላለው ግንኙነትና ትስስር በተመለከተ፡-**

129. ኢንስቲትዩቱ በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት (በዘርፉ የሰው ኃይል በሚያፈሩ፣ በዘርፉ ጥናትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያደርጉ) ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር ሊያሳድግ ይገባል፡፡ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ሊሰራና በጋራ የምርምር ሥራዎችን ሊያካሄድ፤ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና

ተቋማት አስልጣኞችን ሊያስለጥን፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ ሊሰራና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ሊያደርግ ይገባል፡፡

130. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት (በዘርፉ የሰው ኃይል በሚያፈሩ፣ በዘርፉ ጥናትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያደርጉ) ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር የማሳደግ ሥራ ክፍተቶች እንዳሉበት ታውቋል፡፡

➢ **የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤**

131. ኢንስቲትዩቱ የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ ሊደግፋቸው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ በመተንበይ የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ መደረግ እንዳለበት (Forcasting the global market dynamics and preparing the Ethiopian Apparel sector to meet the changing reqourments.) ኢኒስቲትዩቱ በናሽናል ኢንስቲትዩት ኦፍ ፋሽን ቴክኖሎጂ የቁርኝት አጋር ጋር በገባው የስምምነት ሰነድ ላይ ቢቀምጠም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ ፋብሪካዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በኢንስቲትዩቱ የተሰራና ሥራ ላይ የዋለ የገበያ ትንበያ ስለመኖሩ የማያውቁና የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉም የተደረገላቸው ድጋፍ የሌለ መሆኑ፡ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም

- ኢኒስቲትዩቱ ለወደፊቱ የቁርኝት ፕሮግራም ከመተግበሩ አስቀድሞ ፕሮግራሙ ከመከናወኑ በፊት በዘርፉም ሆነ በኢኒስቲትዩቱ በቁርኝት ፕሮግራም መሞላት ያለበት ክፍተትና ችግር መኖሩን የሚሳይ ጥናት ሊያከናውን እንዲሁም ፕሮግራሙ በአገር ውስጥ ባለ አቅም ሊሸፈን አለመቻሉ ሊያረጋገጥ እንደሚገባ፣
- ኢንስቲትዩቱ ከቁርኝት ፕሮግራም የሚገኘውን እውቀት ወደ ፋብሪካዎች በሚፈለገው ደረጃ ለማሸጋገር እና እንደየክፍተታቸውና የሙያ መስክ አንፃር ድጋፍ እንዲያገኙ የእውቀት ሽግግር ንድፈ ሀሳብ ወይም እቅድ ማዘጋጀት እንደሚኖርበት፣

- ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ ያሉት የትምህርት ተቋማት በዘርፉ የሚያፈሩት የሰው ሀይል ተግባር ተኮር እውቀት የተላበሱ እንዲሆኑ እና ፋብሪካዎችም ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል ማግኘት እንዲችሉ በዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር ማሳደግ እንዳበት፣
- ኢንስቲትዩቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞችን ማሰልጠን፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ መስራትና በሚሰጧቸው ትምህርትና ስልጠናዎች ላይ ትብብር ማድረግ እንዳለበት፤
- ኢንስቲትዩቱ የአለም አቀፍ የወደፊት የገበያ ሁኔታ ትንበያ መስራትና የኢትዮጵያ የልብስ አምራቾች የገበያውን የልዩነት መስፈርት እንዲያሟሉ ድጋፍ ማድረግ አለበት፤ ኢንስቲትዩቱ ከቁርኘት አጋሩ (ICT) ጋር በገባው ውል መሰረት የውሉ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት በአመራር፣ በቴክኒካል እና በሙያ ደረጃ ላይ ያለውን የሰው ሀብት ልዩ ስልጠና መስጠት፣ በማደግ ላይ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች መደገፍ፣ ክትትል ማድረግና ሁኔታዎችን ማመቻቸት አንዳለበት፤

የማሻሻያ ሃሳብ ሰጥተናል፡፡

## 11.የመንግሥት ቢሮዎች ሕንጻ ግንባታ ኘሮጀክት ጽ/ቤት ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ህንፃዎች ለሚያከናውነው የኔትዎርክ መሰረት ልማት ዝርጋታዎች የአፈፃፀም መመሪያዎች አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

132. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ የኔትወርክ መሰረተ ልማት ዝርጋትን በተመለከተ የሥራ ተቋራጭ እና የአማካሪ ግዥን ለማከናወን በገንዘብ ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ /Standard Bidding Document (SBD)/ ቢጠቀምም ቀሪ ሥራዎችን ለማከናወን(የክትትል ሥርዓቱ እንዴት መከናወን እንዳለበት፣ የጽ/ቤቱ ሚና እስከ ምን ድረስ መሆን እንዳለበት፣ አማካሪ እና ሥራ ተቋራጭ ጋር ያለው ግንኙነት እና ግንባታ የሚከናወንላቸው የመንግስት መ/ቤቶችም ሆኑ የተለያዩ ቤቶች የመጨረሻ ተጠቃሚ እንደመሆናቸው መጠን የነሱ ሃላፊነትና ትብብር ምን መምሰል እንዳለበት…..) የሚገልፅ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ የለውም፡፡

**ጽ/ቤቱ የፌዴራል መንግስት ተቋማት የኔትዎርክ ሥራ ዲዛይን ከመሰራቱ በፊት የኔትዎርክ መሰረተ ልማት ፍላጎታቸውን ሊያጠና ይገባል፡፡**

133. ይሁን እንጂ ኘሮጀክት ጽ/ቤቱ የኔትወርክ ሥራ ዲዛይን ከመሠራቱ በፊትም ሆነ በሥራ ሂደት ላይ የተጠቃሚ መ/ቤቶችን ፍላጎትና ተስማሚነት አስመልክቶ የፍላጎት ጥናት አለመደረጉ፣ /የጥናት መረጃው አለመቅረቡ/ ታውቋል፡፡

**ጽ/ቤቱ ግዥ ከመፈፀሙ በፊት ስለሚገዛው እቃ ሆነ አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ (Specification) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡**

134. ይሁን እንጂ በጽ/ቤቱ የኔትወርክ እቃዎች ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ሲዘጋጅ የግዥ ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 29 ቁጥር 3/ሀ መሰረት ጠቀሜታን (ማለትም ጥንካሬውን በተመለከተ Signal strength በምን ያህል ፍጥነት መሆን አለበት፣ ዳታ ማስተላለፉን /data transmition/ ምን ያህል ሜጋ ባይት መሆን እንዳለበት፣ የመረጃ መጠላለፉ /Cross-talk/ ምን ያህል መሆን አለበት፣ UTP ሙሉ ወይም ግማሽ ኮፐር/full or half copper/ እና Signal noise Ratio (SNR) ምን ያህል መሆን አለበት) መሰረት አድርጐ አለመሆኑ፤

- በተጨማሪም የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 16.5/ሠ “የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነ አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ማመልከት የለበትም ሆኖም ፍላጎትን በትክክል ሊገልጽ የሚችል መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ግዥው ለተለየ ኘላንት ወይም መሣሪያ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን የሚመለከት ሲሆን ወይም የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችል አንድ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ የአምራቹን ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ስም በመጥቀስ ወይም ተመሳሳይ የሚል ሀረግ እንዲታከል ማድረግ” የሚቻል ስለመሆኑ የሚገልፅ ቢሆንም የኔትወርክ እቃዎችን በተመለከተ የተለያዩ አምራች ድርጅቶችና አቅራቢዎች ማግኘት የሚቻልና ፍላጎትን ከላይ በተገለጸው መሰረት ለመግለጽም አስቸጋሪ ያልሆነ በመሆኑ መ/ቤቱ ከመመሪያው ውጭ በ2006 ዓ.ም. ግዥ የውለታ ሰነድ ላይ እና በ2007 ዓ.ም የኔትወርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ግዥ የጨረታ ሆነ የውለታ ሰነድ ላይ ኤክሴል/Excel/፣ ሊግራንድ/Legrand/ እና ትሪያክስ/TRIAX/ ወይም ተመሳሳይ የሆነ በሚል የተዘጋጀ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

## ጽ/ቤቱ የአማካሪና የሥራ ተቀ̀ራጭ ግዥ የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡

135. ሆኖም በግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መሆኑን ኦዲት ሲደረግ ኅሮኔት ኢንተርናሽናል ሰርቪስና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ የተባለው ተቋራጭ በ2006 ዓ.ም. ለአራት መ/ቤቶች (የኢትዮጵያገቢ.ዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ህንፃ C እና D በብር 12,107,580.00፣ የኢትዮጵያ ኅሬስ ድርጅት በብር 5,641,890.00፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በብር11,084,179.00፣ እና ለማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ህንፃ ቁጥር 1 እና 2 በብር 5,641,890.00 ቫትን ጨምሮ በድምሩ በብር 39,646,869.85 በኔትወርክ ዝርጋታ ሥራ ተቋራጭነት ሲሰራ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የጨረታ ሰነድ ተዘጋጅቶና ጨረታ ወጥቶ የተመረጠ ሣይሆን አስቀድሞ በ2001 ዓ.ም. ለአሥር መ/ቤቶች በኔትወርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ የማማከር ሥራ ለመሥራት ከጽ/ቤቱ ጋር ውል ተዋውሎ የነበረ ቢሆንም ወደ ሥራ ተቋራጭነት እንዲዛወር በማድረግ በቁርጥ ነጠላ ዋጋ ሥራው እንዲሰጥ በመወሰን የሥራ ተቋራጭነቱን ሥራ እንዲሰራ መደረጉ፡

- በሌላ በኩል ኅሮኔት ከላይ በተገለፀው መንገድ ወደ ሥራ ተቋራጭነት ሲገባ ኤም.ኤች ኢንጅነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ደግሞ ኅሮኔት ኢንተርናሽናል ሰርቪስና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሚሠረው የኔትወርክ ዝርጋታ ሥራ ለማማከር ምንም ዓይነት ጨረታ ሣይወጣና ውድድር ሣይደረግ በመ/ቤቱ አስቀድሞ ይሰራ በነበረው የግንባታ ሥራ ላይ የኔትወርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ውል ተቀፅላ (amandment) በማዘጋጀት ለኔትወርክ ዝርጋታውም በቀጥታ ውል የተገባ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

## ጽ/ቤቱ የኔትዎርክ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ለማከናወን የሚፈራረመው ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ የሚወሰን ሊሆን ይገባል፡፡

136. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ለኔትዎርክ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ለሚፈራረመው ዋጋ አስቀድሞ የገበያ ጥናት ያላደረገ እና በግዥ ማንዋሉ ላይ በተጠቀሰው መሰረት በአገር ውስጥ አምራች መኖሩን በተመለከተ ሊገኙ ከሚችሉ ጥቅሞች አንጻር ደሰሳ ጥናት ያልተሰራ መሆኑ፣

- እንዲሁም በ2006 ዓ.ም. ኅሮኔት ኢንተርናሽናል ሰርቪስና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ ማህበር በሥራ ተቋራጭነት ውል ተዋውሎ በተሠራው ሥራ የገበያ ጥናት ስለመደረጉ የቀረበ

ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ሥራ ተቋራጩ ኘሮኔት ባዘጋጀው የእቃዎች ዋጋ ዝርዝር /Bill of Quantity/ መሰረት በማድረግ ወደ ስራ መገባቱ እና የአማካሪ ወይም የሁለተኛ ወገን ማረጋገጫ ሳይኖር ባቀረበው ዋጋ በቀጥታ መስራቱና በዚህ መሰረት ክፍያ መፈፀሙ፤

137. በሌላ መልኩ ኤድናሞል ኤች.ቲ.ኤስ ኃ/የተ/የግል ማህበር በሥራ ተቋራጭነት ሰኔ/2007 ዓ.ም. ተወዳዳሪ በሆነበት ጨረታ፤ ብቸኛ ተወዳዳሪ በመሆን እና በግዥ መመሪያው መሰረት ከገበያ ጥናት ዋጋው የሚያንስ ዋጋ አቅርቧል በሚል በጽ/ቤቱ ቀጣይ የቴክኒክ ግምገማ ሂደት እንዲካሄድ የተደረገ ቢሆንም ኤድናሞል ባቀረበው ዋጋ ላይ ለማነፃፀር "የገበያ ዋጋ ጥናት" ተብሎ በመ/ቤቱ የቀረበው ማስረጃ የተለያዩ ተመሳሳይ አይነትና ጥራት ያላቸውን እቃዎች ዋጋ ለማወዳደርና በገበያ ላይ ስለመኖራቸው ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተጠና ሳይሆን ለተለያዩ የዕቃ አይነቶች የአንድ አይነት ብራንድ ማለትም ኘሮኔት ያቀረበው ኤክሴል/Excel/፣ ሊግራንድ/Legrand/ እና ትሪያክስ/TRIAX/ ዋጋ ዝርዝር መሰረት መሆኑን፤

138. በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሱ እቃዎች አገር ውስጥ ባለመኖራቸውና በገንዘብ ምንዛሪ እጦት ምክንያት ከውጭ ማምጣት ባለመቻሉ የሥራ ተቋራጩ ሊንክ ቤዚክ በተባለ የኔትወርክ ኬብል እንዲሰራ የተደረገ ሲሆን በውሉ ላይ ከተዋዋለው እቃ የዋጋ ልዩነት /ጭማሪ ወይም ቅናሽ/ ስለመኖሩ ማለትም በውሉ ላይ ለተጠቀሱ ብራንዶች የተሰጠው ዋጋ እና ሊንክ ቤዚክ የገበያ ዋጋ እኩል ስለመሆናቸው የገበያ ጥናት ሳይደረግ እና ከውሉ ውጪ እየተሰራ ተገኝቷል፡፡

## ጽ/ቤቱ ተጫራቾች የሚወዳደሩበት የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ግምገማ በግዥ አፈጻጸም መመሪያ ያሉትን መስፈርቶችን የሚያካትት ሊሆን ይገባል፡፡

139. ይሁን እንጂ ኘሮጀክት ጽ/ቤቱ ሰኔ/2007 ዓ.ም ባወጣውና ኤድናሞል ኤች.ቲ.ኤስ ኃ/የተ/የግል ማህበር በሥራ ተቋራጭነት ተወዳዳሪ ሆኖ አሸናፊ በሆነበት ጨረታ ላይ የተደረገው ቴክኒካል ግምገማን ኦዲት ሲደረግ፤

- እንዲሁም "በገበያ ጥናት" በተባለው ላይ እና ኤድናሞል ኤች.ቲ.ኤስ ኃ/የተ/የግል (የሥራ-ተቋራጩ) አቀረበ በተባለው ማነፃፀሪያ ላይ በአይነታቸው 38 የሚደርሱ ተመሳሳይ እቃዎች ዋጋ ከቀረበው "ከገበያ ዋጋ" በላይ ያቀረበባቸው የእቃዎች ዋጋ ያሉ ቢሆንም ኤድናሞል ያቀረበው የፀደቀ መሆኑ፣

- በተጨማሪም ኤድናሞል የኔትወርክ ዝርጋታ ላከናወነላቸው 5ቱ መ/ቤቶች በጽ/ቤቱ የቀረበው የገበያ ዋጋ ጥናት በተባለው መረጃ ላይ ለተመሳሳይ እቃ ተመሳሳይ ነጠላ ዋጋ የቀረበ እና ልዩነት የሌለው ቢሆንም ኤድናሞል ባቀረበው ዋጋ ላይ ግን ለሁለት መ/ቤቶች በተመሳሳይ እቃ የተለያዩ ነጠላ ዋጋ ማቅረቡን፣

140. እንዲሁም በተወዳደረበት ዘርፍ (Specific Construction Experience) ባለፉት ሦስት አመታት በኔትወርክ መሠረተ ልማት ዝርጋታ በተሰራው ሥራ ላይ ልምድ የሚጠይቅ እና አንዱ የመገምገሚያ መስፈርት ቢሆንም በኔትወርክ ዲዛይን ዝርጋታና ትግበራ ሥራዎች ዘርፍ ኤድናሞል የንግድ ፍቃዱን ያወጣው በ30/8/2007 ዓ.ም. በመሆኑና ጨረታው በማስታወቂያ ሰኔ/2007 ዓ.ም. እንደመውጣቱ የአንድ ወር ቆይታ በዘርፉ ልምድ አለው ለማለት የሚያስችል አለመሆኑ፣

141. የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 33.1 በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢነት መመዝገብ ግዴታ መሆኑና በመንግስት ግዥ አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ-ገጽ ለአቅራቢዎች ምዝገባ በተዘጋጀው ክፍል በቅድሚያ ራሱን መመዝገብ እንዳለበት የሚገልጽ ሲሆን የተመዘገበው የኔትወርክ ዝርጋታን በተመለከተ እቃዎች ለማቅረብ በጅምላ አከፋፋይነት እና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በአማካሪነት እንጂ በኔትወርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ የሥራ ተቋራጭነት አለመሆኑ፣

## ጽ/ቤቱ በሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የስራ አፈፃፀም ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላትና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል ጠንካራ የሆነ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ሊተገብር ይገባል::

142. ይሁን እንጂ በጽ/ቤቱ የፕሮጀክትና ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሥራ መዘርዝር ላይ ክፍሉ አግባብነት ያላቸውን የኮንትራት አስተዳደር ውሎች አፈጻጸምን ይከታተላል ቢልም በመ/ቤቱ ኔትወርክ ዝርጋታን መከታተል የሚችል ባለሙያ /የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እውቀት ያለው/ያላት/ የሌለውና ኔትወርክ ሥራውን በተመለከተ በብቃት አለመደራጀቱ፣

**በፌዴራል የመንግስት ህንፃዎች የሚዘረጉ የኔትወርክ ዝርጋታዎች በውሉና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየተፈፀሙ መሆኑን መ/ቤቱ ሊከታተልና አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡**

143. ጽ/ቤቱ የኔትወርክ ዝርጋታዎችን የሚከታተለው በአማካሪ ድርጅቶች ሲሆን ኙሮኔት ኢንተርናሽናል ሰርቪስና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ ማህበር በጨረታ እና በውል ሰነድ ዝግጅትና በውል መፈራረም ሂደት ወቅት የሚሰጥ የማማከር ሥራ ለመሥራት ውል የተፈራረመ ቢሆንም በጽ/ቤቱ የማማከር ሥራውን እንዲሰራ ያልተደረገ ሲሆን በተጨማሪም በትግበራ ወቅት በውሉ መሰረት መፈጸሙን የመከታተል ሥራ ለመሥራት ውል የገባ ቢሆንም ኤድናሞል በዘረጋቸው የኔትወርክ ዝርጋታዎች ላይ የመከታተል ሥራውን ያልሰራ በመሆኑ ያለአማካሪ ክትትልና ድጋፍ ዝርጋታዎች እንዲከናወኑ መሆናቸው፣

144. እንዲሁም ኙሮኔት /በሥራ-ተቋራጭነት/ በመስከረም ወር 2006 ዓ.ም. ለአራት መ/ቤቶች (የኢትዮጵያ ኘሬስ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና የማእከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ)የኔትወርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ፓሲቭ ሥራ በሦስት ወር ለመጨረስ ውል የተዋዋለ ቢሆንም፡-ማእከላዊ ስታትስቲክስ ቁጥር 2 የኔትወርክ ሥራ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከዳታ ሴንተር ጋር የማገናኘት ሥራው እስከ ህዳር/2010 ዓ.ም. ያልተጠናቀቁ ወይም በውለታው መሰረት መጠናቀቅ ከነበረበት ከሦስት አመት በላይ የፈጀ መሆኑ እና መንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት በውለታው ላይ ካለው ፓሲቭ ሥራ ውስጥ የብር 2,204,182.00 ሥራ አለመሰራቱ፣

145. ኤድናሞል ኤች.ቲ.ኤስ ኃ/የተ/የግል ማህበር ህዳር 29/2008 ዓ.ም. የኔትወርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ በሥራ-ተቋራጭነት ለመሥራት ውል የተዋዋለና በውሉ መሰረት በሁለት ወር /የካቲት 2008 ዓ.ም./ የኔትወርክ ሥራው ማለቅ ቢኖርበትም እስከ መጋቢት ወር 2008 ዓ.ም. ድረስ ሥራውን አለመጀመሩ እና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ በስተቀር በተቀሩት አራት መ/ቤቶች እስከ 2009 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ከገመድ ጉተታ በስተቀር ሌሎች ሥራዎች አለመሰራታቸው እና በውለታው መሰረት መጠናቀቅ ከነበረበት ጊዜ ከአንድ አመት ከ8ወር በላይ መዘግየቱ፣

**ጽ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮችም ሆኑ አማካሪዎች በውሉ መሰረት አለማከናወናቸውን ሲያረጋግጥ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡**

146. የሥራ-ተቋራጮችም ሆኑ አማካሪዎች በውለታቸው መሠረት ሥራቸውን ያላከናወኑ ቢሆንም በጽ/ቤቱ አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ አለመውሰዱ፣

**የፕሮጌት ኃላፊነቱ የግል ማህበር በአማካሪነት ውሉ ቢቋረጥም መቋረጥ ከነበረበት ጊዜ በጣም ዘግይቶ/ሦስት አመት/ ወይም በወቅቱ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣**

**ጽ/ቤቱ የሥራ ተቋራጩ የሚያቀርበው የኔትዎርክ ዕቃዎች የናሙና ፍተሻ ውጤት ሊያቀርቡ በሚችሉ ተቋማት ፍተሻ እንዲደረግባቸውና ውሉ ላይ ከተቀመጠው ዝርዝር መግለጫ /Specification/ መሰረት መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡**

147. ኤድናሞል የተባለው የሥራ ተቋራጭ ከስፔስፊኬሽኑ ውጭ የሆነ ወይም በውለታው ላይ ከተገለጹ እቃዎች ጋር ተመሳሳይ /equvalent/ መሆኑ ሳይረጋገጥ ሊንክ ቤዚክ/Link basic/ የኔትዎርክ ኬብሎች እና የኖርደን ራኮችን መጠቀሙ፣

**በሌላ መልኩ የተከናወኑ የኔትወርክ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች ደረጃቸውን/ጥራታቸውን የጠበቁ ስለመሆናቸው በኦዲት ሲመረመር፡-**

- የኢትዮጵያ ኘሮድካስት ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ኘሬስ ድርጅት የኤሌክትሪክ፣ የስልክና የዳታ ሴንተር በአንድ ቦታ አንድ ላይ ዝርጋታው መከናወኑ እና ማግኔቲክ ፊልዱ ዳታውን ሊያፋልስ የሚችል መሆኑ፣
- መንገዶች ባለስልጣን የገመድ ዝርጋታው ዝርክርክ (manageable) አለመሆን፣ የዋናው ኔትወርክ ገመድ (Back Bone) የሚተላለፍበት መስመር በTrunk/pipe አለመሆንና ከሲቪል ሥራው ጋር አብሮ በጥራት አለመሰራት፣ የኔትወርክ ገመድ ማስተላለፊያ ቱቦዎች በትክክል በጥራት የተቀመጡ አለመሆንና የዳታ ኬብል ስኬች ከመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ መስመር ጐን ለጐን በመሰራቱ መስመሩ ችግር ቢገጥመው ወደ ዳታ ኬብሉ በቀላሉ መግባት ስለሚችል ኬብሉ ላይ ከፍተኛ ችግር ሊያስከትል መቻሉ፣
- የኘሬስ ድርጅት ለኬብሎች መሄጃ ላደር፣ ለዳታ ሴንተር ፖርቲሽን አለመሰራቱና የፋይበር ሥራው አለመሟላቱ፣
- ማእከላዊ ስታትስቲክስ ቁጥር 1 ወለል ላይ ያለው ሶኬት /ፖወር/ አለመስራቱ፣

- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የማይሰሩ ፍሎር ቦክሶች መኖራቸው፣ ራከር ላይ ያሉት የስልክና የኔትወርክ ገመዶች አንድ ሳጥን/Box/ ላይ የተቀመጡና በቀለምም ሆነ በሳይዝ አንድ በመሆናቸው እና በመወሳሰባቸው ለመጠገን አመቺ አለመሆኑ እና
- መንገዶች ባለስልጣን፣ ማእከላዊ እስታትስቲክስ ቁጥር 2 እና የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ ሲቪል ኮንትራክተሩ የሚያቀርበው ፐቪሲ ጥራት ስለሌለው መደፈኑ፣ በመታጠፋና በመሰበሩ ፋይበር ኬብል የተቀመጠው /Install/ የተደረገው ከዲዛይን ውጭ መሆኑ እና በፕላን መሰረት መዘርጋት አለመቻላቸው፡፡

**በጽ/ቤቱ የኔትዎርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታውን የሚመለከቱ መረጃዎች ማለትም የፍላጐት ጥናት ሰነድ፣ የጨረታ ሰነድ፣ የቅሬታ ሰነዶች፣ የውል ሰነዶች፣ የሥራ አፈፃፀም ሰነዶች፣ የክትትል ሪፖርቶች ….ተደራጅተው ሊያዙ ይገባል፡፡**

148. የመንግሥት ግዥ ማንዋል 2.2.1 የግዥ ሰነዶች በግዥ አፈፃፀም ሂደት ቅደም ተከተል ተደራጅተው መቀመጥ እንዳለባቸውና ማህደሩ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችና ሰነዶች የመንግሥት ግዥ አስተዳደር ኤጀንሲና ሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት በመ/ቤቱ የተከናወነ ግዥ ተአማኒነትና የግዥ ሂደቱን ለመገምገም እንዲያስችል ማህደሩ ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአሥር አመት ሊያዝ እንደሚገባ ቢያዝም፣ ጽ/ቤቱ ከመቋቋሙ በፊት የነበሩ የግዥ ሰነዶች/ከጨረታ ጥሪ ጀምሮ/ ሥራቸው ያላለቁ ወይም በጽ/ቤቱ ቀጣይ የሆኑ ሥራዎችንም ጨምሮ በጽ/ቤቱ አለመኖራቸው፡፡

**ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በኔትወርክ ዝርጋታ ላይ በሥራ ተቋራጮችና በአማካሪዎች እንዲሁም በተጠቃሚ መ/ቤቶች መካከል የሚፈጠሩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የሆነ ቋሚ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት ሊያወያይ ይገባል፡፡**

149. መ/ቤቱ ከተጠቃሚ መ/ቤቶች፣ ከሥራ ተቋራጭ፣ ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር በጋራ የሚወያይበት መደበኛ የሆነ የመወያያ ጊዜ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

## 12.በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት ጥበቃ ስርዓት ብቃትና ውጤታማነት፣

150. የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት ጥበቃ ስርዓት በተመለከተ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መሆኑን ጽ/ቤቱ ሀገሪቱ አባል የሆነችበት አለም አቀፍ ስምምነቶች ስራ ላይ መዋላቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የአለም አቀፉ የአእምሯዊ ንብረት አባል እንደመሆኗ የአእምሯዊ ንብረት አካዳሚ በጽ/ቤቱ መቋቋም የነበረበት ቢሆንም እንዲቋቋም ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ጽ/ቤቱ የቴክኖሎጂ መረጃ ድጋፍ ማዕከል/TISC/ የፓተንት መረጃን በሚጠቀሙ ተቋማት ማለትም በዩኒቨርስቲዎች፣ በምርምር ተቋማት፣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲዎች በመንግስትና በግል ተቋማት ላይ ቴክኖሎጂ በማላመድ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያደርጉ ማዕከሉ እንዲቋቋም ሁኔታዎች ማመቻቸት የነበረበት ቢሆንም በተወሰኑ ተቋማት ላይ ብቻ የተሰራ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ጽ/ቤቱ ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ የፈጠራና መሰል ስራዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ባለሀብቶችን ለማገናኘት የሚረዱ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

151. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ ፈጠራና መሰል ስራዎች ጥቅም ላይ መዋል እንዲቻል ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሹ ባለሀብቶች ጋር ለማገናኘት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለበት በአዋጅ የተሰጠው ሲሆን፣ ነገር ግን የፈጠራ ባለቤቶች ስለሚሰሯቸውን ስራዎች ምዝገባ የሚያከናወን ቢሆንም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ፈቺ የሆኑ ስራዎች እንዲበራከቱና የተሰሩ ስራዎች ወደ ጥቅም እንዲቀየሩ እና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ተገቢውን ዕገዛ እንዲያደርጉ ከባለሀብቶች ጋር ለማገናኘት ሁኔታዎች የማመቻቸት ስራ ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተሰራ አለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ጽ/ቤቱ በህጋዊ ሰነድ ጥበቃ የተደረገላቸው የውጭ እና የሀገር ውስጥ የፈጠራ ስራዎች  በጥቅም ላይ መዋላቸውን ሊከታተልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግዴታ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡**

152. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ በህጋዊ ሰነድ ጥበቃ  የተደረገላቸውን  የውጭ ሀገር እና አገር ውስጥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ  ችግር ፈቺ የሆኑ የፈጠራ ስራዎች  ጥቅም ላይ መዋላቸው  ክትትል የማያደርግ መሆኑን  በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው የፈጠራ ባለቤቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ የፓተንት ባለቤትነት መብት፣ የግልጋሎት ሞዴል መብት፣ የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መብት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው ሕግ መሰረት አስፈላጊውን ምርመራ በማካሄድ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል፡፡**

153. ጽ/ቤቱ ግልጋሎት ሞዴል መብት እና  የኢንዱስትሪያዊ  ንድፍ ባለቤትነት መብት ማመልከቻዎችን በመቀበል በህጉ መሰረት አስፈላጊውን ምርመራ በማካሄድ ተገቢውን ውሳኔ በወቅቱ የማይሰጥና የሚያዘገይበት ሁኔታ መኖሩና  እንዲሁም ከምዝገባ ጋር ተያይዞ  የደንበኞች ቅሬታ መኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው የፈጠራ ባለቤቶች በሰጡት መልስ በጽ/ቤቱ ማመልከቻዎችን በመቀበል ረገድ ብዙ ችግር መኖሩን ይህም የማይመሳሰልን ፈጠራ ይመሳሰላል በማለት ብዙ ጊዜ ምልልስ የተፈጠረ መሆኑ፣ የማይመሳሰል መሆኑን እንዲያስረዱ እና  አዲስ ፈጠራ መሆኑን ከማረጋገጥ ይልቅ ፈጠራው በፓተንት መያዝ የነበረበት ቢሆንም በዩቲሊቲ ሞዴል እንዲመዘገብ የሚደረግ መሆኑን፡ በተጨማሪም ለሚያቀርቡት  ማመልከቻ  በወቅቱ ውሳኔ  የማይሰጥ መሆኑ እና ጉዳዩ  በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በቶሎ ውሳኔ የማይሰጥ መሆኑን፤ ታውቋል፡፡

154. ጽ/ቤቱ ሀገር በቀል የሆኑ ሀብቶች የጂኦግራፊያዊ ምንጭ አመላካች ምርቶች ማለትም በምርቶች ላይ የሚቀርቡ ምልክቶች ሆነው፣  ምልክቶቹ አንድ የተወሰነ አካባቢን በምርቱ ምንጭነት የሚያመለክቱና ጥራትና ዝናን ከቦታው ጋር አስተሳስረው የሚያንፀባርቁና የሚገኙበትን የቦታ ስም ይዘው እንዲመዘገቡ ሊያደርግ የሚያስችል ስርዓትና የህግ ማዕቀፍ  ተግባራዊ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ሀገር በቀል የሆኑ ጂኦግራፊያዊ ምንጭ አመላካች ምርቶች እንዲመዘገቡ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር

በሚፈለገው መልኩ እየሰራ አለመሆኑ፤ እንዲሁም ይህንም ለማስፈጸም የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ የሌለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ጽ/ቤቱ በውጭ ሀገር የሚገኙ የኢትዮጵያ የአእምሮ ውጤት የሆኑ የስነ ፅሁፍ ቅርሶች ማረጋገጥና ወደ ሀገር ለማስመለስ ወይም ቅጂውን ለማግኘት ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ የኢትዮጵያ የብሄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተ መጻህፍት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 179/1999 ተሰጥቶት የነበረው የቅጂና ተዛማጅ መብት የሚመለከት በጽ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 320/1995 በአንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ መብትና ግዴታው የተላለፈለት ሲሆን፤ ነገር ግን ጽ/ቤቱ በውጭ ሀገር ያሉ የኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ ቅርሶች ባለቤትነታቸዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የአዕምሮ ዉጤት በመሆናቸዉ የመብት ማረጋገጥ ሥራ እየተሰራ አለመሆኑ፣ እንዲሁም ወደ ሀገር ለማስመለስ ወይም ቅጂውን ለማግኘት ጥረት የማድረግ ስራ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እየሰራ አለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ጽ/ቤቱ በቅጅና ተዛማጅ መብት ለማስጠበቅ የወጣ አዋጅ 410/1996 የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 827/2007 መሰረት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ባለቤቶች መብታቸውን በጋራ ለማስተዳደር የጋራ መብት አስተዳደር ለማቋቋም እንዲችሉ ሁኔታዎችን ሊያመቻቸት እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

155. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ በአዋጁ የተጠቀሰውን “የዘርፍ ማህበራት” ለሚለው ፍቺ በህጋዊ ሰነድ መሰረት (በአዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ) ያልተረጎመ መሆኑ፤ ነገር ግን ጽ/ቤቱ የዘርፍ ማህበራት የሚለውን ፍቺ የህግ መሰረት በሌለው ሁኔታ በቅጅና ተዛማጅ መብት ላይ ያሉ የዘርፍ ማህበራት አምስት ብቻ እንደሆኑ በመተርጎም ስራ ላይ እንዲውል ማድረጉና በጋራ አስተዳደር ማህበሩ ህጋዊ ሰነድ ማለትም በመመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንብ ላይ ተጠቅሶ የፀደቀ መሆኑ፤

- እንዲሁም በቅጅና ተዛማጅ ባለመብቶች የሆኑት መካከል የቀድሞው የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር ሙዚቃ ብቻውን የጋራ አስተዳደር ማህበርን ለመመስረት ከጽ/ቤቱ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑን ታውቋል፡፡

**ጽ/ቤቱ በቅጅና ተዛማጅ መብት ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 827/2007 የቅጅና ተዛማጅ ባለመብቶች መብቶቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር የጋራ መብት አስተዳደር ለመመስረት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን መሟላታቸውን በማረጋገጥ እውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡**

156. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ የቅጂና ተዛማጅ ባለመብቶች ስራዎቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር የጋራ አስተዳደር ማኅበር ሲመሰርቱ ቅድመ ሁኔታዎ አሟልተው ማህበሩ የተመሰረተና እውቅና የተሰጠ መሆኑ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ታይተዋል፡፡

- የጋራ አስተዳደር ማህበር ስያሜው የኢትዮጵያ የቅጅና መብቶች የጋራ አስተዳደር ለመባል አምስት እና ከዛ በላይ የሆኑ ክልሎችን መወከል እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ስያሜው የተሰጠው መሆኑ፤

- በተመሰረተዉ የጋራ አስተዳደር ማህበር መመስረቻ ጽሁፍ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀፅ 7.1 ላይ የጋራ አስተዳደር የማህበሩ የስራ ክልል ወሰን በዘጠኝ ክልሎች እና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች ላይ እንደሚሰራ የተገለጸ ሲሆን፣ በሙዚቃ ስራ ዙሪያ የተሰማሩት ሙያተኞች ከትግራይ ክልል ዉጭ ሌሎች ክልሎች በመስራችነት እንዲሳተፉ ያልተደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም ጽ/ቤቱ በበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ ፈቃድ ያልተሰጠው ህጋዊ ህልዉና የሌለዉን ማህበር የኢትዮጵያ ድምጻውያን ማህበር በማለት በሰነዱ መካተተቱና ጽ/ቤቱ ለማህበሩ (የኢትዮጵያ የጋራ አስተዳደር ማህበር) እውቅናን በመስጠት ያጸደቀ መሆኑ፤

157. ጽ/ቤቱ በማሻሻያ አዋጁ 872/2006 ለጋራ አሰተዳደሩ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል በአዋጁ ጥበቃ የሚደረግላቸውን እንዲሁም የውጭ ሀገር ጥበቃ ያላቸውን ስራዎች ከሚጠቀሙ ሰዎች ሮያሊቲ መሰብሰብ እና መብት ላላቸው አካላት ማከፋፈል እንደሆነና የተቀመጠ ሲሆን፤ ነገር ግን ሀገሪቱ ይህ ለማስፈጸም የሚያስችሉ አለም አቀፍ ስምምነቶችና ኮንቬንሽኖች ባልተፈራረመችበት ሁኔታ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ በመመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ መግባቱ ከህጉ አፈፃፀሙ የቀደመ እና ተገቢነት የሌለው መሆኑ፤

- በመመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 7.2 እና በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1፣ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 7 እና 9 ላይ የተጠቀሰው " የጋራ አስተዳደር ማኅበሩ በውጪ ሐገር ከሚገኙ ተመሳሳይ አቻ ማህበራት ጋር የእንካ-

ለእንካ ስምምነት(reciprocity) በመፈራረም ሊሰራ ይችላል” በሚል የተቀመጠ መሆኑ፤ ነገር ግን ኢትዮጵያ ይህን ጉዳይ በአለም አቀፍ ኮንቬንሽኖችና ስምምነቶችን ባልተቀበለችበትና ባልፈረመችበት ሁኔታ አስገዳጅ ሁኔታ ሁኔታ ውስጥ ያስገባ መሆኑ ማለትም ሮያሊቲ ክፍያን ከሀገራችን በብር ሰብስበን በውጭ ሀገር ለሚገኙ አቻ ማህበራት በዶላር ለመክፈል ግዴታ የሚያስገባ መሆኑ እና ሀገራችን በአለም አቀፍ ችሎት ላይ ባትከሰስም እንኳ በሀገሪቱ ህግ መሰረት የሚያስከስስና የሚያስጠይቅ አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ ማድረጉ፤

- በጋራ አስተዳደር ማህበር ውስጥ መስራች ሆኖ መግባት የማይችለው “ … አሳታሚዎች/printers/ ማህበር” መስራች ማህበር መሆኑ፤ እንዲሁም በአባልነት የሚገባም እንኳን ከሆነ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የተቋቋመበት አላማ አንዱና ዋነኛው ሮያሊቲ ክፍያን ለማስተዳደር በመሆኑ ይህን መሰረት ያደረገ ከባለመብቶች በውል የተላለፈለት ስምምነት ሳይኖር/ ሳያቀርብ መግባቱ፤

- የኦዲዮ ቪዥዋል አሳታሚዎች ማህበር የተመሰረተው በንግድ ዘርፍ ማህበራት (Chamber of commerce) የተቋቋመ የነጋዴዎች ማህበር እንጂ የአእምሯዊ ንብረት (የቅጅና ተዛማጅ ባለመብቶች) የስራ ዘርፍ ማህበር አለመሆኑ፤

- በተመሰረተዉ የጋራ አስተዳደር ማህበር በመስራችነት ከተመዘገቡት ውስጥ የአላቲዮንስ የፊልም ሰሪዎች ማህበር በኢትዮጵያ በጎ አድራጎት እና ማህበራት ኤጀንሲ ያልተመዘገበና ፍቃድ ያልተሰጠው መሆኑ፤

- ከመስራች አባላት ውስጥ ሶስት ማህበራት ማለትም የኢትዮጵያ ሰአሊያንና ቀራጺያን ማህበር፣ የኢትዮጵያ ፊልም ሰሪዎች አሶሴሽን ማህበር እና የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር ፈቃድ በወቅቱ ያልታደሰ ሲሆን፣ ፈቃዳቸው ባላደሱ ማህበራት ስም እዉቅና የተሰጠና ሰነዱን ያጸደቀ መሆኑ፤

- የአማራ ክልል ሙዚቀኞች ማህበር መስራች አባል ስለመሆኑ በተዘጋጀው የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ሳይፈርም (በፊርማው ማረጋገጫ ሳይሰጥ) ስሙ በጸደቀዉ ሰነድ የተካተተ መሆኑ፣

- የደቡብ ክልል ሙዚቀኞች ማህበር በሚል የተመሰረተ ህጋዊ ማህበር ሳይኖር የደቡብ የሳውዝ ቪዥን የባህል፣ የኪነጥበብ አገልግሎት እና ፕሮሞሽን ማህበርን የደቡብ ክልልን የሚወክል ማህበር እንደሆነ ተደርጎ በሙዚቃ ዘርፍ በመወከል በጋራ አስተዳደር መስራች ውስጥ የተካተተ መሆኑ፤

- በተመሰረተው የጋራ አስተዳደር በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 46 ተ.ቁ 3.3 ላይ አንድ መራጭ መውሰድ የሚችለው ሆነ መሙላት የሚችለው አንድ የምርጫ ቅፅ ብቻ ይሆናል ቢልም በዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ ስነ ስርዓት ላይ አንድ ሰው ሶስት ጊዜ እና ሁለት ጊዜ ድምጽ ሲሰጥ የነበረ መሆኑ፤

- በቅጂና ተዛማጅ አዋጅ 410/1996 እና በማሻሻያ አዋጁ 872/2007 ከተገለፁ ኃላፊነቶች ውጭ የሆነ እና ያልተፈቀደውን በፀደቀው የጋራ አስተዳደር መተዳደሪያ ደንብ ላይ ተግባራዊ እንዲሆን የተቀመጠ መሆኑ ማለትም "መካኒካል ሪፕሮዳክሽን ማለት የድምጽ ሪከርዲንግ፣ የሙዚቃ ሥራ ወይም የኦዲዮቪዥዋል ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲታተም ማድረግን ሳይጨምር በሲዲ፣ በቪሲዲ፣ በቴፕ፣ በካሴት፣ በሚኒዲስክ፣ በዲጂታል ወይም በሌላ በማንኛቸውም ዓይነት ሪከርዲንግ የመቅረፅ፣ ማራባት/ማባዛትና ለሕዝብ ማከፋፈል ማለት ነው" በማለት ተካቶ መገኘቱ፡

- እንዲሁም በቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 872/2007 አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ ከ1-9 የጋራ አስተዳደር ማህበር ስልጣንና ተግባራት ከተገለጸው ውጪ በጋራ አስተተዳደር መተዳደሪያ ደንቡ ክፍል አምስት፣ በአንቀጽ አምስት 40 ላይ የመካኒካል ሪፕሮዳክሽን ሥራዎችን ማህበሩ የማስተዳደር መብት እንዳለው የተገለጸ መሆኑ ታውቋል፡፡

158. ጽ/ቤቱ በህዝብ ዘንድ የአእምሯዊ ንብረት ግንዛቤ ለመፍጠርና ለማጠናከር ሰፊና የተቀናጀ የአህዝቦት ስልት ሊቀይስ እና የፈጠራ ስራዎችም በተለያዩ ሚዲያዎች እንዲተዋወቁ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ በህዝብ ዘንድ የአእምሯዊ ንብረት ግንዛቤ መፍጠር እንዳለበት በአዋጅ የተሰጠው መሰረት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የሚሰራ ቢሆን በስፋትና

ውጤቱ ሊለካ በሚችል መልኩ እያከናወነ አለመሆኑ፣ ጽ/ቤቱ የፓተንት መረጃዎች ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሰጠው ግንዛቤ አነስተኛና የስራዎቹ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን፣ እንዲሁም ስለ አእምሯዊ ንብረት አጠቃላይ ነገር በተደጋጋሚ ለሁሉም ማህበረሰብ አካላት ስልጠና የሚሰጥበት መድረክ የሌለና በህብረተሰቡ ዘንድ ስለ አእምሯዊ ንብረት ግንዛቤ ያልዳበረ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

## 13.በእርሻ እና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር የግብርና ቴክኒክና ሙያና ትምህርትና ስልጠና አፈፃፀም ውጤታማትን በተመለከተ

159. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል እንዲያስችል 5 የግብርና የማሰልጠኛ ማዕከሎች ማለትም ኮሌጆች ከተመሰረቱበት ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ኦዲቱ መጨረሻ ድረስ የህግ ማእቀፍ ተደርጎላቸው እና በአዋጅ፣ በደንብ ወይንም በህግ ተደግፈው እንደገና ህጋዊ መሰረት ይዘው ስለመቃቋማቸው ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

160. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከቴ/ሙ/ት/ስልጠና ኤጀንሲ የዕውቅና ማረጋገጫ ሊኖራቸው እና በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት እየተገመገሙ የእውቅና ፈቃዳቸው ሊታደስ ይገባል፡፡

161. ይሁን እንጂ ትምህርት ሚኒስቴር ለ25 የግ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን አነስተኛ ደረጃ በማሟላታቸው ዕውቅና የተሰጠ መሆኑና በ2000ዓ.ም. እንደ አጠቃላይ የኮሌጆቹ የዕውቅና ፈቃዱ ተገምግሞ ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን አጥጋቢ የደረጃ መለኪያ (Minimum Standard) አሟልቶ በመገኘቱ እድሳት ስለመደረጉ ከሚገልፅ ማስረጃ ውጭ ከ2000ዓ.ም በኋላ የእውቅና ፈቃዱ ስለመታደሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማስረጃ አለመገኘቱ፣ ታውቋል፡፡

162. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኮሌጆች ማሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች ደረጃ ስታንዳርድ ሊኖረውና በስታንዳርዱ መሰረት ሊከታተላቸው (ምዘና) ሊያደርግባቸው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የቴክኒክና ሙያ ትምህረትና ስልጠና ኮሌጆች ማሟላት ከሚገባቸው ደረጃዎች መካከል ያላሟሉት ደረጃዎች ከመኖራቸውም በላይ በተቀመጡት ደረጃዎች (ስታንዳርድ) መሰረት ክትትል(ምዘና) የማይደረግባቸው መሆኑ፡

163. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በግብርና ሙያ ዘርፉ የሚፈልገውን ተተኪ የልማት ሰራተኞችን ለማፍራት የሚረዳ የስልጠና ፍላጎት/Need Assessments/ ሊያሰባስብ፣ በየወቅቱ ለውጦችን ተደራሽ የሚያደርግ ጥናት በማጥናት ስልጠናዎችን ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2007- በ2009 ዓ.ም ሀገራዊ የስልጠና ፍላጎት ያላጠና መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

164. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየወቅቱ ለኮሌጆች የሚያስፈልጉ መምህራንን ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር በስታንዳርዱ መሰረት (የማስተማር ዘዴ (Training Methodology) እና የብቃት ምዘና (COC) የሚያሟሉ) መምህራንን ሊቀጥር ወይም ሊመድብ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2007-2009ዓ.ም ባለው ጊዜ የማስተማር ስነ-ዘዴ (Training Methodology) እና የብቃት ምዘና የማያሟሉ መምህራን ሲቀጥር እና በየኮሌጆች ሲመድብ እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በአላጌ፣በአጋርፋ፣ በአርዳይታ፣ በገዋኔ እና በሚዛን ኮሌጆች ከ2007-2009ዓ.ም ቅጥር የፈፀሙ 40 የመምህራን የግል ማህደር በናሙና ታይቶ 29ኙ የብቃት ምዘና እንዲሁም 40ዎቹ የማስተማር ስነ -ዜዴ ስታንደርድ የማያሟሉ ሲሆን፤ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ምዘናም ሆነ የማስተማር ስነ-ዜዴ ላይ ስልጠና ስለመውሰዳቸው የሚገልፅ ሰርትፍኬት በማህደራቸው ውስጥ ያልተያያዘ መሆኑና በማስተማር ላይ የሚገኙ መሆኑ፤

165. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ኮሌጆች በአላጌ 6፣ በአጋርፋ 35 እና በአርዳይታ 17 መምህራኖች የብቃት ማረጋገጫ የሌላቸው ሲሆን በአጋርፋ 35ና በአርዳይታ 55 መምህራኖች የማስተማር ስነ-ዘዴ ስልጠና ያልወሰዱ መገኘታቸው፣ እንዲሁም የማስተማር ስነ-ዘዴ ስልጠና ወስደዋል ከተባሉት ውስጥ በአላጌ 130፣ በአጋርፋ 90 እና በአርዳይታ 12 መምህራን ሰርትፍኬት የሌላቸው መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

166. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌደራል ግ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች የሰልጣኝ ተማሪዎች ምልመላና ድልደላ የፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ ባወጣው መስፈርት መሰረት በወቅቱ እንዲከናወን ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌደራል ግ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች የሰልጣኝ ተማሪዎች ምልመላና ድልደላ የፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ ባወጣው መስፈርት መሰረት በተሟላ መልኩ ከ2007-2009 ዓ.ም በወቅቱ እንዲከናወን አለማድረጉ፤

167. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ በአርዳይታ ኮሌጅ በ2009 ዓ.ም ከወጣው መግቢያ መስፈርት ውጭ በቁጥር ሰባት(7) የሚሆኑ ተማሪዎችን ተቀብሎ እስከ ደረጃ I እና II ድረስ እንዲሰለጥኑ በመፍቀድ እየተማሩ እንደሚገኙ በተጨማሪም በ2009 ዓ.ም. በአላጌ ግ/ቴ/ሙ/ት/ስ/ኮሌጅ 140 /17 በመቶ/ ሰልጣኞች ከመመሪያ እና መስፈርት ውጭ ለአላጌ መምህራንና ሰራተኞች ልጆች የትምህርት ዕድል የተሰጣቸው መሆኑ፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

168. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጥራት ማስጠበቂያ ቱሎች/መሳሪያዎች/ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትል ሊያደርግባቸው ይገባል፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስርዓተ-ትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የጥራት ማስጠበቂያ ቱሎች በተገቢው ዝግጅት ተግባራዊ ስለመደረጋቸው በተሟላ መልኩ ክትትል እንደማያደርግ እና የተከታተለውንም በተከታተለው መሰረት ድጋፍ እንደማያደርግ ታውቋል፡፡

169. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየኮሌጆቹ የሚሰጠው የመካከለኛ ደረጃ የግብርና ሙያተኞችን 70 በመቶ በተግባር እና 30 በመቶ በንድፈ ሃሳብ በሚሸፍን ስርዓተ ትምህርት/curriculum/ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት እየሰጡ መሆኑን በመከታተል የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

170. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኮሌጁ የሚሰጠው የመካከለኛ ደረጃ የግብርና ሙያተኞችን በንድፈ-ሃሳብ 30 በመቶ እና በተግባር 70 በመቶ በሚሸፍን ስርዓተ-ትምህርት ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት እየሰጡ መሆኑን በመከታተል በተሟላ መልኩ ተግባሪዊ እንዲደረግ አለማድረጉ እና የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰዱ፣

እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በታዩት በአላጌ፣ በአጋርፋና በገዋኔ ኮሌጆች የተግባር ትምህርት የ70፡30 የስልጠና አሰጣጥ ደረጃ በሚያሟላ ሁኔታ አለመሆኑና በሚፈለገው ደረጃ ስልጠናው አለመሰጠቱ ታውቋል፡፡

171. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጡ መምህራንና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተት አስቀድሞ ሊለይና የአቅም

ግንባታ ስራ/ የስፔሻላይዘሽን ፣ አጫጭር የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን በመስጠት/ በመስራት ክፍተቱን ሊያሟላ ይገባል፡፡

172. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የታዩት 3ቱም ኮሌጆች የመምህራን የክህሎት ክፍተት እንዳለባቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱን ጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ቴክኒክና ሙያ የተግባር ስልጠና የሚሰጡ መምህራንና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ያለባቸው የክህሎት ክፍተት አስቀድሞ በመለየትና ስልጠናዎችን በመስጠት ክፍተቱን እንዳላሟላ ለማወቅ ተችሏል፡፡

173. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎችና በኮሌጆች አካባቢ የሚካሄደውን የአርሶ/ አርብቶ አደሮችን፣ ወጣቶችና የገጠር ሴቶች በደረጃና በብቃት አሃዶች የሚሰጠውን ስልጠናና የብቃት ምዘና ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች እና በኮሌጆች አካባቢ የሚካሄደውን የአርሶ/ አርብቶ አደሮችን፣ ወጣቶችና የገጠር ሴቶች የሚሰጠውን ስልጠና በተሟላ መልኩ በስልጠናና በብቃት ምዘና ላይ ክትትልና ድጋፍ አለማድረጉ፣

እንዲሁም በደረጃና በብቃት አሃዶች ተመዝነው ብቃታቸው ተረጋግጦ እንዲወጡ ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አኳያ የተሰራ ስራ አለመኖሩና ሰልጣኞችን ለመመዘን የሚያስችል የምዘና ስርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

174. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከልህቀት ማዕከላት ጋር ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሰልጣኞች በኮሌጆች በታቀደው ጊዜ መሰረት ሀገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና እንዲሰጥ ድጋፍ በማድረግ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰልጣኞች ከልህቀት ማዕከላት የሙያ ብቃት ምዘና ወስደው ብቃታቸው ተረጋግጦ እንዲወጡ ሁኔታዎችን አለማመቻቸቱና አፈፃፀሙን በተሟላ መልኩ አለመከታተሉ እና ድጋፍ አለማድረጉ አለማድረጉ የታወቀ ሲሆን፤ እንዲሁም በኮሌጆች በታቀደው ጊዜ መሰረት ሀገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና እንዲሰጥ ድጋፍ አለማድረጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

175. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኮሌጆች ወጥ የሆነ ስታንደርድ በማውጣት የትምህርት መርጃና የተግባር መለማመጃ መሳሪያዎችንና ሌሎች ማቴሪያሎችን በማዕከል በመግዛት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኮሌጆች ወጥ የሆነ ስታንደርድ በማውጣት የትምህርት መርጃና የተግባር መለማመጃ መሳሪያዎችንና ሌሎች ማቴሪያሎችን በማዕከል በመግዛት የማያሰራጭ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኮሌጆች ለትምህርት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (መፃህፍት፣ ሰርቶ ማሳያዎች፣ ላብራቶሪዎች፣ ቤተ-መፃህፍቶች፣ የተግባር መለማመጃ መሳሪያዎች እና ቦታዎች ወዘተ) በሚፈለገው መጠንና ጥራት እንዲደራጁ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ስለመደረጋቸው በመከታተል ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

177. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኮሌጆች ለትምህርት የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች(መፃህፍት፤ ሰርቶ ማሳያዎች ላብራቶሪዎች፣ ቤተ-መፃህፍቶች፣ የተግባር መለማመጃ መሳሪያዎች እና ቦታዎች ወዘተ) በሚፈለገው መጠንና ጥራት እንዲደራጁ በማድረግ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው በተሟላ መልኩ ተከታትሎ ድጋፍ አለማድረጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

178. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል የግ/ቴ/ሙ/ት/ሥ/ ኮሌጆች ውስጥ ለሚከናወኑ የተለያዩ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራል የግ/ቴ/ሙ/ት/ሥ/ ኮሌጆች ውስጥ ለሚከናወኑ የተለያዩ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው ግልጋሎት እንዲሰጡ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ አለማድረጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

179. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በሶስቱም ኮሌጆች ግንባታቸው መጠናቀቅ ከነበረበት ጊዜ ከ 9 እስከ 18 ወራት የዘገየ መሆኑንና ግንባታውን ለማከናወን ውል ከተገባው ጠቅላላ የግንባታው ወጪ በላይ የተጠቀሙ ስለመሆናቸው የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- ✓ በአጋርፋ በ2005ዓ.ም የተጀመረው መኖሪያ የሆኑ ህንፃ ግንባታ በ18 ወራት መጠናቀቅ ቢኖርበትም እስከ 2009 በጀት ዓመት ድረስ ክንውኑ 35.47% ብቻ ሲሆን፤ በተመሳሳይ በዚሁ ኮሌጅ መኖሪያ ያልሆኑ ህንፃ ግንባታ በ14 ወራት ተጠናቆ ለአገልግሎት ይውላል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም ህንፃው ሳይጠናቀቅ ከውል በላይ ብር 4,331,103.28 ክፍያ የተፈፀ መሆኑና የግንባታ ስራው ከሚፈለገው በላይ እየተጓተተ እስከ 2009ዓ.ም ዓመት ድረስ 61.28% ብቻ ክንውን የደረሰ መሆኑ፣

- ✓ እንዲሁም በአላጌ ኮሌጅ የተገነባው የአስተዳደር ቢሮ ለግንባታው ከተመደበው በጀት በላይ ብር51,813 የወጣ መሆኑ በተጨማሪም የመምህራን መኖሪያ ቤት ግንባታ ለማከናወን ውል ከተገባው ጠቅላላ የግንባታው ወጪ በላይ ብር 527,925.39 የተጠቀሙ መሆናቸው የታወቀ መሆኑና የግንባታ ስራው ከሚፈለገው በላይ የተጓተተ መሆኑና በተመሳሳይም በአርዳይታና በገዋኔ ኮሌጆች ይሄ ችግር እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

180. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራል የግ/ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጆች በተዘጋጀው ስርዓተ-ትምህርት መሰረት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጡ ለማስቻል ወቅቱን የጠበቀ የክትትልና የድጋፍ ግምገማ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራል የግ/ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጆች በተዘጋጀው ስርዓተ-ትምህርት መሰረት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጡ ለማስቻል በተሟላ መልኩ ወቅቱን የጠበቀ የክትትልና የድጋፍ ግምገማ አለማድረጉ የታወቀ መሆኑ ታውቋል፡፡

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየደረጃው ካሉት ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ እንዲሁም በቴ/ሙ/ት/ስልጠና መሰል መስኮች ምርጥ ተሞክሮዎችን የማሰባሰብና የማስፋት ስራዎች እና የትብብር ስልጠና እንዲከናወኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየደረጃው ካሉት አካላት ጋር በሚፈለገው ደረጃ ተቀናጅቶ እየሰራ አለመሆኑ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቴ/ሙ/ት/ስልጠና መሰል መስኮች ምርጥ ተሞክሮዎችን የማሰባሰብና የማስፋት ስራዎች እና የትብብር ስልጠና በተሟላ መልኩ እንዲከናወኑ አለማድረጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

182. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኮሌጆች የምርምርና ስርፀት ስራ እንዲከናወን ሊያበረታታ እና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኮሌጆች የምርምርና ስርፀት ስራ እንዲከናወን የማያበረታታ እና አፈፃፀሙን የማይከታተል መሆኑ፤ ለምሳሌ፡-

- ✓ በጥናትና ምርምር እንዲሁም በልምድ ልውውጦች የሰራተኞችን አቅም ማሳደግ እንዳለበት በ2009ዓ.ም ዕቅድ እንደ አንድ ግብ ቢያስቀምጥም በሁሉም ኮሌጆች የምርምር ስራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የማይሰራ መሆኑ፣
- ✓ በአርዳይታና በአጋርፋ ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የመመረቂያ ፁሁፍ ካልሆነ በስተቀር የምርምርና ስርፀት ስራ እየተከናወነ እንዳልሆነ፤ በዋናነትም

በዚህ ረገድ ግልፅና ወጥነት ያለው መመሪያ የሌለ መሆኑ  እንዲሁም ለዚህም ተብሎ የሚመደብ በጀት እንደሌለ ታውቋል፡፡

183. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየወቅቱ ለአካባቢው ህብረተሰብ የተሸጋገሩ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎች በአይነትና በብዛት ተደራጅተው እንዲቀመጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በየወቅቱ ለአካባቢው ህብረተሰብ ሽግግር የተደረገባቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች በአይነትና በብዛት በማደራጀት ማስረጃዎች የሚያዝበት የመረጃ አያያዝ  ስርዓት አለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

184. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከየተቋማቱ የሚወጡ የተመራቂ ተማሪዎችና ሰልጣኞች  በግብርና ዘርፍ ላይ ያበረከቱን አስተዋጽኦና ያሉበትን ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችል የመረጃ አያያዝ  ስርዓት ሊዘረጋ  እና በግብርና ቴ/ሙ/ት/ስልጠና  ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ያደረገው ፋይዳ፤ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫ ለመፈተሽ ከባለ-ድርሻ አካላት ጋር በመሆን የጥናት ሰነድ /Impact assessment/ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

185. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከየተቋማቱ የሚወጡ የተመራቂ ተማሪዎች በግብርና ዘርፍ ላይ ያበረከቱትን አስተዋጽኦና ያሉበትን ሁኔታ መከታተል የሚያስችል የመረጃ አያያዝ  ስርዓት በመዘርጋት ዙሪያ የሰራው ስራ አለመኖሩ እንዲሁም የግብርና ቴ/ሙ/ት/ስልጠና  ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ያደረገው ፋይዳ፤ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫ ለመፈተሽ ከባለ-ድርሻ አካላት ጋር በመሆን የጥናት ሰነድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

186. እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የሚሰጡት ስልጠናዎች በስልጠናው ትርጉምና ፋይዳ/Impact assessment / እንዲቀመጥ በተደጋጋሚ መነገሩ እንዲሁም **በ2007** ብዙ ስልጠና  ተሰጥቶ በስልጠናው የተገኘው ውጤት  አለመጠናቱ በተጨማሪም በዚሁ በጀት ዓመት ሰልጣኞች ወደ ስራ አለም ከተሰማሩ በኋላ አስተዋጽአቸው በሚፈለገው ደረጃ ስለመሆኑ የዳሰሳ ጥናት አለመካሄዱ ችግር ከመነሳት ውጭ ምንም ዓይነት ጥናት አለመደረጉ ታውቋል፡፡

187. ሚኒስቴር መ/ቤቱ  የግብርና ትምህርትና የስልጠና ስርዓት በአጠቃላይ ከግብርና ምርታማነት ስርዓት ጋር በየጊዜው እየተገመገመ ማሻሻያ ሊያደርግ ይገባል፡፡
ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2007-2009ዓ.ም የግብርና ትምህርትና የስልጠና ስርዓት በአጠቃላይ ከግብርና ምርታማነት ስርዓት ጋር በየጊዜው ያለውን ስራ እና ክፍተትን በመገምገም ዙሪያ የተሰራ ስራ አለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 14.በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የመንገድ ትራፊክ ደህንነት አፈፃፀም

188. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት የመንገድ ትራፊክ ደህንነት አፈጻጸም ውጤት በሚያመጣ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑ፣ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ከክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች፣ ከአሽከርከሪ ብቃት ማረጋገጫ ማሠልጠኛና ከተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተቋማት፣ ከቅርንጫፍ የትራንስፖርት ቢሮዎች፣ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ውጤታማ የሆነ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በሰውና ንብረት ላይ የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ በመቀነስ ላይ ለውጥ የሚያመጣ ሥራዎችን ማከናወኑን በመገምገም በአግባቡ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት በሚመለከተው የመንግሥት አካል ትኩረት እንዲሰጠው በማድረግ እና ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡ከዚህ ዓላማ አንፃር የአሰራር ስርዓቱ አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ የኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች እና በኦዲቱ የተገኙት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡እነርሱም፡-

189. የፌዴራል የትራንስፖርት ባለሥልጣን የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን አስመልክቶ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው በመገምገም መሻሻል የሚያስፈልጉትን በመለየት እንዲሻሻሉ ሊደረግ፤ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ፖሊሲ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል በማድረግ ተግባራዊ መሆናቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዙሪያ የወጡ ህጐች፣ ደንቦች አሁን ካለው የከተሞች ዕድገት ከዘመናዊ ተሽከርካሪዎች ብዛትና ለውጥ ከመንገዶች ከመስፋፋት ሁኔታ ጋር ተገናዝበው ረጅም እድሜ ያስቆጠሩትን ወቅታዊ እንዲሆኑ እንዲሁም ያልወጡ ህጐችና ፖሊሲ እንዲወጡ ማድረግን በተመለከተ በቆዩ ህጐች ላይ ማሻሻያ ቢደረግላቸውም ፀድቀው ሥራ ላይ ያልዋሉ መሆኑ፡
- እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦችን አዘጋጅቶ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ቢቀርብም ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ ታውቋል፡፡

190. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማስጠበቅ ማንኛውንም የመንገድ ምልክትና ማመላከቻ እንዲተከል፣ የተተከለው እንዳይነሳ፣ እንዳይበላሽ፣ ከቆመበት እንዳይዛወር፣ እንዳይለወጥ ወይም በማናቸውም አኳኋን በግልጽ እንዲታይ ወይም እንዲነበብ በህግ ኃላፊነት በተሰጣቸው ፈፃሚ አካላት ተግባራዊ መደረጉን በየወቅቱ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የመንገድ ምልክትና ማመላከቻዎችን ጥበቃና ክትትል በተመለከተ የሚከተሉት ታይተዋል፡-

191. በአማራ ክልል ውስጥ ከሚገኙ 200 አደገኛ ቦታዎች ውስጥ ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ የሚከሰትባቸው ቦታዎች መካከል፤ ለምሳሌ ከደብረ ማርቆስ ኮሶበር፣ ከኮሶበር ባህርዳር፣ ከደሴ አጣየ፣ ከደብረማርቆስ ደጀን፣ ከአጣየ አዲስ አበባ እንዲሁም ከአዲስ አበባ አፋር ለሚደርሰው አደጋ ዋና መንስኤ የመንገድ ዳር ምልክትና ማመልከቻ ያልተተከለባቸው መሆኑ፣

- ከአዲስ አበባ 300 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ በሚገኙት የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በሚገኙ ከተሞች፣ በአፋር ክልል በሚገኙ አጐራባች ከተሞች እና በደቡብ ክልል በሚገኙ የጉራጌ ዞን፣ የስልጤ ዞን እና የሀድያ ዞን በሚገኙ መንገዶች ላይ ከፍተኛ አደጋ የሚከሰትባቸው መንገዶች ሲሆኑ ለአደጋው መከሰት አንዱ ምክንያት በተሟላ ሁኔታ የመንገድ ዳር ምልክት ባለመተከሉ መሆኑ፣
- ከአዲስ አበባ በ5ቱ መውጫዎች 22 በጣም አደገኛ ቦታዎች በተለይም በፊንፊኔ ዙሪያ የሚኙ እጅግ አደገኛ 10 ቦታዎች መሆናቸውን የመለየት ሥራ ቢሠራም የትራፊክ ምልክትና የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያ አለመተከሉ፣
- ከአለም ገና አዋሽ ከሱሉልታ እስከ ሰሜን ሸዋ ጫንጮ እንዲሁም ሰንዳፋ ያሉት መንገዶች ላይ የተተከሉ የመንገድ ዳር ምልክቶች ወድቀው ያልተተከሉ መሆኑን፣
- በደቡብ ክልል ከተሞችን አቋርጠው የሚያልፉ በተለያዩ ደረጃዎች የተገነቡ መንገዶች ከሚሰጡት ዘርፈ ብዙ ጥቅም ባሻገር በየጊዜው ከፍተኛ የህይወትና የንብረት ውድመት እየደረሰ የመሆኑ ምክንያት መንገዶች ተገንብተው ለትራፊክ ክፍት ከመሆኑ በፊት ተገቢው የመንገድ ላይ ቅብና የመንገድ ዳር ምልክቶች በትክክል መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሥራ ያልተሰራ መሆኑ፣

- ከአርባ ምንጭ ሳውላ፣ ከሳውላ መሎ፣ ከመሎ ማጂ እየተሠራ ያለው መንገድ በ2003 ዓ/ም ተጀምሮ እስከ አሁን ያልተጠናቀቀ ቢሆንም ምልክት ሳይተከል ለትራፊክ ክፍት በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ፣ እንዲሁም ከአርባ ምንጭ ቦንኬ ያለው የፌደራል መንገድ ግንባታው ተጠናቆ ሙሉ አገልግሎት እየሠጠ ቢሆንም ምልክት ስላለመተከሉ ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን እና ከክልሎች ጋር ባላቸው የመድረክ ግንኙነት ቢነሳም ችግሩ አለመቀረፉን፤

- እንዲሁም በጎንደር 543.5 ኪሎ ሜትር ፣ በኮምቦልቻ 653.5ኪሎ ሜትር፣ በአዲግራት 1,867 ኪሎ ሜትር ፣ በአለምገና 1,097ኪሎ ሜትር ፣ በደበረማርቆስ 491ኪሎ ሜትር፣ በነቀምት 1,258ኪሎ ሜትር ፣ በሻሸማኔ 1,175 ኪሎ ሜትር፣ በሶዶ 1,228ኪሎ ሜትር ፣ በጅማ 1,823 ኪሎ ሜትር፣ በጠቅላላው በዘጠኙም ዲስትሪክቶች 11,436 ኪሎ ሜትር የሚሸፍኑ የመንገድ ምልክቶች የሌላቸው መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ከከለሳቸው ማስረዳዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

192. **ባለሥልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም ሰው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ማናቸውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ እንዳያሽከረክር እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በአሻራ የተደገፈ የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡**

193. ይሁን እንጂ አሽከርካሪዎች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረት ስለማሽከርከራቸው እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በአሻራ የተደገፈ የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ስለመዘርጋቱ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- በሶማሌ ክልል በጅጅጋ ከተማ በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥና አሠራር አዋጅ ቁጥር 600/2000 ላይ ከተጠቀሰው ውጪ በክልሉ ኘሬዝዳንት ትዕዛዝና በማናጅመንት ውሳኔ ለ120 ልዩ ፖሊስ መሰጠቱ፣

- በጅጅጋ የሚኖሩ 1,253 የህብረተሰብ ክፍሎች ህገ ወጥ የመንጃ ፈቃድ ይዘው የተገኙ ሲሆን ባለሥልጣን መ/ቤቱም የማጣራት ሥራ ሰርቶ ከፖሊስ አባላት 41 ህገወጥ መንጃ ፈቃድ፣ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች 138 ህገወጥ መንጃ ፈቃድ፤ በጠቅላላው 179 ህገወጥ የመንጃ ፈቃድ የተመለሰ ቢሆንም ቀሪዎቹ 1,074 ህገወጥ መንጃ ፈቃዶች ያልተመለሰ መሆኑ፣

- ባለሠልጣን መ/ቤቱ አንድ መንጃ ፈቃድ ቁጥር ለ2 እና ለ3 የተለያዩ ሰዎች የተሰጠ መሆኑ በግምገማ ያገኘ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- የውጭ ሀገር መንጃ ፈቃድ ይዘው በሀገር ውስጥ ያለምንም ማረጋገጫ የመንጃ ፈቃድ እንዲቀየርላቸው ጠይቀው የተቀየረላቸው አሽከርካሪዎች መኖራቸው እንዲሁም እርምጃ ስለመወሰዱ የሚያመለክት ማስረጃ አለመኖሩ፣
- ከተለያዩ የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት የአሽከርካሪ ፈቃድ ተሰጥተው ወደ ፌደራል መንጃ ፈቃድ የተቀየሩ በቀን 22/08/2007 40 የመንጃ ፈቃድ እንዲሁም በቀን 02/06/2008 43 በጠቅላላው 83 ፎርጅድ የመንጃ ፈቃዶች ለዕድሳት ወደ ባለሥልጣኑ ሲመጡ መንጃ ፈቃዳቸው በፎርጀሪነት ቢያዝም አሽከርካሪዎችን ወደ ህግ አቅርቦ እርምጃ ስለመወሰዱ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አለማቅረቡ፣
- በሀገሪቷ ያሉ ክልሎች የራሳቸውን የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ህግ በማውጣት አንዱ ክልል ከሌላው ክልል ጋር የመናበብ ሁኔታ ባለመኖሩ በአጥፊ አሽከርካሪያዎች ላይ ቅጣት ለመጣል እና በትራንስፖርት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ መገኘቱ፣
- በሲዳማ ዞን ህገወጥ የመንጃ ፈቃድ የሚያትሙ 42 አታሚዎችን ከነማሽኑ የተያዙ ቢሆንም በህግ ስለመጠየቃቸው የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣ ታውቋል፡፡

**ባለሥልጣን መቤቱ የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማትና የአሽከርካሪነት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጪ አካላት በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ህጐችን አክብረው መሥራታቸውን ድጋፍ በማደረግ ሊከታተል ይገባል፡፡**

194. የትራንስፖርት ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሠራር መመሪያ 01/2007 በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆን ያደረገ ቢሆንም በዚህ መመሪያ አተገባበር ላይ በተሟላ መልኩ ክትትልና ቁጥጥር ባለመድረጉ የታዩ ችግሮች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡
    - የተግባር ፈተና ሠዓት እንደ ተሽከርካሪዎች ዓይነት ወደ 60 ፣ 75 እና በ90 ደቂቃ የተሻሻለ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ፣
    - ለንድፈ ሃሣብ ፈተና ሰዓት ከ50 ወደ 60 ደቂቃ የተሻሻለ ቢሆንም በዚሁ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ፣

- በሁሉም ተቋማት በኮምፒዩተር መጫን ያለበት 3000 የፈተና ጥያቄ ተግባራዊ አለመሆኑ፣
- ለሁሉም ምድቦች የተግባር መፈተኛ መስመር መነሻ እና መደረሻ ፤ የመንገድ ዳር ምልክቶች የመንገድ ላይ ቅቦች፤ አደባባይ፤ የትራፊክ መብራቶች ያለው መፈተኛ ቦታ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- አብዛኞቹ ማሠልጠኛ ተቋማት ለሥልጠና የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች በሌላ አገልግሎት አቅማቸውን የጨረሱና የቴክኒክ ብቃታቸው ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ለማሰልጠኛ ተብለው የተዘጋጁ ኮምፒዩተሮች ደረጃቸውን የጠበቁና ለሥልጠና በቂ አለመሆናቸው፣
- የማሰልጠኛ ተቋማት ዕድሜያቸው ለምድቡ የማይመጥን ሠልጣኞችን ተቀብለው የሚያሰለጥኑ መሆኑ፣
- በማሰልጠኛ ተቋማቱ የተዘጋጁ የመመሪያ ክፍሎች ደረጃውን ያልጠበቁና ለመማር ማስተማር የማይመቹ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን የሚያስተዳደረው የቃሊቲ አሽከርካሪ ማሰልጠኛ ማዕከል በማዕከሉ የሚመጡ በርካታ የተግባር ተፈታኞች ማስተናገድ እንዲቻል የትራፊክ ኮምኘሌክስ ማስፋፊያ ለመሥራት አለመቻል እና በኮምኘሌክሱ መሟላት ያለባቸው /የመንገድ ላይ ቅብ፣ ካሜራ፣ የመንገድ ላይ ምልክት….ወዘተ/ አለመሟላት እንዲሁም የማዕከሉ የግቢ አጥር ክፍት በመሆኑ ሠልጣኞች ክፍት በሆነው አጥር በኩል የሚፈተንላቸው ሌላ ተፈታኝ በማስገባት የማጭበርበር ሥራ የሚሠራ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

**ባለሥልጣን መቤቱ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተቋማት በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ህጐችን አክብረው መሥራታቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡**

195. በሀገሪቷ የሚገኙ አንድ አንድ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ የአሠራር መመሪያና በዓመታዊ የተሽከርካሪዎች ቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ በዘመናዊ የመመርመሪያ መሣሪያ ለማስተግበር በወጣው የአሠራር ማንዋል ቁጥር 01/2004 መሠረት ተግባራዊ ባለማድረጋቸው የተስተዋሉ ችግሮች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፣-

- አንዳንድ የምርመራ ተቋማት ተሽከርካሪው በአካል ሳይቀርብ በካሜራ በማንሳትና ሠሌዳውን ፎቶ ኮፒ በማድረግ ተሽከርካሪው ብቁ እንደሆኑ ተደርጐ ቦሎ እንዲሰጣቸው የማስደረግ ሁኔታ መኖሩ፤

- በምርመራ ወቅት በቼክ ሊስቱ በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ምርመራው ስለመደረጉ ሳይሟላ እና ሳይረጋገጥ ምርመራው ስለመካሄዱ በፎርማ የሚረጋገጥ መሆኑ፣

- በቼክ ሊስቱ ላይ መሞላት ያለበት የተሽከርካሪው ዓይነትና የተፈቀደለት የጭነት መጠን ሳይሞላ የምርመራ ማረጋገጫው የሚፈረም መሆኑ፣

- ምርመራ የተከናወነበት ቦታና ምርመራ የተደረገበት ቀን እንዲሁም የአሽከርከሪው ስም ሳይጠቀስ የምርመራ ማረጋገጫው የሚሰጥ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

196. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንገዶች የሚጠቀሙ ባለሁለት እግር ሞተር ሳይክሎች ከሚሰጡት አገልግሎት አይነት ሊኖራቸው የሚገባው የደህንነት መሳሪያዎች፣ የተሳፋሪ ብዛትና የጭነት ክብደትና ወሰን እንዲሁም በመንገዶች ስለሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች አመዘጋገብና ቁጥጥርን አስመልክቶ የወጣው መመሪያ በትክክል መተግበሩን ሊከታተል ይገባል፡፡

197. ይሁን እንጂ በመንገዶች የሚጠቀሙ ባለሁለት እግር ሞተር ሳይክሎች ከሚሰጡት አገልግሎት አይነት ሊኖራቸው የሚገባው የደህንነት መሳሪያዎች፣ የተሳፋሪ ብዛትና የጭነት ክብደትና ወሰን እንዲሁም በመንገዶች ስለሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች አመዘጋገብና ቁጥጥር መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ባለመደረጉ ታውቋል፡፡

198. በተጨማሪም በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገር የገቡ ባለሁለት እግር ተሽከርካሪዎች /ሞተር ሳይክል/ ሳይመዘገቡና ሰሌዳ ሳይለጥፉ በመንግስትና በግለሰብ ባለቤትነት በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፣ ለምሳሌ፡-

    - በደቡብ ክልል 109,345 እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል 25,000 በጠቅላላው 134,345 ባለሁለት እግር ተሽከርካሪዎች /ሞተር ሳይክሎች/ ተመዝግበው ሠሌዳ ሳይሰጣቸው በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው፤

    - በደቡብ ክልል የሞተሮቹ ባለቤቶች ያስገቧቸውን ሞተር ሳይክሎች ህጋዊ ምዝገባ ሳይደረግላቸውና ሠሌዳ ሳይኖራቸው እንዲሁም የአሽከርካሪነት ስልጠና ሳይወስዱ

ከ2-5 ሰው እና መጠኑ ከአንድ ኩንታል በላይ የሚገመት ዕቃ በመጫን በክልሉ ባሉ ወረዳዎችና ዞኖች በመንቀሳቀስ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ሲሆን በክልሉ ባሉ መንገዶች ላይ በሚገኙ የትራፊክ ፖሊሶችም እንደማይጠየቁ፤ ታውቋል።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቁጥር 208/2003 ለመንገድ ደህንነት ትራፊክ አደጋ ተገላጭ በሆኑትና በጥናት በተረጋገጡ ሁሉም ተሽከርካሪዎች ላይ የፍጥነት መግቻ መሳሪያ እንዲገጠም እንዲሁም አደጋ አድራሽ ቦታዎች ላይ የፍጥነት መቀነሻ /Speed breaker/ እንዲሰራ የወጣው ህግና መመሪያ ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡

199. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመንገድ ትራፊክ አደጋ ተጋላጭ የሆኑት ተሽከርካሪዎችን በማጥናት የፍጥነት መግቻ መሳሪያ ለመግጠም የሚያስችል እንዲሁም አደጋ አድራሽ ቦታዎች ላይ የፍጥነት መቀነሻ /Speed breaker/ እንዲኖር የሚያደርግ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ባለመደረጉ፡-

200. እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል አደጋ የሚባዛባቸው 229 ቦታዎች የተለዩ ቢሆንም ቁጥጥር የሚደረግባቸው 41 (18%) ሲሆን ቀሪዎቹ 188 (82%) ቦታዎች ላይ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

- በተጨማሪም በደቡብ ክልል በጋሞጐፋ ዞን ከምዕራብ አበያ ጀምሮ ወደ ወላይታ ሶዶ የሚወስደው መንገድ አደጋ የሚበዛበት ቦታ ቢሆንም የፍጥነት መቀነሻ /Speed breaker/ ባለመሠራቱ ተሽከርካሪዎች በየጊዜው የመገልበጥና በሰውና ንብረት ላይ አደጋ እየደረሰ የሚገኝ መሆኑታውቋል።

ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመቀንስ እና ለመከላከል ከቅርንጫፍ መ/ቤቶች፣ ከፈቃድ ሰጪና ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ከቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተቋማት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት፣ በትብብርና በቅንጅት ሊሠራና ቋሚ የውይይት መድረክ ሥርዓት ዘርግቶ ሊሰራ ይገባል።

201. ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በትራፊክ አደጋ በህይወትና በንብረት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ፣ ከቅርንጫፍ መ/ቤቶች፣ ከፈቃድ ሰጪና ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ከቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተቋማት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ለመሥራት በ2008-2009 በጀት ዓመት መሪ ዕቅዱ ላይ አካቶ ቢያቅድም ቅንጅታዊ አሠራሩ የሚጠበቀውን ውጤት እያመጣ አለመሆኑ ታውቋል።

ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራልና በክልሎች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት በካሪኩለም እንዲካተት የማድረግ ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡

202. ይሁን እንጂ የትራንስፖርት ባለሥልጣን በሀገሪቱ የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመቀነስና አደጋን ለመከላከል የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ትምህርት በካሪኩለም ተካቶ በሁሉም ክልሎች ከ1-8ኛ ክፍል ስርዓተ ትምህርት መሰጠቱን ለመከታተል በ2008-2012 የውጤት ተኮር ምዘና ዕቅዱ እና በ2009 በጀት ዓመት መሪ ዕቅዱ ላይ ቢያቅድም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በካሪኩለም ተካቶ እየተሰጠ አለመሆኑ ታውቋል፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ትምህርታዊ ኘሮግራም በአገር አቀፍ ደረጃ በማዘጋጀት የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያን በመጠቀም የግንዛቤ ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡

203. ይሁን እንጂ የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት ቢዘረጋም የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግና በየጊዜው የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን /የትምህርት መ/ቤቶች፣ የትራንስፖርት መ/ቤቶች፣ የፖሊስ መ/ቤቶች፣ የሚዲያ ተቋማት ወዘተ../ በማስተባበርና በመደገፍ  የሚፈለገውን ውጤት በሚያመጣ መልኩ እየተሰራ አለመሆኑ፤

- በተጨማሪም ባለስልጣኑ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቢሲ) ጋር በገባው ውል መሠረት ለማህበረሰቡ  መተላለፍ ያለባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶች በተሟላ እና በቂ የአየር ስዓት ሽፋን ተመድቦለት  የማይተላለፈለት መሆኑ እንዲሁም የተያዘው የኘሮግራም መለዋወጥ ችግር መኖሩን ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ቢያሳውቅም ችግሩ መቀረፍ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

- በባለስልጣን መ/ቤቱ  በከተማ ውስጥ የሚታዩ መንገድ ለመውጣት ብቁ ያልሆኑ ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ ወይንም እንዲያስተካክሉ ለማድረግ የመንገድ ላይ ድንገተኛ ቴክኒክ ምርመራ ለማድረግ በ2008 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ተግባራዊ ያላደረገ ሲሆን፤ በ2009 በጀት ዓመት በ 4,147 ተሽከርካሪዎች ላይ በተደረገ ድንገተኛ የመንገድ ላይ የቴክኒክ ምርመራ መሰረት 892 (22%) ተሽከርካሪዎች ብቻ ብቁ ሆነው ሲገኙ የተቀሩት 3,255 (78%) ተሽከርካሪዎች ከደረጃ በታች ሆነው የተገኙ ቢሆንም በምርመራው ተገኙ በተባሉት ተሽከርካሪዎች ላይ ስለተወሰደው የእርምት እርምጃ ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

## 15.በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር  የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት አፈፃፀምን መገምገም

204. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በፐብሊክ ሰርቪስ እና ሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር እተተገበረ የሚገኘው የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር የሀገሪቱን የመንግሥት ተቋማት የሰው ሃብት መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዳታ ቤዝ በማደራጀት በመንግስታዊ ተቋማት የሚገኘውን የሲቪል ሰርቫንት የቅጥር፣ የዕድገት፣ የዝውውር እና የስንብት ሁኔታ ለመመዝገብና የተገኘውንም መረጃ ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ፣ ታራሚ፣ ተስተካካይና ለክትትልና ግምገማ አመቺ እንዲሆን የማድረጉን ተግባር ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

205. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተቀመጠለት መዋቅር /አደረጃጀት ጥናት/ መሰረት የተዋቀረ መሆኑንና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከውስጥና ከውጪ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡

206. ይሁን እንጂ ኘሮጀክቱ በ2004 በጀት ዓመት የመጨረሻው ሩብ አመት ጀምሮ በሦስት ተከታታይ አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም የኘሮጀክቱ አደረጃጀትና በጀት ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ፀድቆ የመጣው በግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም. እንደሆነና እስከ ሚያዝያ 2006 ዓ.ም. ድረስም የራሱ የሆነ ፕሮጀክት ፅ/ቤትና ፕሮጀክትሥራ አስኪያጅ አለመመደቡን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

207. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አስተባባሪ ኮሚቴ እንደሚያስፈልገውና እንደሚቋቋም ቢታመንም እስከ 2009 በጀት ዓመት ሶስተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ድረስ ተግባራዊ ሳይሆን እንደቆየ የፕሮጀክቱ የ2009 በጀት ዓመት የ9 ወራት አፈፃፀም ሪፖርት በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

208. የሶፍትዌር ማልማት ስራ በውል ስምምነት ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተፈፀሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሶፍትዌሩን ለማልማት በአለም አቀፍ የጨረታ ሂደት በኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ እ.ኤ.አ. አፕሪል 22 ቀን 2012 (በ30/09/2004 ዓ.ም.) የወጣ እና ከከስተር ኮምፒውቲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጋር ውል የተፈራረመው እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 8 ቀን 2012 (28/01/2005 ዓ.ም.) መሆኑን፣ ይህም ከአምስት ወራት በላይ የፈጀ መሆኑን፣

209. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 8 ቀን 2012 (28/01/2005 ዓ.ም.) ከከስተር ኮምፒውቲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጋር የሶፍትዌሩን ማልማት ሥራ በስድስት ወር ሰርቶ ለማስረከብ በብር **5,393,500.00** የተዋዋለ ቢሆንም፣ በተገባው ውል መሰረት ስራው ስለመስራቱ የተሟላ ማስረጃ ማለትም የመጨረሻው ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች እንዲያቀርብ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሰነዱን ማቅረብ ያልቻሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

210. የፌዴራልና የክልሎች የዳታ ማዕከሉ ግንባታ በውል ስምምነት ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

211. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀን 16/10/2007 ዓ.ም. ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ ግብአት ግዥ ቅድመ ክፍያ ብር 12,480,054.38 ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የከፈለ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

212. የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ከሁለት አመት ከአምስት ወር በኋላ በብር 7,150,964.85 የተገዛ ለዳታ ማዕከል ግንባታ የሚውል ዕቃ በቀን 24/04/2010 ዓ.ም. ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንብረት ክፍል ያስገባና ሂሳቡም እንዲወራረድ ያደረገ ቢሆንም ቀሪውን የብር 5,323,089.53 ዕቃ ማቅረብ ባለመቻሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤጀንሲው ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርግ በቀን 26/04/2010 ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር ፐ/ሠ/ል/ሚ/ ፍግ/199/2010 በተፃፈ ደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን፣

213. በፕሮጀክቱ የሚካተቱ (ሲስተሙ የሚስፋፋባቸው) ተቋማትን ከወረዳኔት መስመር ጋር እንዲገናኙ የማድረግ እንዲሁም የማረጋገጥ ስራ ሊሰራና ወደ ሙሉ ትግበራ ሊገባ ይገባል፡፡

214. ይሁን እንጂ በኦዲት ቡድኑ በናሙና ከተወሰዱት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ ዝርዝራቸው በአባሪ ከተያያዘ 11 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስተቀር የወረዳ ኔት ቢኖራቸውም የሠራተኞችን መረጃ ወደ ተዘጋጀው ሲስተም የማስገባት ስራ ያልተጀመሩ መሆኑ በመስክ ምልከታ ታውቋል፣

215. ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉት ዝርዝራቸው በአባሪ ከተያያዘው 24 በክልልና ከተማ አስተዳደር ስር በተለያየ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ከባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ በስተቀር የወረዳ ኔት የተዘረጋላቸው ቢሆንም የሠራተኞችን መረጃ በተዘጋጀው ሲስተም ማስገባት ያልጀመሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

216. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሲስተሙን ከሚጠቀሙ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ከአጠቃቀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት፤ የተቋማቱን አፈጻጸም በመከታተል እና የመስክ ጉብኝት በማድረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፓይለት ሳይቶችን (በ2007 በጀት ዓመት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት ) ወደ ሙሉ ትግበራ ለማስገባት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል አነስተኛ መሆኑ መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

217. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 እና በ2009 በጀት አመት ለተካተቱ ሁሉም ተቋማት በአካል እየተገኙ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ትግበራ እንዲገቡ የማድረግ ስራ ያልተሰራ መሆኑ መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

በኦዲት ቡድኑ በናሙና በታዩት ከ11 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ከገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በስተቀር በቀሪዎቹ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

*218.* በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በስራ ወቅት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ጥያቄ ቢያቀርቡም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መፍትሄ ያልተሰጠ መሆኑ በቃለመጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣ ፣

በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመለየት፣ የተቋማቱን እቅድ አፈጻጸም በመከታተል ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

219. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበትን ሁኔታ ለመከታተል ቋሚ መድረክ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 11 የፌዴራል እና 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበት ሁኔታ ለማወቅ ለወደፊትም በምን መንገድ ስራዎችን ማከናወን እንዳለባቸው ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ የሌለ መሆኑን እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደርጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የግንኙነት ጊዜ ስለመኖሩ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

**16.የኢትዮጵያ መድሃኒት ፈንድ ኤጀንሲ በመድሃኒት ፈንድ ኤጀንሲ በሀገሪቱ የተለያዩ አከባቢዎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖች የኮንትራት አስተዳደር እና የግንባታ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነት**

220. ኤጀንሲው የመጋዘንና ቢሮ ግንባታ ስራ ከመጀመሩ በፊት የረጅም ጊዜ የበጀት እንድምታ በመለየት ስራውን ሊያሰራ የሚያስችል የካፒታል በጀት ስለመኖሩ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖችንና ቢሮዎች ግንባታ የጀመረው የበጀት እንድምታ በመለየት ሳይሆን ለድርጅቱ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች የሚሰጡ የገንዘብ ድጋፎችንና ከክልል ደግሞ መሬት በነፃ ማግኘትን ታሳቢ አድርጎ ሲሆን፣ በመጋዘኖችና ቢሮዎች ግንባታ እና ተዛማጅ ጉዳዮች የሚያስፈልግ የአምስት ዓመት ካፒታል በጀት ፍላጎት እና የበጀት ምንጭ በሎጀስቲክስ ማስተር ፕላን 38,076,403 ዩኤስ ዶላር በጥቅሉ ለ New pharmid (የአሁኑ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ) የተቀመጠ ቢሆንም ነገር ግን ለ17ቱን መጋዘኖችና ቢሮዎች ግንባታ፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ለሚገኝ ባለ አንድ ፎቅ መጋዘንና ባለ ሰባት ፎቅ ቢሮ እና ቀዝቃዛ መጋዘን ግንባታ በጀት ተሸንሽኖ የተዘጋጀ አለመሆኑ፣

221. ኤጀንሲው በተለያዩ የሃገሪቷ ክልሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖችና ቢሮዎች በአዋጪነት ጥናት ላይ እንዲመሰረቱ እና በጥናቱ መሰረት አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ሆኖም በአዲስ አበባ ለሚገኘው የባለሰባት ፎቅ ህንጻ ከተደረገ የአፈር ጥናት ወጪ ለ17 ቱ መጋዘኖችና ቢሮዎች ግንባታ የአዋጭነት ጥናት ያልተደረገ መሆኑ

222. ኤጀንሲው በቅድመ-ጨረታ ሂደት ወቅት የተጫራቾችን የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ብቃት/Qualification/ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ሆኖም በባለ ሰባት ፎቅ የዋና መስሪያ ቤት ህንፃ፣ በቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ መጋዘን እና በ መድኃኒት ማከማቻ መጋዘን ግንባታ በጨረታ ሂደት ዝርዝር አፈፃፀም ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶች መኖራቸው፣ ለማሳያ፤

- በጨረታው ላይ የተሳተፉ ተቋራጮችን የጨረታ ሰነድ መግዢያ ቀሪ የደረሰኝ ሰነዶች ያልተገኘ መሆኑ፣
- የጨረታ ሂደቱ ላይ አስፈላጊ የሆኑ እና በአግባቡ መያዝ ያለባቸው የጨረታ ሰነዶች (የጨረታ መክፈቻ ላይ የነበሩ ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር፣ የጨረታ አከፋፈት ዝርዝር ሂደትን የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ እና የጨረታ ኮሚቴው የ Anti-Bribery Pledge (አድሎ ያለመፈጸም ክዳን) ቅፅ የፈረሙበት ሰነዶች ያልተገኘ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ለተቋራጩ ስራውን የሰጠበት ዋጋ ኤጀንሲው ካወጣው የራሱ ግምት ዋጋ 71,932,438.00 ብር አንፃር ተቋራጩ ባቀረበው የ 97,626,623.90 ብር ላይ ኤጀንሲው በድርድር ስራውን ተቋራጩ ካቀረበው የ5% ቅናሽ በተጨማሪ 7.8% በድምሩ ብር 12,496,207.85 ቅናሽ እንዲያደርግ በማድረግ በ 85,130,416.04 ብር ስራውን ለማስራት ውል የተፈራረመ ቢሆንም ነገር ግን ኤጅንሲው ካወጣው የራሱ ዋጋ ግምት እና ውል ከተፈራረመበት /85,130,416.04-71,932,438.00/ የስራ ውል ዋጋ ጋር የ ብር13,197,978.04 ልዩነት ያለው መሆኑ፣

223. የኤጀንሲው ፕሮጀክት ማናጀር /የሥራ አመራር/ በየወሩ ወይም በየሩብ ዓመቱ ወይም በሌላ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከእቅድ የሚጠበቀው /Plan Target/ እና የተሰራው ሥራ ወይም አፈፃፀምን /Target Achieved/ የማነፃፀር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

ሆኖም የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ባያቸው በአዳማ፣ በሃዋሳ፣ በአርባ ምንጭ፣ እና በነገሌ ቦረና የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፦

- የክትትልና ቁጥጥር ዕቅድ እና የክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት አለመኖሩ እና ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑን፣

- የኤጀንሲው ፕሮጀክት ማናጀር ወይም የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች በየወሩ ወይም በየሩብ ዓመቱ ወይም በሌላ የጊዜ ሰሌዳ እቅድ መሰረት ፕሮጀክቶችን ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፣
- ከእቅድ የሚጠበቁ ሥራዎችን በዝርዝር ለይተው እና የተሰራውን ሥራ ወይም አፈፃፀም /Target Achieved/ በማነፃፀር ሥራዎቹ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፣
- ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶቹ በተደጋጋሚ ችግሮችን እንዲፈቱ በደብዳቤ ቢጠይቁም መልስ የማይሰጣቸው መሆኑ፣

224. የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖችና ቢሮ ግንባታዎች በዕቅድ በተያዘላቸው የጊዜ በጀት ሊጠናቀቁ ይገባል። ይሁን እንጂ የ17ቱም የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘን እና ቢሮዎች ግንባታ ከ 476 እስከ 1542 ቀናት ድረስ የዘገዩ መሆኑን እንዲሁም እስከ አሁን የሁለት ግንባታ ፕሮጀክቶች ማለትም የነገሌ ቦረና እና ቀብሪ ደሃር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያልተጠናቀቁ መሆኑ፡

225. የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖችና ቢሮ ግንባታዎች በዕቅድ በተያዘላቸው የገንዘብ በጀት ሊጠናቀቁ ይገባል።

ይሁን እንጂ በኤጀንሲው የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ የመድኃኒት ማከማቸ መጋዘንና ቢሮዎች ግንባታ በተያዘላቸው የገንዘብ በጀት ያልተከናወኑ መሆኑ፡

- የ17ቱን የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖችና ቢሮዎች ለማስገንባት በብር 152,013,924.34 ከተለያዩ የሥራ ተቋራጮች ጋር ውል የገባ ቢሆንም ተገንብተው ያለቁት ግን በብር 311,172,926.38 ሲሆን፣ ከ17ቱ ሁለቱ (ነገሌ ቦረና እና ቀብሪ ደሃር) እስከ አሁን ያልተጠናቀቁ ግንባታዎችን ጨምሮ ክፍያው በብር 159,159,002.04 ከመጀመሪያው ስምምነት የጨመረ መሆኑ፡
- በአዲስ አበባ በዋናው ግቢ ውስጥ G+1 ለሚገነባው የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘን በዋናው ውል ስምምነት የተዋዋለው ቫትን ጨምሮ ብር 50,130,220.40 / ሃምሳ ሚሊዮን፣ አንድ መቶ ሰላሳ ሺ ሁለት መቶ ሃያ፣ ከ40 ሣንቲም/ ቢሆንም የተከፈለው ግን ቫትን ጨምሮ ብር 79,985,821.04 / ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺ ስምንት መቶ፣ ሃያ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ  በዋናው ግቢ  ውስጥ G+1 ለሚገነባው የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘን ለሱፐር ስትራክቸር (ከመሬት በላይ ግንባታ)  ለኮንክሪት  ስራ  የውል ስምምነት የተዋዋለው  331,200 / ሶስት መቶ  ሰላሳ  አንድ ሺህ ሁለት መቶ  ብር  የነበረ ሲሆን፣  ነገር ግን  የተከፈለው ብር 3,617,079.48 /  ሶስት  ሚሊዮን  ስድስት መቶ  አሰራ ሰባት  ሺህ  ሰባ ዘጠኝ ብር ከ 48 ሳንቲም /  መሆኑ፣

226. በኤጀንሲው የተገነቡና በመገንባት ላይ ያሉ የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖችና ቢሮዎች ግንባታ  የፀደቀ ዲዛይን ሊኖራቸው እና በዲዛይኑ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የባለ ሰባት ፎቅ የዋና መስሪያ ቤት ህንፃ፣ የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ መጋዘን እና የ17ቱን የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘን እና ቢሮዎች የፀደቀ ዲዛይን የሌላቸው መሆኑ

እንዲሁም የአማካሪው ዲዛይነር ፊርማ፣ ማህተም እና በመንግስት የግንባታ እና ፍቃድ ሰጪ ኤጀንሲ የህንፃ ሹም ፊርማ፣ ማህተም፣ ተፈቅዷል የሚል ፅሁፍ፣ ወጪ የተደረገበትን ቀን እና መዝገብ ቁጥር በያዘ ማህተም የተረጋገጡ የፀደቁ የዲዛይን ሰነዶች (አርክቴክቸራል፣ እስትራክቸራል፣ ኤሌክትሪካል፣ ፍሳሽ (ሳኒታሪ))፣ የመካኒካል እና የBOQ/ የስራ መዘርዝር/ ሰነዶች ያልተገኙ መሆኑ፣

227. በኤጀንሲው የተገነቡና የሚገነቡ መጋዘንና ቢሮዎች በግንባታ ኮንትራት ውሉ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውለታ ሰነዱ የጥራት ስታንደርድ መሰረት ተገንብተው ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት በነገሌ ቦረና፣ በአርባ ምንጭ፣ በሀዋሳ፣ በአዲስ አበባ ባለ አንድ ፎቅ መጋዘን (እየተሰራ ያለው/፣ በአዲስ አበባ ኤክቴንሽን፣ በአዲስ አበባ እና አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመጋዘንና ቢሮዎች በግንባታ ኮንትራት ውሉ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/  መሰረት ያልተገነቡ መሆኑ፣ ለማሳያ (በሥራ ዝርዝሩ ውስጥ ያልነበሩ፣ በሥራ ዝርዝሩ ውስጥ ቢኖሩም በጥራትና በመጠን ያነሱ፣ ያልተሰሩ ሥራዎች፣ ከመስፈርቱ በላይ የተሰሩ፣ የጥራት ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ  እና በዲዛይኑ መሰረት ያልተሰሩ) ያሉ መሆኑ፣

እንዲሁም ኤጀንሲው ባስገነባቸው በሁሉም መጋዘኖች  የወለሉ ኢፖክሲ/epoxy/ የጥራት ችግር ያለበት መሆኑና  36,242 m2  ስፋት  ያላቸው  ኢፖክሲ የተበለሹ

መሆናቸው፣ ለዚህም ኢፖክሲ/epoxy/ ማሰሪያ የወጣው ወጪ በአማካኝ 25 ሚሊዮን ብር መሆኑ፣

228. ግንባታቸው የተጠናቀቁ የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘን እና ቢሮዎች ጊዜያዊ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ365 ቀናት በኋላ የመጨረሻ ርክክብ ሊደረግና በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ ድርጅቱ ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

229. ይሁን እንጂ የ16ቱ የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘንና ቢሮዎች ግንባታ ጊዜያዊ ርክክብ ከተደረገ ከአንድ ዓመት በላይ ቢሆንም በጊዜያዊ ርክክብ ወቅት የተለዩት ግድፈቶች ያልተስተካከሉ እና ቋሚ ርክክብ ያልተደረገ እንዲሁም የሁለቱ (የነገሌ ቦረና እና ቀብሪደሃር) ግንባታዎች ያልተጠናቀቁ ሲሆን ኤጀንሲው በዚህ ዙርያ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

**17.በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የሞጆ-መቂ እና መቂ-ዝዋይ ፍጥነት መንገድ፣ ሀዋሳ-ጩኮ እና ይርጋጨፌ-ሀገረማሪያም መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ውጤታማነት**

230. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በፌዴራል ደረጃ ለሚያሰራቸው መንገዶች ግንባታ ፕሮጀክት አፈፃፀም ተግባሮች ቀልጣፋ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የተላበሱ ለመሆናቸው እንዲሁም በመንገድ ግንባታው ውል የገቡ አማካሪ መሀንዲሶች እና ተቋራጮች በገቡት ውል መሰረት እየፈፀሙ መሆኑን እና በመንገድ ግንባታ ምክንያት የሚነሱ ንብረቶች ለካሳ ክፍያ በወጡ አዋጅ እና ደንብ መሰረት የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ

231. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ለመቀነስ የአካባቢ እና የማህበረሰብ ተፅዕኖ መገምገሚያ መመሪያ/Environmental Social Impact Assessment/፣ የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር እቅድ/Resettlement Action Plan/ እና የአካባቢ ተፅዕኖ እና ማህበረሰብ ደህንነት መከታተያ እቅድ/Environmental Social Management Plan/ እንዲዘጋጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ሆኖም የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር እቅድ/Resettlement Action Plan/ እና የአካባቢ ተፅዕኖ እና ማህበረሰብ ደህንነት መከታተያ እቅድ/Environmental Social Management Plan/ በተፈጠረ የአተገባበር ችግር የይርጋ ጨፌ ሃገረ ማሪያም መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ከ8 ወር በላይ የቆመ መሆኑ

232. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጨረታ ሂደት ወቅት ከዚህ በፊት በተሳተፉባቸው የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ደካማ የሥራ አፈፃፀም ያሳዩ ተቋራጮች እና አማካሪዎች በአዲስ የጨረታ ሂደት ውስጥ እንዳይሳተፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

233. ኤ አይ ሲ ፕሮጌቲ /AIC PROGETTI/ የቀድሞው የሀዋሳ-ጩኮ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት አማካሪ የሆነው ፣ በተቋራጭ /SEW INFRA STRUCTURE/ ለተሰራው 22 ኪ.ሜ አስፓልት በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ ሳይኖራቸው እያሳለፈ እና እያፀደቀ ሲከታተል የነበረ እና ለተሰራው ሥራ ጥራት ችግር የበኩሉን የተጠያቂነት ኃላፊነት መውሰድ ሲገባው እንደገና በተጨማሪ ውል ማራዘሚያ ስምምነት ከአዲሱ ተቋራጭ ሲኖሃድሮ ኮርፖሬሽን ጋር ከህዳር እ.ኤ.አ 2/2016 እስከ መስከረም 30/2019 ድረስ የማማከር ስራ እንዲቀጥል የተደረገ መሆኑ፡

234. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እና በኮንትራት ውል በተገባበት ዋጋ እንዲጠናቀቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

235. ይሁን እንጂ፦

- የቀድሞው የሀዋሳ-ጩኮ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጭ ሰው ኢንፍራ እስትራክቸር 66 ኪ.ሜ ርዝመት ያለውን ለመሥራት እ.ኤ.አ ሚያዚያ 22/2013 ጀምሮ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 23/2016 እንዲያጠናቅቅ ቢታቀድም በማጠናቀቂያው ወቅት የመንገዱን ሥራ 34 ከመቶ ብቻ ያከናወነ መሆኑ፤
- ይርጋጨፌ-ሀገረማሪያም መንገድ ግንባታ ፕሮጀክትን በተመለከተ፡- እ.ኤ.አ ሚያዚያ 1/2013 ተጀምሮ የመነሻ ማጠናቀቂያ ጊዜው እ.ኤ.አ መጋቢት 31/2016 ቢሆንም፤ባለመጠናቀቁ እስከ እ.ኤ.አ እስከ ሀምሌ 12/2017 የተራዘመ ቢሆንም በዚህም ወቅት ባለመጠናቀቁ የኦዲቱ በድኑ በመስክ እስከነበረበት እ.ኤ.አ ታህሳስ 19/2017 ያልተጠናቀቀ መሆኑ፡

236. ባለስልጣን መ/ቤቱ ንብረት በወቅቱ ባለመነሳት ምክንያት የመንገድ ግንባታው እንዳይደናቀፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

ባለስልጣን መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታ ሂደት የሚነሱ ንብረቶችን በወቅቱ ለማስነሳት የመንገድ መስመሩ ከሚያልፍባቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት እስቲሪንግ ኮሚቴ በማቋቋም ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እያደረገ ቢሆንም በኮሚቴው የተካተቱ ዓባላት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ባለመወጣታቸው መነሳት ያለባቸው ንብረቶች በወቅቱ ባለመነሳታቸው በግንባታ ሥራው ላይ ተፅዕኖ የፈጠረ መሆኑ፡

## 18.በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓት አመራርና ቁጥጥር አፈጻጸምን በተመለከተ

237. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተቋቋመበት አላማ አንፃር፤ የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓት አመራርና ቁጥጥርን ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፤ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

238. የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ  ግብይት ማዕከላት ግንባታ ሥራ  ዝርዝር የግንባታ ስታንዳርድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ባሉ ሰባት ክልሎች (በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ በሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት) ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተገነቡ ያሉ ሞዴል የ2ኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ሊያሟሉ የሚገባቸው ዝርዝር የግንባታ ስታንደርድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀና ግንባታውም በስታንደርዱ መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልተቻለ መሆኑ፣

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው መስፈርት መሠረት የቁም እንስሳት ኳራንቲን[1] ጣቢያ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል የግንባታ ስታንዳርድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የቁም እንስሳት ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታን ለመከናወን የሚያስችል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው መስፈርት እና መሠረታዊ የሆኑ  የእንስሳት ጤና ደህንነት ስታንዳርድ (very high Standard of biosecurity) እና የእንስሳት ደህንነት ስታንዳርድ (Animals Welfare Standards) የተዘጋጅ የግንባታ ስታንዳርድ አለመሆኑ፤

[1]በቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 መሠረት ኳራንቲን ጣቢያ ማለት የቁም እንስሳትን በተከለለ ስፍራ ለተወሰነ ጊዜ ከሌሎች እንስሳት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳይገናኙ በማድረግ ጤንነታቸውን ለመከታተል እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ የክትባት ወይም የህክምና አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ የተለየ ሥፍራ ነው፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት፣ የአዋጭናት ጥናት እና ዝርዝር የግንባታ ዲዛይን ጥናት ሊጠናና በባለሙያዎች ሊገመገም ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦሮሚያ፣ በአፋር፣ በአማራ፣ በትግራይ፣ በሱማሌ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተገነቡ ያሉ ሞዴል የ2ኛ ደረጃ ቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግንባታን በተመለከተ ግንባታው ከመጀመሩ በፊት የአካበቢ ተጽዕኖ ጥናት እና የአዋጭነት ጥናት ስለመከናወኑ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

የቁም እንስሳት ኳራንቲን ጣቢያዎች ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት፣ የአዋጭነት ጥናት እና ዝርዝር የግንባታ ዲዛይን ጥናት ሊጠናና በባለሙያዎች ሊገመገም ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ለሚሌ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት፣ለጅጅጋ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት፣ለመተማ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ፕሮጅክት፣ ለሁመራ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ፕሮጅክት እና ለአልማሃል ቼክ ፖይንት ጣቢያ ግንባታ ፕሮክጅትን የግንባታ ሥራው ከመጀመሩ በፊት የአዋጭነት ጥናት እና የአካበቢ ተጽዕኖ ጥናት ስለመጠናቱ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

የሁለተኛ ደረጃ ግብይት ማዕከላት እና ኳራንቲን ጣቢያዎች የግንባታ እና የማማከር አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ለአሸናፊ ድርጅቶች ሊሰጥና ውል ሊፈረም ይገባል፡፡

239. ይሁን እንጂ በአፋር ክልል ሚሌ የኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ፡-

- ❖ እ.አ.አ በቀን 20/12/2016 በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር የሚሌ ኳራንቲን የጣቢያው ማስተካከያ ፕሮጅክት (Construction of Mile Quarantine Station Modification Works Project) በ16,472,256.36 ብር ለአፋር ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በቀጥታ/ ያለጨረታ የተሰጠ መሆኑ፤
- ❖ በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር በአፋር ክልል የሚገነባውን የሚሌ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታን በተመለከተ የቀድሞ ዲዛይን ውስጥ ያልተካተተ ሥራዎች አንድ የጎርፍ መከላከያ ሥራ ፕሮጅክት (Quarantine Flood Protection project)

በሚል ለአፋር ገጠር መንገዶች ባለስልጣን በ9,999,300.44 ቀጥታ ያለ ጨረታ የተሰጠ መሆኑ፤

- ❖ በቀድሞ ግብርና ሚኒስቴር በአሁኑ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በኩል በአፋር ክልል የሚገኘው ለሚሌ የኳራንቲን ጣቢያ ጅቡቲ በሚወሰደው ከዋና አሰፋልት እስከ ጣቢያው ድረስ ያለውን የ5 ኪ.ሜ የጠጠር የመንገድ ግንባታ ሥራ የአፋር ገጠር መንገዶች ባለስልጣን በመጀመሪያ አንዱን ኪ.ሜትር በ1,700,000.00 ብር እና 5.5ኪ.ሜትር በ9,350,000.00 እንደሚሠራ ዋጋ መስጠቱን የተገለጸ ቢሆንም በውል ስምምነት መሠረት ግን በ12,654,926.72 ብር ቀጥታ ያለ ጨረታ የተሰጠ መሆኑ፤

240. በሶማሌ ክልል የቀብሪ-አህመድ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ሥራ፡-

- ❖ እ.አ.አ መጋቢት 2015 የተጀመረ በሶማሌ ክልል የሚገነባውን የቀብሪ-አህመድ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ሥራ (Kebri Ahmed Construction of Quarantine Station) በተመለከተ በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ለሶማሌ ፖሊስ ኮንስትራክሽን ግዝ እና ልዩ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ በ74,769,808.58 ብር ቀጥታ ያለ ጨረታ የተሰጠ መሆኑ፤
- ❖ በቀድሞ ግብርና ሚኒስቴር በአሁኑ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በኩል በሶማሌ ክልል የሚገኘው ለቀብሪ-አህመድ የኳራንቲን ጣቢያ ከአዲስ አበባ-ጎዴ ከሚወስደው ከዋና አስፋልት መንገድ እስከ ጣቢያው ድረስ ያለውን የ5-6 ኪ.ሜትር የጠጠር መንገድ ግንባታ ሥራ የሶማሌ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን በመጀመሪያ በብር 11,789,486.09 እንደሚሠራ ዋጋ መስጠቱን የተገለጸ ቢሆንም፣ ከተቋሙ ጋር በተገባው ውል ስምምነት መሠረት ግን በብር 11,904,486.09 ቀጥታ ያለ ጨረታ የተሰጠ መሆኑን፣

241. የኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክቶች የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በሚያደርግበት ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት መጠን ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ 25% መብለጥ የለበትም፡፡

በእምሩ ወርቁ የውሃ ሥራ ተቋራጭ የሚሰራ የሁመራ ኳራንቲን ጣቢያ የውሃ መስመር ዝርጋታ ስራ በብር 7,365,970.39 ጠቅላላ ግንባታ ዋጋ እ.አ.አ በ30/09/2016 ተጀምሮ በአምስት ወራት ውስጥ የሚጠናቀቅ ቢሆንም፣ ከጠቅላላ የግንባታ ሥራው ወይም ከመጀመሪያ የውል ስምምነት ዋጋ የብር 2,609,052.81 ወይም የ35.42% ቧንቧዎችን

የመዘርጋት ስራ በውል ውስጥ ሳይካተት በመዘለሉ ምክንያት በሚል ተጨማሪ ሥራ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለተቋራጩ ቀጥታ የተሰጠ መሆኑ፤

242. በአፋር ክልል የሚገኘው የሚሌ ኳራንቲን ጣቢያ የ5 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ ግንባታ ሥራው እ.አ.አ 10/01/2013 ተጀምሮ በ120 ቀናት ወይም 4 ወራት ጊዜ ውስጥ የግንባታ ሥራው የሚጠናቀቅ በብር 12,654,926.72 ጠቅላላ የግንባታ ዋጋ ለአፋር ገጠር መንገዶች ባለስልጣን የተሰጠ ሲሆን፣ የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ከ18 ወራት በታች ሆኖ ሳለ ከጠቅላላ ግንባታ ሥራው ዋጋ መጠን ተጨማሪ የብር 7,628,547.46 ወይም 60.28% የዋጋ ማስተካከያ መደረጉ፤

የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ  ግብይት ማዕከላት ግንባታ ስለቁም እንስሳት ግብይት በወጣው በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

243. በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሞዴልነት በየክልሎች የተገነቡት ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት በደንቡ ላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ በናሙና ተመርጠው በታዩ ሁለት (አዳማ እና አዋሽ-7) ሞዴል ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ግንባታ ውስጥ መሠረታዊ የሆኑ መስፈርቶች አለመካተቱ፣

የሁለተኛ ደረጃ  ግብይት ማዕከላት ግንባታ እና ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታን ፕሮጀክት በውል ስምምነት እና በተጠናው ዲዛይን መሠረት ስለመከናወኑ የፕሮጀክቶችን ግንባታ ሥራ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ በታቀደው ገንዘብ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

244. የአልማሃል ቼክ ፖይንት ጣቢያ ግንባታን በተመለከተ በቱሊፕ ኮንስራክሽን ድርጅት ሥራው እ.አ.አ በ19 ግንቦት 2011 ተጀምሮ በ18/05/2012 መጠናቀቅ እንደለበት በውል ስምምነቱ ላይ ቢገለጽም ሥራው ከግንቦት 18 2015 (10/09/2007 ዓ.ም) ጀምሮ ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ የግንባታው ሥራው የተቋረጠ መሆኑ፤

በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ የቁም እንስሳትን መግዛት የሚችሉ አርቢዎች፤ህብረት ሥራ ማህበራት፤ አድላቢዎች፤ ላኪዎች፤ ቄራዎች፤ ሉኳንዳ ቤቶች፤ ሸማቾች እና በዘርፉ ላይ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያለው አካል ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦሮሚያ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ የቁም እንስሳትን ሽያጭ የሚያከናውኑት አርቢዎች ብቻ ሳይሆኑ ያልተፈቀደላቸው አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን የቁም እንስሳትን ግዥም የሚፈጽሙ ህጋዊ ያልሆኑ አካላት የሚሳተፉ መሆኑ፣

245. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ መሸጥ የሚችሉት አርቢዎች፤ አድላቢዎች፤ እና ህብረት ሥራ ማህበራት ብቻ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀንድ ከብቶች የሚገበያዩበት የሸጎሌ የ2ኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ገበያ ማዕከል እና የቄራ የ2ኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ገበያ ማዕከል እንዲሁም የአስኮ ብርጭቆ የፍየል እና የበግ ገበያ ማዕከል ውስጥ የተቆጣጣሪ ሠራተኞች ቢመደቡም የአገልግሎት ክፍያ ከመሰብሰብ ውጪ በማዕከላት ውስጥ ግብይት የሚያከናውኑ ቢሆንም ህጋዊ ያልሆኑ ነገዴዎችና ደላሎች ላይ ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣

246. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ ከአርቢው በስተቀር ማንኛውም የቁም እንስሳት ሻጭ ለሚሸጠው የቁም እንስሳት ለገዢዎች ደረሰኝ ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ውስጥ ባሉት በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ እንስሳት ለሽያጭ በሚቀርቡበት ወቅት የጤና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የባለቤትንት ማረጋገጫ ሰነድ (ደረሰኝ) ሻጩ የእንስሳቱ ሽያጭ ከፈጸመ በኂላ ሰነዶቹን ለገዥው የሚያስረክብበት አሰራር አለመኖሩ፤

247. የቁም እንስሳት ግብይት የሚከናወነው በመጀመሪያ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ውስጥ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በህገ ወጥ ከግብይት ማዕከላት ውጭ ግብይት የሚከሄደው የበግ እና ፍየል ግብይት ማዕከላት በሌለባቸው በየጎዳና ወይም በየሰፈሩ፤ የአስኮ ብርጭቆ የፍየል እና የበግ ገበያ ማዕከል እያለ ፍየልና በግ ከማዕከሉ ፊትለፍት በየጎዳና ላይ ግብይት የሚፈጸም ሲሆን የቀንድ ከብቶች በሸጎሌ ከገበያ ማዕከል ውጭ፤በካራ ምንም አጥር በሌለው ቦታ ላይ እና በአቃቂ በየአስፋልት ዳር ግብይት እየተካሄደ መሆኑን

248. የቁም እንስሳት ህገ ወጥ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ጣቢያዎች በፌዴራል ደረጃ በከተሞች መግቢያና መውጫ፤በክልሎች በወረዳ ደረጃ፤ እንዲሁም እንደ

አስፈላግነታቸው በታመነባቸው ቦታዎች ላይ ተጨማሪ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን ሊቋቋም ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ደረጃ የቁም እንስሳት ህገ ወጥ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ጣቢያዎች በከተሞች መግቢያና መውጫ እንዲሁም በክልሎች በወረዳና አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ላይ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ያልተቋቋሙ መሆኑ፤

249. የቁም እንስሳትን ከማድለቢያ ወይም ከግብይት ማዕከላት ወደ ቀጣዩ መዳረሻ በሚጓጓዝበት ወቅት የማጓጓዣ ፈቃድ፤ የጉዞ መሸኛ፤ግዢ የተፈጸመበትን ደረሰኝ እና ከኳራንታይን ጣቢያ ወደ ወደብ ሲሆን ደግሞ የእንስሳት ጤና ምስክር ወረቀትና የማጓጓዣ ፈቃድ፤ ስለመኖሩ በየመቆጣጠሪያ ኬላዎች ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል::

ይሁን እንጂ የቁም እንስሳትን ከማድለቢያ ወይም ከግብይት ማዕከላት ወደ ቀጣዩ መዳረሻ በሚጓጓዝበት ወቅት የማጓጓዣ ፈቃድ፤ የጉዞ መሸኛ፤ ግዢ የተፈጸመበትን ደረሰኝ ስለመኖሩ በየመቆጣጠሪያ ኬላዎች ቁጥጥር ስለመደረጉ ለመረጋገጥ የኦዲት ቡድኑ በቀን 07/02/2010 ዓ.ም በአካል በአዋሽ መቆጣጠሪያ ኬላ በማገኘት ማታ ከ2፡00 ሰዓት ጀምሮ መዳረሻቸው አዲስ አበባ የሆኑ በደረቅ ትራንስፖረት የተጫኑ ቁም እንስሳትን የሚያገጓጉዙ አካላት የንግድ ፈቃድ፤ የማጓጓዣ ፈቃድ እና የጉዞ መሸኛ ወረቀት የሌላቸውና የማይጠያቁ መሆኑ፣

250. በሀገሪቱ ድንበር አከባቢ በመግቢያ እና በመውጫ በሮች የቁም እንስሳት ድንበር ዘለል ህገወጥ ንግድን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በአፋር ብሔራዊ ክልል በአሳይታ ዞን በኩል ከአማራ ክልል እና ከትግራይ ክልል በተሸካሪካሪዎች ተጭኖ አሳይታ ከተረገፉ በኂላ በእግር በአፋንቦ ወረዳ በኩል በትንሹ በሳምንት ውስጥ እስከ 3,000 ወይፋኖች፤ ከፍተኛ ቁጥር ያለቸው ፍየል እና በግ ድንበር አቆርጠው በእግር እየተነዱ ወደ ጁቡቲ የሚገቡ መሆኑ፣

251. ከኦሮሚያ ክልል ከምዕራብ ሐረርጌ ዞን ተነስቶ በሱማሌ ብሔራዊ ክልል በሽነሌ ዞን በኡመር ጉሉፍ በኩል ዲክል ጅቡቲ የሚገቡ ከፍተኛ ቁጥር ያለቸው ቀንድ ከብቶች መኖራቸው፣

252. በህገወጥ የተያዙ የቁም እንስሳት ተገቢው ውሳኔ እስኪያገኙ ድረስ ወደ ተዘጋጀላቸው ማቆያ ጣቢዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መቆጣጣሪያ ጣቢያዎች በሚገኙበት አካባቢ በህገ ወጥ የሚያዙ እንስሳትን ለማቆየት እና

በግብይት ማዕከላት አቅርቦ ለመሸጥ የማቆያ ጣቢያ፤በወቅቱ እንስሳት ለመሸጥ ገበያ እና መኖ ባለመኖሩ ምክንያት በህገ ወጥ የሚዘዋወሩና ግብይት የሚፈጸምባቸው እንስሳትን መውረስ አለመቻለቸው፣

253. ማንኛውም ላኪ መስፈርቱን የሚያሟላ የራሱ ወይም የተከራየው የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያ ስለመኖሩ በሚ/ር መስሪያ ቤቱ ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በቆቃ መገንጠያ የሚገኝ የሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም እንስሳት ላኪ ማድለቢያ/ ማቆያ ጣቢያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ብቁ ነው ተብለው የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠ ጣቢያ የመመገቢያ ገንዳ ጥላ፤የውሃ መጠጫ ገንዳ ጥላ፤ የክትባት መስጫ በረት፤የእግር ኬሚካል መርጫ ቦታ ፣የታማሙ እንስሳት መለያ፣ የበድን ማቃጠያ ፣ከእንስሳቱ የሚወጡ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (Drainage System) እና ሚዛን አለመኖሩ፤

254. ማንኛውም ለውጭ ገበያ የሚዘጋጁ የቁም እንስሳት የኳራንቲን አገልግሎት የሚሠጠው ደረጃውን በጠበቀ ኳራንታይን ጣቢያ ውስጥ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር የሚገኙ የአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ ፤ድሬ ዳዋ ኳራንቲን ጣቢያ፤ሚሌ ኳራንቲን ጣቢያ እና ጅጅጋ ኳራንቲን ጣቢያ የኳራንታይን አገልግሎት የሚሰጡት በግለሰቦች በቁም እንስሳት ላኪዎች ማቆያ ጣቢያ ውስጥ መሆኑ፣

255. በድሬዳዋ ኳራንቲን ጣቢያ የላብራቶሪ ምርመራ መስጫ ፋሲሊቲ የሌለ በመሆኑ ኤክስፖርት የሚደረጉ እንስሳት ላብራቶሪ ምርመራ እንደማይከናወንና በቆይታ ጊዜያቸው የእንስሳቱ ጤንነት የጣቢያው ባለሙያዎች የሚያረጋግጡት በአይን ምልከታ ብቻ መሆኑ፣

256. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጪ ንግድ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ጤንነታቸው በተቀባይ ሀገር በሚጠይቀው መስፈርት መሠረት የላብራቶሪ ምርመራ፤ክትባት እና ሌሎች ጥያቄዎች በተሟላ ሁኔታ ካከናወነ እና የኳራንቲን ጊዜያቸውን ከጨረሱ በኋላ የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ሠርተፊኬት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሲሪቃ በዳሶ የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅት በአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ በቀን 22/06/2008 ዓ.ም በቁም እንስሳት ጤና ሰርተፊኬት ቁጥር AQS-01/857/2016 ለ100 ፍየሎች የፍየል ሳንባ በሽታ (contagious caprine CCPP)፣ የፍየሎች ደስታ

መሰል በሽታ Peste Des petits ruminants (PPR)፣ and Goat Pox፣ ለአባ ሰንጋ (Anthrax) ለሚባሉ በሽታዎች ክትባት እንዲሁም በሰርተፊኬት ቁጥር AQS-01/856/2016 ለ900 በጎች ደግሞ የከብት ሳንባ በሽታ (contagious bovine CBPP) ፣ ፈንጣጣ (Sheep and Goat pox)፣ ለአባ ሰንጋ (Anthrax) and ጎሪርሳ (pasteurollosis)፣ ለሚባሉ በሽታዎች ክትባት ወስደው ወደ ዱባይ የተላኩ ቢሆኑም ዋጋቸው 110,000.00 የአሜሪካ ዶላር የሚያወጡ እንስሳቶቹ በሻርጃ/ዱባይ ጤንነታቸው የተሟላ አይደለም ተብለው በቦታው እንዲቃጠሉ መደረጉ፤

257. አባኪይ ጀኔራል ትሬዲንግ (በረከት ደመቀ) የቁም አንስሳት ላኪ በአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ በቀን 09/11/2008 ዓ.ም የእንስሳት ጤና ሰርተፍኬት ቁጥር AQS-01/1116/2016 ተሰጥቶት 900 ፍየሎችን ወደ ዱባይ ሳርጃ የተላኩ ቢሆንም ከ900 ፍየሎች 61 ፍየሎች ሳይመለሱ የቀሩ ሲሆን 59,780 የአሜሪካ ዶላር የሚያወጡ ፍየሎች ወደ ሀገር የተመሉና ለአውሮፕላን መጓጓዣ ብቻ 46,970 የአሜሪካ ዶላር ኪሳራ የደረሰ መሆኑን፣

258. ሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም አንስሳት ላኪ ለ2,500 ፍየሎች ለ21 ቀናት በኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ እንደቆዩ እና ለአባ ሰንጋ (Anthrax), የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ Peste Des petits ruminants (PPR), ፈንጣጣ (Sheep and Goat pox) እና የፍየል ሳንባ በሽታ (contagious caprine CCPP) ለሚባሉ በሽታዎች ክትባት የወሰዱ መሆኑን ተጠቅሶ እ.አ.አ በቀን 21/04/2017 በእንስሳት ጤና ሰርተፍኬት ቁጥር AQS-01/397/2017 የቁም እንስሳት ጤና ሰርተፍኬት ከአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ የተሰጣቸው ቢሆንም፣ ከ2,500 ፍየሎች ውስጥ 1,298 ወይም ዋጋቸው 90,860 የአሜሪካ ዶላር የሚያወጡ በተለያየ ቦታ የሞቱ መሆኑና በጂቡቲ የወደብ አገልግሎት ዋጋ ብር 4,322,222.7 ላኪው የተጠየቁ መሆኑ፣

259. ከሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም አንስሳት ላኪ ጋር በመሆን በአማረ ገ/እግዚያብሔር የቁም እንስሳት ላኪ፤ በሙሉ መሀሪ አስመጪና ላኪ፤ በደጀኔ ገ/መስቀል በርሔ የቁም እንስሳት ላኪ ስም በአጠቃላይ ለ1633 የቀንድ ከብቶች በአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ ለ30 ቀናት በከኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ እንዳቆዩ እና ለአባ ሰንጋ Anthrax, አባ ጎርባ (Black Leg), ጎሪርሳ (pasteurollosis), የዳልጋ እንስሳት ጉርብርብ በሽታ (lumpy skin diseases LSD),የአፍና እግር በሽታ (foot and mouth diseases FMD) እና የከብት ሳንባ በሽታ (contagious bovine CBPP) ለሚባሉ በሽታዎች ክትባት የወሰዱ መሆኑ

ተጠቅሶ እ.አ.አ በቀን 21/04/2017 የቁም እንስሳት ጤና ሰርተፍኬት ከአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ የተሰጣቸው ቢሆንም ከ1,633 ውስጥ 82 ወይም 49,200 የአሜሪካ ዶላር የሚያወጡ ቀንድ ከብቶች የሞቱ መሆኑን፤በጂቡቲ የወደብ አገልግሎት ዋጋ 1,552,306 የአሜሪካ ዶላር ላኪው እንዲከፍሉ መጠየቃቸው፣

260. በአልፎዝ የቁም እንስሳት ላኪ ወደ ዱባይ የተላኩ 2379 የቀንድ ከብቶች በአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ ለ30 ቀናት በከኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ እንደቆዩ እና ለአባ ሰንጋ (Anthrax), አባ ጎርባ (Black Leg), ጎሪርሳ (pasteurollosis), የከብት ቆዳ በሽታ lumpy skin diseasis (LSD), የአፍና እግር በሽታ foot and mouth diseasis (FMD) እና የከብት ሳንባ በሽታ (contagious bovine CBPP) ለሚባሉ በሽታዎች ክትባት የወሰዱ መሆናቸው ተጠቅሶ እ.አ.አ በቀን 21/07/2017 የቁም እንስሳት ጤና ሰርተፍኬት ከአዳማ ኳራንቲን ጣቢያ የተሰጠ ቢሆንም የተባለው ክትባት በባለሙያ ስለመሰጠቱ ጣቢያው የተሟላ ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበና ከተላኩ 2,379 የቀንድ ከብቶች ውስጥ 2,189 እንስሳቶቹ ከዱባይ “Infectious Epidemic Disease” ያሳያሉ በሚል ወደ ሀገር የተመለሱ መሆናቸው፣

261. ለውጭ ገበያ የተዘጋጁ የቁም እንስሳትን በሀገር ውስጥ የሸጡ የቁም እንስሳት ላኪዎችን ቦጋለ ይስማው አይናለም የተበሉ ላኪ ከባንክ ብድር የወሰዱ በመተሀራ በሚገኘው በረት ውስጥ ያሉት 10,000 በጎች፤ራሄል ስሜ የተባሉ የቁም እንስሳት ላኪ ከንግድ ባንክ ብድር 3.5 ሚሊዮን ብር የወሰዱ 166 ዳልጋ ከብቶችን፤ስዩም ባልቻ ፍሬንሰበት የተባለ የቁም እንስሳት ላኪ ከንግድ ባንክ ብድር የወሰዱ 850 ዳልጋ ከብቶች፤ ፀጋዬ ገብረመስቀል ገብረእግዚአብሔር የቁም እንስሳት ላኪ 2,500 ፍየሎችን እና ሀጂ ሀሰን ዲዳ የቁም እንስሳት ላኪ 574 ዳልጋ ከብቶችን ለሌላ አካል የሸጡ መሆናቸው፤

262. የቁም እንስሳት ኳራንቲን አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ በቅድመ ኳራንቲን/በግለሰቦች መቆያ ጣቢያ እና በኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ ለእንስሳት የጤና አገልግሎት ለሚሰጡ የህክምና ባለሞያዎች ሙያዊ ሥነምግባር (Code of Ethics) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊዘጋጅ ይገባል።

ይሁን እንጂ የቁም እንስሳት ኳራንቲን አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ በቅድመ ኳራንቲን/በግለሰቦች መቆያ ጣቢያ እና በኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ ለእንስሳት የጤና አገልግሎት ለምሰጡ የህክምና ባለሞያዎች ሙያዊ ሥነምግባር (Code of Ethics) ስለመዘጋጀቱ ማስረጃ ተጠይቀው በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ፤

263. በኢትዮጵያ የጤና ሠርተፊኬት በጁቡቲና በሶማሌ ላንድ በኩል የሚላኩ የቁም እንስሳት መዳረሻቸው ግን ሌላ አገር የሆኑ በተጠቀሱት አገሮች ሲደርሱ ሠርተፊኬተኬታቸውን (Origin of Animals Certificate) ሳይቀየር ወደ መዳረሻ አገራት ሊላኩ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ወደ ሶማሌ ላንድ እና ጅቡቲ የሚላኩ የቁም እንስሳቶች መዳረሻቸው ግን ሌላ አገር የሆኑ በኢትዮጵያ የጤና ሠርተፊኬት ወደ ተጠቀሱት አገሮች ሲደርሱ ሠርተፊኬተኬታቸውን እንዲቀየር ተደርጎ አዲስ የጤና ሰርተፊኬት በአገሮቹ ሥም (Origin of Animals Certificate) ለውጥ ተደርጎባቸው ወደ መዳረሻ አገራት እንዲላኩ (Re-export) እንደሚደረጉ በደብዳቤ በቁጥር 15/እአ/12/232 በቀን 28/09/2009 ተገልጸ እንዲቆም ቢደረግም በቁጥር 15እዓ1/1/8 በቀን 03/03/10 በተጻፈ ደብዳቤ ደግሞ ጉዳዩ ሳይፈታ እንደገና በቀጥታ መዳረሻቸው ወደ ተባሉት ሀገራት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንስሳቶቹ እንዲላኩ እውቅና የተሰጠ ወይም የተፈቀደ መሆኑ፣

264. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቁም እንስሳት በባህር ወደብ ቆይታን በተመለከተ የቁም እንስሳት ማቆያ ቦታ በቂና የሚያስፈልገውን ፋስሊቲ ባሟላ መልኩ ሊዘጋጅና አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በመርከብ ላይ እስከሚጫኑ ድረስ ለቁም እንስሳት ኤክስፖርት የተዘጋጀ እና የተሟላ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የቁም እንስሳት ማቆያ ቦታ በጂቡቲ ባህር ወደብ የሁለቱም ሀገራት ስምምንት ሂደት የተጀመረ ቢሆንም ይህ ኦዲት እስከተጸፈበት ቀን ድረስ ስምምነት ሰነድ አለመፈረሙ፣

12. በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው መስፈርት መሠረት የቁም እንስሳት ኳራንቲን[2] ጣቢያ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል የግንባታ ስታንዳርድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ በስታንዳርዱ መሠረት ተገነቡ ከተባሉት መከካል አንዱ የሆነውን የሚሌ ኳራንቲን ጣቢያን ግንባታ መረጃ በአለም አቀፍ ስታንዳርድ መሠረት ዝቅተኛው ለአንድ ቀንድ ከብት የተወሰነ ቦታ 9m$^2$ ቢሆንም የሚሌ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት ግን 4m$^2$ መሆኑ፤ ለአንድ ቀንድ ከብት የመመገቢያ ገንዳ ርዝመት 38cm መሆን ቢኖርበትም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው ስታንደርድ ግን 15cm ብቻ ከመሆኑ በተጨማሪ በሚሌ ኳራንቲን ጣቢያ የተገነባው 9.7 cm መሆኑ፤ ለአንድ ቀንድ ከብት የውሃ መጠጫ ገንዳ መጠንን በተመለከተ በአለም አቀፍ ስታንዳርድ ዝቅተኛው 15cm

ቢሆንም፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው ስታንዳርድ ግን 3cm መሆኑና በጣቢያው የተገነባው ግንባታም ደግሞ 1.2 cm ብቻ መሆኑ፤

13.በቁም እንስሳት ግብይት የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 341/2007 መስፈርት መሠረት የሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ግንባታ የተከናወነ መሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና በታዩት የአዳማና አዋሽ 7 ኪሎ ሞዴል 2ኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት የመጠለያ ታዛ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና ፈሳሽ ማስወገጃ (Drainage System)፣ ለጨረታ አመቺ የሆኑ መሰረተ ልማቶች፣ የተሸጡ እንስሳት መለያ ቦታ፣ የግብይት ተሳታፊ ለሆኑት ለህብረት ስራ ማህበራት፣ ለአርቢዎች፣ እና ለአድላቢዎች የቁም እንስሳት መገበያያ ተሸንሽኖ የታጠረ ቦታ፣ የተለያዩ የቁም እንስሳት ዓይነቶችን ለመመዘን የሚያስችሉ የተለያዩ ሚዛኖችና የጥበቃ ማማ አለመኖሩ መታየቱ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

## 19.<u>የፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ</u>

265. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ፦ በፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ፣ምዝገባና መረጃ አያያዝ አፈጻጸም

266. የፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የፌዴራል እና የክልል ከተሞች የምዝገባ ተቋማትን በማስተባበር በቴክኖሎጅ የተደገፈና ወጥ የሆነ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ስርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

ሆኖም በፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እና በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በጥር 21/2008 ዓ.ም ብሔራዊ የካዳስተር እና የቋሚ ንብረት ምዝገባ ስርዓት ለማልማትና ለመተግበር በብር 68,829,800.00 እና 1,736,339.00 የአሜሪካን ዶላር በሃያ ሁለት ወራት ማለትም ህዳር 8/2010 ዓ.ም ለማጠናቀቅ የውል ስምምነት የተደረገ ቢሆንም ስራው በስምምነቱ በተቀመጠለት ጊዜ ያልተጠናቀቀ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

267. ኤጀንሲው በከተሞች የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ እና መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ስራ ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ሁለተኛውን ሀገር አቀፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለመደገፍ ከ2008 እስከ 2012 ባዘጋጀው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ ትግበራን በሃገር ደረጃ የሚመራ የአለም አቀፍ ተሞክሮ (በማኔጅመንት ኮንትራት) ወደ ሃገር ውስጥ በፌደራል ደረጃ በማስገባት በ2008 በጀት ዓመት በ6 ከተሞች 200,000 እና 150,000 ፤በ2009 በጀት ዓመት በ17 ከተሞች 320,000 እና 200,000 ይዞታዎችን በቅደም ተከተል ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ዕቅድ ያስቀመጠ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት ምንም ያልተፈጸመ መሆኑ፣በ2009 በጀት ዓመት በሃገራዊ ማኔጅመንት አቅም በ230,000 የመሬት ይዞታዎች የማረጋገጥ ስራ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ ተይዞ 15,640 (6.8%) ይዞታዎችን ብቻ ማረጋገጥ የተቻለ መሆኑ፣

268. ኤጀንሲው በከተሞች የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ማስፋፋት ላይ እና ደረጃውን የጠበቀ የካዳስተር መሰረታዊ ካርታ እንዲዘጋጅ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል።

በቅየሳ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን ስታንዳርድ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማና በአራት የክልል ከተሞች ውስጥ በተመረጡ አምስት ቦታዎች ላይ ለካሊብሬሽን የሚሆኑ የቅየሳ ነጥብ ትክል ድንጋይ (ሞኑመንቶች) እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ የዕቅዱ 5% ብቻ የተፈጸመ መሆኑ፣

269. ኤጀንሲው የከተማ መሬት ምዝገባና ይዞታ ለማረጋገጥ የወጡ ህጎች፤ ደረጃዎችና የአሰራር ስርዓቶች ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል።

በአዲስ አበባ ከተማ ስለከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የወጣ አዋጅ 818/2006 ላይ በአንድ ማረጋገጫ ሰፈር የማረጋገጥ ስራው የሚጀመረው የሰነድ አልባና ህገ ወጥ ይዞታዎች ሙሉ ለሙሉ ስርዓት መያዛቸው ከተረጋገጠ በኂላ እንደሆነ የተቀመጠ ቢሆንም ቢያንስ በአንድ ሰፈር ከ1-2 ይዞታ የሰነድ አልባ /ህገ ወጥ ይዞታዎች የሚገኙ መሆኑ፣

270. ኤጀንሲው እያንዳንዱ ማህደር የሚደራጀው በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድን ቁራሽ መሬት ለመለየት በሚያስችል መልኩ የወጣውን ስታንዳርድ ተከትሎ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል።

በአዲስ አበባ ከተማ በከተማ ካዳስተር ቅየሳ መመሪያ ቁጥር 44/2007 እና በከተማ ካዳስተር ቅየሳ ስታንዳርድ ቁጥር 04/2007 የቁራሽ መሬት መለያ ኮድ አሰጣጥን በተመለከተ የተቀመጠ ቢሆንም በክፍለ ከተማውም ሆነ በሌሎች ክፍለ ከተሞች ያለው አሰራር ግን የተለየና ኮዱ የሚሰጠው ለመሬት ይዞታ ምዝገባው ሲባል በለማው ሲስተም አማካኝነት መሆኑ፣የሚሰጡት ኮዶችም ተከታታይነት የሌላቸውና የዲጂቶችም ብዛት በስታንዳርዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት አለመሆኑ ለምሳሌ ለኮንዶሚኒየም ይዞታዎች -- እስከ 22 የፊደልና የቁጥር ዲጂቶችን እየተጠቀሙ መሆኑ፣

271. ኤጀንሲው የምዝገባ ተቋሙ ወደ ስልታዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሂደት ከመግባቱ በፊት የካዳስተር መሰረታዊ ካርታው ከመሬት ይዞታ ማህደሮች ጋር ተሳስሮ ለካዳስተር ቅየሳ ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠሩ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል።

272. ይሆን እንጂ በሃያ ሶስቱ ከተሞች ፕሮጀክት ዋነኛ ውጤት በሆኑት የዲጂታል መስመር ካርታና ኦርቶሞዛይክ ላይ በተደረገ ጥናት በሃዋሳ በሁለት የምዝገባ ሰፈሮች በነበረው የማረጋገጥ ሂደት የይዞታ ካርታ ማምረት ስራው ይሰራ የነበረው ሙሉ በሙሉ በመስክ ቅየሳ (ቶታል ስቴሽን) በመጠቀም መሆኑ፣የዲጂታል መስመር ካርታ እና ኦርቶሞዛይክ በሃዋሳ ከተማ በተሰራው የይዞታ ምዝገባ ስራ ያልተተገበረ መሆኑ፣መረጃዎች ከታለመላቸው ዓላማ፣ከወጣባቸው ወጪ እና ለመመረት ከወሰዱት ጊዜ አንጻር ሲታይ እየሰጡ ያሉት ጥቅም ይህ ነው የማይባል መሆኑ፣

273. ኤጀንሲው የካዳስተር ቅየሳ ከመጀመሩ በፊት ለካዳስተር ስራ የሚሆን መነሻ የከተማ ካዳስተር መሰረታዊ ካርታ ሃገራዊ ስታንዳርድ ጠብቆ መዘጋጀቱንና ለካዳስተር ቅየሳ ጥቅም ላይ የሚውል መሆኑን ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል።

ለሃያ ሶስቱ ከተሞች በተዘጋጀ የኦርቶ ሞዛይክና የመስመር ካርታ የተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ገጽታዎች መገኘት ካለባቸው ቦታ ርቆ መገኘት፣መረጃዎች ወጥነት ባለው መልኩ አለመገኘት፣ የሞዛይክና የመስመር ካርታ አለመጣጣም፣የኦርቶ ፎቶዎች መጋጠሚያ መስመር በትክክል እርማት አለመስራት፣የመረጃ ስርዓት መጓደልና በሞዛይኮች መጋጠሚያ ላይ የጥቁር መስመር መታየት ከተገኙ ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ፣እነዚህ የተለዩ ችግሮችን ስርዓት ባለው የጥራት ቁጥጥርና ማረጋገጫ ወቅት መለየትና ወደ አመረተው ክፍል ተመልሰው መፍትሄ እንዲሰጣቸው መደረግ የነበረባቸው መሆኑ፣

274. ኤጀንሲው ህጋዊ ካዳስተርን ተግባራዊ ለማደረግ እንዲችል ወቅታዊና የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ያገኘና የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል።

ሆኖም በኤጀንሲው አዲስ የተጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በሚመለከተው አካል ጸድቆ ወደ ተግባር ያልተገባ መሆኑ፣በ2009 በጀት ዓመት ለኤጀንሲው በነባሩ መዋቅር የተፈቀደ የሰው ሀይል ብዛት 126 ሲሆን በስራ ላይ ያለው 69 ወይንም 54.8% መሆኑ፣በዘርፉ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ፤ስታንዳርዶችን ለማዘጋጀት እና ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል ብቃት በተሟላ ሁኔታ አለመኖር፤ከአመራር ጀምሮ እስከ ባለሙያ ድረስ በፌዴራል ተቋም እና በክልልም ደረጃ የሚፈለገው ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ያልተሟላ መሆኑ፣

275. ኤጀንሲው የፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ምክር ቤት ሊኖረው ይገባል።

በኤጀንሲው በማቋቋሚያ ደንቡ በተቀመጠው መሰረት የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረትን ለመመዝገብ በሚነደፉ ዋና ዋና ግቦች ላይ የሚመክር፣ሀሳብ የሚያቀርብ፣የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረትን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ የመረጃ መሰረት ልማትን የማልማት፣ የማመንጨት፣የማምረት፣የማሻሻል፣የማስተዳደር ሂደቶችን አፈጻጸም የሚገመግም፣በጥናት በግብረ መልስ በተለዩ ችግሮች ላይ ተወያይቶ የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ምክር ቤት ያልተቋቋመ መሆኑ፣

### 20.1በውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማነት

276. የኦዲቱ አላማ፡-ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታፕሮጀክትወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማበሆነመልኩ እያከናወነ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፤ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው።

277. የኦዲቱ አካባቢ፡-ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ"የመገጭ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን እና አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን መገምገም" የሚል ነው።

278. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እና በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን ለመተግበር የሚያስችለው ፕሮጀክቶች የሚመሩበትደንብና መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህ ኦዲት እስከ ተከናወነበት ጊዜ ድረስ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ወቅት ከላይ የተገለጹትን ጉዳዮች አስመልክቶ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እና አዳዲስ ክስተቶችን መሰረት ያደረገ ጥናት በማጥናት ደንብና መመሪያ እንዳላወጣና እንዳልተገበረ በኦዲቱ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

279. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶችን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ሊያከናውን ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመገጭ መስኖ ግንባታ ወቅት እንዚህን መመሪያዎች ተግባራዊ ስለማድረጉ በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ማጣራት መመሪያዎቹ የመስኖ ግድብ ግንባታ አፈጻጸምን የሚከታተለውና የሚቆጣጠረው የመስኖና ድሬኔጅ ዳይሬክቶሬት እጅ እንደማይገኙና ተግባራዊ እንዳልተደረጉ፣ ነገር ግን መመሪያዎቹ በፕላኒንግ እና የውጭ ግንኙነት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት እንደሚገኙ፣ ለወደፊቱ ግን ስራ ላይ እንደሚያውሏቸው ለውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ሚኒስተር ዲኤታ፣ ለሚመለከታቸው የውኃ መስኖና ድሬኔጅ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና ፕሮጀክት አስተባባሪዎች ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

280. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመስኖ ግድብ ግንባታ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የመስሪያ ቤቱንና የስራውን ነባራዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የውለታ ማስተዳደሪያ እስታንዳርድ ማንዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የመገጭ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም ከ40% በላይ እስከተከናወነበት እስከ ህዳር 2010 ዓ/ም ድረስ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅት ተችሏል፡፡

281. የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ እና በጀት ከመለቀቁ በፊት በሚመለከታቸው ገለልተኛ ባለሞያዎች የተገመገመ የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት /Pre-feasibility and feasibility Study/ ሊዘጋጅለት እና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን የያዘ ፕሮፋይል ሊኖረው ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት የመገጭ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ እና በጀት ከመለቀቁ በፊት የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት /Pre-feasibility and

feasibility Study/ የተሰራለት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ጥናቱ በሌሎች ባለሞያዎች የተገመገመ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

282. የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ እና በጀት ከመለቀቁ በፊት በባለሞያዎች የተገመገመ፣ የተሟላና የጸደቀ ዲዛይን ሊኖረው ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ስር በነበረበት ወቅት የፕሮጀክቱ ስራ ከመጀመሩ በፊት የመስኖ ግድቡ የግንባታ ዲዛይን ታህል በሚባል የእስራኤል ካምፓኒ እንደተሰራ፡፡ የዋናው ግድብ የመሰረት ቁፋሮ / design excavation level/፣ የሙሌት ስራ/Grouting work/ ፣ /የውኃ መቆጣጠሪያ ማማ/Intake tower/፣ Conduit፣ instrumentation location፣የመስኖ ውሃ ማስወጫ ቱቦ መሠረት እና የስፒል ዌይ ዊንግ ዎል/Spill way wing wall/ የዲዛይን ማስተካከያ የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የመስኖ ግድቡ ግንባታ ዲዛይን በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በሌላ ገለልተኛ የመንግስት ተቋም የቅድመ ትግበራ ግምገማ እንደተደረገበት የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ማግኘት አልተቻለም፡፡

283. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ጥበቃ /ተጽእኖ/ ግምገማ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ሆኖም የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ዶክመንቱ ሲዘጋጅ ለአካባቢ ደህንነት የሚውል በጀት አለመመደቡና ይህንን ስራ በሃላፊነት የተሰጠው (ባለቤት) አለመኖሩ ከመገለጹ ባሻገር እስከ ጥቅምት 2010 ዓ/ም በመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የአካባቢ አጠባበቅን ትግበራ የሚያስፈፅም የአካባቢ አሃድ (Environmental unit) ወይም ባለሙያ አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው የመስክ ጉብኝት ለመረዳት ተችሏል፡፡

284. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ በፊት ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል መዋቅር ሊኖረው እና በመዋቅሩ መሰረት የተቀመጠውን የሰው ኃይል በስብጥሩ መሰረት ሊያሟላ ይገባል፡፡

ሆኖም በሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ 2009 ዓ/ም መጨረሻ የመስኖና ድሬኔጅ ዳይሬክቶሬት በመደቡ የተፈቀደው የሰራተኛ ብዛት 50 በሰው ሀይል የተሞላ 21፣ ለመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ለመደቡ የተፈቀደው የሰው ሀይል 5 የተሟላው 2 መሆኑ፤

በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመስኖ ግድቦች የማስገንባት የተሰጠው ኃላፊነት ለመወጣት፤ የመስኖ ግድብ ግንባታዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የመዋቅር ችግር እንዳለ በመስኖና ድሬኔጅ ዳይሪክቶሬት ለለውጥ ስራ አመራር ዳይሪክቶሬት በተጻፈው ሪፖርት እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደረገው ቃለ መጠይቅ በወቅቱ በተገኙ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

285. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ለመስራት ሲያቅድ ህብረተሰቡን ያሳተፈና ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡

286. የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ በፊት ግድቡ ሲጠናቀቅቅ ለህብረተሰቡ እና ለሀገር ልማት ያለው ጠቀሜታ ተረድቶ የበኩሉን ተሳትፎ እንዲያበረክት ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ የተሰራው ስራ ክፍተት እንዳለበት ቀጥለው በተዘረዘሩ ጉዳዮች ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ✓ ለፕሮጀክቱ አሸዋ ማምረቻ ተፈቅዶ ስራ የተጀመረበት ቦታ በተለያዩ ባለመብት ነን በሚሉ ግለሰቦችና ማህበራት የተያዘ ነው በሚል እስከ ፍርድ ቤት በመሄድ የስራ ማገጃ በማውጣት የፕሮጀክቱን የስራ እንቅስቃሴ እንዲቆም መደረጉ፤ የፍርድ ቤቱ እግድ እንዲነሳለት ለፍርድ ቤቱ በፕሮጀክት ደረጃ 06/12/2008 ዓ.ም አቤቱታ አቅርቦ በፍርድ ቤቱ በኩል ቀጠሮ እየተራዘመ የእግድ ትዕዛዝ ሳይነሳ እስከ 02/03/09 ዓ.ም ድረስ መቆየቱና ስራ ማስተጓጎሉ፤ ከዚህ በተጨማሪ የፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ ባልተሰጣቸው አካባቢዎች አሸዋ ለማምረትና ለማጓጓዝ ጥረት ያደረገ ቢሆንም የተለያዩ ግለሰቦች ተሽከርካሪዎቻቸውንና ሾፌሮቻቸውን በማገት የአሸዋ አቅርቦት ላይ እንቅፋት መፍጠራቸው፤ በአሸዋ እጥረት ምክንያት የፕሮጀክቱን የግንባታ ስራ በእቅዱ መሰረት ለማከናወን ካለመቻሉ በተጨማሪ በኮርፖሬሽኑ ላይ ግምቱ ከፍተኛ የሆነ የወጪ ጫና እያስከተለ መገኘቱ በኦዲቱ ወቅት ከተገኙ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ✓ የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ላይ እንደሌሎቹ ፕሮጀክት ሁሉ ወሰን ማስከበር እና ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ በህብረተሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎች ዋነኛ ምንጫቸው ፕሮጀክቱ በሚጠናበት ወቅት ህብረተሰቡ ስለ ፕሮጀክቱ ያለውን አስተያየት እንዲሁም ፍላጎት ባካተተ መልክ ጥናቶች ባለመከናወናቸው የመጣ መሆኑን በነሐሴ 2009 ዓ/ም በኢትዮጵያ ቢሄራዊ የፐላን ኮሚሽን በፌደራል

መንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በመገጭ ግድብ የመስኖ ፕሮጀክት ከተደረገው የዳሰሳ ጥናት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

287. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ለማስጀመር ጥቅም ላይ ለሚያውለው መሬት እና ንብረት ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ሰው ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የሚለቀቀው መሬት ሕጋዊ ባለይዞታና ካሣ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረቡን በቅድሚያ ማረጋገጥ አለበት፡፡

288. ሆኖም ለልማት የዋለ መሬት እና ንብረት ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ሰው ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የሚለቀቀው መሬት ሕጋዊ ባለይዞታና ካሣ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረቡን በቅድሚያ መረጋገጥ እንዳለበት ካሳ ክፍያን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/1999 ያመለክታል፡፡ ሆኖም ለመገጭ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ለልማት የሚውል በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተወሰኑ ካሳ ተከፋዮች ለመሬት፣ ለዛፎች እና ለአዝርእት የተከፈለ ካሳ ክፍያ 2007 ዓ/ም ከተከፈለው ውጪ የ2005፣ 2006፣ 2008 እና 2009 ዓ/ም ክፍያው ከመፈጸሙ በፊት መሟላት የነበረበት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ሳይሟላ ክፍያ እንዲፈጸም መደረጉ እንዲሁም ክፍያ ከተፈጸመ በኂላ ሰነዱ እንዲሟላ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ከሚ/ር መ/ቤቱ ፋይናንስ ክፍል ቀርበው ከተከለሱ የካሳ ክፍያ ሰነዶች እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

289. የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት በዕቅድ በተያዘለት የገንዘብ እና የጊዜ በጀት ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

ሆኖም የመገጭ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ዋጋ መጀመሪያ ብር 2,451,953,789.66 ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ብር 5,654,431,490.95 እና ለሶስተኛ ጊዜ ብር 5,667,130,760.53 የተከለሰ መሆኑ ለኦዲቱ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፤

- የመገጭ ግድብ ፕሮጀክት ውል በባለቤቱና በተቋራጩ እ.ኤ.አ በ2008 ከተፈረመ በኃላ በተለያዩ ችግሮች ማለትም በበጀት እጥረት፣ በይገባኛል ጥያቄ እንዲሁም በተቋራጩ የአቅም ውስንነት ምክንያት ግንባታው ለአምስት ዓመታት ያህል ሳይከናወን የቆየ መሆኑ የውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ዋና ስራ አስፈፃሚ ለውሃ መስኖና ኢነርጅ ሚኒስቴር የመገጭ ግድብ የግንባታ ዋጋ ማሻሻያ ጥያቄን በሚመለከት በቁጥር ውሥዲ137/392/06 በቀን 18/10/06 ዓ.ም በተፃፈው ደብዳቤ ለመረዳት ተችሏል፤

- እንደገና ፕሮጀክቱ ግንባታው በጥር 2004 ዓ/ም ተጀምሮ ከ4 (አራት) ዓመት በኋላ መጋቢት 2009 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ውል ቢገባም በተለያዩ ምክንያቶች 2 ዓመት ከ2 ወራት ጊዜ ተጨምሮ የሚጠናቀቅበት ቀን ወደ ግንቦት 23/2011 ዓ/ም የተራዘመ መሆኑ፤ ነገር ግን፡-
    - ✓ በዲዛይኑ መሰረት የግድቡ ቁፋሮ ይገኛል ተብሎ የተቀመጠ ፋውንዴሽን ልዩነት መፍጠሩ፣
    - ✓ የመስኖ ውሃ ማስወጫ ቱቦ Condit በተሟላ መልኩ በጥናቱ ያልተካተተ እና በጥናቱ ያልተለየ የነበረ መሆኑ እና እንደ አዲስ እንዲካተት መደረጉ፣
    - ✓ የፍሊተር ማቴሪያል (አሸዋ) በጥናቱ ለፕሮጀክቱ ያስፈልጋል ተብሎ በተለየው ቦታ ላይ ፕሮጀክቱ አፈጻጸም 30 % ሳይሞላው በማለቁ  በጥናቱ ከተቀመጠው ወደ ሰሜን 110 ኪ.ሜ ወደ ደቡብ 70 ኪ.ሜ ርቆ በሌላ ጥናት የተገኘ መሆኑ (አማካሪውና ስራ ተቋራጩ በጋራ ፈልገው ያገኙት)
    - ✓ እንዲሁም የተደረገው ተጨማሪ ጊዜም ሊጠናቀቅ የቀረው ከአንድ አመት ተኩል በታች ባለበት ሁኔታ ከአማከሪ ድርጅቱ በተገኘ መረጃ መሰረት ግንባታው ያለበት ደረጃ 40 % መሆኑ፣
    - ✓ ስራው ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ኦዲቱ እየተደረገ እስካለበት ድረስ በአማከሪው ድርጅቱ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመስኖና ድሬኔጅ ዳይሬክቶሬት፣ ከአማካሪ ድርጅቱ እና ከራሱ ከስራ ተቋራጩ ከተገኙ ሪፖርቶች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች የስራ ተቋራጩ ስራው ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2010 ዓ/ም የአቅም ውስንነት እንዳለበት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ፕሮጀክቱ በተሻሻለው ጊዜ እና ወጪ ይጠናቀቃል ለማለት እንደማያስደፍር ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ለፕሮጀክቱ መጓተት በኦዲቱ ከተለዩ ምክንያቶች መካከል በየአመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚውል በጀት በተፈለገው ልክ አለመቅረቡ እንዳለ ሆኖ በዋናነት የባለቤቱ የመከታተል እና የመቆጣጠር አቅሙ ውስን መሆኑ፣ በወቅቱ አስፈላጊ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎችን አለመወሰዱ  እንዲሁም ለስራው ወሳኝ የሆኑ ውሳኔዎችን በተሎ አለመወሰኑ ዋነኞቹ ቢሆኑም የአማካሪ ድርጅቱና የስራ ተቋራጩ የአቅም ውስንነትም ቀላል ድርሻ እንዳልነበረው   ከተሰበሰቡና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመራዳት ትችሏል፡፡

290. ሚኒስቴር መ/ቤቱ /ፕሮጀክት አስተባባሪው / በየወሩ፣ በየሩብ አመቱ፣ ከአማካሪ ድርጅቱ የሚላኩ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም የሚያስረዱ ሪፖርቶች መሰረት በማድረግ ወይም በሌላ

የግዜ ሰሌዳ በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ የመስክ ምልከታ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት የጽሁፍ ግብረመልስ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

291. ሆኖም እስከ ነሐሴ 2009ዓ/ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቱን በኃላፊነት የሚመሩ የመስኖና ድሬኔጅ ዳይሪክቶሬት እና ፕሮጀክት አስተባባሪው በታቀደ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ ፕሮጀክቱን ባለበት ሂደው የመስክ ምልከታ ለማድረግ መስክ ወጥተው ምን እንደሚየዩ፣ መቼ እንደሚሄዱና ስራው ስንት ቀን እንደሚፈጅ፣ ለስራው የሚያስፈልግ የባለሞያ ስብጥር በሚያሳይ ፣ የሚያስፈልገውን በጀት በመመደብ ክትትል ያለደረጉ መሆኑ እና በመስክ በክትትል የታዩ የፕሮጀከረቱን አፈጻጸም አፈጻጸም የሚያሳይ /ጠንካራና ደካማ ጎን/ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የተደረገበት የመስክ ምልከታ ግብረመልስ የጽሁፍ ሰነድ የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ እና በተከለሰው ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

292. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ወጪ እየተገነባ የሚገገኝ የመገጭ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ከመስኖ እርሻ መሬት ዝግጅት እና ከመጠጥ ውኃ መስመር ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ጋር የተቀናጀ የጋራ ዕቅድ እንዲኖር በማድረግ አፈጻጸሙን ሊገመግም ይገባል፡፡

ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ወጪ እየተገነባ የሚገኘው የመገጭ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የሚጠበቅበትን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች በተያዘው ጊዜ /ዕቅድ/ እንዲሰጥ የመስኖ ግድቡ ግንባታው፣ ከውኃ መስመር ዝርጋታና የመስኖ እርሻ መሬት ዝግጅት ጋር የተቀናጀ የጋራ ዕቅድ እንደሌለው፤ አፈጻጸሙን ከሚመለከታቸው አካላት በጋራ እንደማይገመግም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስጃዎች ለመረዳት ተችሏል፤

## 20.2 በውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የዛሬማ ሜይዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም ብቃት ባለውና ውጤታማ

293. የኦዲቱ አካባቢ፡-ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ፣ የዛሬማ ሜይዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን እና አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን መገምገም የሚል ነው፡

294. የኦዲቱ አላማ፡-የውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የዛሬማ መይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ሥራ አፈጻጸም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ በተያዘለት የጊዜና

የገንዘብ በጀት መጠናቀቁን ለመገምገም ሲሆን በስራው ወቅት የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ለመስፈን ነው፡፡

295. የዛሬማ መይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ እና በጀት ከመለቀቁ በፊት በሚመለከታቸው ገለልተኛ ባለሞያዎች የተገመገመ የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት /Pre-feasibility and feasibility Study/ ሊዘጋጅለት እና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን የያዘ ፕሮፋይል ሊኖረው ይገባል፡፡

296. በኦዲቱ ወቅት የዛሬማ ሜይዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ እና በጀት ከመለቀቁ በፊት የቅድመ አዋጭነት /Pre-feasibility Study/ ያልተሰራለት መሆኑንና ጥናቱ ስራው በተጀመረበት በስኳር ኮርፖሬሽን መሰራት የነበረበት መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በእስቲዲዮ ጋሊ ኢንጅነሪያ አማካሪ ድርጅት የተሰራ የአዋጭነት ጥናት/ feasibility Study/ የቀረበ ቢሆንም ግንባታው ስራ ከጀመረ በኋላ የተሰራ ከመሆኑም ባሻገር በሚመለከታቸው ባለሞያዎች ስለመገምገሙና ይሁንታ ስለማግኘቱ የሚያስረዳ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

297. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን በተመለከተ የስኳር ኮርፖሬሽን የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ በ15/01/2010 ዓ/ም ለኦዲቱ በሰጡት የጽሁፍ ማስረጃ መሰረት የዛሬማ ሜይዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ በፊት የተሰራና የጸደቀ የቅድመ አዋጭነት ጥናት እና የአዋጭነት ጥናት እንደሌለ ነገር ግን ስራው ከጀመረ በኋላ እ.ኤ.አ ታህሳስ 2011 ረቂቅ የአዋጭነት ጥናት ቢጠናም ያልጸደቀ እና በገለልተኛ ባለሞያዎች ያልተገመገመ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

298. የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ እና በጀት ከመለቀቁ በፊት የተሟላና የጸደቀ ዲዛይን ሊኖረው ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት በስኳር ኮርፖሬሽን ስር በነበረበት ወቅት በቀድሞ የውኃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ከመነሻው የፕሮጀክቱ ዲዛይን የተከናወነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ይሁን እንጂ የመስኖ ግድብ ግንባታው ዲዛይን የተሟላና የጸደቀ ስለመሆኑ ለማጣራት በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡና ከተከለሱ ማስረጃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ የዛሬማ መይጼይ መስኖ ግድብ ግንባታ ዲዛይን ስራ የተሰራው በስኳር ኮርፖሬሽን መሆኑ፣
- ✓ የዛሬማ መይጼይ መስኖ ግድብ ግንባታ ዲዛይን ሁሉንም የግድቡ አካላትና ተያያዥ ስትራክቸሮችን የሚያጠቃልል እንዳልነበረ፣
- ✓ በዚህ ዲዛይን መሰረት የግድቡ አይነት በአፈር ሙሌት የሚገነባ /EARTHFILL EMBANKMENT DAM / የሚባል እንደነበረ እና በዚሁ ዲዛይን የሎት 1 /CONSTRUCTION OF EMBANKMENT DAM AND DIVERSION STRUCTURES / ውለታ ተፈርሞ የግንባታ ስራው መጀመሩ፤
- ✓ የዲዛይን ስራውን እንዲያከናውን የማማከር ውል የነበረው የቀድሞ የውኃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ደረጃውን ያልጠበቀና ዘገምተኛ የስራ አፈጻጸም የነበረው መሆኑን እንዲሁም ይጠበቁ የነበሩ የዲዛይን ውጤቶችን በወቅቱ ሊያቀርብ አለመቻሉ፣
- ✓ ተሰርቷል ተብሎ የቀረበው ዲዛይን በሞያው በቂ ልምድ ያላቸው ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ሞያተኞች ባደረጉት ግምገማ ዲዛይኑ ዝቅተኛና ደረጃውን ያልጠበቀ ከመሆኑም በላይ ወደ ተግባር ሊያስገባ የሚችል ሰነድ ባለመሆኑና የተቀጠረውን የስራ ተቋራጭ ለረጅም ጊዜ ስራ በማስፈታቱ ከስኳር ኮርፖሬሽን ጋር የነበረው ውለታ እንዲቋረጥ ተደርጎ የማማከርና የዲዛይን ስራው በቀጥታ ስቴዲዮ ጋሊ ኢንጅኔሪያ ለተባለ የውጭ ድርጅት የተሰጠው በኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ስብሰባ መወሰኑ፤
- ✓ የመጀመያው ዲዛይን በተለይ የስትራክቸር ስራው በስቴዲዮ ጋሊ ኢንጅኔሪያ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ መከለሱ፣
- ✓ የቀድሞው ዲዛይን የቦታውን ጂኦሎጂካል ሁኔታ የማያሟላ በመሆኑ በዲዛይኑ ክለሳ መሰረት በመጀመሪያው ዲዛይን የነበረው የአፈር ሙሌት(EARTHFILL EMBANKMENT DAM) ወደ ድንጋይ ወይም አለት ሙሌት (ROCKFILL EMBANKMENT DAM) መለወጡን፣
- ✓ በዲዛይን ክለሳው ወቅት በመጀመሪያው ዲዛይን ውስጥ ያልተካተቱ ስራዎች (spillway, irrigation intake pressure tunnel and irrigation intake right creek diversion, left creek diversion, road, bridge, approach channel, intake tower, cut and cover towers, outlet tower, outlet channel, road outlet) በዲዛይኑ እንዲካተቱ መደረጉ፣

- ✓ በዲዛይኑ ክለሳ የግድቡ የሙሌት አይነት በመለወጡና አዳዲስ የስራ አይነቶች በመጨመራቸው ለተጨመሩት አዲስ የስራ አይነቶች የነጠላ ዋጋ ያካተተ የውለታ ማሻሻያ ቁጥር 1 እ.ኤ.አ በየካቲት 13/2013 ከስራ ተቋራጩ ጋር የተፈረመ መሆኑ፣
- ✓ ዲዛይኑና ግንባታው ጎን ለጎን እንደሚከናወኑ ታሳቢ በማድረግ የመጀመርያው ውለታ የተፈረመ በመሆኑ፣
- ✓ በተጨማሪም በዚህም የተነሳ የግድቡ አይነት ከመለወጡም በተጨማሪ በርካታ የግድቡ ተያያዥ አካላት በመጨመራቸው ቀድሞ በነበረው ኮንትራት ሥራው የሚከናወንበት አግባብ እንዳይኖር ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፤

299. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ጥበቃ ግምገማ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

300. ሆኖም የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ጥበቃ ግምገማ ስለመደረጉ የሚያስረዳ ጸድቆ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገ ሰነድ በኦዲቱ ወቅት አልተገኘም፤ እንዲሁም በስኳር ኮርፖሬሽን ሆነ በውኃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር እስከ ነሐሴ 2009 ዓ/ም የአካባቢ አጠባበቅን ትግበራ የሚያስፈፅም የአካባቢ አሃድ (Environmental unit) ወይም ባለሙያ ስለመኖሩ እና ለዚህም አስፈላጊ በጀት ስለመመደቡና ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም በፕሮጀክቱ ውስጥ የአካባቢ ጉዳይን የሚከታተል የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያ አለመኖሩ ሁለት ጊዜ በተደረገው የመስክ ጉብኝትና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀረበው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

    እንዲሁም የግድቡ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ጥበቃ ግምገማ ሰነድ መዘጋጀት የነበረበት ስራው በተጀመረበት በስኳር ኮርፖሬሽን እንደሆነ፤ ነገር ግን ውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴርም ስራውን ከተረከበበት ከሚያዚያ 2008 ዓ/ም ወይም የግድቡ አፈጻጸም ከ40% እስከ 90% በላይ እስከደረሰበት ጊዜ እስከ 2009 ዓ/ም ይህንን ችግር ተረድቶ የመፍትሄ እርምጃ ስለመውሰዱ የሚያስረዳ ሰነድ በኦዲቱ ወቅት አልቀረበም፡፡

301. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ በፊት ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል መዋቅር ሊኖረው እና በመዋቅሩ መሰረት የተቀመጠውን የሰው ኃይል በስብጥሩ መሰረት ሊያሟላ ይገባል፡፡

ሆኖም በሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ 2009 ዓ/ም መጨረሻ የመስኖና ድሬኔጅ ዳይሬክቶሬት በመደቡ የተፈቀደው የሰራተኛ ብዛት 50 ቢሆንም በሰው ሀይል የተሟላው 21 ብቻ መሆኑን፣ ለዛሬማ መይዴይ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ለመደቡ የተፈቀደው የሰው ሀይል ብዛት 18 ቢሆንም የተሟላው 1 ብቻ መሆኑን እሱም የፕሮጀክት አስተባባሪው ሲሆን ሌሎች ፕሮጀክቶች የሚመራ በመሆኑ የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ደርቦ እንዲከታተለው ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑ፤ በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግድብ ግንባታ ፕሮጀክቱን ከስኳር ኮርፖሬሽን ሲረከበው 40% የደረሰ ቢሆንም የግድቡ ግንባታ አፈጻጸም 90% አካባቢ እስኪደርስ እስከ ነሐሴ 2009 ዓ/ም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በቋሚነት ፕሮጀክቱ ባለበት /ሳይት/ ሆኖ የሚከታተል ባለሞያ አለመመደቡ ከተሰበሰበው ማስረጃና ከተደረገው መስክ ጉብኝት ለመረዳት ትችሏል፡፡

302. የዛሬማ ሜይዴይ  የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የዲዛይን ሥራ፣ የስራ ተቋራጭ እና የአማካሪ ድርጅት ግዢ የመንግስት ግዥ ዘዴዎች መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

303. ሆኖም የቀድሞ የኢትዮጵያ የዉሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ምንም እንኳ መንግስታዊ ተቋም ቢሆንም የዛሬማ ሜይ ዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የዲዛይን ስራውን ለመስራት በቅድሚያ አቅም ያለው ስለመሆኑ በሚመለከታቸው አካላት ስለመገምገሙ ለማረጋገጥ በተደረገው የሰነድ ማስረጃ ክለሳ ቀጥለው የተዘረዘሩ ነጥቦች ተገኝቷል፡-

- ✓ ድርጅቱ የግድቡን ዲዛይን ለመስራት በገባዉ ዉል መሠረት ደረጀዉን የጠበቀ እና በተባለው ጊዜ ዉስጥ ሰርቶ ማቅረብ አለመቻሉ፤
- ✓ ተሰርተዋል ተብሎ የቀረበዉ ዲዛይን በሙያው በቂ ልምድ ያካበቱ ከተለያዩ ተቋማት የተዉጣጡ ባለሙያዎች ባደረጉት ግምገማ ዲዛይኑ ደካማ እና ከደረጃ በታች መሆኑ በማረጋገጣቸው ውሉ ተቋርጦ ለሌላ የውጭ ሀገር ድርጅት ስራው መሰጠቱ፣
- ✓ በተጨማሪ የዛሬማ ሜይዴይ  የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የዲዛይን ሥራ፣ የስራ ተቋራጭ እና የአማካሪ ድርጅት ግዢ ስራው በጀመረው በስኳር ኮርፖሬሽን የተከናወነ መሆኑ በኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ✓ በአጠቃላይ ድርጅቱ አቅም ያለው ስለመሆኑ የተገመገመበት የሰነድ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት አለመቅረቡ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

304. የስኳር ኮርፖሬሽን የበላይ ሥራ አመራር ግንቦት 21-22/2005 ዓ.ም በአካሄዱት ስብሰባ ያለ ጨረታ በቀጥታ ለ SGI Studio Galli Ingegneria S.P.A in association with SC Sembenelli Consulting S.R.L and Metaferia Consulting Engineers PLC በተሰኘ የዉጭ አማካሪ ድርጅት የዲዛይን ሥራ እንዲያከናዉን መወሰኑን ከቃለ-ጉበኤዉ ለመራዳት ተችሏል፡፡

305. ምንም እንኳ ሥራ ተቋራጩ /ሱር ኮንስትራክሽን/ ለሥራዉ ባለዉ ተነሳሽነት እና አቅም እንዲሁም የዛሬማ መይዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ዉስብስብነት ተገንዝቦ አዲስ ቴክኖሎጅ (New technology ) ለሚተገብር በመስኩ ልምድ ያለዉ ንዑስ የሥራ ተቋራጭ (sub-contractor) በመቅጠር እና የመንግስት የፋይናንስ እጥረት ሳያስቆመው ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ ሳይከፈለው በገባው ዉለታና ሥራ መርሃ-ግብር (Schedules) መሠረት የግድቡን ግንባታ በተያዘለት ጊዜ ዉስጥ ለመጠናቀቅ ቀን ከሌሊት ያለውን ሙሉ አቅም በማንቀሳቀስ እየሰራ አፈጻጸሙ ከ90 % በላይ ያደረሰው መሆኑን በመስክ ምልከታ ጊዜ እና በኦዲቱ በተከለሱ ማስረጃዎች ለመገንዘብ ቢቻልም ሥራ ተቋራጩ የግድቡን ሥራ ለመሥራት ሲቀጥር የመንግስት የግዥ አፈጻጸም ዘዴ አዋጅ የሚደነግገውን ጨረታ በተከተለ መንገድ አለመሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

306. የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት በዕቅድ በተያዘለት የገንዘብ እና የጊዜ በጀት ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

307. ይሁን እንጂ የዛሬማ መይደይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት በጥቅምት17/2011እ.ኤ.አ በብር 4,179,655,504.67 (ብር አራት ቢሊዮን አንድ መቶ ሳበ ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሰ አምስት ሺህ አምስት መቶ አራት ከ67/100 ሳንትም ብቻ) የተፈረመዉ ዉለታ ባልተሟላ ዲዛይን ግንባታ ከመጀመሩም በላይ በአዲስ መልክ በSGI Studio Galli Ingegneria S.P.A in association with SC Sembenelli Consulting S.R.L and Metaferia Consulting Engineers PLC በተሠራ ዲዛይን መሠረት የፕሮጀክቱን ዋጋ መጀመሪያ ከነበረው 347.7 % ጨምሮ ወደ ብር 14,532,594,103.68 (ብር አሥራ አራት ቢሊዮን አምስት መቶ ሰለሳ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠነ አራት ሺህ አንድ መቶ ሶስት ከ68/100 ሳንትም ብቻ) ከፍ እንዲል እና የኮንትራት ዉለታው እንደገና እንዲከለስ አስገዳጅ ሁኔታ እንዲፈጥር ማድረጉን በኦዲቱ ወቅት በተከለሱ ዶክመንቶች ለመረዳት ተችሏል፤ በተጨማሪ፡-

✓ የግራውቲንግ ስራው ውለታው ላይ ከተቀመጠው የ60% ጭማሪ ያለው በመሆኑ፤

- ✓ ውለታው ሲታሰር የዲዛይን ስራቸው ያላለቁ ስራዎች ውለታው ላይ ሳይካተቱ በመቅረታቸው፤ ለምሳሌ (የintake Electro mechanical) ስራዎች፤
- ✓ በአማካሪ ድርጅቱ የተሟላ ዲዛይን ቢቀርብ እንኳን በስኳር ኮርፖሬሽን ያለ ምንም ቴክኒካል ምክንያት (Without any technical background) ዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያዝዘዉን የግድቡን እስታንዳርድ የሆነዉን የመሀል ደረጃ ዉሃ ማስወጫ (Middle level outlet) የሚባል እስትራክቸር እንዲቀር መደረጉ ነገር ግን አሁን ስለ አስፈላጊነቱ በቀረበው ጥያቄ መሰረት ውሳኔ እየተጠባበቀ የሚገኝ በመሆኑ፤

308. በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ የተጨመሩ እና ያልተጀመሩ ስራዎች በመኖራቸው ምክንያት የዛሬማ ሜይዴይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ተጠናቆ የሚጠበቅበትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እስኪሰጥ ምን ያህል ገንዘብ እና ጊዜ እንደሚያስፈልገው ኦዲቱ እስከተደረገበት ጊዜ የማይታወቅ መሆኑ ከቀረቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

309. ሚኒስቴር መ/ቤቱ /ፕሮጀክት አስተባባሪው / በየወሩ፣ በየሩብ አመቱ፣ ከአማካሪ ድርጅቱ የሚላኩ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም የሚያስረዱ ሪፖርቶች መሰረት በማድረግ ወይም በሌላ የግዜ ሰሌዳ በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ የመስክ ምልከታ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት የጽሁፍ ግብረመልስ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

310. ይሁን እንጂ ከአማካሪ ድርጅቱ የቀረቡ ክፍያ ሰነዶች ከመጽደቃቸውና ክፍያው ከመፈጸሙ በፊት በሪፖርቱ የተቀመጠው ስራ በትክክል ጥራቱን ጠብቆ የተከናወነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቱ በገባው ውል መሰረት ስራውን እያከናወነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ፕሮጀክቱን የሚከታተሉ በሚኒስቴር መ/ቤት ስር የሚገኙ ዳይሪክቶሬቱ እና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ውጤታማ በሆነና በታቀደ ሁኔታ ፕሮጀክቱን ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያስችል እስከ ነሐሴ 2009 ዓ/ም የባለሞያ ስብጥር ያሟላ የሰው ሀይል የሌላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ የግድቡ አፈጻጸም ከስኳር ኮርፖሬሽን ሲረከበው 40 % የደረሰ ቢሆንም ከርክክቡ በኋላ አፈፈጻጸሙ 90% እስኪደርስ ድረስ በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ የመስክ ስራ ባለመሰራቱ ለሚመለከታቸው አካላት የቀረበ የመስክ ምልከታ የጽሁፍ ግብረመልስ አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅና በተደረገው የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

311. በተጨማሪ የታቀደና ተከታታይነት ያለው በተገቢ ባለሞያዎች የተደገፈ የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ባለመኖሩ የዛሬማ ሜይዴይ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ደርበው ከሚከታተሉ የከሰም ተንዳሆ የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ በ01/09/09 ዓ/ም ለኦዲቱ በቀረበው የጽሁፍ መረጃ መሰረት የዛሬማ ሜይደይ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ አፈጻጸም በ2008 ዓ/ም መጨረሻ ከነበረበት 49.38 % ወደ 57.18 % ከፍ እንዲል መደረጉ የተገለጸ ቢሆንም፤ በ18/11/2009 ዓ/ም ፕሮጀክቱ በሚገኝበት መስክ በመውጣት በተደረገው ቃለ መጠይቅና እና ምልከታ መሰረት አፈጻጸሙ 86 % አካባቢ የደረሰ በመሆኑ በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ዙሪያ ከአማካሪ ድርጅቱ እና የፕሮጀክቱ ባለቤት የሚቀርቡ መረጃዎች የተለያዩ መሆናቸው ለመረዳት ተችለዋል፡፡

312. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዛሬማ ሜይዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የመስኖ ግድቡ ግንባታ፣ የመስኖ እርሻ መሬት ዝግጅት እና የስኳር ፋብሪካው ተከላ /ግንባታ/ የተቀናጀ የጋራ ዕቅድ ሊኖር ይገባል፡፡ አፈጻጸሙም ሊገመገም ይገባል፡፡

313. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ወጪ እየተገነባ የሚገኙ የዛሬማ ሜይዴይ መስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የሚጠበቅበትን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች በተያዘው ጊዜ /ዕቅድ/ እንዲሰጥ የመስኖ ግድቡ ግንባታው፣ ከመስኖ እርሻ መሬት ዝግጅት እና የስኳር ፋብሪካው ግንባታ ጋር የተቀናጀ የጋራ ዕቅድ በማውጣት በዕቅዱ መሰረት አፈጻጸሙን ከሚመለከታቸው አካላት በጋራ እንደማይገመግም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የክትትል ኦዲት፡-

### 21.የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት መንገድ ፈንድ አስተዳደር አፈጻጸም በተመለከተ

### እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

314. ድንበር አቋርጠው ከሱዳን ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ በወጋገንባንክ በኩል የሚሰበሰው ገቢ 2009 በጀት አመት ላይ መዘግየት ያልታየ መሆኑ፡፡

315. በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ለማስፈፀም በየካቲት 340/2007 ደንብ መውጣቱ እንዲሁም ዕ/ቤቱ ከፖስታ ቤት አገልግሎት

ድርጅት ጋር ውል በመዋዋል ከመስከረም 2008 ጀምሮ ገቢዎች እየተሰበሰቡ መሆኑ ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት ጥበቃ የሚውል ተጨማሪ ገቢ እንዲገኝ የሚያደርግ ሆኖ ታይቷል፡፡

- በፅ/ቤቱ የቴክኒካል ኦዲት ክፍል ለብቻው መዋቀሩ፡፡
- ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን በተመከተ ፅ/ቤቱ በ3 አይነት አማራጮች የፊዚካልና የፋይናንሻል እቅድ እንዲያዘጋጁ የሚያሳስብ ደብዳቤ እና የእቅድ አቀራረብ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚልክ መሆኑ እና የመንገድ ኤጀንሲዎች የፋናንሻልና የፊዚካል እቅዳቸውን ለፅ/ቤቱ በሚልኩበት ጊዜ በተላከላቸው መስፈርት መሰረት ማቀዳቸውን በቴክኒካል ግምገማ እና ክትትል ባለሙያዎች እየተገመገመ እቅዳቸው የሚፀድቅ መሆኑ ስራዎች በእቅዱ መሰረት እንዲሳኩ እያደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

316. የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በተመለከተ በፅ/ቤቱ የውስጥ የቴክኒካል ክትትልና ግምገማ ቡድን የተካሄዱ የመስክ ግምገማ ሪፖርቶች መኖራቸው፡፡ ፣ በፅ/ቤቱ 1 የቴክኒካል ኦዲት እና በውጭ ዩንቨርስቲዎችን ቀጥረው ያሰሯቸው 3 የቴክኒካል ኦዲት ሪፖርቶች መኖራቸው፤ ክፍያዎች በሚጠየቁበት ጊዜ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና የአማካሪው ሪፖርት እየታዩ መፅደቃቸው፣ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች በእቅድ ተይዘው እየተሰራባቸው መሆኑ፣ በፅ/ቤቱ የውስጥ የፋይናንሻል ኦዲት ክፍል በመንገድ ኤጀንሲዎች ፣በፖስታ ቤት እና በኮሜት ትራንስፖርት ላይ የተሰሩ የተወሰኑ የኦዲት ሪፖርቶች መኖራቸው እና በኦዲት ኮርፖሬሽን በመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ በሚሰሩ ኦዲት ስራዎች እንዲሁም በመንገድ ኤጀንሲዎቹ በውስጥ ኦዲት ለሚሰሩ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ግብረ መልስ መስጠታቸው

- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚቀጠሩ አማካሪዎች ቢጋር (Terms of Reference) TOR በፅ/ቤቱ ተከለሶ መዘጋጀቱ፣
- ጽ/ቤቱ በ 2005 በጀት አመት በጽ/ቤቱ እና በዜጎች (ደንበኞች፣ባለድርሻ አካላት፣ተባባሪ አካላትና ሌሎች) መካከል የተጠናከረ ግንኙነት እንዲኖር እና ግልጽነትና ተጠያቂነት የተላበሰ አሰራር ለማስፈን የዜጎች ቻርተር ያተዘጋጀ ሲሆን በተጨማሪም በ2009 በጀት አመት በጽ/ቤቱ በመንገድ ኤጀንሲዎች ለመንገድ ጥገና ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለሚቀጠሩ አማካሪዎች መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑ

## እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

317. በኢትዮጲያ ነዳጅ ድርጀት በኩል እየተሰበሰበ የሚገኝ ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ እና በነዳጅ ማደያ ድርጅቶች በኩል የሚሰበሰብ ከቅባትና ዘይት መሰብሰብ ያለበት ገቢ ወቅቱን ጠብቀው ገቢ የማያስገቡ መሆኑ፡፡

318. ድንበር አቋርጠው ከጅቡቲ ከሚገቡ ተሸከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ ገቢ በኮሜት ትራንስፖርት(የኢትዮጲያ ባህር ትራንዚት አክሲዮን ማህበር) በኩል የሚሰበሰብ ሲሆን ለፅ/ቤቱ የሽያጭ ሪፖርት የማይቀርብ፣ የመቼ ወር የተሰበሰቢ ገቢ እንዳስገቡ የማይገለፅ እና የሰበሰቡትን ገቢ ወደ ፅ/ቤቱ አካውንት ዘግይቶ የሚያስገቡ መሆኑ፡፡

319. ኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ የ2008 እና የ2009 በጀት አመት ተሰብሳቢ ሂሳብ ወደ ፅ/ቤቱ ምንም አይነት ገቢ ያላስገቡ መሆኑ፡፡ ፅ/ቤቱ ከላካቸው ኩፖኖች ከ2005-2009 በጀት አመት ብዛታቸው 25256 ኩፓን የሚሆኑ ማለትም በአንድ ኩፓን ዋጋ 15 ዶላር በወቅቱ አማካኝ የምንዛሪ ተመን መሰረት(1 ዶላር በ 22.8874 ብር) 8,670,662.62 ብር ገቢ ያላደረገ መሆኑ ፤በተጨማሪም ከኩፓን ቁጥር 040501 — 041500 ብዛታቸው 1000 ኩፓኖች ተሸጦ በሽያጭ ሪፓርት ላይ የቀረበ ቢሆንም ኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ያልተረከበው መሆኑ፡፡

320. ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሸከርካሪዎች የሚሸጡ ኩፖኖች በወቅቱ ባለው የምንዛሬ ምጣኔ መሰረት መሸጣቸውን በተመለከተ ወጋገን ባንክ አ.ማ በሁመራ ቅርንጫፍ በኩል የሚሸጣቸውን ኩፖኖች በአንዱ ቀን የምንዛሬ መጠን ሁሉንም አስልቶ ገቢ የሚያደርግ መሆኑ፡፡ ኮሜት ትራንስፖርት ኩፖኖች በትክክለኛው ምንዛሬ መጠን መሸጣቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መቼ እንደተሸጡ የሚያሳይ ማስረጃ አለመያያዙ፡፡

- ከነዳጅና ቅባት ከአንድ ሊትር የሚሰበሰበው 10 ሳንቲም የገቢ መጠን ያልተሻሻለ መሆኑ፡፡
- ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሸከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ በአግባቡ እና ወቅቱን ጠብቀው እየተሰበሰቡ አለመሆኑ

321. በፈንዱ ገንዘብ ለተሰራው ስራ ተገቢውን ክፍያ መፈጸሙን በተመለከተ የጥገና ስራዎች ተሰርተው ሳይጠናቀቁ እንዳለቁ ተደርጎ ክፍያ የሚጠየቅባቸው አማካሪውም የክፍያ ጥያቄ የሚያፀድቅበት ሁኔታ መኖሩ፣ በአንድ የጥገና መንገድ ላይ በሁለት የተለያዩ የስራ መደቦች ሁለቴ ክፍያ እንደሚፈጸም እንዲሁም አማካሪው ድርጅት የተሰራውን ስራ በመለካት ሳይሆን የነዳጅ ወጪያቸውን ወደ መንገድ ፈንድ ነጠላ ዋጋ ስሌት በመቀየር የሚሰራ መሆኑ፤ አማካሪው ድርጅት በክልል ቢሮ እንደሌለው ክፍያ እንዲያጸድቅ ሲጠየቅ ብቻ እንደሚያፀድቅ ፣መንገድ ኤጀንሲዎች ስር የሚጠገኑ መንገዶች ለመንገድ ጥገና የሚጠቀሙበትን ግብዓት ስለትክክለኝነቱ አማካሪው ላብራቶሪ ቴስት የማያደርግ መሆኑ፣ አማካሪዎች ያላቸው የሰው ሀይል አነስተኛ መሆኑ ይህ ደግሞ ስራዎች ከተሰሩ በኃላ ለመመልከት ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ስራዎችን በቦታው ተገኝቶ እንዲደግፍና ሙያዊ እገዛ በማድረግ ፈንዱ ለታቀደለት ዓላማ እንዲውል አለማስቻሉ፡፡

322. በመንገድ ኤጀንሲዎች የሚቀርቡ እቅዶች በፅ/ቤቱ የሚሰጡ የእቅድ ግምገማዎች በበጀት አመቱ እስከ 2ኛ ሩብ አመት የሚዘገዩ መሆኑ

- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ እቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋል አለበት የሚለውን በተመለከተ በመንገድ ፅ/ቤት ቦርድ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ፈንድ ያፀደቀው በ2008 እና 2009 እስከ 2ኛ ሩብ አመት መዘግየት የሚታይበት ከመሆኑም በተጨማሪ ለመንገድ ኤጀንሲዎች 20 ፐርሰንት ቅድሚያ ክፍያ እንዲጠቀሙ የሚፈቀድላቸው ከ1ኛ-4ኛሩብ አመት የሚዘገይ መሆኑ፡፡
- በናሙና በመስክ ከታዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች እና ማስረጃ በመከለስ በተገኙ ግኝቶች መሰረት የመንገድ ኤጀንሲዎች በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ road mentenance, design and standared መመሪያ ያልደረሳቸውና በዛም መሰረት ተግባራዊ እያደረጉ አለመሆኑ

323. አማካሪዎች በገቡበት ውል መሰረት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን በተመለከተ የአማካሪዎች ቅጥር በወቅቱ የማይፈጸም መሆኑ፣ ከተሞች ከአማካሪዎች ሊያገኙ የሚገባቸውን ክትትል እና ድጋፍ ሳያገኙ የሚሰሩ ስራዎች ጥራት እና ደረጃቸውን ጠብቀው መሰራታቸውን ሳይረጋገጥ እየሰሩ መሆኑ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቱ ከእቅድ አወጣጥ ጀምሮ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ክትትልና ሙያዊ እገዛ ባለማድረጉ የጥገና መስመሮች ተለይተውና ለተለያዩ የጥገና መስመሮች ተገቢ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ

የጥገና ስልት በመለየት ላይ ክፍተት እንዲፈጠር ማድረጉ እንዲሁም አማካሪው በገባው ውል መሰረት በእቅድ የተያዙትን መስመሮች ለይቶ የተመደበላቸው የጥገና ዘዴ ተገቢ መሆኑን ማረጋገጥ እና የተለዩ ክፍተቶችን ለመንገድ ፈንድ ሪፖርት ማድረግ ላይ ክፍተት መኖሩ፣ከአማካሪ ድርጅቱ በቂ የሆነ የቴክኒክ እርዳታ ለመንገድ ኤጀንሲዎች እንደማይደረግላቸው ፣ አማካሪ ድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ ስራዎች በመለየትና በጣም ለተጎዱ የመንገድ ክፍሎች ቅድሚያ በመስጠትና ጥገና የሚፈልጉትን የመንገድ ክፍሎች እና የጥገና አይነቶችን በመለየት የውሉ ሰነዱ በሚያዘው መሰረት ለኮንትራክተሩ የስራ ትእዛዝ በመስጠት ስራዎቹ እንዲከናወኑ አለማድረግ እንዲሁም ከአማካሪዎች ሊያገኙ የሚገባቸውን ክትትል እና ድጋፍ ሳያገኙ የሚሰሩ ስራዎች ጥራት እና ደረጃቸውን ጠብቀው መሰራታቸውን ሳይረጋገጥ እየሰሩ መሆኑ የታዩ ክፍተቶች መሆናቸው፡፡

324. የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በተመለከተ የመስክ ግምገማ ሪፖርቶቹ ወጥ የሆነ ፎርማት ያልተከተሉ መሆናቸው፣ አብዛኛውን የመንገድ ኤጀንሲ የማይሸፍኑ፣ ተከታታይነት የሌላቸው እና በመስክ ምልከታው ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በተሰጡ ግብረመልሶች ስለመስተካከላቸው የተጠናከረ ክትትል የማይደረግባቸው መሆኑ፤ ከኦዲት ኮርፖሬሽን ሪፖርት በመነሳትም ሆነ በውስጥ በተሰሩ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በተሰጡ ግብረመልሶች ስለመስተካከላቸው የተጠናከረ ክትትል የማይደረግባቸው መሆኑ እንደ ክፍተት የታዩ መሆናቸው፡፡

325. በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ በፅ/ቤቱ ከ2005-2009 1 በውስጥ ኦዲት የቴክኒካል ኦዲት እና በዩንቨርስቲዎች የተሰሩ 3 የቴክኒካል ኦዲት ስራዎች ብቻ እንዲሁም በውስጥ ፋይናንሻል ኦዲት ክፍል ከ2007-2009 በጀት አመት ተሰርተዋል ተብለው ከተገለፁ 33 ኦዲት ሪፖርቶች ውስጥ 13ቱ ብቻ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑ፡፡

- በመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ የጥገና ታሪክን፣ በምንያህል ወጪ መቼ እንደተጠገነ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ በተደራጀና ዘመናዊ በሆነ መልኩ ተይዞ የማይገኝ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩ በአንዳንድ የመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ መረጃዎቹ ተሰርቷል ተብሎ የቀረበ ቢሆንም በተሟላና ዘመናዊ በሆነ መልኩ ያለመያዝ ክፍተት መኖሩ

- ለመንገድ ካውንስል ለመንገድ ደህንነት በሚል ፈንድ ከመመደብ ውጪ የተመደበው ፈንድ ለታለመለት አላማ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ የማይደረግ መሆኑ ለዚህም ማሳያ በ2007፣በ2008 እና በ2009 የፋይናንስ አፈፃፀማቸው እንደቅደም ተከተላቸው ሲቀመጥ 0%፣ 0% እና 36.49% ሲሆን አፈፃፀም በማይኖርበት ወይም ዝቅተኛ አፈፃፀም በሚኖራቸው ጊዜ ምንም አይነት ግብረ መልስ ለመንገድ ካውንስል የማይላክ መሆኑ
- ጽ/ቤቱ ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳውቅ መረጃ ወይም መመሪያ ለሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች እንዲደርሳቸው ያላደረገ መሆኑ፣

22. **በፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት በአግባቡ መፈፀሙንና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤**

326. እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ የህብረት ሥራን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦች ተሰባስበው የተቀመጡ መሆኑ፡፡
- በ2009 ዓ.ም የህብረት ስራ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እያተዘጋጀ መሆኑና ረቂቅ ላይ መድረሱ፣
- ባንክና ኢንሹራንስን በተመለከተ የህብረት ስራ ማህበራት ባንክና ኢንሹራንስ እንዲኖራቸው ኤጀንሲው አጥንቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ማቅረቡ
- በአለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) በየጊዜው የሚወጡ ውሳኔዎችንና ስምምነቶችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ የአለም ስራ ድርጅት ከአለም የህብረት ስራ ማህበራት ጋር በመሆን የሚወጣቸውን ነጥቦች በአዲሱ አዋጅ 985/2008 ላይ ለማካተት ከ ILO እና ICA ግብአት መጠየቁ፣
- ፕሮጀክቶችን መቅረፅ በተመለከተ በኤጀንሲው የተቀረፀ አግሮ ፕሮጀክት ክልሎች በግብርና ምርቶች ላይ ለተሰማሩ ህብረት ስራ ማህበራት ላይ የሚሰራ መኖሩ፡፡
- የሶሺዮ ኢኮኖሚ እና አዋጭነት

- የአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅን ወደ ህብረት ስራ ማህበራት ማሰልጠኛ ተቋም ለመቀየር የሚቻልበትን ደንብ አስጠንቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረቡ፣ በረጅም፣በመካከለኛና በአጭር ግዜ ለተቋሙ የሚያስፈልጉ የውስጥ ቁሳቁሶች ለማሟላት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ሰነድ መዘጋጀቱ፣ ተቋሙን ወደ ስራ ለማስገባት የሚያስችል ልምድ በተሞክሮ ከውጭ ሀገራት እንዲገኝ መደረጉ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የስልጠና ካሪኩለም መዘጋጀቱ እና የስራ መዘርዝሮች የረቀቁ መሆናቸው፣ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2002-2005 ዓ.ም ለተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት መጠናቱ፣ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ አማካኝነት ከ2006-2008 ዓ.ም ለሚሰጡ ስልጠናዎች የስልጠና ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት መደረጉ በክትትል ኦዲቱ ወቅት የተስተካከሉ ተግባራት መሆናቸው፣

  ~~23.~~በ 2005 ዓ.ም በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና ከ2006-2008 በጀት አመት በህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም በህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የስልጠና ፍላጎት የተጠና መሆኑ፣

- በፌደራል የህብረት ስራ ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 985 /2008 ህ/ስ/ማህበራት የስራ ቦታ ማግኘት የሚችሉ መሆኑ በአዋጁ እንዲካተት መደረጉ፣ የተገለፀ መሆኑ፣
- በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ሀገር አቀፍ የህብረት ስራ መረጃ አሰባሰብ፣ ትንተና እና ስርጭት የአሰራር ስርዓት ማኑዋል መዘጋጀቱ መሻሻል የታየበት ተግባር መሆኑ፣
- በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን በናሙና በመምረጥ በመመሪያው መሰረት ስለመስራታቸው በቼክ ሊስት የማሻሻያ ሃሳብ በመስጠት እንዲጠናከሩ የማድረግ ሥራ መከናወኑ፣
- የሴቶችና ወጣቶች በማህበራት ተሳትፎ እና በአመራር ሰጪነት ዙሪያ ያላቸውን ድርሻ ለማሳደግ የተዘጋጁ መመሪያዎች በተመለከተ አዲሱ አዋጅ 985/2008 ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ቢያንስ 30 በአመራርነት በሚል መቀመጡ፣ የስርዓተ ፆታ ኦዲት በ2006 በኤጀንሲው መደረጉ እና የስርአተ ፆታን በተመለከተ የተዘጋጀ ማንዋል መኖሩ፣
- አዲሱ የህብረት ስራ አዋጅ (985/2008) የህብረት ስራ ማህበራትን በአመት ቢያንስ 1 ጊዜ ሂሳብ ምርመራ ማካሄድ እንዳለባቸው በአዋጁ እንዲካተት መደረጉ፣
- የኦዲት ሽፋንን ከማሳደግ አኳያ በውክልና ለማስመርመር የሚያስችል መመሪያ እንዲወጣ መደረጉ፣

- በአገር ደረጃ የህብረት ስራ ማህበራትን ደህንነት ለማስጠበቅና በማህበራት ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ተከታትሎ ለማስመለስና ከፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ ወረዳ ድረስ የህግ ባለሙያ መዋቅር ኤጀንሲው የዘረጋ መሆኑ፣
- የብቃት ደረጃ ምስክር ወረቀት ለመሰጠት በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት በ2007 ዓ.ም እንዲዋቀር መደረጉ፣
- በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የተዘጋጁ 4 የንቅናቄ ሰነዶች (የህብረት ስራ ማህበራት ሁሉ አቀፍ ተጠቃሚነት ያረጋግጣሉ የሚል ለ 9ኛው የህብረት ስራ ቀን ለፓናል ውይይት የቀረበ ፅሁፍ ከሰኔ 2-4/2009 ፣ የኢትዮጵያ የህብረት ስራ እንቅስቃሴ ስኬቶችና ተግዳሮቶች በጥር 2007፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት አገራዊ ንቅናቄ ሰነድ በታህሳስ 2009፣ የኢትዮጲያ ህብረት ስራ እንቅስቃሴ ተሞክሮዎች ማነቆዎችና ቀጣይ አቅጣጫዎች ለአ.አ ከተማ ከተማ አስተዳደሮች ለውይይት የቀረበ ሰነድ በመጋቢት 2008) መኖራቸው፣
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለተወሰኑ ህብረት ስራ ዩኒየኖች እና ለክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የአገር ውስጥ የገበያ መረጃዎችን በኢሜል የሚልኩ እና ለተወሰኑ ህብረት ስራ ማህበራት የገበያ ትስስር የተፈጠረ መሆኑ፣

327. እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው፡-

- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን ሊያግዝ የሚችል እንደየ ህብረት ስራ ማህበራት አይነት ፕሮጀክቶችን ቀርፆ ተግባር ላይ አለማዋሉ
- ኤጀንሲው በእቅዱ መሰረት መጋዘኖችን እና የገበያ ማዕከላትን ገንብቶ ለህብረት ስራ ማህበራት አለማስተላለፉ
- ኤጀንሲው የሶሺዮ ኢኮኖሚ እና የአዋጭነት ጥናት አጥንቶ ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት አለማሰራጨቱ
- ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት (እድር፣ መረዳጃ ማህበር ወዘተ) ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናት እና ምርምር አለመደረጉ
- እስከ 2009 በጀት አመት በፌደራል ደረጃ 6 መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ብቻ የተቋቋሙ መሆናቸው እንዲሁም ህብረት ስራ ዩኒየን አለመቋቋሙ፡፡
- ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ከተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲው ያቋቋማቸው ትንሽ መሆኑ

- ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ ዩኒየንና ፌዴሬሽን ለማቋቋም ስምምነት ላይ ያልደረሰ መሆኑ
- በፌዴራል ደረጃ ፌደሬሽን እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ ህብረት ስራ ሊግ ያልተቋቋመ መሆኑ
- በአገሪቱ የህብረት ስራ ማሰልጠኛ አለመቋቋሙ፤ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የስልጠና ፍላጎት ጥናት ከ2004 በጀት አመት በኃላ አለመጠናቱ፣የአገሪቱ ስልጠና እቅዶች አፈፃፀም አናሳ መሆኑ፤ የተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት የማይለካ መሆኑ
- የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጆችና ደንቦች ተግባራዊ ለማድረግ ካዘጋጃቸው 21 የአፈፃፀም መመሪያዎች ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እና ማህበራት በተሟላ መልኩ አለማድረሱ
- የህብረት ስራ ማህበራት ማግኘት የሚገባቸው ማበረታቻዎች አፈፃፀም ላይ ክፍተት መኖሩ
- የህብረት ስራ ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት ስለመስራታቸው እና በዚህ ዙሪያ ስላጋጠሚቸው ችግሮች በየሩብ ዓመቱ ክትትል አለመደረጉ
- ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት አባላትም ሆነ አመራር ሰጭነት ተሳትፎዋቸው እንዲያድግ የተጠናከረ ስራ አለመሰራቱ
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ወጥ ወይንም ለእያንዳንዱ ህብረት ስራ  ዘርፍ የአደረጃጀት መመሪያ አለማውጣቱ
- የህብረት ስራ ማህበራት ወቅቱን የጠበቀ ሂሳብ ምርመራ አለማድረጋቸው፤የኦዲት ሪፖርቶች ለህብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አለመቅረባቸው፤ እንዲሁም በኦዲት ግኝቶቹ ላይ ማህበራቱ ያለባቸውን ክፍተቶች ስለማስተካከላቸው በፌደራል እና በክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች  ክትትል አለማድረጋቸው፤
- የህብረት ስራ ማህበራት ብቃታቸው ተመዝነው የሚያገኙት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በሁሉም ክልሎች በተጠናከረ መልኩ እየተሰራ አለመሆኑ
- የህብረት ስራ ማህበራት የኢንስፔክሽን ሽፋን አናሳ መሆኑ እንዲሁም በኢንስፔክሽን ግብረ መልሶች ላይ ክትትል አለመደረጉ

- የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ስለ ሕብረት ስራ ጠቀሜታ፣ እንቅስቃሴ እና እድገት ለተደራጅዎችና ለባለድርሻ አካላት የተጠናከረ እና ተደራሽ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን አለማዘጋጀታቸው፤
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለህብረት ስራ ማህበራት ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ የማይሰጡ መሆኑ ፣ ለማህበራቱ የተፈጠረው የገበያ ትስስር አነስተኛ መሆኑ፣ የተፈጠሩ የገበያ ትስስሮችም ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣ ህ/ስ/ማህበራቱ የውጭ አገር መረጃ ገበያ መረጃ እንዲያገኙ እንዲሁም ተደራሽ በሆነ መልኩ የአገር ውስጥ የገበያ መረጃ እንዲያገኙ እና የምርትና የገበያ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ አለመደረጉ፤
- የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶቻቸው ላይ እሴት ጨምረው ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ እንዲገቡ አለመደረጉ
- የፌደራል እና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ህብረት ስራ ማህበራት ብድር እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በተጠናከረ እና ተደራሽ በሆነ መልኩ አለማመቻቸታቸው፤
- የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ አገር አቀፍ የህብረት ስራ መረጃ ስብሰባ፣ ትንተና እና ስርጭት የአሰራር ስርዓት ሲያዘጋጅ ከፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ወደ ክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች፣ ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ወደ ዞን፣ ከዞን ወደ ወረዳ፣ ከወረዳ ወደ ህብረት ስራ ማህበራት ለሚሄደው ጊዜ የተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ አለመኖሩ፤
- የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለኤጀንሲው በየሩብ አመቱ እቅድ አፈፃፀም መላክ ቢኖርባቸውም ሁሉም የክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች በተሟላ መልኩ የማይልኩ መሆኑ፣
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በሀገሪቱ ያሉትን የእያንዳንዱን ህብረት ስራ ማህበራት መሰረታዊ መረጃ ማለትም የስም ዝርዝር፣ የተመዘገቡበት ቀን፣ ያስመዘገቡት የካፒታል መጠንና በስራ ላይ ያሉትን የሚገልፅ መረጃ በዳታ ቤዝ ያልያዘ መሆኑ፣
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ጋር በድጋፍ አሰጣጥ ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ (MoU) የሌለው በመሆኑ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዳይኖር ማድረጉ፣

## 23.በስትራቴጂክ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ የምግብ ክምችት አጠባበቅ ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ፡-

328. እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ንብረትነቱ የኤጀንሲው የሆነው የመቀሌና ኮምቦልቻ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ የምድር ሚዛኖች በ2005፣2008 እና 2009 ዓ.ም በሚመለከተው አካል የብቃት ፍተሻ /ካላብሬት/ መደረጉ፣
- የእህል ክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት እና የጥራት ቁጥጥር ስራ አመራር ዳይሮክቶሬት በቅንጅት በቅ/ጽ/ቤት በመገኘት በዕቅድና የጊዜ ሰሌዳ በማስቀመጥ የእህል ክምችት ደህንነት የጥራት ፍተሻ ስራ የሚያካሂድ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የእህል ኦዲትን አስመልክቶ አዲስ አሰራር በመዘርጋቱ በመጋዘን የገባው የእህል ክምችት ሙሉ በሙሉ ከመጋዘን ወጪ ሆኖ ሲያልቅ ኦዲት መደረጉ፣
- ወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚገኙ መጋዘኖች ለሚሰሩ የመጋዘን ክለርኮችና እና ጽዳት ሰራተኞች የእለት ተዕለት ስራዎች የሚያካሂዱበት ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ መሰራቱ ፣
- በአዳማ፣ ወረታና ወላይታ ሶዶ  የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ በመጋዘኖች በውጪኛው በር ላይና በመጋዘኑ ውስጥ በአደጋ ጊዜ የአደጋ ጥሪ የስልክ ቁጥሮች በግልጽና በሚታይ ቦታ ተለጥፎ መገኘቱ፣
- በአዳማ፣በሻሸመኔ እና በወላይታ ሶዶ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከስራ ሰዓት ወጪ አደጋ ቢደርስ የመስመር ስልክ በጥበቃዎች ጋር መኖሩ፣
- በአዳማ ፣በመቀሌ እና በወላይታ ሶዶ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ደረጃውን የጠበቀ ጉድጓድ የተዘጋጀና ጉድጓዱም በቆርቆሮ የታጠረና በቁልፍ የተዘጋጀ በር ያለው መሆኑ፣
- መብራት ቢቋረጥ አገልግሎች ሊሰጡ የሚችሉ ሶስት ጄኔሬተሮች በኤጀንሲው የተገዙ መሆኑ፣

329. እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው

- የመቀሌ እና የኮምቦልቻ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ የምድር ሚዛኖች በ2006፣2007 እና 2010 ዓ.ም በሚመለከተው አካል የብቃት ፋተሸ /ካላብሬት/ ያልተደረጉ መሆኑ፣

- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስር የሚገኘው የምድር ሚዛን የኤጀንሲው ንብረት ባለመሆኑ የምድር ሚዛኑ ካላብሬት መደረግ ከነበረበት ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ብቃቱን በማስፈተሽ የብቃት ደረጃውን ማወቅ አለመቻሉን
- በቅርንጫፉ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የሚገኙት ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች በመንግሥት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ያለመደረጉ
- በወረታ፣ በአዳማ፣ በሻሸመኔ፣ በሽንሌ እና በወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤቶች ኤጀንሲው የራሱ የሆነ የምድር ሚዛን የሌለው በመሆኑ ፣
- በሽንሌ፣ በወላይታ ሶዶ እና በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በቅርንጫፉ የምድር ሚዛን ባለመኖሩ እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ የሚያደርጉ መሆኑ፣
- የምድር ሚዛን ባለባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምድር ሚዛን ቢኖርም እህል ወደ መጋዘን ገቢ እና ወጪ ሲደረግ ባለመመዘኑ በመቀሌ 27185.3 ኩንታል ፣ በሻሸመኔ 23.4 ኩንታል፣ በኮምቦልቻ 735.13 ኩንታል፣ በአዳማ 3026.83 ኩንታል በብልጫ የታየ መሆኑ
- የአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት መጋዘን ቁጥር 36 እና 37 በውጪ ባለሙያ ጥገና የተደረገላቸው ቢሆንም ስራው ውጤታማ ባለመሆኑ ተመልሰው የሚያፈስ በመሆኑ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ መሆኑ፣
- በሻሸመኔ፣ በወረታ እና በአዳማ ቅርንጫፉ ጽ/ቤቶች በሚገኙ የእህል መጋዘን በመጋዘኑ ውስጥ የጣራ ፋሳሽ በመኖሩ እህሉ እንዳይበላሽ በእስታኩ አናት ላይ ሸራ ሸፍነው እየሰሩ መሆኑ፣
- የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ በወር 1 ጊዜ ፍተሸ ያለመደረጉ፣
- የቅርንጫፉ ጽ/ቤት የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ በወር 1 ጊዜ በቅርንጫፉ ጽ/ቤት በሚገኙ የእህል መጋዘኖች ፍተሸ በማካሄድ ሪፖርት ለኤጀንሲው የማያቀርቡ መሆኑ፣
- በቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚገኙ የእህል መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች ፡- የተበላሹ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች ፣ወንበሮች፣የፅዳት ቃዎችና ቆርቆሮዎች በእህል ክምችት መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣

- በሻሸመኔና በወላይታ ሶዶ መጋዘን የኤጀንሲው ንብረት ያልሆኑና በሰነድ ያልተመዘገቡ የሌላ መ/ቤት ንብረት የሆኑ ዱቄት፣ ጥራጥሬ እና ዘይት ከኤጀንሲው እህል ጋር በአንድ መጋዘን ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፣
- የአዳማ፣ ወረታ፣ ሻሸመኔ፣ ወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለመጋዘን ኃላፊዎች፣ ጸሀፊና የጽዳት ሰራተኞች እንዲሁም በወላይታ ሶዶ ለመጋዘን ኃላፊዎች የዘውትር ስራቸውን የሚያከናውኑበት ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ የሌላቸው መሆኑ፣
- በአዳማና መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር በሚገኘው የኤጀንሲው የማዕከሉ የዕቃ መጋዘን ውስጥ የተለያዩ መጠንና አይነት ያላቸው አዲስና አገልግሎት የሰጡ የእሳት ማጥፊያ ሲሊንደሮች የሚገኙ ሲሆን በየ 6 ወሩ ሰርቪስ መደረግ ቢኖርባቸውም እ.ኤ.አ በ26/5/2011 እና በ9/06/2013 ሰርቪስ እንደተደረገላቸው ተከማችተው መገኘታቸው፣
- በወረታ መጋዘን በቅ/ጽ/ቤቱ ውስጥ በሶስቱ ሸራ መጋዘን (ራቦሎች)፣ በወላይታ ሶዶ በሶስቱ ሸራ መጋዘን (ራቦሎች)፣ በኮምቦልቻ መጋዘን በመጋዘን ቁጥር 1 እና 2 ምንም የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ የሌለ መሆኑ፣
- በአዳማ፣ የወላይታ ሶዶ እና ሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤቶች ከ2008 ዓ.ም ወዲህ ለመጋዘን ሰራተኞቹ በእሳት አደጋ መሳሪያ አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ
- በአውሮፓ ህብረት በተሰጠ ዋስትና ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የምግብ ዋስትና ዘርፍ እ.ኤ.አ በሜይ 02/2005 ከተወሰደው ብድር 24,950.57 ሜትሪክ ቶን እህል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከኤጀንሲው የብድር መዝገብ ላይ እንዲዘረዝ የጸደቀበት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣
- ኤጀንሲው እ.ኤ.አ ከ2013-2017 ለአደጋ መከላከል ዝግጁነትና ምግብ ዋስትና ለምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ፣ለገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ ምግብ ዋስትና ዘርፍ እና ለኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በጠቅላላው 996,762.11 ሜትሪክ ቶን እህል ብድር የሰጠ ቢሆንም በጠቅላላ ከሰጠው ብድር ውስጥ 571,242.7 ሜትሪክ ቶን (57.3 % ) እህል ያላስመለሰ መሆኑ፣

- የአዳማ፣ ወረታ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ ሽንሌ እና ሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤቶችን ከዋናው መ/ቤት ጋር በሰርቨር ለማገናኘት አለመቻሉ፣ ኤጀንሲው ዳታ ቤዝ ሲስተም የማይጠቀም በመሆኑ፣
- ኤጀንሲው በእርዳታ ካገኛቸው ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች መካከል ሚዛኖች በብልሽት ምክንያት ለረዥም አመታት አገልግሎት ሳይሰጡ መቀመጣቸው እና የማይሰሩ ሚዛኖችን የሚወገዱበት ስርዓት የሌለው መሆኑ፣
- በኮምቦልቻ፣ በሽንሌ፣ በሻሸመኔ እና በመቀሌ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ መጋዘኖች በሚገኙበት አካባቢዎች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች በግልጽና በተነበባቢ ቦታ ላይ ተለጥፈው የማይገኙ መሆኑ፣
- በኮምቦልቻ፣ በሽንሌ እና በሻሸመኔ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ጉድጓድ ደረጃውን የጠበቀ ያለመሆኑ እና ከእህል ህክምና በኂላ የመድሃኒት መያዥ ጣሳዎች በደንብ ተጨፍልቀው የማይወገዱ መሆኑ፣
- በሽንሌ፣ አዳማ፣ መቀሌና ወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውና የማከም ብቃታቸው አነስተኛ የሆኑ 1,254.2 ኪሎ ግራም አልሙኒየም ፎስፋይድ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣
- በአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት 134.6 ሊትር ማላታይን እስካሁን ድረስ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣
- በወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት አስታይል ባለ 1 ሊትር ፊሻስ አገልግሎት የማይሰጥና የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መድሃኒት በንብረት መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጥ መደረጉ፣
- በሽንሌ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በሚገኙ መጋዘኖች በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ መጋዘኖች መካከል ከሶስት መጋዘኖች በቀር በሌሎቹ፣ በመቀሌ መጋዘን በመጋዘን ቁጥር 08፣ በኮምቦልቻ መጋዘን  ቁጥር 2 ፣ በአዳማ 7 መጋዘኖች የመጋዘን መብራት የሌላቸው በመሆኑ
- በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ጀኔሬተር የሌለ ሲሆን በሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የተገዛው ጄነሬተር ከተበላሸ 8 ወር የሞላው ሲሆን አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣

330. የክትትል ኦዲቶቹ የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

- በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑ ነጥቦች ላይ የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡
- ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሚመለከታቸው በሁሉም አካላት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡

## 24.የንግድ ሚኒስቴር የገቢና ወጪ እቃዎች እና የህጋዊ ስነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

331. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል እንዲደራጁ በማድረግና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣

- ✓ በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት የሰው ኃይል የተሟላ መሆኑን እና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎች/ግብዓቶች/ እንዲሟሉ የተደረገ ሲሆን ያለው ላብራቶሪ አንድ ብቻ በመሆኑ የውጤት መዘግየት የሚፈጠር በመሆኑ በዚህም የተነሳ ደንበኞች ቅሬታ እያቀረቡ እንደሚገኙ፣ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የኮምፒውተር እጥረት፣ የኢንተርኔት አለመኖር፣ የጠረጴዛና የወንበር እጥረቶች መኖራቸውን፣ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የግብዓት፣ የክህሎት/የዕውቀት/ ክፍተቶች፣ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ በወቅቱ አለመድረስ፣ የተሽከርካሪ ችግር፣ ክፍተቶች መኖራቸውን ለሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡
- ✓ በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የሰው ኃይል እና ለስራ የሚሆኑ መገልገያዎችን አለሟሟላቱን፣ በቅ/ፅ/ቤቱ በሰው ሀይል በኩል ፀሀፊ፣ የሒሳብ ሰራተኛ፣ ካሸር፣ ጥበቃ የሌለ መሆኑን፣ ተሽከርካሪ ባለመኖሩም ናሙና ለመውሰድ ከሀዋሳ ሻሸመኔ ድረስ በትራንስፖርት እየሄዱ የሚሰሩ እንደሆነ፣ በቂ የሠው ሀይልና የሥራ መገልገያዎች ባለመኖራቸው ስራቸውን በቅልጥፍና እንዳይሰሩ ማድረጉን፣ በበከልቻ ተወካይ ፅ/ቤት የገንዘብ ያዥ፣ ፀሀፊ፣ የሂሳብ ባለሞያ፣ የፅዳት ባለሞያ ተሟልቶ አለመቀጠሩን፣ ለአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የፅዳት እና የጥበቃ ሰራተኛ አለመቀጠሩ ታውቋል፡፡

- ✓ እንዲሁም የተሸከርካሪ ችግር በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት አሁንም መሰረታዊ መፍትሄ ያላገኘ ችግር መሆኑን፣ በዋናው መ/ቤት፣ በቅ/ፅ/ቤቶችና በህጋዊ ስነ ልክ ቡድን በየሥራ ዘርፉ የሰው ሀይል እጥረት በመኖሩ ቅጥር እንዲፈፀም በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም እስካሁን አለመፈፀሙን፣ በአንዳንድ ቅ/ፅ/ቤቶች የቢሮ ጥበት መኖር እና ለስራ አመቺ ያልሆነ የሥራ ቦታ መኖሩንየደንበኞች ናሙናዎች ከተወሰደ በኂላ ላቦራቶሪ በወቅቱ አለመድረስና ነጋዴውን ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን ከንግድ ሚኒስቴር ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

332. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ያገደ መሆኑን ፣ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፣

  - ✓ የፀሀይ ኢንዱስትሪ አ.ማ. የቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ በኢንቮይስ ቁጥር J-1608-008 DTD እ.ኤ.አ ነሀሴ 08/2016 እና በዲክላራሲዮን ቁጥር C-25329 እና C- 26798 የተመዘገበ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡት ለኮርኒስ ፍሬሞች፣ ለመፃህፍት መደርደሪያዎችና ለኬብል ትሬይ የሚገለገሉበት የተጠቀለለ ልሙጥ የዚንክ ቅብ ቆርቆሮ (coil) በ CES 40 አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መሰረት በላብራቶሪ ተፈትሾ የደረጃውን መስፈርት አላሟላም በማለት ጥሬ እቃው እንዳልተለቀቀላቸው በመግለፅ በመቸገራቸውና ቀጣይ የማምረት ሂደት ማከናወን ባለመቻላቸው መፍትሔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ ማቅረባቸውን፣

  - ✓ የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ፀሀይ ኢንዱስትሪ አ.ማ የቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ በፋብሪካው ግቢ የተራገፈው የተጠቀለለ ልሙጥ የዚንክ ቅብ ቆርቆሮ በምን ስራ ላይ እንደዋለ ከሪጉላቶሪ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ጽ/ቤት እና ከገበያና ድርጅት ኢንስፔክሽን ባለሞያዎች ከአመራሩ በተሰጠው አቅጣጫ በማምረቻ ቦታው ተገኝተው ከላይ የተጠቀሰው ቆርቆሮ በምን አግባብ ጥቅም ላይ እየዋለ እንዳለ ሪፖርት መቅረቡን፣ ኮሚቴው በባለሞያዎች የቀረበውን ሪፖርት በመገምገምና አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ CES40 በአንቀፅ 6.2 የተቀመጠው መስፈርት በግርጌ ማስታወሻ እንደተገለፀው የደረጃው ተፈፃሚነት ለቤት ክዳን ቆርቆሮ ብቻ መሆኑን ከግንዛቤ በመውሰድ ፋብሪካው ያስመጣው የተጠቀለለ ልሙጥ የዚንክ ቅብ ቆርቆሮ ከመደበኛው የጣሪያ ቆርቆሮ ማምረት ውጪ

ለኮርኒስ ፍሬሞች፣ ለመፃህፍት መደርደሪያዎችና ለኬብል ትሬይ ምርቶች በግባዓትነት ሊጠቅም እንደሚችል ኮሚቴው የፈቀደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ ኮምቦልቻ ብረታ ብረት ምርቶች ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ለጣሪያ ክዳን የማይውል ቆርቆሮ የጥራት ደረጃ ፍተሻ የመይከናወን በመሆኑ ጥሬ እቃው መንግስት አምራች ድርጅቶችን ለማበረታታት የውጭ ፍተሻ በፈቀደው መሰረት በፋብሪካው ግቢ በመራገፉ የማምረት ሂደት ወዲያውኑ በመከናወኑ ለጥራት ቁጥጥር ፋብሪካው ናሙና ሲጠየቅ ምርቱን ለገበያ በማዋሉ የላብራቶሪ ፍተሻ ተከናውኖ ጥራቱን ማረጋገጥ ባለመቻሉ ሙሉ መልቀቂያ አለመስጠቱን እና አዲሱን አሰራር በመገንዘብ የተፈፀመ ስህተት መሆኑን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመገንዘብ መልቀቂያ እንዲሰጠው ፋብሪካው ማመልከቱን፣ በገቢና ወጪ እቃዎች ጥራት ቁጥጥር በኩል የምርት ጥራት ቁጥጥር ሳይደረግ ፋብሪካው ጥሬ ዕቃውን ጥቅም ላይ ማዋሉን ፣ በመሆኑም ከገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር እና ከገበያና ድርጅት ኢንስፔክሽን ሪጉላቶሪ ዳይሬክቶሬት የተውጣጣ የባለሞያ ቡድን በፋብሪካው ቅጥር ግቢ በመገኘት ምልከታ ያደረገ ሲሆን ቡድኑ ያቀረበውን ሪፖርት የማኔጅመንት ኮሚቴው በዝርዝር መመልከቱን፣ በሪፖርቱም ከባለሞያዎች እንደተመለከተው ፋብሪካው በዲ/ዮን ቁጥር C-47713 ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ባለ 0.5 ሚ.ሜ 46 ጥቅል (colil) የዚንክ ቅብ ልሙጥ ቆርቆሮ የላብራቶሪ ፍተሻ ሳይከናወንበት ለምርት አገልግሎት በማዋል ለገበያ ያሰራጨው በመሆኑ ምንም ዓይነት ናሙና በቡድኑ ሊወሰድ እንዳልቻለ ግንዛቤ መወሰዱ ፣ በመሆኑም የነበረውን ግድፈት የማኔጅመንት ኮሚቴው ፋብሪካው እስከዛሬ ያስመዘገበው የጥራት ሪኮርድ በመገምገም በጥሩ ደረጃ የሚገኝ መሆኑ መረጃውን በመመልከትና ምርቱ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በሦስተኛ ወገን SGS ተፈትሾ የጥራት ደረጃውን ያሟላ መሆኑን በሠርተፊኬት በመረዳት የማኔጅመንት ኮሚቴው ፋብሪካው ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደግም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው በማስገንዘብ መፍቀዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ኖርክ አግሮ ኢንዱስትሪያል ኃ/የ/የግል ማህበር ከውጭ ሀገር ያስመጣው አምስት ጥቅል ቆርቆሮ (5 coli) በቤት ክዳን ቆርቆሮ ደረጃ በ CGS40፡2015 ተፈትሾ የኢትዮጵያ ደረጃ አላሟላም ተብሎ መውደቁን ፣ይሁንና ድርጅቱ ምርቱን የሚጠቀመው የቤት ክዳን ቆርቆሮ ለማምረት ሳይሆን በፋብሪካ ለሚከናወነው የምግብ ማሸጊያ ( Food Canning ) በመሆኑ እና አስመጪው የቆርቆሮ አምራች ባለመሆኑ እንዲሁም የምርቱ ብዛት

አነስተኛ በመሆኑ ያስመጡት ምርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ የቀረበ ሲሆን የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ምርቶቹ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የመጡ እቃዎች በመሆናቸው እና መጠናቸውም አነስተኛ በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ውሳኔ መስጠቱ ታውቋል፡፡

- ✓ ጂ.ኢ.ሲ. ስቲል ኤም.ኤስ ጂ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለኢንቨስትመንት ካስመጣው የአርማታ ብረት ውስጥ ባለ ስምንት ሚ.ሜ ዲያሜትር በmass per lenegth ፓራሜትር የኢትዮጵያ ደረጃ ያለማሟላቱን፣ ይሁንና የድርጅቱ ዋናው ግንባታ የተጠናቀቀ በመሆኑ ለሌሎች ቀሪ ስራዎች ለማሽነሪ ማስቀመጫ አገልግሎት ለሚያውለው ቀላል ግንባታ የሚጠቀምበት በመሆኑ፣ አርማታ ብረቱ ለራሱ ኢንቨስትመንት አገልግሎት ብቻ የሚውል እና የምርቱም ብዛት አነስተኛ (ከ25 ሜትሪክ ቶን) በመሆኑ ያስመጡት ምርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ መቅረቡን፣ የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ምርቶቹ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የመጡ እቃዎች በመሆናቸው እና መጠናቸውም አነስተኛ በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ውሳኔ መስጠቱ ታውቋል፡፡

333. ኢ.ቲ.ኢ.ኤስ ኢንዱስትሪያል ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር ከውጭ ሀገር ያስመጣቸው ጥቅል ቆርቆሮ በኢትዮጵያ ደረጃ CGS40፡2015 በላብራቶሪ ተፈትሾ ዝቅተኛውን የዚንክ ቅብ መጠን ባለሟሟላቱ ወደ ሀገር እንዳይገባ መታገዱን፣ ይሁንና ምርቱ ለቤት ክዳን ቆርቆሮ ማምረቻነት ሳይሆን ለተገጣጣሚ የመጋዘን ፓርቲሽንና ለኮርኒስ አገልግሎት በመሆኑ እና ያመጣቸውም ብዛት 23 ኮይል ብቻ በመሆኑ ያስመጡት ምርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ መቅረቡን ፣ የንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴው ምርቶቹ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የመጡ እቃዎች በመሆናቸው እና መጠናቸውም አነስተኛ በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ውሳኔ መስጠቱ ታውቋል፡፡

334. የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁንና ክትትል ና ቁጥጥር ማድረጉን፣ ናሙናዎች ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ላብራቶሪ እንዲቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣

- ✓ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት እንደተቻለው የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የፍተሻ ውጤት መግለፅ ባለበት ጊዜ የማያሳውቅ መሆኑን፣ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት የሚያዘገይ መሆኑን፣ በአዳማ

ቅ/ፅ/ቤት የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ያለው ላብራቶሪ አዲስ አበባ ብቻ አንድ በመሆኑ የላብራቶሪ ውጤት እንደሚዘገይ፣ በዚህም ምክንያት ደንበኞች ለተጨማሪ የዲሜሬጅ ወጪ መዳረጋቸውን ፣ እና

- ✓ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የመፈተሻ አቅም ውስንነት ምክንያት አሁንም የላብራቶሪ ውጤቶች እንደሚዘገዩ፣ በፀሀይ ሀይል የሚሰሩ የሶላር መገልገያዎች የጥራት ደረጃቸው እንዲረጋገጥ ለኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ላብራቶሪ ናሙና ተሰጥቶ ውጤት ሳይገለፅ ከሁለት አመት በላይ በመሆኑና ተገላጋዮች ለዋስትና ያስያዙት ገንዘብ ባለመመለሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ደንበኞች በተደጋጋሚ ቅሬታ ማንሳታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

335. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ቁጥጥር ማድረጉን፣ የመለኪያ መሣሪያዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፣

- ✓ ከምርትና አገልግሎት ጥራት ከማረጋገጥ አንፃር አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸውን የወጪና የገቢ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር ስርዓቱ ያልተጠናከረ በመሆኑ ምክንያት ብልሹ አሰራርና ተግባር ከማበረታታቱም በላይ የሸማቹን ጤንነት ደህንነት አደጋ ላይ እየጣሉ፣ የንግዱን ማህበረሰብ ለፀረ-ውድድር እያጋለጡና በወጪ ንግድ እንቅስቃሴው በጥራት መጓደል ምክንያት የሀገር ገፅታ እያበላሹ መሆኑን ከንግድ ሚኒስቴር የማኔጅመንት ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በትግራይ ክልል ቁጥጥር ( Inspection ) ከተደረገላቸው ሚዛኖች 491 ጥፋት የተገኘባቸው ሲሆኑ ማለትም ትክክለኛ ክብደት ማነፃፀሪያ የማይጠቀሙ 240፣ በተበላሸ ሚዛን የሚጠቀሙ 81፣ ክብደት ሊያዛቡ የሚችሉ ባዕድ ነገር የሚጨምሩ 58 እንዲሁም 112 የሚሆኑ የተለያየ ጥፋቶች የተገኙባቸው ሚዛኖች መኖራቸውን እና በእቅዱ መሰረት የቬሪፊኬሽን ስራ አለመሰራቱን ፣
- ✓ በጋምቤላ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በ2009 ዓ.ም ሩብ ዓመት በ 10 ስጋ ቤቶች ላይ የሚዛን ጥናትና ቁጥጥር ተደርጎ 5 ስጋ ቤቶች ከግራም በታች እየሸጡ መገኘታቸው፣ በ20 አትክልት ቤቶች እና የችርቻሮ ቤቶች በተደረገው የሚዛን ጥናትና ቁጥጥር 10 አትክልት ቤቶች እና የችርቻሮ ቤቶች ከግራም በታች እየሸጡ

መገኘታቸውን፣በ10 ወፍጮ ቤቶች ላይ  የሚዛን ጥናትና ቁጥጥር ተደርጎ 5 ወፍጮ ቤቶች ከ 1 ኪ.ግ ከ 10-100 ግራም ቀንሰው እየሸጡ መገኘታቸውን ፤

- ✓ በደቡብ ክልል በተደረገ የሚዛን ምርመራ 424 ሚዛኖች እና 942 ክብደቶች ላይ ጉድለት የተገኘ ሲሆን በክልሉ ኮንታ ልዩ ወረዳ እስካሁን ምንም ዓይነት የሚዛን ምርመራ አለመከናወኑን፣
- ✓ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ 9 ቀበሌዎች እና 38 የገጠር ገበሬ ማህበሮችን አገልግሎት ለማዳረስ የስነ-ልክ መሳሪያዎች እጥረት ያለ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል የመስፈሪያ መሳሪያዎች ማነፃፀሪያ በበቂ ሁኔታ ያለማሟላት በወረዳና በከተሞች ስራው በተፈለገው ፍጥነት አለመሄዱን፣ የሥነ-ልክ ባለሞያዎች በአንዳንድ ወረዳዎች ያለመሟላት ችግሮች መኖሩን ፤ በአማራ ክልል በመለኪያ መሳሪያዎች ቬሪፊኬሽንና ኢንስፔክሽን ስራ ከተሰራባቸው የመለኪያ መሳሪያዎቹ ውስጥ 6017 በሚሆኑት ላይ ጉድለት የተገኘ መሆኑን፣
- ✓ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አብዛኛውን ኖዝሎች ላይ የሚሰጡት የነዳጅ መጠን ከ20 ሊትር መጠን ላይ ከ 50 ሚሊ ሊትር በታች ወርደው መታየታቸው፣ በዋናነት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ካዛንችስ ሱፐር ማርኬት ላይ ከ 200 ሚሊ ሊትር በታች በብዛት (ከአንድ ኖዝል በስተቀር) መታየቱን፣ በንግድ ሚኒስቴር ፕሉፕ የተሰሩ ማደያዎች ላይ ክፍተት በስፋት መታየቱን፣ በልዩነት ቦሌ የተባበሩት ላይ ብቻ 160 ሚሊ ሊትር ነጭ ጋዝ እንዲሁም አንድ የቢንዚን ኖብል ላይ 140 ሊትር ተጨማሪ በየ 20 ሊትር ላይ እየሰጠ መታየቱ ፤
- ✓ በትግራይ ክልል የነዳጅ ማደያዎች ካኖፒ (ጥላ) ባለመኖሩ ካላብሬት ማድረጊያ ቁጥሮች እንደማይሰሩ ፤ በክልሉ ካለው 112 የአንድ አገልግሎት ብዛት ሲታይ 23 የሚዛን ማነፃፀሪያ ክብደቶች ብቻ መኖራቸውን እንዲሁም ግራማቸው የተጓደሉ በመሆናቸው በሚዛን ማጭበርበር በሚገባ አለመሰራቱን ፤
- ✓ በጋምቤላ ክልል አዲስ የሚተከሉ የነዳጅ ማሽኖች ካሊብሬት ማድረግና በመለኪያ መሳሪያ በየወሩ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በባለሞያ እጥረት ምክንያት ስራው አለመከናወኑን፣ የተሰጣቸው ሚዛን ጥቂት በመሆኑ ምክንያት በየወረዳዎቹ አለመዳረሱን ፤ በቤኒሻንጉል

ጉምዝ ክልል በነዳጅ ላይ ክትትል ለማድረግ በማደያው ባሉ ማሽኖች ላይ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው፣ የዳቦና የወርቅ የልኬት መሳሪያዎች አለመኖሩን፣

- ✓ በአማራ ክልል የመለኪያ መሳሪያዎች ስታንዳርድ በወቅቱ ካሊብሬት አለመደረጋቸውን፣ የፈሳሽ ልኬታዎችን ለመለካትና ከዓለም አቀፍ የልኬት ስታንዳርዶች ጋር ለማነፃፀር የማነፃፀሪያ ስታንዳርዶች አለመኖራቸውን፣ አብዛኛው የቬሪፊኬሽን ስራ ወደ ዞን የተሰጠ ስለሆነ በትጋት አለመሰራቱን፣ በነዳጅ ማደያ ቬሪፊኬሽን የባለሞያዎች የክህሎት ክፍተት መኖሩን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

336. የአውቶ ቦቴ የቬሪፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር መሆኑን ፣ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር ( ቦቴ) የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት የሚሰጥና ተግባራዊ መደረጉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬርፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ቀደም እንደነበረው ዋጋው በ1966 ዓ.ም የሚዛንና መስፈሪያ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 431 መሰረት የወጣ መሆኑን እና የዋጋ ማሻሻያ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

337. ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት የውይይት መድረክ ያለው መሆኑን በተመለከተ፣

- ✓ የኦዲት ቡድኑ ከቃለ-ጉባኤ መመልከት እንደቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሀምሌ 11/2009 ዓ.ም ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ ሳይሆን የንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትሩን፣ የንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታን፣ የንግድ አሰራርና ሪጉላቶሪ ዘርፍ ሚኒስተር ዴኤታን፣ የሚኒስቴር ፅ/ቤት ዋና ዳይሬክተርን እና የህዝብ ግኑኙነትና ኮሚኒኬሽን ጉዳች ፅ/ቤት ሃላፊን ብቻ ያካተተ መደበኛና እና ተከታታይ የማናጅመንት /የስራ አመራር/ የውይይት መድረክ መኖሩን እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን በቃለ ጉበኤ በአግባቡ የተያዙ መሆናቸውን ከቃለ-ጉባኤዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 25.በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትና የወጪ ንግድ አፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ፣ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛት ድጋፍ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍ፣ በብድር አቅርቦትድጋፍ ፣ በውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍ ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- ✓ እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ፣ የመሳሰሉ የድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃላፊነት፣ ድጋፍ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያላዘጋጀ መሆኑን ፣
- ✓ በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲያውቁት አለማድረጉን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሆዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንትን ለማቆየት፣ ለመሳብና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በፌዴራል ደረጃ ተዘጋጅቶ የወረደ ቢሆንም በተለይ በዞን ደረጃ ከአሁን

በፊት በተለመደ መልኩ ባለሀብቱ በአትክልትና ፍራፍሬ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማውጣት መሬት ተረክቦ ወደ ስራ ከመግባት ውጪ ሌላ የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን፣ በተለመደው አሰራር ወደ ስራ የገቡትም ቢሆን ከባንክ ብድር ጋር በተያያዘ በስራው ለመቆየት ችግር እየሆነ እንደሚገኝ ከጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረጋ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል።

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተደጋጋሚ በህዝብ ክንፍ መድረክ ለሚነሱ የመሰረተ ልማት፣ የገበያና ሌሎች ችግሮች በሚፈለገው ደረጃ መፍትሔ መስጠት አለመቻሉን፣ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ለመሳብ የአቅም ውስንነት መኖሩን፣ ከ 2009 ዓ.ም የባለስልጣን መ/ቤቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል።

338. ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆኑ መሬቶችን በማጥናት ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ በየክልሉ የሚገኙ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ የሆኑ መሬቶችን (ማሳዎችን) በመለየት መሰረታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ወደ መሬት ቋት እንዲገቡ እና ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የማስተዋወቅ ስራ ያልሰራ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል።
- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሆርቲካልቸር ዘርፍ ልማትን ለማስፋፋት የመሬት አቅርቦት ችግርን ፈጥኖ መፍታት ያለመቻሉን፣ የዘርፉ የመሰረተ ልማት አገልግሎት አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ አለማሟላቱን ከባለስልጣን መ/ቤቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ታውቋል።

339. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ለባለሀብቶች በወቅቱ እንዲሟሉላቸው የተዘረጋ ስርዓትን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግልቶች(መብራት፣ ውኃ፣ ስልክ፣ መንገድ፣ወዘተ…) በወቅቱ እንዲሟላላቸው እንደማያደርግ ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

340. አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ሊይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ...ወዘተ አገልግልቶችን እንዲያገኙ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የብድር አገልግሎቶች የሚያገኙበት አሰራር ያልዘረጋ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች የገለፁ ሲሆን ኢትዮ ቬዥ ፍሩት እርሻ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች አስፈላጊውን ትብብር ለማግኘት የትብብር ደብዳቤ እንደሚፅፍላቸው ገልፀዋል፡፡

341. የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ መዋላቸውን በተመለከተ፤

- ✓ በአርባምጭ ዞን በኢንቨስትመንት ለተሰማሩ ማለትም በሶስት ዘርፍ / ግብርና፣አገልግሎት እና ኢንዱስትሪ/ በአንድ ላይ ከመከታተል ውጪ የተለየ ለአትክልትና ፍራፍሬ ብቻ የተዘረጋ የክትትል የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡
- ✓ አልሜታ ወንዶ ጢቃ እርሻ ልማት ኩባንያው የሚገኘው በዶሬ ባፈና ክ/ከተማ ሰማ ኤጀርሳ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን ውል የገባው 23/11/2004 ዓ.ም መሆኑ፣ መጀመሪያ የተረከበው የመሬት መጠን 500 ሄ/ር ሲሆን የተሰማራበት የሥራ መስክ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ሲሆን በኢንቨስትመንት ፈቃዱ መሰረት ማልማት ያልጀመረ መሆኑን፣

ኩባንያው በኢንቨስትመንት ፈቃዱ መሰረት አትክልትና ፍራፍሬ ሳይሆን በየምርት ዘመኑ በቆሎ እያመረተ እንደሚገኝ፣

- ✓ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ ኩባንያ የሚገኘው ቱላ ክ/ከተማ ዳቶ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ውል የገባው በ 06/06/2005 ዓ.ም መሆኑ፣ የተረከበው መሬት መጠን 21 ሄ/ር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከኢንቨስትመንት ፈቃዱ ውጪ በቆሎ እያመረተ እንደሚገኝ ከሀዋሳ ከተማ ኢነቨስትመንት ኮሚሽን የመስክ ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ✓ በ 2009 ዓ.ም በአትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ በ 34 ባለሀብቶች የለማ መሬት በሄ/ር 2,152.76 መሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ በምርት የተሸነ መሬት በሄ/ር 1,007.72 ሲሆን ጥቅም ላይ ያልዋለ መሬት መጠን በሄ/ር 1,288.39 ወይም 59% መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ✓ ኤስ ኤም አር የተባለ እርሻ የሚገኘው በደብረዘይት ሲሆን ኩባንያው በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ልማቱን እየሰራ እንደማይገኝ፣
- ✓ ኦክሊፍ የተባለው እርሻ የሚገኘው በሆለታ አዲስ አለም ሲሆን ኩባንያው ከ 6 ወር በፊት ስራ ያቆመ መሆኑን እና በአሁኑ ሰዓት ኩባንያው ላይ ከጥበቃ ሰራተኞች በስተቀር ምንም እንቅስቃሴ የሌለ መሆኑን፣
- ✓ ጋሎብ አግሮ ኢንዱስትሪ እርሻ  በሰገን ዞን በአማሮ ክሌ ወረዳ በአቡሎ ክሌ ወረዳ በአቡሎ አልፋጮ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን አጠቃላይ ይዞታው 2792 ሄ/ር መሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ 500 ሄ/ር በሙዝ ለመሸፈን አቅዶ እስከአሁን 14 ሄ/ር / የዕቅዱን 2.5% / ያለማ መሆኑን፣ የመብራት ችግር ስላለባቸው በአጠቃላይ በጀነሬተር የሚጠቀሙ መሆኑን ፣
- ✓ በአርባምንጭ የሚገኘው ሉሲ የእርሻ ኩባንያ አጠቃላይ የእርሻው ስፋት 1500 ሄ/ር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 36 ሄ/ር ለተለያዩ መሰረተ ልማት ሲውል የተቀረው 1464 ሄ/ር መሬት በተለያዩ ሰብሎች ሊሸፈን የሚችል መሬት ሲሆን ከዚህ መሬት ውስጥ 600 ሄ/ር ሙዝ የተሸፈነና 12.5 ሄ/ር በማንጎ/ አፕል ማንጎ/ ሰብል ሲሸፈን 851.5 ሄ/ር /58%/ ሄ/ር ያልለማ መሆኑን፣
- ✓ በሆለታ ልማት ከላስተር ውስጥ በቁጥር 7 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 191 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው

የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 122 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 69 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

- ✓ በመርቲ ልማት ክላስተር ውስጥ በቁጥር 10 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆኑ አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 1286 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 325 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 961 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣
- ✓ በቆቃ ልማት ክላስተር ውስጥ በቁጥር 8 በአትክልት ፍራፍሬን ሀርብስ የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆን አጠቃላይ የመሬት ይዞታቸው 675 ሄክታር መሆኑ፣ ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ ስፋቱ 344 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአትክልት ፍራፍሬ መሰረተ ልማት የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 331 ሄክታር የሚሆነው መሬት በአግባቡ ለልማት ያልዋለ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

342. የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የምርት አመራረትና አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በመሰብሰብና ማንዋልች በማዘጋጀት በስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተከታታይ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደረጉ የቴክኖሎጂ ማስረፅ (የሆርቲካልቸር ስራ ዘርፍ በቂ ክህሎትና የስራ ተነሳሽነት በማዳበር ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር) የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ ለባለሀብቱም ሆነ ለአውትግሮዎሩ ያልሰጠ መሆኑን እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ የአፈፃፀም ማንዋሎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ አለመደረጋቸውንከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

343. ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችንና ስታንዳርዶችን ያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ በሆልቲካልቸር የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጓቸው ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችን እና ስታንዳርዶችን (ኤምፒኤስ፣ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፐና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች መሰረት የሚመረቱ ስለመሆናቸው ክትትል እንደማያደርግ እና ባለሀብቶችም ሆነ አውትግሮዎሮች እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል።

344. ባለስልጣን መ/ቤቱ የምርት ግብዓት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች በማጠናከር ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነትና በመጠን እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ እንዲሁም እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ የማያደርግ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል።

345. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጀስቲክስ ፍላጎቶችን እንዲሟሉላቸው ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች የተሟላ የምርት ማደራጃና ማከማቻ መጋዘን ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች

ከመጓጓዣቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዢያ፣ የትራንስፓርትና ሌሎችም የሎጀስቲክስ ፍላጎቶች እንዲሟሉ ለባለሀብቶች ድጋፍ እንዳላደረገ ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

346. የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤትን በተመለከተ፤

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች በምርምር ማዕከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑን ከላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ከኢትዮ ቬጅ ፍሩት እርሻ፣ ከመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፣ ከአልሜታ ኢምፔክስ ኩባንያ የሀዋሳ እርሻ፣ ከአርባምንጭ እርሻ /ጂነሪ/ አሚባራ ከኦሞቲክ አጠቃላይ ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ከሙላት ሀይሌ የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የሥራ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ማዕከላትና የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች በክልሉ ስለመኖሩ እንደማያውቁ የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የጋሞጎፋ ዞን ኢንቨስትመንት ፅ/ቤት የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

## 26.በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ ፣ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

347. ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛት ለማወቅ ያጠናው ጥናት መኖሩን በተመለከተ፤

- ✓ በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት እና በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞችን ብዛት ለማወቅ በኤጀንሲው የተጠና ጥናት የሌለ

መሆኑን እና  አሁን እየሰሩ ያሉት ከስታትስቲክስ ኤጀንሲ እና ከግብር ከፋዮች መረጃ በመነሳት እንደሆነ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

348. ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ መሸፈን ያለባቸው የግል ድርጅቶችና ሠራተኞች እንዲሸፈኑ ማድረጉን በተመለከተ፤

- ✓ በደቡብ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም 1,704 ድርጅቶችን እና 12,288 ለመመዝገብ ታቅዶ አፈፃፀሙ 1,104 (64.8%) ድርጅቶች እና 5,854 ( 47.64%) ሰራተኞቸን የመዘገበ መሆኑን ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በምስራቅ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም 2,124 ድርጅቶችን እና 12,696 ሰራተኞችን ለመመዝገብ ታቅዶ አፈፃፀሙ 1,358 (64%) ድርጅቶች እና 6,171 (48.6%) ሰራተኞችን የተመዘገቡ አንደሆነ፣ እና በአዲስ አበባ ቁጥር 2 ቅርንጫፍ ፅ/ቤት መሰራት የነበረባቸው የምዝገባ ስራዎች በተለያዩ ምክንያቶች ቀድመው ባለመሰራታቸው አጠቃላይ የፅ/ቤቱ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩን እንዲሁም የድጅትና የሰራተኞ አቅድ አባልነት ካርድ ወዲያውኑ መሰጠት ያለመቻሉን  ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በሰሜን አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም 1,944 ድርጅቶችን እና 12,060 ለመመዝገብ ታቅዶ አፈፃፀሙ 972 (50.%) ድርጅቶች እና 3,927 (31.17%) ሰራተኞቸን የመዘገበ መሆኑን ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

349. ኤጀንሲው የግል ድርጅቶች በአዋጁ መሰረት በየወሩ እንዲከፍሉ ማድረጉንና ስለመክፈላቸውም የሚከታተልበትና የሚቆጣርበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

- ✓ በባህርዳር የሚገኘው ግራንድ ሆቴልና ስፓ የጡረታ መዋጮ ገቢ ከመጋቢት 2007 ዓ.ም እስከ ጥር 2009 ዓ.ም ድረስ የ 22 ወር ያልተከፈለ የድርጅቱንና እና የሠራተኛውን የጡረታ መዋጮ ያልተከፈለ የጡረታ መዋጮ ገቢ ድምር 1,289,444.61 / አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ አርባ አራት ብር ከስልሳ አንድ ሳንቲም/ ፣ እስካሁን ባልተከፈለ መዋጮ ገቢ ላይ ቅጣት ብር 613,144.55 / ስድስት መቶ አስራ ሶስት ሺ አንድ መቶ አርባ አራት ብር ከ ሃምሳ አምስት ሳንቲም/ ፣
- ✓ እስካሁን ባልተከፈለ መዋጮ ገቢ ላይ ወለድ ብር 51,098.26 /ሃምሳ አንድ ሺ ዘጠና ስምንት ብር ከ ሃያ ስድስት ሳንቲም/ በአጠቃላይ ድምር ብር 1,953,684.45 /አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሶስት ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከአርባ አምስት

ሳንቲም/ ውዝፍ እዳ እንዳለበት እና ማስረጃ ባለማቅረብ ክስ የመሰረተ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በግራንድ ሆቴልና ስፓ በአካል በመገኘት ባደረገው ማጣራት ኤጀንሲው ገቢ አልተደረገም ያለው ብር 1,289,444.61 / አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ አርባ አራት ብር ከስልሳ አንድ ሳንቲም/ ገቢ የተደረገ መሆኑን በማስረጃ ያጣራ ሲሆን ቅጣት እና ወለድ ድምር ብር 664,239.84 / ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም/ ገቢ እንዳልሆነ የኦዲት ቡድኑ ለማጣራት ችሏል፡፡

- ✓ በባህር ዳር ሰሜን ምዕራብ ሪጅን /ፅ/ቤት ለሳትኮን ኮንስትራክሽን ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል ፕሮጀክት ከ01/05/2006 እስከ 30/03/2007 ድረስ ከውዝፍ ቀሪ የጡረታ መዋጮ ብር 244,319.21 /ሁለት መቶ አርባ አራት ሺ ሶስት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከ21/100 ሳነቲም/ ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በባህር ዳር ሰሜን ምዕራብ ሪጅን /ፅ/ቤት እያሱ አዳምጤ ህንፃ ተቋራጭ የተባለው ድርጅት የራሳቸውንና የሰራተኛውን ድርሻ በየወሩ ማስገባት ሲገባቸው ለእንቁ ፕሮጀክት ከሀምሌ 2006 ዓም እስከ ታህሳስ 2007 ዓ.ም 63,316.23 ብር /ስልሳ ሶስት ሺ ሶስት መቶአስረሳ ስድስት ብር ከ23/100 ሳንቲም/ ፣
- ✓ ለእያሱ ኮንስትራክሽን ከሀምሌ 2006ዓ.ም -ታህሳስ 2007ዓ.ም 151,859.77 ብር / አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ አጠኝ ብር ከ77/100 ሳንቲም / በአጠቃላይ 215,173 ብር /ሁለት መቶ አስራ አምስት ሺ አንድ መቶ ሰባ ሶስት ብር እና ከጥር 2007 እስከ ጥቅምት 2008 ዓ.ም የጡረታ መዋጮ ገቢ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ሀዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000027435 የሚታወቀው ድርጅት ቀጥሮ ለሚያሰራቸው ሰራተኞች መክፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ ዋናውንና ቅጣትና ወለድ ጨምሮ በአጠቃላይ ብር 4,317, 619.18/አራት ሚሊየን ሶስት መቶ አስራ ሰባት ሺ ስድስት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከ18/100 ሳንቲም፣ በግብር መለያ ቁጥር 0000056023 የተመዘገበው ማውንት ኦሊቭ ት/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 1,116,493.93 ( አንድ ሚሊየን አንድ

መቶ አስራ ስድስት ሺ አራት መቶዘጠና ሶስት ከ93/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በግብር መለያ ቁጥር 0001517282 የተመዘገበው ያማር ካፌና ሬስቶራንት የተባለው ድርጅት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 392,883.13/ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ስምንት መቶ ሰማኒያ ሶስት ብር ከ13/100 ሳንቲም፣ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ፣
- ✓ በደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት በይርጋለም ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ 45 ድርጅቶች ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን፣ ደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት ለይርጋለዓም ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ከፃፈው ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በአርባ ምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ተመዝግበው የሚገኙና ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ያለባቸው ድርጅቶች አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር ከሰኔ 01/2007 እስከ ጥቅምት 30/2009 ብር 2,205,884.77 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከ 77/100 ሳንቲም) ፣በርሄ ሀጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/ግ/ማ ከግንቦት 01/2007 እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም ብር 1,186,534,15 ( አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሺ አምስት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከ 15/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ዲ.ኤም.ሲ ኮንስትራክሽን /ሁምቦ አርባ ምንጭ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ከየካቲት/ ከ ከሚያዚያ 01/2007 እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም ብር 423,675.11 ( አራት መቶ ሃያ ሶስት ሺ ስድስት መቶ ሰባ አምስት ብር ከ 11/100 ሳንቲም)፣ሳትኮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግ/ማ / ላሳክ ሳላይሽ መንገድ ስራ ፕሮጀክት/ ከየካቲት 01/2007 እስከ ታህሳስ30/2008 ዓ.ም ብር 2,595,667.66 ( ሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከ 66/100 ሳንቲም) ፣
- ✓ ሳትኮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግ/ማ /አ/ምንጭ ዩኒቨርስቲ ስፖርት ፊልድ ግንባታ ፕሮጀክት/ ከህዳር 01/2006 እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም ብር 100,672.50 ( መቶ ሺ ስድሰት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከ 50/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ እንዲሁም ሳትኮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግ/ማ / ሳውላ ላሳክ ኮንትራት -1 መንገድ ስራ ፕሮጀክት/ ከመስከረም 01/2009 እስከ ጥር30/2008 ዓ.ም ብር 1,672,550.60 ( አንዲ

ሚሊዮን ስድሰት መቶ ሰባ ሁለት ሺ አምስት መቶ ሀምሳ ብር ከ 60/100 ሳንቲም)፣ አኬር ኮንስትራክሽን ከ03/03//2007 እስከ 30/05/2009 ብር 1,620,076,66 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሺ ሰባ ስድሰት ብር ከ 66/100 ሳንቲም)፣

- ✓ ናሩስ ባዮ ቴክኖሎጅ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከግንቦት01/2006 እስከ መስከረም30/2008 ብር 62,077.04( ስልሳ ሁለት ሺ ሰባ ሰባት ብር ከ04/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።
- ✓ ጂ.ዋይ.ቢ.ኤስ አግሮ ኢንዱስትሪ ከ30/10/2008 እስከ 30/05/2009 ዓ.ም ብር 18,843( አስራ ስምንት ሺ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ብር)፣ ፍሊንት እስቶን አንጅነሪንግ /ዲላ ዩኒቨርስቲፕሮጀክት/ ከሰኔ01/2007 እስከ መስከረም 30/2009 ብር 1,813,552.81 ( አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ሶስት ሺ አምስት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከ 81/100 ሳንቲም)፣
- ✓ እንዲሁም ፍሊንት እስቶን አንጅነሪንግ /ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ፕሮጀክት ከነሀሴ01/2007- እስከ ጥቅምት 30/2009 ብር 929,889.69 9 ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከ 69/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።
- ✓ ማይ ፌቦራይት ካፍና ሪሰቶራንት/ሀዋሳ/ ከመስከረም 01/2006 እስከ ጥቅምት 30/2009 ዓ.ም ብር 232,336.34( ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ ስድሰት ብር ከ 34/100 ሳንቲም)፣ በሃላባ ያማረ ካፌና ሬሰቶራንት ከሀምሌ01/2008 እስከ ሰኔ30/05/20098 ዓ.ም ብር 392,883.13 ( ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ ሶስት ብር ከ 13/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።
- ✓ በደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0036723128 እና ሲው/sew/ ኢንፍራ እስትራክቸር ሊምትድ በሚል ንግድ ስያሜ የሚጠራው እና በሪጅን ፅ/ቤት ተመዝግቦ የሚገኝ የመንገድ ግንባታ ስራ ድርጅት በድርጅቱ ቀጥሮ ያሰራቸው ለነበሩ 415 ሰራተኞች ከየካቲት 01/2008 እስከ ሰኔ 30/2008 ድረስ ያለውን ጊዜ በድርጅቱ መክፈል የነበረበት የአምስት /5/ ወር የጡረታ መዋጮ ወለድና ቅጣት ጨምሮ ብር 4,709,699.87 /አራት ሚሊየን ሰባት መቶ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ሃያ ዘጠና ዘጠኝ

87/100 ሳንቲም/ ውዝፍ ዕዳ ያለበትና የስራ ውሉን አቋርጦ አካባቢውን ጥሎ የሄደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት ኢንተርፕራይዝ ሊሚትድ /ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ / በሚል የንግድ ስያሜ ተመዝግቦ የሚገኘው እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000034517 እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር አህመት አዶሊዝ ኬኤምሲ ጆይንት ቬንቸር በሚል የንግድ ስያሜ ተመዝግቦ የሚገኘው እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0005123671 የአገር አቋራጭ የመንገድ ስራ ድርጅቶች የሆኑት የጡረታ መዋጮ የተከፈለበት ፔሮል የባንክ ስሊፕ ጉድለት ያለባቸው መሆኑና ስራችውን አጠናቀው አካባቢውን ለቀው የወጡ መሆናቸው እና መክፈል የነበረባቸውን የጡረታ መዋጮ እንዳልከፈሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000039973 የሚታወቀው ድርጅት ከጥቅምት 01/2006- ጥቅምት 30/20089 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ብር 845,893.60 (ስምንት መቶ አርባ አምስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከ60/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለበት መሆኑን፣

- ✓ በደቡብ ሪጅን ጽ/ቤት ሐሮኒ ኢንተርናሽናል ሆቴል ከሐምሌ 1/2005 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ያልተከፈለ የአሰሪ እና የሰራተኛ ድርሻ ጠቅላላ መዋጮ ቅጣትና ወለድን ጨምሮ 1,365,510.31 (አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ አምስት መቶ አስር ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም) ዕዳ ያለበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በደብረ ማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት ከሀምሌ 2008ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2009 ዓ.ም ከተለያዩ የግል ድርጅቶች ያልተሰበሰበ ብር 1,800,389.81 (አንድ ሚሊየን ስምንት መቶ ሺ ሶስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከ81/100 ሳንቲም) መኖሩን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

350. የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ሂሳብ በኤጀንሲው ውክልና የተሰጣችው ገቢ ሰብሳቢ አካላት በአዋጁ መሰረት በትክክል ገቢ ሊያደርጉ፣ ኤጀንሲውም በውሉ መሰረት እየሰሩና በትክክል ገቢ ማድረጋችውን መከታተሉን በተመለከተ፣

- ✓ በየካቲት ወር 2009 ዓ.ም ከልደታ ክፍለ ከተማ ገቢዎች የተሰበሰበው ብር መጠን 727,160.41 / ሰባት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አንድ መቶ ስልሳ ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም/

ሲሆን የተላለፈው የገንዘብ መጠን 262,609.41 / ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ዘጠኝ ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም/ መሆኑን፣ ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ ገቢዎች የተሰበሰበው ብር መጠን 4,689,350.07 / አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም/ ሲሆን የተላለፈው የገንዘብ መጠን 864,019.38 / ስምንት መቶ ስልሳ አራት ሺ አስራ ዘጠኝ ብር ከ ሰላሳ ስምንት ሳንቲም መሆኑን፣

- ✓ በ2008 ዓ.ም በገቢዎች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ብር መጠን 6,341,572.85 / ስድስት ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ አንድ ሺ አምስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ አምስት ሳንቲም/ ሲሆን ወደ ባንክ የተላለፈው 5,615,096.39 / አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራአምስት ሺ ዘጠና ስድስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ ፣
- ✓ ከሀምሌ 2007 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ.ም ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ብር 50,084,665.83 / ሀምሳ ሚሊዮን ሰማንያ አራት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከሰማንያ ሶስት ሳንቲም/ ሲሆን ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፈው የገንዘብ መጠን 49,302,218.21 / አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሁለት ሺ ሁለት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ ሃያ አንድ ሳንቲም/ ሲሆን በዚሁ መሰረት ከተሰበሰበው የተላለፈው ሲቀነስ (50,084,665.83 - 49,302,218.21 ) = 782,447.62 / ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ አራት መቶ አርባ ሰባት ከስልሳ ሁለት ሳንቲም/ ብር ሲሆን በባንክ ያለ ቀሪ ብር 90,563.68 / ዘጠና ሺ አምስት መቶ ስልሳ ሶስት ከ ስልሳ ስምንት ሳንቲም/ መሆኑን፣
- ✓ ከ 782,447.62 ላይ 90,563.68 ባንክ ያለ ገንዘብ ሲቀነስ 691,883.94 / ስድስት መቶ ዘጠና አንድ ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ ሶስት ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም/ ከገቢዎች ያልተላለፈ ገንዘብ መኖሩን፣
- ✓ ከሀምሌ 2007 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ.ም ከልደታ ክፍለ ከተማ የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ብር 9,689,805.18 / ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ አምስት ብር ከ አስራ ስምንት ሳንቲም/ ሲሆን ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፈው የገንዘብ መጠን 8,553,813.34 / ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ አራት ሳንቲም/ መሆኑን፣
- ✓ በዚሁ መሰረት ከተሰበሰበው የተላለፈው ሲቀነስ (9,689,805.18-8,553,813.34 )= 1,135,991.84 / አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ

ብር ከ ሰማንያ አራት ሳንቲም/ ብር ሲሆን በባንክ ያለ ቀሪ ብር 359,690.27 /ሶስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም/ መሆኑን እና ከ 1,135,991.84 ላይ 359,690.27 ባንክ ያለ ገንዘብ ሲቀነስ 776,301.57 / ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺ ሶስት መቶ አንድ ብር ከሀምሳ ሰባት ሳንቲም/ ከገቢዎች ያልተላለፈ ገንዘብ መኖሩን፣

- ✓ በኤጀንሲው እስከ ሚያዝያ 30,2009 ወደ ብ/ባንክ ተላልፈዋል ተብለው እስከ ጥቅምት 09፣2009 ድረስ የኤጀንሲው ብሄራዊ ባንክ አካውንት ገቢ ያልሆኑ ገንዘቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-
  - ➢ በደቡብ ሪጅን የሚያዚያ ወር 7,050.42 ብር፣
  - ➢ በመርካቶ 1 የመጋቢት 446,976.06 ብር፣
  - ➢ በአቃቂ የመጋቢት ወር ብር 202,415.86
  - ➢ በልደታ የመጋቢት ወር 15,967.7 ብር
  - ➢ በቂርቆስ የመጋቢት ወር 1,896.00 ብር
  - ➢ በቦሌ የጥር ወር 188,284.00 ብር ሲሆን
- ✓ በጠቅላለው 862,590.04 ወደ ብሄራዊ ባንክ ተላልፈው ወደ ኤጀንሲው አካውንት ገቢ ያልሆኑ መሆንቸውን እንዱሁም በወር አራት ጊዜ ገንዘብ ወደ ብሄራዊ ባንክ ማስተላለፍ ሲገባቸው በጥር ወር 2009 ዓ.ም መርካቶ1፣ አራዳ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ ልደታ፣ እና መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር2 ከ አራት ጊዜ በታች ማስተላለፋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## II. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብ ኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች

### 1 መግቢያ፣

ዳይሬክቶሬቱ በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS) እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ት/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ሶስተኛ ዙር (PBS III) እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ( በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2009/10 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃለው በሚከተለው ሁኔታ ለዓይነት ቀርበዋል፡፡

## ሀ/ በ2009/10 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ እነሱም;-

**ጥሬ ገንዘብ፤**

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም ቆጠራዉ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣ እንዲሁም፣ እንዳንድ ወረዳዎች ላይ የባንክ ማስታረቂያ የሚዘጋጅ ቢሆምን በባንክ ሌጀር እና በባንክ ሂሳብ መግለጫ መካከል ልዩነት (አንዱ ከፍ ወይም ዝቅ ) የለ መሆኑ፤
- ከከዝና (ከሳጥን) በተንጠልጣይ የሚከፈል የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች በወቅቱ የማይወራረድ፣ አሊያም ወደ ሂሳብ ክፍል ዞሮ በተሰብሳቢ የማይያዝ መሆኑ እና ለረጅም ጊዜ ተከሚሮ የሚቀመጥ መሆኑ፣
- በካዝና ሆነው ለጥቃቅን ክፊያዎች የሚውለው ( petty cash system) የገንዘብ አጠቃቀም ሥርዓት የልተዘረጋ መሆኑ እና በፊይናንስ መመሪያ መሠረት ከዝና ውስጥ ማደር የለበት ሳይሆን ከሚፈቀደው በላይ በከዘና በርካታ ገንዘብ የሚያዝ መሆኑን እና በባንክ መከፈል የለበትን የገንዘብ መጠን( ከ 2000.00) ብር በላይም ከከዝና የሚፈጸም መሆኑ፣

**ተሰብሳቢእና ተከፋይ ሂሳብ፤**

- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረዳቸው እና አለመፈጸማቸዉ፣፣
- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች ዋና እና ተቀጽላ ሌጀሮች አለመቋቋም እና የተቀጽላ ሌጀሮች ምዝገባ ወቅታዊ አለመደረግ፤
- ለተወሰኑ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች የመነሻ ሰነድ ስለሌላቸው እና ተቀጽላ ሌጀሮች በለማቋቋሙ ምክንያት ባለቤቱ የማይተወቅ መሆኑ፤

**ወጪዎች፡**

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የውሎ አበል ፎርምና ተመኑ (rate) በአግባቡ አለመሞላት፡
- ለነዳጅና ለቅባት ፍጆታ ደካማ የውስጥ ቁጥርጥር (ስርዓት አልባ ስምሪት፣ የተሽከርካሪዎች የኪሎሜትር መቆጣጠሪያ ጌጅ የማይሰራ በመሆኑ) ስርዓት መኖሩን፣
- አልፎ አልፎ ግዥዎች ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚፈጸም መሆኑ
- አልፎ አልፎ ትክክለኛ የሂሳብ መደብ እና ትክክለኛ የሂሳቡን ሚዛን ( ኖርማል ባላንስ ማይጠበቅ) መሆኑ፡
- በጀት ለአንድ ባለበጀት መ/ቤት ከተመደበ በኂላ ለታለመለት ዓላማ ሳይውል አለአግባብ ለሌላመ/ቤት የሚታላለፍ በመሆኑ፤

**የሂሳብ ሪፖርት፡**

- ወርሃዊ እና ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ከፍ ላለው የመንግሰት አከል አለመላካቸው፣

**ንብረት፡**

- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊዎች አለመቋቋም፣
- ለቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ፤
- አልፎ አልፎ አዳድስ ማሽኖች እና የህክምና መገልገያዎች ያለሥራ ለረጅም ጊዜ መቀመጣቸው፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣
- በአብዘኛዉ መ/ቤቶች የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያዎች አለመመዝገብ፡
- የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች በወቅቱ አለመወገድ እና ተለይቶ ለብቻ የማይቀመጡ መሆኑ፣
- በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊዎች የተሽከርካሪ ፕሮፋይል፣ የባለቤትነት ደብተር ያለመኖር እና አልፎ አልፎ ታርጋ ቁጥር/ሰሌዳ ቁጥር (በአብዘኛው ሞተር ሳይክሎች) የማይሰጥ መሆኑን፣

- በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊዎች የአንዳንድ ተሽከርካሪ የኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ (ጌጅ) የማይሰራ መሆኑ፣

**የክትትል ኦዲት**

- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚኬድበት ወቅት፣ ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ እና ተጨማሪ ድክመቶች መታየቱ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፣

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና ( በስብሰባ እና በተለየዩ ጊዜ) መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣
- ተገቢው ትኩረት አለመስጠት
- የኃላፊዎችና የሥራ ሂደት ባለቤት ቶሎ ቶሎ ከቦታቸው መነሳት፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## በ2009/10 የኦዲት ዘመን በተከናወኑ ተከታታይ ኦዲቶች ላይ የተዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች( ግድፈቶች) identified internal control weakness)

በ2009/10 የኦዲት ዘመን (ከመጋቢት 1/2009 እስከ ጥር/2009) 300 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሶስተኛ ዙር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ (PBS III) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች እና ፍታሃዊ አገልግሎት ለሁለ አቀፍ እድገት ተጠቃሚነት (ESPES) የማረጋገጥ ሥራ የተከናወኑ ሲሆን፣ በተከታታይ ኦዲቱ ወቅት በውስጥ ቁጥጥር ላይ የተለዩት (የተገኙት) ድክመቶች/ ግድፈቶች እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች /አስተያየቶች (Recommendation ) እንደሚከተለው ተጠቃሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተራ.ቁ | ወጭ ተደርጎ ለሚመለከተው አከል የተላከ የስራ አመራር ሪፖርት | የኦዲቱ ብዛት (በቁጥር) | | | በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | PBS | ESPES | ድምር | |
| 1 | በስራ አመራሩ የተገለጹት፣ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች/ ግድፈቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች | 250 | 16 | 266 | 100 |
| | ድምር | 250 | 16 | 266 | 100 |

ማስገንዘቢያ፡-

1. ለእያንዳንዱ መ/ቤት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች/ ግድፈቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦችን የስራ አመራር የተላከ ሲሆን ዝርዝራቸው በተቀጽላ (Annex I and II ) ተያይዟል፡፡
2. በ'PBS III' ፕሮጀክት 2009 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ (PFS) ኦዲት ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር “ነቀፌታ የለበት” (qualified, Except for) ሲሆን፤ ይህ ኦዲት ተከታታይ ኦዲት ሳይሆን፤ ዓመታዊ ኦዲት በመሆኑ፤ ከላይ በተመለከተዉ ሠንጠረዥ ውስጥ አልተካተተም፤፤ስለሆነም በተጨማሪነት ሊያዝ ይችላል፡፡

## **የ2009/2010 ኦዲት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች**

### 1. መግቢያ

የፌዴራልዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የብድርና እርዳታ ሂሣቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ወይም እንደሚያስደርግ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት መ/ቤቱ ኦዲት ከሚያደርጋቸው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሣቦች በሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ያስደርጋል፡፡ በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መሰረት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች እንዳስፈላጊነቱ ማሳሰቢያ በመስጠት፣ ውጤቱን ከሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2009/2010 ኦዲት ዓመት /ከየካቲት 2009 እስከ ጥር/2010 ዓ.ም የኦዲት ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የደረሱን የመንግስት ልማት ድርጅቶችና በመንግስትና የልማት አጋር ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እንዲደረጉ የተመደቡ 6 ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲትን ጨምር፤ እንዲሁም የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወነው ኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርቧል፡፡

## 2. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2009 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ

### 2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲቋቋም፣ መንግሥታዊ የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻና የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ኮርፖሬሽኑ በስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲመራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በቦርድ አስጸድቆ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምር በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

### 2.2 የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት

የሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል፡፡

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው ክትትል እንዲያደርጉና አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ በግልባጭ እንዲያውቁት ያይደረጋል፡፡

### 2.3 የስራ ዕቅድና ክንውን

ኮርፖሬሽኑ በ2009 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዘቸውና ያከናወናቸው የሂሳብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| መግለጫ | የ2009 በጀት ዓመት | | | የ2008 በጀት ዓመት ሲነጻጸር | የ2009 ክንውን በመብለጥ(በማነስ) |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዕቅድ | ክንውን | ልዩነት % | ክንውን | ልዩነት |
| ወጪ የተደረጉ ኦዲት ሪፖርቶች | 257 | 239 | (18) (7%) | 238 | (1) (0.4%) |

ከላይ እንደተመለከተው የ2009 ክንውን ሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነጻፀር በ18 ሪፖርቶች ወይም በ7% የሚያንስ ሲሆን፣ ከ2008 በጀት ዓመት ክንውን ጋርም ሲነጻፀር ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለዕቅድ ክንውኑ ልዩነት ዋና ምክንያቱ በቁጥር 49 ረቂቅ ኦዲት ሪፖርቶች ለደንበኞች ተልከው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምላሽ ያልተሰጠባቸው በመሆኑ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ወጪ የሆኑት 239(የአንድ መ/ቤት/ድርጅት ከአንድ በጀት ዓመት ሂሳብ በላይ ኦዲት የተደረጉት ለየብቻ ተቆጥረው ነው) ሪፖርቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነተኑ፤ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቃፊታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው /Clean opinion/ 140፤ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆኑም ነቀፊታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው/Except for/ 45 ፤አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው /Disclaimer/ 50 ልዩ ኦዲቶች 4 ናቸው፡፡

## 2.4 የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ

በ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበረው የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል 143 ሲሆን፣ በ2009 በጀት ዓመት አዲስ የተቀጠሩ 17 በድምሩ 160 ሰራተኞች ውስጥ በጡረታ የተገለሉ 2 እና በፈቃዳቸውና ልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ 9 በመሆኑ፣ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 149 ሰራተኞች በስራ ላይ እንደነበሩ ተውቋል፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል ሙያ ደረጃ ሲተነተን ፕሮፌሽናል /ኦዲተሮች/ 100፤ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 49 ሲሆኑ፣ በፆታም ሲታይ ወንድ 98 እና ሴት 51 በድምሩ 149 ናቸው ፡፡

## 2.5 የሰው ኃይል ስልጠናን በተመለከተ

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ ከሆነው የኦዲት አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር የኦዲት ሙያ ይበልጥ የሚዳብርበትንና ሀገርቱም በዚህ ሙያ ረገድ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ በመሆኑ፣በእንግሊዝ ሀገር ከሚገኘው አሶሴሽን ኦፍ ሰርቲፋይድ አከውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የኮርፖሬሽኑ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ የፈተና ዝግጅት ጊዜ፣ በገንዘብና ሁኔታዎችን በማመቻቸት እና በደመወዝ ጭማሪና በመሳሰሉት ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት 21 ኦዲተሮች የመጀመሪያ ደረጃ/Fundamental stage/፣ 7 ደግሞ በፕሮፌሽናል ደረጃ/ ትምህርቱን በተለያየ ደረጃ በመከታተል ላይ ናቸው፡፡

የኮርፖሬሽኑን ሰራተኞች የሙያ ብቃት ከፍ ለማድረግና የስልጠናውንም ጥራት ለማገዝ ባለው ዓላማ መሰረት የኮርፖሬሽኑ ቤተ መጽሐፍት ለተጠቃሚዎች ዘወትር በስራ ቀናት ክፍት በማድረግ እና እንዳስፈላጊነቱ ከ11፡30 በኋላ ፣ቅዳሜና እሁድ እና በበኃላት ቀናት ክፍት በማድረግና የሚያስፈልጉ መጻሕፍት በማቅረብ በአገልግሎቱ ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ለአንድ ሰራተኛ የሀገር ውስጥ የስልጠና ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የኦዲት ሙያ ያለቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ፣ ኮርፖሬሽኑ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሰጠው ስልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

## 2.6 የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

በኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከሂሣብ ማጣራትና ከሕንጻ ቢሮዎች በሚገኝ ኪራይ ነው፡፡

በ2009 በጀት ዓመት በእቅድ የያዘውና አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ፣ እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የ2009 የፋይናንስ እቅድና ክንውን/በብር/**

| መግለጫ | ገቢ | ወጪ | ያልተጣራ ትርፍ /ከታክስ በፊት/ | የተጣራ ትርፍ /ከታክስ በኂላ/ |
|---|---|---|---|---|
| ዕቅድ | 35,635,309.00 | 27,477,245.00 | 8,158,064.00 | 5,710,645.00 |
| ክንውን | 34,967,369.00 | 25,952,955.00 | 9,0140,414.00 | 6,310,090.00 |
| ክንውን፤በመብለጥ (በማነስ) | (667,940.00) | (1,524,290.00) | 856,350.00 | 599,445.00 |
| ልዩነት በመቶኛ/%/ | (2) | (6) | 10 | 10 |

የ2008 የእቅድ ክንውን ከ2007 ጋር ሲነጻፀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ ብር

| የበጀት ዓመት | ገቢ | ወጪ | የተጣራ ትርፍ |
|---|---|---|---|
| 2009 | 34,967,369.00 | 25,952,955.00 | 6,310,090.00 |
| 2008 | 33,920,965.00 | 22,299,745.00 | 8,118,887.00 |
| ልዩነት የ2009 ክንውን በመብለጥ (በማነስ) | 1,033,878.00 | (3,732,075.00) | (1,88,738.00) |
| ልዩነት በመቶኛ/%/ | 3 | (17) | (23) |

የ2009 ገቢና ወጪ ሂሳብ ከ2008 ጋር ሲነጻፀር ገቢና ወጪው በሰንጠራዡ እንደሚታይ ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተጣራ ትርፍ ዕቅድ ክንውንም በስትራቴጂክ ዕቅዱ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ኮርፖሬሽኑ የሚጠበቅበትን የትርፍ መጠን በመሸፈን ለስትቴጂክ ዕቅዱ ትግበራ ተጨማሪ ትርፍ የተገኘ መሆኑን ያመላክታል፡፡

## 3. የ2009/2010 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶች

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና ከየካቲት1/2009 እስከ ጥር 30/2010 ዓ.ም ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 46 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 145 በድምሩ 191(ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡

በነዚህ ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) 131፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) 44 ፣አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 10፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቀውሞ አስተያየት የቀረበባቸው(Adverse) 1 ፤ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት ኢንቲሪም ኦዲት 5 በድምሩ 191 ናቸው፡፡ አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው መ/ቤቶች ሁለቱ የቀድሞ ተገጣጣሚ ሕንጻ አካላት ማምረቻ ድርጅትና የቀድሞው ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ከሌላ ድርጅት ጋር ስለተወሃዱ የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ግኝቶቻቸው በዚህ ሪፖርት ውስጥ በዝርዝር አልተያዘም፡፡

## 4. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

በ2009/2010 ኦዲት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች የተነሳ የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻል ነው ተብለው ወይም የጎላ ችግር ስላለበት ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሠጠባቸው ድርጅቶች ሁኔታ እና ከአንድ በጀት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.1. አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው ድርጅቶች

አቋም ሊወሰድበት ስላልተቻለ (Disclaimer opinion) የኦዲት አስተያየት መስጠት የተሰጠባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና አስተያየቱን ሊያሰጡ ያላስቻሉ ዋና ዋና ምክንያቶች/ድክመቶችና የሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ

ሰኔ 30/2005 ዓ.ም. የተጠናቀቀው የኤጀንሲ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ለኦዲቱ ሥራ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት የተወሰኑ ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የሂሳብ ምዝገባዎቹ የተሟሉ እና ትክክለኛ ስለመሆናቸው የምናረጋግጥበት ሌላ ተለዋጭ የኦዲት አሰራር ባለመኖሩ፣
- በተጠቃለለው የሀብት እዳ ሂሳብ መግለጫ በተመለከተው የክምችት እቃዎች ብር 5,713,741,538.00 ሂሳብ ላይ የተደረሰው የጤና ፕሮግራም ክምችት ዕቃዎች ብር 13,147,027.00 እና የተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ /Revolving Fund/ ክምችት ብር 48,892,260.00 በማስተካከል ነው፡፡ ይህም ማስተካከያ የተደረገበት ምክንያት የሂሳብ ምዝገባው፣ በፒችትሪ ሂሳብ አያያዝ ምዝገባውና በዓመታዊ ቆጠራ ሂሳብ ፤ እንዲሁም የኤጀንሲው የመሳሪያዎች/ዕቃዎች መረጃ አስተዳደር ሥርዓት የክምችት መቆጣጠሪያ ምዝገባዎች መካከል የነበረውን ልዩነት ለማስታረቅ እንዲሆን ተገልጿል፡፡ ሆኖም በሁለቱ የምዝገባ ሥርዓቶች መካከል የተፈጠረውን ልዩነት በግልጽ የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው የተደረገውን ማስተካከያ ተዓማኒነት/እውነተኛነት ለማመንና ለመቀበል አስቸጋሪ በመሆኑ፣ የክምችት እቃዎች ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ (Revolving Drug Fund) ሂሳብ ውስጥ የተመለከተው ጊዜው ያለፈበት እና የተበላሸ ክምችት የመጠባበቂያ ሂሳብ ያልተያዘለት ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ ሂሳብ ተለይተው የተመለከቱ ቢሆንም፤ ዋጋ ያልተቀመጠላቸው በመሆኑ ምን ያህል መጠባበቂያ ሊያዝለት እንደሚገባ አይታወቅም፡፡ የሥራ አመራሩ ለዚህ ሂሳብ መጠባበቂያ ቢይዝለት ኖሮ ሰኔ/2005 በትርፍና ኪሳራ መግለጫ የተመለከተው ትርፍ በዚያው ልክ መቀነስ ነበረበት፡፡ ሆኖም በተግባር ይህን ያህል ብሎ ለመወሰን አልተቻለም፡፡ ከዚህም በላይ በጤና ፕሮግራም ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ (ከዓመታዊ ቆጠራ ጋር በመገምገም) አልተደረገለትም፤ በመሆኑም የተያዘው የክምችት ዕቃዎች መጠባበቂያ ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በዋና መ/ቤት ፤በነቀምት፣ ባህር ዳር፣ ጉለሌ እና ጂማ ቅርንጫፎች የተመለከተው የተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሲገመገም እና ከተያዘለት መጠባበቂያ ሂሳብ ጋር ሲመሳከር የተያዘለት መጠባበቂያ በቂ አይደለም፡፡ በኦዲተሮች አስተያየት በብር 14,489,813.00 ስለሚያንስ የዓመቱን ገቢ እና ሰኔ 30/2005 የተመለከተውን ጠቅላላ ሀብት በዚሁ ልክ ያለአግባብ ከፍ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል የጤና ፕሮግራም የተሰብሳቢ ሂሳብ በቆይታ ጊዜው አልተተነተነም፣ የዋና መ/ቤት እና የጂማ ቅርንጫፍ ብቻ ሲታይ ረዥም ጊዜ የቆየ ብር 3,248,663.00 ተሰብሳቢ የሚገኝ ሲሆን ምንም መጠባበቂያ ስላልተያዘለት ጠቅላላ ሀብቱን እና የአጋር ድርጅቶች ፈንድ (Donors Fund) በዚሁ ልክ ያለአግባብ ከፍ አድርጎታል፡፡
- በክምችት እቃዎች ውስጥ ያልተጣራና ለረዥም ጊዜ የቆየ ሂሳብ ብር 296,493,852.00 ተካቷል፡፡ ይህም ሂሳብ እስከአሁንም እንዲጣራ ስላልተደረገ ትክክለኛ ሚዛን መሆኑንና ድርጅቱ በገንዘብ (ሀብትነት) ሊያገኘው እንደሚችል ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ ከተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 129,762,045.00 በቅርንጫፎች መካከል የሚታይ የሂሳብ ልዩነት (difference in inter-branch accounts) ሲሆን፣ በመሰረቱ ይህ ሂሳብ ዜሮ ሚዛን ማሳየት ነበረበት፡፡ በመሆኑም ስለልዩነቱ በቂ ማስረጃ እና ማብራሪያ ባለመቅረቡ በቅርንጫፎች መካከል ያለው ሂሳብ በትክክል ስለመገለጹ ለማመን ወይም እርግጠኛ ለመሆን አልተቻለም፡፡
- በተጠቃለለው የሀብትና እዳ መግለጫ ከተመለከቱት ውስጥ ተሰብሳቢ ብር 264,886,374.00 እና ተከፋይ ብር 241,478,169.00 የሚጣሩ የክምችት እቃዎች ጉድለት/በመብለጥ ተብለው በ2005 ቆጠራ ወቅትና ከዚያ በፊት የተከሰተ ሂሳብ ሲሆን፤ የዚህ ዓመት ጉድለት በድምሩ ብር 23,169,484.00 ሌሎች ተሰብሳቢዎች ተብሎ በዋና መ/ቤት ተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዟል፡፡ ከዚህም በላይ የክምችት ዕቃዎች ብልጫ የጤና ፕሮግራም ብር 55,235,215.00 በኤጀንሲው ምዝገባ ውስጥ አልተካተተም፡፡ በእነዚህ ችግሮች ምክንያት በተጠቃለለው ሀብትና እዳ የተመለከቱት ተሰብሳቢ ብር 1,496,243,468.00 እና ተከፋይ ብር 1,071,156,798.00 ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ እና ትክክል ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በእርዳታ የተገኘ የተሽከርካሪ ሂሳብ ብር 65068170.00 ከአጋር ድርጅቶች በስጦታ የተገኘ ሂሳብ ላይ የተያዘ ሂሆን፡ ይህንን የሚገልጹ ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በኦዲት ዓመቱ የአጋር ድርጅቶች ፈንድ (Donors Fund) በድምሩ በዴቢት ብር 143,105,830.00 ፤ በክሬዲት ብር 178,778,271.00 ማስተካከያ ተብሎ የተመዘገበ ሲሆን፤ ስለማስተካከያው ደጋፊ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው የማስተካከያዎቹን አስፈላጊነት እና ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ በተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የተካተተው በድምሩ ብር 172,212,372.00 ሂሳብ በዋና መ/ቤት፤ በጉለሌ፣ በነቀምት እና በባህርዳር ቅርንጫፎች ለረዥም ጊዜ ሳይከፈል የቆየ ሂሳብ እና ከዚያ ወዲህ ስላልተከፈለ፣ የኤጀንሲው ትክክለኛ እዳ ይሁን/አይሁን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በዋና መ/ቤት ብር 31,783,547.00 እና በሀዋሳ ቅርንጫፍ ብር 24,407,040.00 የተመለከተው ተከፋይ ሂሳብ የተዛባ ሚዛን (Abnormal debit) የሚያሳይ ሲሆን፣ የተዛባ ሚዛን ሊታይ የቻለበት ምክንያት ወይም በዚህ መልኩ እንዲመዘገብ የተደረገበት ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረቡ እና ማብራሪያው ባለመሰጠቱ በሂሳብ መግለጫዎች በእነዚህ ተከፋይ ሂሳቦች ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተጠቃለለው የሀብትና እዳ ሂሳብ መግለጫ የተካተተው ብር 469,501,907.00 በየሂሳቦቹ መካከል የተከሰተ ልዩነት (difference in inter-fund accounts) የተመለከተና በመሰረቱ ይህ ሂሳብ ሲጠቃለል ዜሮ ሚዛን ሊኖረው የሚገባ ነው፡፡ ይህም በመከሰቱ በቂ ማስረጃዎች ያልቀረቡና ማብራሪያ ሊሰጥበት ያልቻለ በመሆኑ በየፈንዱ መካከል ያለው ሂሳብ በትክክል የተገለጹ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተጠቃለለው የሀብትና እዳ ሂሳብ መግለጫ የተመለከቱት ተከፋይ ድርሻ (Dividend Payable) ብር 23,711,964.00 እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብር 30,149,257.00 ለረዥም ጊዜ ሳይከፈል የቆየ ሲሆን የቀድሞ የመድኃኒትና ሕክምና መሳሪያዎች አስመጪና አከፋፋይ የተጣራ ትርፍ ለመንግሥት (60%) ለኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ (40%) በየድርሻቸው በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 107/1996 መሰረት ሊከፋፈል ይገባ ነበር፤ ሌላ ይህን የሚቃረን ማስረጃ እስከሌለ ድረስ የመድኃኒት የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች አስመጪና አከፋፋይ ድርጅት መብትና ግዴታዎች ለኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 553/1999 የተላለፉ በመሆኑ፣ ለመንግሥት ሊከፈል የሚገባው ሂሳብ ሲሆን ኤጀንሲው ይህንን ክፍያ እስካሁን አልፈጸመም፡፡
- በውጭ ምንዛሪ ምጣኔ መዋዠቅ ምክንያት የተከሰተ ትርፍ ብር 113,223,453.00 በተዘዋዋሪ የመድኃኒት ፈንድ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ የተመለከተ ቢሆንም የቀረቡት

ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከዚህ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛው መጠን የጤና ፕሮግራም እንደሆነ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ሂሳቡ በድርሻው የአጋር ድርጅቶች ፈንድ ሂሳብ ውስጥም መካተት ነበረበት፡፡ በዚህ ምክንያት የተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ የገቢ ሂሳብ የተጋነነ/ከፍ የተደረገ/ ሲሆን በምን ያህል እንደሆነ ግን ለመገመት የሚያስችል የተሟላ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ጉልህ የሆኑ ግድፈቶች ምክንያት ኦዲተሮቹ በተዘጋጁት የኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት አልተቻለም በማለት አቅርበዋል፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን እንደደረሰን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር እና ለኤጀንሲው በጉዳዩ ትኩረት ለማሰጠት በኦዲተሮቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የተቀሩት 4 በጀት ዓመታት ሂሳብም ኦዲት ተደርገው ሪፖርቱ እንዲቀርብ በቁጥር ቸመ 40/9 በ22/05/2010 እና ቀደም ባሉት ዓመታት በተመሳሳይ ማሳሰቢያ የተሰጠ ሲሆን፤ ሂሳቡን ወቅታዊ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን፤ችግሮቹም የቆዩና በርካታ በመሆናቸው ቀጣይ ባሉት ሂሳቦች ኦዲት ተስተካክለው እንደሚቀርቡ ገልጸው ኤጀንሲው ምላሽ ሰጥቷል፡፡

በመሆኑም ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ ለሕብረተሰቡ ጤና አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎችን መንግሥት የሚያቀርብበት ዋነኛ መንገድ መሆኑ ታውቆ የኤጀንሲው የፋይናንስ እና መድኃኒት አስተዳደር ሕግን ተከትሎ በግልጽነት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሥርዓት እንዲመራ እንዲደረግ አስፈላጊ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

#### 4.1.2 የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት

የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት July 2015 እ.አ.አ የተጠናቀቀው ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ በሂሳቡ ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ገልጿል፡፡ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻለቸውም ጉዳዮች፡-

- የድርጅቱን ሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት እንድናደርግ የተጠየቅነውና የተስማማነው ከJuly 7/2014 እ.ኤ.አ በኋላ በመሆኑ፤ በተዘረጋው የሂሳብ አያያዝ የቁጥጥር ሥርዓት ላይ አመኔታ ለማሳደር የሚያስችል አስተማማኝ ማስረጃ ለማግኘት ባለመቻላችን የተዘጋጁት ሂሳብ መግለጫዎች ከከፍተኛ ስህተት የፀዱ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አልቻልንም፡፡ ይህም ጉዳይ ጉልህ በመሆኑና በሌሎችም ምክንያቶች አስተያየት በመስጠት መሠረት ሊሆን የሚችል በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በJuly 7/2014 የተጠናቀቀው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት ስላልተቻለ፤

ይኸው ሂሳብ በአሁኑ የJuly 7/2015 ሂሳብ መግለጫዎች የመነሻ ሂሳብ በመሆኑ፣ በዓመቱ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል መጠን የያዘ ስለሆነ የዓመቱ ሂሳብ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ፤ ይህም በምን ያህል ማስተካከያ ሊደረግለት እንደሚገባ ለመወሰን ስላልተቻለና ጉዳዩም በሂሳቡ ማነጻጸሪያ ሂሳብ ላይ ጭምር ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድር በመሆኑ፣

- የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሁሉም ገቢዎች በትክክል ስለመመዝገባቸው ማረጋገጫ የሚሆን አይደለም፡፤ አንዳንድ የገቢ ደረሰኞች በዕዳ ተመዝግበው የሚታዩ ሲሆን ተገቢው ማጠራት አልተደረገለትም፤ከዚህም በላይ ምዝገባዎቹ ከስሕተትና ሳይመዝገቡ ከመቅረት/መዘለል የጸዱ ስለመሆናች ቁጥጥር አልተደረገም፡፡ በመሆኑም በትርፍና ኪሳራ መግለጫው የተመለከተው ብር 5,092,630,305.00 ትክክል ስለመሆኑ የሚያሰምን ማረጋገጫ መግኘት አልተቻለም፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው በቋሚ ንብረት ሂሳብ ሥር ከውጭ ምንዛሪ መዋዠቅ የተነሳ የተጠራቀመው ኪሣራ (Capitalized losses ) ብር 164,521,476.00 መያዙ ከመሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎች ያፈነገጠ አሠራር በመሆኑና በሂሳብ መርሆዎቹ መሠረት ኪሣራው በወጪ ሂሳብ ውስጥ መካተት ነበረበት፤ይህም የዓመቱን ትርፍ /Year ended 7 july 2015 Financial Performance/ በብር 164,521,476.00 እና የተጣራ ሀብቱንም በዚሁ ልክ ይቀንሳል/ዝቅ ያደርጋዋል፡፡
- የቋሚ ንብረት ማሸነሪ፤ በሂደት ላይ ያሉ ስራዎች ሂሳብና የመሳሰሉት በርካታ ስህተቶች የሚታዩበት ሲሆን፤ ሌላ በቂና አሰተማመኝ የኦዲት ማስረጃ ስልልቀረበ በሂደት ያሉ ስራዎችም አሁንም በሂዳት ላይ ስለመሆናቸው፤ማረጋገጥ አለመቻሉ፤ እነዚህ በሂዳት አሉ የተባሉት ስራዎች ቢጠናቀቁ ወደ ቋሚ ንብረትነት በመተላለፍ የእርጅና ተቀናናሽ ሊሰራላቸው ይገባ ነበር፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሣብ በግምት ብር 4,000,000,000 ቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ (Advance) በተመለከተ በቂና አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃ ያልቀረበለት፣ ይህም ሂሣብ ከገቢ ሂሣብ ጋር ወይም ከተሰጠ አገልግሎት ጋር የተጣጣ (Off set) ፤ካልሆነም ሊሰበሰብ የሚችል ስለመሆኑ ማረጋገጥ ወይም አጠራጣሪ ሂሣብ ስለመሆኑ፤

- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሣብ ብር 7,724,562,948 በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ያልቀረበለትና ለወደፊት ለድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያስገኝ የሚችል ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

- ከላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ምክንያት በሀብትና ዕዳ መግለጫ ሂሣቡ የተመለከተው ጠቅላላ የቋሚ ንብረት ሂሣብ ብር 25,517,137,448 በትክክል የተገለጸ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- ለክምችት ዕቃዎች መጠባበቂያ ብር 123,599,384 ተይዞለታል፣ ሆኖም በዚህ ሂሣብ ላይ እንዴት ሊደረስ እንደቻለ በቂና አስተማማኝ ማስረጃና ማብራሪያ ሊሰጥበት አልተቻለም፣ በዚህም ምክንያት በሀብትና ዕዳ ሂሣብ መግለጫ የተመለከተው የክምችት ዕቃዎች ብር 4,088,065,761 ሂሣብ ማስተካከያ ያስፈልገው እንደሆነ፣ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው የክምችት ዕቃዎች ተብሎ በትርፍና ኪሣራ ሂሣብ ላይ በወጪ የተያዘው ብር 25,749,768 ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በሀብትና ዕዳ ሂሣብ መግለጫ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሣብ ውስጥ በግምት ጠቅላላው ብር 1,000,000,000.00 መሰብሰብ ስለመቻሉ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ያልቀረበለት፣ በሂሳብ መግለጫ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 2,932,508,998.00 ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የረጅም ጊዜ ዕዳ (noncurrent liability) ብር 1,514,392,807.00 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሊያወጣ የሚገባው እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ይኸው ዕዳ /መዋጮ/ በትክክል የድርጅቱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ሊቀርብ ስላልቻለ፤ እውነተኛ ዕዳ ስለመሆኑ የሚያሳምን ማስረጃ ለኦዲት ስላልቀረበ በትክክል ስለመገለጹ ማወቅ፣አልተቻለም፤

- በሀብትና ዕዳ በረዥም ጊዜ ዕዳዎች ስር ምደባ ያልተደረገላቸው ተሰብሳቢዎች (unallocated collections) በሚል ብር 2,680,580,159.00 የተመለከተ ሲሆን፣ ይህም ሂሣብ ልዩ ልዩ የክሬዲት ሂሣብ ዝውውሮች በገቢ ሊያዙ የሚችሉ ሂሣቦች ናቸው፤ በመሆኑም ይህ ሂሣብ ትክክል ስለመሆኑ የሚያስረዳ ዕዳውም በትክክል ስለመገለፁ የሚያሳምን በቂ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ስለሂሳቡ የኦዲት አስተያየት መስጠት አለመቻላቸውን ኦዲተሮቹ ገልጿል፡፡ በዚህ በመጋቢት/2010 ዓ.ም ላይ የሂሳቡም ኦዲት በሁለት ዓመታት ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት እና ለአገልግሎቱ በመ/ቤታችን ለተፃፈ ደብዳቤ ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወስዱ በተገለፀው መሠረት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እርምጃ እየወሰዱ ስለመሆናቸው የተሰጠን ምላሽ ያሳያል፡፡

በመሆኑም አሁንም በቀረበው ኦዲት ሪፖርት መሠረት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግና የተቀሩት ሃሳቦችም ኦዲት ተደርጐ ሪፖርት እንዲቀርብ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

### 4.1.3 የኢትዮጵያ ኤልክትሪክ ኃይል

እ.አ.አ. July 7/2015 የተጠናቀቀው የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ ቀጥሎ በተጠቀሱት ጉልህ ጉዳዮች የተነሳ በሂሳቡ ላይ አሰስተያየት መስጠት እንደሚችሉ በሪፖርቱ ተጠቅሷል፡፡

- የድርጅቱን ሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት እንድናደርግ የተጠየቅነውና የተስማማነው ከJuly 7/2014 እ.ኤ.አ በኂላ በመሆኑ በተዘረጋው የሂሳብ አያያዝ የቁጥጥር ሥርዓት ላይ አመኔታ ለማሳደር የሚያስችል አስተማማኝ ማስረጃ ለማግኘት ባለመቻላችን የተዘጋጁት ሂሳብ መግለጫዎች ከፍተኛ ስህተት የፀዱ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አልቻልንም፡፡ ይህም ጉዳይ ጉልህ በመሆኑና በሌሎችም ምክንያቶች አስተያየት በመስጠት መሠረት ሊሆን የሚችል በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በJuly 7/2014 የተጠናቀቀው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት ስላልተቻለ ይኸው ሂሳብ በአሁኑ የJuly 7/2015 ሂሳብ መግለጫዎች የመነሻ ሂሳብ በመሆኑ፣ በዓመቱ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል መጠን የያዘ ስለሆነ የዓመቱ ሂሳብ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ይህም በምን ያህል ማስተካከያ ሊደረግለት እንደሚገባ ለመወሰን ስላልተቻለ ይህም ጉዳይ በሂሳቡ ማነጻጸሪያ ሂሳብ ላይ ጭምር ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድር በመሆኑ፣
- ሀብትና ዕዳ መግለጫው በቋሚ ንብረት ሂሳብ ሥር ከውጭ ምንዛሪ መዋዠቅ የተነሳ የተጠራቀመው ኪሣራ (Capitalized losses ) ብር 2,942,644,256.00 መያዙ ከመሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎች ያፈነገጠ አሠራር በመሆኑና በሂሳብ መርሆዎቹ መሠረት ኪሣራው በወጪ ሂሳብ ውስጥ መካተት ነበረበት፤ይህም የዓመቱን ትርፍ /Year ended 7 july 2015 Financial Performance/ በብር 873,092,220.00 እና የተጣራ ሀብቱን ደግሞ በብር 2,942,644,256.00 ይቀንሳል/ዝቅ ያደርጋዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ጉልህነት የተነሳ ሂሳቡ ላይ አስተያየት ለመስጠት በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ስላልቀረበ በሂሳብ መገለጫዎቹ ላይ አስተያየት አንሰጥም በማለት ኦዲተሮቹ ገልፀዋል፡፡

### 4.1.4 የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት

ሰኔ 30/2004 ዓ.ም. የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ጉልዕነት ምክንያት ኦዲተሮቹ በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

- ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ ከሆኑት ማስረጃዎች እና ማብራሪያዎች የተወሰኑት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የሂሳብ ምዝገባዎቹ የተሟሉ እና ትክክለኛ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ባለመቻሉ፤
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው የተመለከቱት በርካታ የክምችት ዕቃዎች ሂሳብ በአብዛኛው ያልተገመገመና በቆጠራ ወቅት በአካል ስለመኖሩ እና የዋጋው ትክክለኛነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣ በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የክምችት እቃዎች ሂሳብ ብር 145,141,218.00 ትክክል ስለመሆኑ፤ እንዲሁም በዚህ ላይ ማስተካከያ ሊደረግበት ያስፈልግም እንደሆነ ለመወሰን ባለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ከተመለከተው ሂሳብ በግምት በድምሩ ብር 17,000,000 ተሰብሳቢ ሂሳብ ከ1 ዓመት በላይ ሳይሰበሰብ የቆየ ሲሆን፤ ሊሰበሰብ የሚችል ስለመሆኑ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣ በሐብትና እዳ መግለጫ ላይ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 86,981,219.00 ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ/በምን ያህል ለመወሰን አለመቻሉ፣
- በርካታ የባንክ ሂሳቦች የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ያልተዘጋጀላቸውና አንዳንዶቹ ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ ከመሆኑም በላይ በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ በገለልተኛ አካል ስለመቆጠሩ የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ፤ በሀብትና እዳ ሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ብር 119,042,215.00 በትክክል ስለመኖሩና ማስተካከያም ያስፈልግ እንደሆነ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፤
- በሀብትና እዳ ሂሳብ መግለጫው ከተመለከተው ተከፋይ ውስጥ በድምሩ ብር 15,700,000.00 ከ1ዓመት በላይ የቆየና ለምን ሳይከፈል እንደቆየ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ተከፋይ ሂሳቡም በእውነት የድርጅቱ ትክክለኛ እዳ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣
- ከሂሳብ ሪፖርት ማቅረቢያ ቀን በኂላ ስለተከሰቱ ጉዳዮች የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች ሊቀርቡልን ስላልቻሉ፣ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ ማስተካከያ የሚያስፈልጉ ካሉ አብሮ

ከሚያያዙ አስረጂዎች ውስጥ ስለመካተታቸውና ትክክል ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ባለመቻሉ፤ ምክንያት አስተያየት ለመስጠት የሚያስፈልጉ በቂና አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤

ኦዲተሮቹ በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን እንደደረሰ ለኮሙኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ለድርጅቱና ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር አስፈላጊው እርምጃ ተወስዶ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ፣ የተቀሩት በጀት ዓመታት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ ያሳሰብን ቢሆንም፣ የተሰጠን ምላሽ የለም፡፡ አሁንም የሂሳብ ኦዲቱ በ5 ዓመታት ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡

በመሆኑም በቀረበው ሪፖርት ለተጠቀሱት ግኝቶችና በተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት እርምጃ እንዲወሰድና የተቀሩት በጀት ዓመት ሂሳቦች ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወስዱ ክትትል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

### 4.1.5 <u>የመንግሥት ቤቶች ኮርፖሬሽን</u>

ሰኔ 30/2007 ዓ.ም የተጠናቀቀው የቀድሞ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ/ አሁን ኮርፖሬሽን/ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

- በጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ላይ የተመለከተው ያልተለመደ ሚዛን (Negative balance) ብር 11,235,551.00 መቼና እንዴት ሊከሰት እንደቻለና በሀብትና ዕዳ መግለጫው ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሚዛን ብር 502,058,475.00 ላይ ለመድረስ ይሀው ሂሳብ ለምን እንደተቀነሰ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠው በመሆኑና ባጠቃላይ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቡ ትክክለኛነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ፣
- በባንክ ሂሰብ ማስታወቂያዎች ላይ የተመለከቱት የተለያዩ ወጪዎች በጠቅላላ ብር 5,414,480.00እና በጠቅላላ ብር 3,501,058.00 ገቢ በኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ለምን እንዳልተመለከተ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠበት በመሆኑ፣እንደዚሁም የተለያ ወጪዎች ከብር 146,393.00 እናባንክ ገቢ የሆነ ሂሳብ ከብር 820,820.00 በላይ በኤጀንሲው

ያልተበዘገበ በመሆኑ በሳጥንና ባንክ ሂሳብ ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ከሆነም በምን ያህል ለመገመት አለመቻሉ፤ ና

- ኤጀንሲው በሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ላይ የዘረጋው የውስጥ የቁጥጥር ሥርዓት ባለመኖሩ፤ሌላ ሊታመንበት የሚቻል አሰራር በለመኖሩ የተመዘገበው ከኪራይ የተሰበሰበ ገቢ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የቀድሞ የቤት ባለቤቶችን በመወከል በመንግሥት ለተወረሰባቸው ቤቶች የባንክ ዕዳ ተብሎ ለባንክ የተከፈለው የረዥም ጊዜ የባንክ ዕዳ ክፍያ ብር 20,637,574.00 ሚሊዮን የመሰብሰብ ዕድሉ በጣም ዝቅተኛ በሆኑ በሙሉ በወጪ ሊመዘገብ የሚገባ መሆኑ፣ይህ ሂሳብ የመሰብሰብ ዕድሉ ዝቅተኛ በመሆኑ ሊሰበሰብ ስለመቻሉ እረግጠኛ ለመሆን የሚስረደ ማስረጃ በመለመቅረቡ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ካለም በምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መወሰን አለመቻሉ
- በሀብት ዕዳ መግለጫው በተሰብሳቢነት የተመለከተው ብር 315,842,257.00 ለበርካታ ዓመታት የቆየ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ብር 11,759,798.00 ከሰራተኞችና ሌሎች ተሰብሳቢዎች ለረዥም ጊዜ ሳይሰበሰቡ የቆዩ ሂሳቦች መኖራቸው፤እነዚህ ሂሳቦች በእውነት ሊሰበሰቡ የሚችሉ ነቸው ለማለት አስቸጋሪ በመሆኑ፤
- በሀብት ዕዳ መግለጫው በተሰብሳቢነት የተመለከተው ብር 45,868,953.00 ለተለያየ ኮንትራክተሮች ቅድሚያ ክፍያ ለበርካታ ዓመታት የቆየና ወደ ሕንፃ ሂሳብ ያልተካተተ ወይም በግንባታ ሂደት ላይ ወዳለ ሂሳብ ያልዞረ በመሆኑ፤ ወደ ሕንፃ ሂሳብ ገብቶ የእርጅና ተቀናሽ ሊሰላለት የሚገባው ምን ያህሉ እንደሆነ ባለመታወቁ የተጣራ ትርፉን ለወሰን አዳጋች በመሆኑ፣
- በሌሎች ገቢዎች የተካተተውና በሂሳብ መግለጫዎች ማብራሪያ የተመለከተ ብር 60,702,480.00 ከፈረሱ መኖሪያ ቤቶች የተገኘ ካሳ በሚል ቢሆንም፤በቂና አስተማመኝ ደገፍ ሠነድ ያልቀረበላው ብር 21,313,998.00 የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ብቻ የቀረበለት ነው፡፤ በመሆኑም ይህንን የካሳ ሂሳብ ኤጀንሲው በሙሉ በሙሉ ስለመመዝገቡ እርግጠና መሆን አልተቻለም፡፡

በኤጀንሲው ተዘጋጅተው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች  የዓለም አቀፍ የሂሳብ አሠራር ደረጃዎች ተከትሎ ያልተዘጋጁና በተጠቀሱት ምክንያቶች በቂና አሳማኝ መረጃ ባለማግኘታቸው አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

በዚሁ መሠረት እነዚህና ሌሎች በሪፖርቱ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ እንዲገለጽልን በመ/ቤታችን ተጠይቆ በተሰጠ ምላሽ ኮርፖሬሽኑ በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት መርዓ-ግብር ማዘጋጀቱንና በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ማስተካከያ ስለወሰደ በቀጣይ ሮፖርቶች ተመሳሳይ ግኝቶች እንደማይከሰቱ ጠቅሶ በ2009ና በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ማስተካከያዎች እንደተደረጉ ተቅሷል፡፡ የኤጀንሲው/ኮርፖሬሽኑ ሂሳብ ኦዲት በሁለት ዓመት ወደኃላ የቀረ ነው፡፡

በመሆኑም በኦዲት  ሪፖርቱ የተጠቀሱት ችግሮች ተቀርፈው የኮርፖሬሽኑ ሂሳብ እንዲስተካከልና ወደኃላ የቀረው ሂሳብም ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

### 4.1.6 በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የጎማ ተክል እና ማምረቻ ፕሮጀክት

June 30/2016 G.C የተጠናቀቀው የፕሮጀክቱ ሂሣብ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የቀረበው ውጤት እንደሚከተለው ነው፡፡

- ከሂሣብ መግለጫዎች ጋር በተያያዘው ማብራሪያ መሠረት <<ከጎማ ሽያጭ የተገኘ ገቢና ሌሎች ገቢዎች በመዋጮ ድርሻ ሂሳብ/ closed to Contribution Account/ ውስጥ በማካተት እንዲመዘገቡ ሆኖል>> ተደርጎ ተመዝግቧል፡፡ በሂሣብ አያያዝ ፖሊሲ መሠረት ይህ ትክክለኛውን ገቢ እና ወጪ የሚደብቅ ሲሆን፤ ገቢዎች እንደተገኘ ወጪወዎችም እንደተከሰቱ ሊመዘገቡ ይገባል የሚለውን መሠረታዊና  ዘመናዊ የሂሣብ አያያዝ (Accrual Basis of Accounting) የሚቃረን አሠራር በመሆኑ፣
- በሀብት ዕዳ መግለጫዉ  ለወደፊት የዘገዩ ወጪዎች/Deferred Expenditure/ ብር 38,709,724.00 ሲሆን፤ የዚህ ሂሣብ የወደፊት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያሳይ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ወይም ለምን ይህ ሂሳብ በወጪ በመመዝገብ ፋንታ እንደሀብት (Asset) እንደተያዘ ማብራሪያ ሊሰጠን ባመቻሉ ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የተክል ልማት ወጪ ተብሎ ብር 128,300,904.00 በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ቢሆንም፤ ይህ ሂሣብ እንዴት እንደተጠራቀመ፣ ከሂሣቡ ጋር ያለው ግንኙነት፤ ዋጋው  በእርጅና እየቀነሰ ሊሄድ የሚችልበትን የሚያስረዳ ማስረጃ

ባለመቅረቡ፣ በኦዲተሮቹ አስተያየት የሂሣብ መግለጫዎቹን ግልጽና ሊረዱት የሚቻል እንዲሆን የሚያስችሉ ማብራሪያዎች ሊደረጉበት ይገባል፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ተከፋይ ሂሣብ ብር 4,500,391.00 ውስጥ ብር 2,701,693.00 ለበርካታ በዓመታት ሳይከፈል የቆየ ሲሆን፤ሳይከፈል የቆየበት ምክንያት የሚያሳይ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ስላልቀረበ፤ ይህም ሂሳብ ትክክለኛ የፕሮጀክቱ ዕዳ ስለመሆኑና ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ስለማይተወቅበሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ሂሣብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በፕሮጄክቱ በተዘጋጁት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን እንደደረስን ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድና መርሃ-ግብር አዘጋጅተው እንዲልኩ ለኮርፖሬሽኑ ለፃፍነው ደብዳቤ በቀድሞ አጠራር የብሔራዊ ኒኩለስ ፕሮጀክት ይባል የነበረው በአዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር የጎማ ዛፍ ልማትና ምርት ፕሮጀክት ተብሎ እንደሚጠራ ገልጸው በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ መርሀ-ግብር አዘጋጅተው በቁጥር ኬኢኮ22.30/08 ጥቅምት 22/2008 ዓ.ም ልኳል፡፡

በመሆኑም በተዘጋጀው መርሀ-ግብር እና በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት የማስተከከያ እርምጃዎቹ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

## 5. ስለመንግስት ልማት ድርጅቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ ፣ንብረት አጠባበቅና አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔያቸው እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

### 5.1 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ቢኖሩ ምዝገባቸው ያልተሟላ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፤ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ በመዝገብ ያለው

የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣

- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብና ልዩነት ከተገኘም እንዲታረቅ ሳይይደረግ ለሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት የሚጠቀሙበት መሆኑ፣

- በአንዳንድ ድርጅቶች በውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ ያልተካሄድና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡
- አንዳንድ ድርጅቶች በጉዞ ላይ ያለ ንብረት ሂሳብ እና በሂዳት ላይ ያለ ንብረት /ለምሳሌ ግንባታ ሊሆን ይችላል/ በሚል የቆሚ ንብራት ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎቻቸው ላይ የሚያሳዩ ለበርካታ ዓመታት በዚሁ ሂዳት የሚታይ የአንዳንዶቹ እያጨመረ የመሄድ ሁኔታ የሚታይ ሲሆን፤ ስለጉዳዩ በበቂ ማስረጃ የተደገፈና ትክክለኛነቱን በአስተማማኝ የሚያሳይ አለመሆኑ፤

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

## 6.1. <u>በመጋዘን ያሉ እቃዎች</u>

- በመጋዘን ያሉ ክምችት እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራውን ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ ሳያደርጉ ለሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት የሚጠቀሙ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ፤ ሌሎች ደግሞ አሟልተው የማይመዘግቡና የምዝባ ስህተቶች/ልዩነት ሲያጋጥሟቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በጊዜያዊነት/Suspense Account/ የሚይዙ መሆኑ፣
- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣
- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በሚል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝግቦ መቆየት የሚቻል ቢሆንም በበርካታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች፤ የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑም በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየቀባቸው መሆኑ፣
- በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም ከውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ዕደት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም ለምርት ግብዓት ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይዳረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው።

በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከርና የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል።

## 6.2. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት ስለሚያሸጋግሩ ተሰብሳቢው እየጨመረና ጊዜው እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ባለዕዳዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው፤እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት/ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት በአብዛኛው የማይሳካ መሆኑ፤
- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለአጣጡ ወይም፤ አፈቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው፣ መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገበሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ የብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለዕዳ ሁለትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል፡፡

በመሆኑም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ፤ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ ሂሳቦቹ ትክክለኛ የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ ገጽታ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየተ ተሰጥቷል፡፡

### 6.3. <u>በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙ፤ በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደማያስታርቁ፤ የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣
- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ፣ አንዳንዶቹ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ምንም ማስረጃ የሌላቸው፡ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማያጣሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

### 6.4. <u>ተከፋይ ሂሳቦች</u>

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መከፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳለባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ መግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪዎች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ ቢሰጡም ድርጅቶቹ አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በወቅቱ እንዲከፍሉና ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

### 6.5. ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኂላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶት ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች የሚያደርጉት ቁጥጥር አናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደማይደረግ፤ ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምልክት እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሂሣቦችም የአርዕስት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ፤ የሂሣብ ሠነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት ስለማይቻል ፤ሠነዶች  በጥንቃቄ እንዲያዙና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች  ሪፖርት ተልኳል፡፡

## 6. በመንግሥትና የልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

በመንግሥትና የልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የሂሳብ አያያዛቸው በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሲሆን፣ በአብዛኛው የተሰጠው የኦዲት አስተያየትም ነቀፌታ የሌለበት (clean opinion) እንደሆነ ተመልክቷል፡፡
ሆኖም በአብዛኛዎቹ ፕሮጀክት ፈፃሚዎች ትኩረት ያልተሰጣቸውና በተደጋጋሚ በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ የሚጠቀሱ በኦዲት ሪፖርቱም መሠረት የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

- የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ለብቻ የባንክ ሂሳብ አለመክፈትና በየወቅቱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አለማዘጋጀት፣

- በባንክ ሂሳብ ማሳወቂያ እና በባንክ መዝገብ መካከል የሚታዩ ልዩነቶች መንስኤ አለማጣራት፣
- ከፍተኛ መጠን ያለው ጥሬ ገንዘብ በሳጥን እንዲቀመጥ የሚደረግ መሆኑ፣
- በዓመቱ መጨረሻ የሚታየውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አለማድረግ እና ወይም የቆጠራውን ውጤት ከመዝገብ ጋር አለማመሳከር፣
- በበርካታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖር እና በዕድሜ ተተንትኖ አለመገለጽና በወቅቱ እንዲወራረድ አለማድረግ፤
- አልፎ አልፎ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሚታዩ መሆኑ፣
- ቅድሚያ ክፍያና ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ፤
- የአንዱን በጀት ዓመት ፕሮጀክት ወጪ ሂሳብ ለሌላው በጀት ዓመት የመመዝገብ ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚታይ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የፕሮጀክት ሂሳብ መዝገብ ያለመቋቋማቸው፣አልፎ አልፎም ደጋፊ የሂሳብ ማስረጃዎቹን ለኦዲት አለማቅረብ፣የሂሳብ ማስረጃዎች አያያዝና ፋይል አደራረግ ደካማ መሆን፤
- ከዋናው መ/ቤት የሚተላለፈው ገንዘብ መጠንና በፈፃሚ መ/ቤት ወይም ቅ/ጽ/ቤት ገቢ የሆነው/ የተመዘገበው ሂሳብ መካከል አልፎ አልፎ ልዩነት መኖሩና የተላለፈውም ገንዘብ ስለመድረሱ መረጋገጫ የማይሰጥ ወይም በደረሰኝ ገቢ እንዲሆን የማይደረግ መሆኑ፣ በፈጻሚ መ/ቤትና ፈንድ አስተላለፊ ድርጅት/መ/ቤት መካከል ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ አለማድረግ፤
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል ወደ ቀጣይ ዓመት የሚዞር መሆኑ፣
- ከፕሮጀክት ሂሳብ ላይ ያለበቂ ምክንያት/የፕሮጀክቱ ባለቤት ይሁንታ ውጭ ለሌላ ተግባር ወጪ ማድረግና ክፍያውም አልፎ አልፎ ከተተመነው በላይ መሆን፡
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ሂሳብ የሚካሄዱ ስብሰባዎች/ወረክሾፕ/ የተሳታፊዎች ዝርዝር የማይያዝ፤ ተሳታፊዎች ከመጡበት መ/ቤት/ድርጅት እንዲሳተፉ የተወከሉ መሆኑን

የሚገልጽ ማስረጃ የማይያዝና ተሳታፊዎች በተሰተፉበት ጊዜያት የሰዓት መቆጣጠሪያ የማይያዝ/ የማይቀርብ መሆኑን አልፎ አልፎ ለስልጠነው ቆይተዋል ከተባለው ቀናት በላይ የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ የሚገኝ መሆኑ፤

- ከስልጠናና ወርክሾፐ ፕሮግራሞች ጋር በተያየዘ አስፈለጊ መረጃዎች ማለትም ስልጠነው /ወርክሾ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ፤ የት ቦታ እንደተካሄደ፤ የሚገልጽ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዶች ጋር ያለመያያዝ፤
- በፕሮጀክት ሂሳብ ለተገዙ ዕቀዎች/አገልግሎቶች ከአቅራቢዎች የሚሰጥ ደረሰኝ በፕሮጀክቱ ስም እንዲዘጋጅ አለማድረግ፤
- በኘሮጀክት ሂሳብ የሚገዙ ቋሚ ንብረቶች ምዝገባ የማይካሄድና መለያ ቁጥር በአግባቡ የማይሰጥ መሆኑ፣
- በውስጥ ኦዲተሮች ሊታዩና ሊስተካከሉ የሚችሉ ጥቃቅን ግድፈቶች ጭምር የሚታለፉና የሚታዩ፤በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት የተደረጉ ግኝቶች ላይ እርምጃ አለመውሰድና ተመሳሳይ ግኝቶች በተደጋጋሚ የሚታዩ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም በየፕሮጀክቶቹ ሂሳብ አያያዝ የተመለከቱት ችግሮች እንዲስተካከሉ በየኦዲት ሪፖርቶቹ አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ፣የየፕሮጀክቶቹ አስፈጻሚዎች ችግሮቹን ሊያስተካክሉትና የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ስለተግባራዊነቱ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።

## 7. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው

### 8.1. የችግሮቹ ምክንያቶች

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ በሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- በብዙዎቹ ድርጅቶች ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋትና ካለም ተግባራዊ አለማድረግ፤
- በውስጥ ኦዲተሮች ስራውን በጥልቀት ያለመከታተልና በሚያቀርቡት ግኝቶች ላይም እርምጃ አለመውሰድ፡

- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ለሂሳብ ስራው በቂ ትኩረት አለመስጠትና በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

## 8.2. ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃች

የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ በመከልከል፣ የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ቅልጥፍናና የውጤት ጥራት እንዲኖር ለማድረግ፣ ያስችላል፡፡ በመሆኑም፡

- ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ተገቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብት በተሞ፤ ሁኔታና በእንክብካቤ አመቺ በሆነ ቦታ እንዲቀመጡና በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርቡ፡
- ለማንኛውም የድርጅቱ ንብረት በማንኛውም ጊዜ ኃላፊና ጠጠያቂው ግለሰብ ማን እንደሆነ ተለይቶ የሚታወቅበት ዘዴ እንዲቀየስ፡ለግለሰቦች ተደራራቢ ተግባርና ሃላፊነት በመስጠት ለምዝበራ አመቺ ሁኔታ እንዳይፈጠር በተለይ በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፤ በንብረትና ገንዘብ አጠባበቅ ረገድ የማያሻማ ግልጽ የሆነ ስራ ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ፤
- ከውስጥና፤ ከውጪ ኦዲተሮች የሚሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም በኦዲት ሪፖርቶች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

## 8. ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች

በመ/ቤታችን እስከ መጋቢት 30/2010 ዓ.ም ባለው መረጃ መሰረት ከ1 ዓመት በላይ ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ 47 የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የ4 ቱ ደግሞ በውል ያልተወቀ/ ዝርዝራቸው በአባሪ-37 ተመልክቷል/ እንዳሉ ታውቋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ፣ የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡